# የወንጌላት ስምምነት

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ |
|---|---|---|---|---|
| **ለኢየሱስ ማንነት አጭር መግለጫ** | | | | |
| ሉቃስ መልእክቱን የጻፈበት ዐላማ | | | 1፥1-4 | |
| የዮሐንስ መግቢያ፦ ኢየሱስ ክርስቶስ ትስብእት የሆነ ዘላለማዊ ቃል | | | | 1፥1-18 |
| የኢየሱስ ሕጋዊ ዘርዐ ትውልድ በዮሴፍ፤ እንዲሁም ከማርያም ማሕፀን መውጣቱ | 1፥1-17 | | 3፥23-38 | |
| **የመጥምቁ ዮሐንስ የልጅነት ዘመን** | | | | |
| ዮሐንስ እንደሚወለድ ለዘካርያስ ትንቢት ተነገረው | | | 1፥5-25 | |
| ኢየሱስ እንደሚወለድ ለማርያም ትንቢት ተነገራት | | | 1፥26-38 | |
| ማርያም ኤልሳቤጥን መጎብኘቷና የኤልሳቤጥ መዝሙር | | | 1፥39-45 | |
| የማርያም የደስታ መዝሙር | | | 1፥46-56 | |
| የዮሐንስ መወለድ | | | 1፥57-66 | |
| የዘካርያስ ትንቢታዊ መዝሙር | | | 1፥67-79 | |
| የዮሐንስ እድገትና የልጅነት ዘመኑ | | | 1፥80 | |
| **የኢየሱስ ክርስቶስ የልጅነት ዘመን** | | | | |
| የኢየሱስ እንደሚወለድ ለዮሴፍ ተነገረው | 1፥8-25 | | | |
| የኢየሱስ መወለድ | | | 2፥1-7 | |
| የመላእክት ምስጋናና የእረኞች ምስክርነት | | | 2፥8-20 | |
| የኢየሱስ መገረዝ | | | 2፥21 | |
| ኢየሱስ ለስምዖንና ለሐና ለመታየት ወደ ቤተ መቀደስ ሄደ | | | 2፥22-38 | |
| የሰብአ ሰገል መጎብኘት (የምሥራቅ ጠቢባን ኢየሱስን መጐብኘት) | 2፥1-12 | | | |
| ወደ ግብፅ መሸሽና በቤተልሔም የሕፃናት መገደል | 2፥13-18 | | | |
| ወደ ናዝሬት መመለስ | 2፥19-23 | | 2፥39 | |
| የኢየሱስ እድገትና የልጅነት ዘመን | | | 2፥40 | |
| ኢየሱስ የፋሲካን በዓል ለማክበር ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም መሄዱ | | | 2፥41-50 | |
| የኢየሱስ እድገት | | | 2፥51-52 | |
| **የመጥምቁ ዮሐንስ የአደባባይ አገልግሎት** | | | | |
| አገልግሎቱን መጀመሩ | | 1፥1 | 3፥1-2 | |
| ማንነቱ፣ ስብከቱና ማጥመቁ | 3፥1-6 | 1፥2-6 | 3፥3-6 | |
| ለፈሪሳውያን፣ ለሰዱቃውያን፣ ለሕዝቡ፣ ለቀረጥ ሰብሳቢዎችና ለወታደሮች የነበረው መልእክት | 3፥7-10 | | 3፥7-14 | |
| ስለ ክርስቶስ የነበረው ገለጻ | 3፥11-12 | 1፥7-8 | 3፥15-18 | |
| **የዮሐንስ አገልግሎት ማብቂያና የክርስቶስ የአደባባይ አገልግሎት ጅማሬ** | | | | |
| የኢየሱስ በዮሐንስ መጠመቅ | 3፥13-17 | 1፥9-11 | 3፥21-23 | |
| ኢየሱስ በምድረ በዳ መፈተን | 4፥1-11 | 1፥12-13 | 4፥1-13 | |
| ዮሐንስ ስለ ራሱ ለካህናትና ለሌዋውያን የሰጠው ምስክርነት | | | | 1፥19-28 |
| ዮሐንስ፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆኑ የሰጠው ምስክርነት | | | | 1፥29-34 |
| የመጀመሪያዎቹ የኢየሱስ ታምር፦ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ መቀየሩ | | | | 2፥1-11 |
| ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ ከእናቱ፣ ከወንድሞቹና ከመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ቅፍርናሆም ሄደ | | | | 2፥12 |
| በፋሲካ በዓል ጊዜ የተደረገ የመጀመሪያው ቤተ መቅደስን ማንጻት | | | | 2፥13-22 |
| ለኢየሱስ ታምራት ሰዎች የነበራቸው የመጀመሪያው ምላሽ | | | | 2፥23-25 |
| ኒቆዲሞስ ለኢየሱስ ያደረገው ቃለ መጠይቅ | | | | 3፥1-21 |
| ዮሐንስ በኢየሱስ መተካቱ | | | | 3፥22-36 |
| ኢየሱስ የይሁዳን ምድር ትቶ መሄዱ | 4፥12 | 1፥14 | 3፥19-20፤4፥14 | 4፥1-4 |
| ከሳምራዊቷ ሴት ጋር የተደረገ ውይይት | | | | 4፥5-26 |
| የመንፈሳዊ መከር ተግዳሮቶች | | | | 4፥27-38 |
| በሲካር የተካሄደ የወንጌል ሥርጭት | | | | 4፥39-42 |
| የኢየሱስ ገሊላ መድረስ | | | | 4፥43-45 |
| **የኢየሱስ ክርስቶስ የገሊላ አገልግሎቱ** | | | | |
| *ተቃውሞ ከቤት ተነሣ፤ አዲስ የአልገግሎት በር ተከፈተ* | | | | |
| የገሊላው አገልግሎት ባሕርይ | 4፥17 | 1፥14-15 | 4፥14-15 | |
| ኢየሱስ በቃና ሆኖ በቅፍርናሆም የነበረውን ልጅ መፈወሱ | | | | 4፥46-54 |
| ተቃውሞና አገልግሎት በናዝሬት | | | 4፥16-31 | |
| ወደ ቅፍርናሆም መዛወር | 4፥13-16 | | | |

## የወንጌላት ስምምነት

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ |
|---|---|---|---|---|
| ***የደቀመዛሙርት መጠራትና አገልግሎት በገሊላ ምድር*** | | | | |
| የአራቱ መጠራት | 4፥18-22 | 1፥16-20 | 5፥1-11 | |
| በቅፍርናሆም ምኵራቦች የተሰጠው ትምህርት አጋንንትን በማስወጣት እውነተኛነቱ ተረጋገጠ | | 1፥21-28 | 4፥31-37 | |
| የጴጥሮስ ዐማትና ሌሎች ተፈወሱ | 8፥14-17 | 1፥29-34 | 4፥38-41 | |
| ከስምዖንና ከሌሎች ጋር ወደ ገሊላ የተደረገ ጕዞ | 4፥23-25 | 1፥35-39 | 4፥42-44 | |
| የለምጻሙ መንጻትና ነገሩ በአደባባይ መታወቁ | 8፥2-4 | 1፥40-45 | 5፥12-16 | |
| ሽባው ይቅርታን ማግኘቱና መፈወሱ | 9፥1-8 | 2፥1-12 | 5፥17-26 | |
| የማቴዎስ መጠራት | 9፥9 | 2፥13-14 | 5፥27-28 | |
| በማቴዎስ ቤት የተደረገው ግብዣ | 9፥10-13 | 2፥15-17 | 5፥29-32 | |
| ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ለምን እንደማይጸሙ በሦስት ምሳሌዎች ገለጸ | 9፥14-17 | 2፥18-22 | 5፥33-39 | |
| ***ሰንበትን በተመለከተ የተነሣ ክርክር*** | | | | |
| ኢየሱስ በሰንበት ቀን ፈወሰ | | | | 5፥1-9 |
| ኢየሱስ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል በማድረጉና ሰንበትን በመሻሩ ለመግደል የተደረገ ሙከራ | | | | 5፥10-18 |
| ወልድ ከአብ ጋር እኩል መሆኑን ለማስረገጥ የተሰጠ ትምህርት | | | | 5፥19-47 |
| ደቀ መዛሙርት በሰንበት ቀን እሸት በመቅጠፋቸው ምክንያት የተነሣ ክርክር | 12፥1-8 | 2፥23-28 | 6፥1-5 | |
| እጁ የሰለለችበት ሰው በሰንበት ቀን ተፈወሰ | 12፥9-14 | 3፥1-6 | 6፥6-11 | |
| ከብዙ ስፍራ ካመጡ እጅግ ብዙ ሰዎች ጋር ወደ ገሊላ ባሕር ሄደ | 12፥15-21 | 3፥7-12 | | |
| ***የዐሥራ ሁለቱ መመረጥና የተራራው ስብከት*** | | | | |
| የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መመረጥ | | 3፥13-19 | 6፥12-16 | |
| የስብከቱ ቦታ | 5፥1-2 | | 6፥17-19 | |
| መንግሥተ ሰማያት የሚወርሱ ሰዎች በረከትና የማይወርሱ ሰዎች ወዮታ | 5፥3-12 | | 6፥20-26 | |
| መንግሥቱን ለሚጠባበቁ የተሰጣቸው ኀላፊነት | 5፥13-16 | | | |
| ሕግ፣ ጽድቅና መንግሥተ ሰማያት | 5፥17-20 | | | |
| የሕግን አተረጓጎም በተመለከተ ስድስት ንጽጽሮች | 5፥21-48 | | 6፥27-30:32-36 | |
| የጽድቅን ሥራ በተመለከተ ሊወገዱ የሚገባቸው ሦስት "የግብዝነት" | 6፥1-18 | | | |
| ሀብት፣ ተገቢ ያልሆነ ፍርድና የተቀደሱትን ነገሮች አግባብ ባልሆነ መንገድ መጠቀም የሚከለክሉ ሦስት እገዳዎች | 6፥19-7፥6 | | 6፥37-42 | |
| የሕይወት ተዛምዶና ድምዳሜ | 7፥7-27 | | 6፥31:43-49 | |
| የሕዝቡ ምላሽ | 7፥28-8፥1 | | | |
| ***የዝናው መጨመሩና ንስሓን አጽንዖት ሰጥቶ ማስተማሩ*** | | | | |
| የመቶ አለቃው እምነትና የአገልጋዩ መፈወስ | 8፥5-13 | | 7፥1-10 | |
| በናይን ከተማ የመበለቲቱ ልጅ ከሞት መነሣት | | | 7፥11-17 | |
| መጥምቁ ዮሐንስ ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር ያለው ግንኙነት | 11፥2-19 | | 7፥18-35 | |
| ኮራዚና ቤተ ሳይዳ ንስሓ ባለመግባታቸው ወዮ ተባለላቸው | 11፥20-30 | | | |
| በኀጢአቷ እጅግ ባዘነች ሴት የክርስቶስ እግር በሽቱ ተቀባ | | | 7፥36-50 | |
| ***የአይሁድ መሪዎች የመጀመሪያው የአደባባይ ተቃውሞ*** | | | | |
| ከዐሥራ ሁለቱና ከሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ጋር የተደረገ ጕዞ | | | 8፥1-3 | |
| የሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን በጽርፈት ተወነጀሉ | 12፥22-37 | 3፥20-30 | | |
| ምልክት ለማየት የተቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት አለማግኘት | 12፥38-45 | | | |
| አዲስ ስለ ሆነው መንፈሳዊ ዝምድና የቀረበው ንግግር | 12፥46-50 | 3፥31-35 | 8፥19-21 | |
| ***ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ምስጢር የቀረቡ ምሳሌዎች በባሕሩ አጠገብ ለሕዝቡ የተነገሩ*** | | | | |
| የምሳሌዎቹ መቼት (ምሳሌዎቹ የተነገሩበት ቦታ፣ ጊዜና ሁኔታ) | 13፥1-3 | 4፥1-2 | 8፥4 | |
| የዘሪው ምሳሌ | 13፥3-23 | 4፥3-25 | 8፥5-18 | |
| በግብታዊነት የሚያድገው ዘር ምሳሌ | | 4፥26-29 | | |
| የእንክርዳዱ ምሳሌ | 13፥24-30 | | | |
| የሰናፍጩ ዘር ምሳሌ | 13፥31-32 | 4፥30-32 | | |
| የእርሾው ምሳሌ | 13፥33-35 | 4፥33-34 | | |
| ***በቤት ውስጥ ለደቀ መዛሙርት የተነገሩ*** | | | | |
| የእንክርዳዱ ምሳሌ ፍቺ | 13፥36-43 | | | |
| የተደበቀው ሀብት ምሳሌ | 13፥44 | | | |
| የከበረው የዕንቍ ምሳሌ | 13፥45-46 | | | |

| የወንጌላት ስምምነት | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ |
|---|---|---|---|---|
| የመረቡ ምሳሌ | 13፥47-50 | | | |
| የቤቱ ባለቤት ምሳሌ | 13፥51-53 | | | |
| ***የተቃውሞው መቀጠል*** | | | | |
| ባሕሩን ማቋረጥና ማዕበሉን ጸጥ ማድረግ | 8፥18:23-27 | 4፥35-41 | 8፥22-25 | |
| በጌርጌሴኖን አገር አጋንንት ያደሩባቸው ሁለት ሰዎች መፈወሳቸውና ፈውሱ ያስከተለው ተቃውሞ | 8፥28-34 | 5፥1-20 | 8፥26-39 | |
| ወደ ገሊላ መመለሱ፣ የኢየሱስን ልብስ ዳሳ የተፈወሰችው ሴትና የኢያኢሮስ ሴት ልጅ ከሞት መነሣቷ | 9፥18-26 | 5፥21-43 | 8፥40-56 | |
| ሦስት የፈውስ ታምራትና ዳግም እግዚአብሔርን ስለመጻረፍ የቀረበ ክስ | 9፥27-34 | | | |
| ወደማታምነው ናዝሬት የተደረገ የመጨረሻ ጉዞ | 13፥54-58 | 6፥1-6 | | |
| ***የመጨረሻው የገሊላ ስብሰባ*** | | | | |
| የሠራተኞች ማነስ | 9፥35-38 | 6፥6 | | |
| የዐሥራ ሁለቱ ተልእኮ | 10፥1-42 | 6፥7-11 | 9፥1-5 | |
| የሠራተኞች መላክ | 11፥1 | 6፥12-13 | 9፥6 | |
| ሄሮድስ ስለ ኢየሱስ ማንነት የነበረው የተሳሳተ ግንዛቤ | 14፥1-2 | 6፥14-16 | 9፥7-9 | |
| የመጥምቁ ዮሐንስ መታሰርና ዘመንና ዐንገቱ ስለመቀላቱ | 14፥3-12 | 6፥17-29 | | |
| **የክርስቶስ አገልግሎት በገሊላ አካባቢ** | | | | |
| ***ስለ ሕይወት እንጀራ የተሰጠ ትምህርት*** | | | | |
| የሠራተኞቹ መመለስ | | 6፥30 | 9፥10 | |
| ከገሊላ ወጥቶ መሄድ | 14፥13-14 | 6፥13-34 | 9፥10-11 | 6፥1-3 |
| አምስት ሺህ ሰዎችን መመገቡ | 14፥15-21 | 6፥35-44 | 9፥12-17 | 6፥4-13 |
| ኢየሱስን ንጉሥ ለማድረግ ተሞክሮ በእንጭ ጭንቱ የተቀጨው ሙከራ | 14፥22-23 | 6፥45-46 | | 6፥14-15 |
| የባሕሩ ማዕበል በተነሣ ጊዜ በውሃው ላይ መራመዱ | 14፥24-33 | 6፥47-52 | | 6፥16-21 |
| በጌንሴሬጥ የተደረገ ፈውስ | 14፥34-36 | 6፥53-56 | | |
| ስለ ሕይወት እንጀራ የተሰጠ ትምህርት | | | | 6፥22-59 |
| ከደቀ መዛሙርት መካከል አንዳንዱ ወደ ኋላ አፈገፈገ | | | | 6፥60-71 |
| ***ከፈሪሳውያን፣ ከሰዱቃውያንና ከሄሮድስ ሰዎች እርሾ ስለመጠበቅ*** | | | | |
| አለመንጻትን በተመለከተ በትውፊት ላይ የተደረገ ክርክር | 15፥1-3:7-9: 3-6:10-20 | 7፥1-23 | | 7፥1 |
| በጢሮስና በሲዶና አገር ያመነችው ግሪካዊት ሴት | 15፥21-28 | 7፥24-30 | | |
| በዐሥሩ ከተሞች የተደረገ ፈውስ | 15፥29-31 | 7፥31-37 | | |
| አራት ሺህ ሰዎችን በዐሥሩ ከተሞች መመገቡ | 15፥32-38 | 8፥1-9 | | |
| ወደ ገሊላ መመለሱና ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ጋር መገናኘቱ | 15፥39-16፥4 | 8፥9-12 | | |
| ለፈሪሳውያን፣ ለሰዱቃውያንና ለሄሮድስ ሰዎች የተሰጠ ማስጠንቀቂያ | 16፥5-12 | 8፥13-21 | | |
| ዐይነ ሥውሩን በቤተ ሳይዳ መፈወሱ | | 8፥22-26 | | |
| ***ስለ መሲሑ የተሰጠ ትምህርትና የትምህርቱ አጽንዖት*** | | | | |
| ጴጥሮስ ኢየሱስ መሲሑ መሆኑን ማወቁና ለቤተ ክርስቲያን የተነገረው የመጀመሪያው ትንቢት | 16፥13-20 | 8፥27-30 | 9፥18-21 | |
| ስለ መነቀፉ፣ ስለ መሰቀሉና ስለ ትንሣኤው ለመጀመሪያ በቀጥታ የተነገረ ትንቢት | 16፥21-26 | 8፥31-37 | 9፥22-25 | |
| የሰው ልጅ ምዕጽአትና ፍርድ | 16፥27-28 | 8፥38-9፥1 | 9፥26-27 | |
| የኢየሱስ መለወጥ | 17፥1-8 | 9፥2-8 | 9፥28-36 | |
| ትንሳኤን፣ ኤልያስንና መጥምቁ ዮሐንስን በተመለከተ የተነሣ ክርክር | 17፥9-13 | 9፥9-13 | 9፥36 | |
| ***ሌሎች ሰዎችን በተመለከተ የተሰጠ ኀላፊነት*** | | | | |
| ጋኔን ያደረበት ልጅ መፈወሱና ስለ አለማመን የቀረበ ተግሣጽ | 17፥14-20 | 9፥14-29 | 9፥37-43 | |
| ስለ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ የተነገረ ሁለተኛ ትንቢት | 17፥24-27 | 9፥30-32 | 9፥43-45 | |
| ለቤተ መቅደስ የሚከፈል ግብር | 17፥24-27 | | | |
| በመንግሥተ ሰማይ የእኔ እበልጥ ፉክክር | 18፥1-5 | 9፥33-37 | 9፥46-48 | |
| ለኀጢአት ምክንያት ስለሚሆኑ ነገሮች የተሰጠ ማስጠንቀቂያ | 18፥6-14 | 9፥38-50 | 9፥49-50 | |
| ወንድምን የማስናከል ኀጢአት ይቅርታና መፍትሔው | 18፥15-35 | | | |
| ***ለዳስ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም የተደረገ ጉዞ*** | | | | |
| ከደቀ መዛሙርት የሚጠበቅ ፍጹም መሰጠት | 8፥19-22 | | 9፥57-62 | |
| የኢየሱስ ወንድሞች ፌዝ | | | | 7፥2-9 |
| በሰማርያ በኩል የተደረገ ጉዞ | | | 9፥51-56 | 7፥10 |

## የወንጌላት ስምምነት

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ |
|---|---|---|---|---|
| **ክርስቶስ በይሁዳ ያገለገለባቸው የኋለኞች ጊዜያት** | | | | |
| *በዳስ በዓል የጀመረው አገልግሎት* | | | | |
| የኢየሱስ ትምህርትና ታምር ያስከተሏቸው የተለያዩ ውጤቶች | | | | 7፥11-31 |
| ኢየሱስን ለመያዝ የተደረገ ሙከራ | | | | 7፥32-52 |
| ኢየሱስ በዝሙት የተያዘችውን ሴት ይቅር አለ | | | | (7፥53-8፥11) |
| ኢየሱስ የዓለም ብርሃን ነኝ ማለቱ ያስነሣው ክርክር | | | | 8፥12-20 |
| ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ጋር ያለው ግንኙነት | | | | 8፥21-30 |
| ኢየሱስ ከአብርሃም ጋር የነበረው ግንኙነትና በድንጋይ ለመውገር የተደረገው ሙከራ | | | | 8፥31-59 |
| ከመወለዱ ጀምሮ ዐይነ ሥውር የነበረው ሰው | | | | 9፥1-7 |
| የዐይነ ሥውሩ ጎረቤቶች ምላሽ | | | | 9፥8-12 |
| ፈሪሳውያን በዐይነ ሥውሩ ሰው ላይ ያደረጉት ምርመራና ማባረር | | | | 9፥13-34 |
| ኢየሱስ ለዕውሩ ሰው ራሱን አስተዋወቀ | | | | 9፥35-38 |
| የፈሪሳውያን መንፈሳዊ ዕውርነት | | | | 9፥39-41 |
| ስለ መልካም እረኛና ሌባ | | | | 10፥1-18 |
| በአይሁዶች መካከል የተካሄደው ተጨማሪ ክፍፍል | | | | 10፥19-21 |
| *ስለ ፍቅር አገልግሎትና ስለ ጸሎት ለግለሰቦች የተሰጠ ትምህርት* | | | | |
| የሰባዎቹ ተልእኮ | | | 10፥1-16 | |
| የሰባዎቹ መመለስ | | | 10፥17-24 | |
| የደጉ ሳምራዊ ታሪክ | | | 10፥25-37 | |
| ኢየሱስ ማርያምንና ማርታን ጎበኘ | | | 10፥38-42 | |
| ስለ ጸሎት የተሰጠ ትምህርትና የግልጹ ወዳጅ ታሪክ | | | 11፥1-3 | |
| *ከሕግ መምህራንና ከፈሪሳውያን ጋር የተደረገ ሁለተኛ ክርክር* | | | | |
| እግዚአብሔርን የመጻረፍ ሦስተኛው ክስና ሁለተኛው ክርክር | | | 11፥14-36 | |
| ከፈሪሳዊው ጋር እየበላ ለፈሪሳውያንና ለሕግ መምህራን ወዮ አለ | | | 11፥37-54 | |
| ለደቀ መዛሙርት ስለ ግብዝነት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ | | | 12፥1-12 | |
| የሰው ልጅን ምጽአት ተዘጋጅቶ ባለመጠበቅ ላይ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ | | | 12፥35-48 | |
| ስለሚመጣው ክፍፍል የተሰጠ ማስጠንቀቂያ | | | 12፥49-53 | |
| የአሁኑን ጊዜ ባለ መለየት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ | | | 12፥54-59 | |
| ሁለቱ አማራጮች:- ንስሓ መግባት ወይም መጥፋት | | | 13፥1-9 | |
| አንዲት ሴት በሰንበት ቀን ስለ ተፈወሰች የምኵራብ አለቆች ያስነሡት ተቃውሞ | | | 13፥10-21 | |
| በቤተ መቅደስ መታደስ በዓል ኢየሱስ እግዚአብሔርን ተጻርፎአል በሚል እርሱን ለማሰር ወይም በድንጋይ ለመውገር የተደረገ ሙከራ | | | | 10፥22-39 |
| **ብፔሪያና አካባቢው የክርስቶስ አገልግሎት** | | | | |
| *የደቀ መዝሙርነት መርሆች* | | | | |
| ከኢየሩሳሌም እስከ ፔሪያ | | | | 10፥40-42 |
| ስለ ድነትና መንግሥተ ሰማይ ስለ መግባት የቀረበ ጥያቄ | | | 13፥22-30 | |
| የኢየሱስ ሞት መቃረብና ለኢየሩሳሌም ያዘነው ሐዘን | | | 13፥31-35 | |
| ኢየሱስ በሰንበት ቀን ከፈሪሳውያን አለቆች ወደ አንዱ ቤት ምሳ ሲበላ ሰውነቱ የሚያብጥበትን ሰው መፈወሱና በዚያን ወቅት የተናገራቸው ሦስት ምሳሌዎች | | | 14፥1-24 | |
| ደቀ መዝሙር ሊከፍለው የሚገባው ዋጋ | | | 14፥25-35 | |
| ከኀጢአተኞች ጋር ኅብረት ማድረግ ተገቢ እንደ ሆነ ለማሳየት የተሰጠ ምሳሌ | | | 15፥1-32 | |
| ገንዘብን በተገቢው መንገድ ስለመጠቀም የተሰጠ ምሳሌ | | | 16፥1-13 | |
| ስለ ገንዘብ አደገኝነት ለማስተማር የተሰጠ ታሪክ | | | 16፥14-31 | |
| ስለ ደቀ መዛሙርነት የተሰጡ አራት ትምህርቶች | | | 17፥1-10 | |
| የአልዓዛር መታመምና መሞት | | | | 11፥1-16 |
| የአልዓዛር ከሞት መነሣት | | | | 11፥17-44 |
| ሸንጎው ኢየሱስ እንዲሞት በየነ | | | | 11፥45-54 |
| *ወደ ኢየሩሳሌም ለመጨረሻ ጊዜ በሚሄድበት ወቅት ያስተማረው ትምህርት* | | | | |
| በሰማርያና በገሊላ በኵል ሲያልፍ ዐሥር ለምጻሞችን ፈወሰ | | | 17፥11-21 | |
| የሰው ልጅ ምጽአትን/በተመለከተ የተሰጠ ትምህርት | | | 17፥22-37 | |
| ስለ ጸሎት፣ የተሰጡ ሁለት ምሳሌዎች:- ድኻዋ መበለትና ዐመፀኛው ዳኛ እንዲሁም ፈሪሳዊውና ቀረጥ ሰብሳቢው | | | 18፥1-14 | |
| በስስታምነትና በገንዘብ ስለ መመካት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ | | | 12፥13-34 | |

## የወንጌላት ስምምነት

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ |
|---|---|---|---|---|
| ከፈሪሳውያን የፍቺ ትምህርት ጋር የተደረገ ፍጥጫ | 19፥1-12 | 10፥1-12 | | |
| መንግሥተ ሰማይን በተመለከተ የሕፃናት ምሳሌ | 19፥13-15 | 10፥13-16 | 18፥15-17 | |
| መንግሥተ ሰማይና ባለ ጠግነት | 19፥16-30 | 10፥17-31 | 18-18-30 | |
| የመሬት ባለቤቱ ሉዓላዊነት ምሳሌ | 20፥1-16 | | | |
| ስለ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተነገረው ሦስተኛው ትንቢት | 20፥17-19 | 10፥32-34 | 18፥31-34 | |
| ከፍ ማለትን ለሚፈልጉ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ | 20፥20-28 | 10፥35-45 | | |
| በርጤሜዎስና ጓደኛው ተፈወሱ | 20፥29-34 | 10፥46-52 | 18፥35-43 | |
| የዘኬዎስ መዳን | | | 19፥1-10 | |
| መንግሥተ ሰማይ በምትዘገይባት ጊዜ ኀላፊነትን ስለመወጣት የተሰጠ ምሳሌ | | | 19፥11-28 | |
| **ኢየሱስ በክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱና የበለሲቱ ዛፍ** | | | | |
| ቢታንያ ደረሰ | | | | 11:55-12፥1: 9-11 |
| በክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ | 21፥1-3:6-7: 4-5:8-11: 14-17 | 11፥1-11 | 19፥29-44 | 12፥12-19 |
| ፍሬ ስለሌላት የተረገመችው የበለስ ዛፍ | 21፥18-19 | 11፥12-14 | | |
| ቤተ መቅደስን ዳግም ማጽዳቱ | 21፥12-13 | 11፥15-18 | 19፥45-48 | |
| ጥቂት ግሪካውያን ኢየሱስን ለማየት ያቀረቡት ጥያቄና የሰው ልጅ ከፍ ከፍ የማለቱ አስፈላጊነት | | | | 12፥20-36 |
| ሰዎች ስለ ኢየሱስ የነበራቸው የተለያዩ ምላሾችና ኢየሱስ ስለ ሕዝቡ የነበረው ምላሽ | | | | 12፥36-50 |
| የበለሲቱ ዛፍ መድረቅና ስለ እምነት የተሰጠ ትምህርት | 21፥19-22 | 11፥19-25 | 21፥37-38 | |
| *ስለ ክርስቶስ ባለ ሥልጣንነት በግልጽ የቀረበ ጥያቄ* | | | | |
| የኢየሱስ ክርስቶስን ሥልጣን በተመለከተ ካህናት፣ የሕግ መምህራንና ሽማግሌዎች የጠየቁት ጥያቄ | 21፥23-27 | 11፥27-33 | 20፥1-8 | |
| ኢየሱስ ለራሱ ጥያቄ የመለሰው መልስና ሦስቱ ምሳሌዎች | 21፥28-22፥14 | 12፥1-12 | 20፥9-19 | |
| ኢየሱስን ለማጥመድ ፈሪሳውያንና የሄሮድስ ሰዎች ለቄሳር ቀረጥ ስለ መክፈል የጠየቁት ጥያቄ | 22፥15-22 | 12፥13-17 | 20፥20-26 | |
| ትንሣኤን አስመልክቶ ሰዱቃውያን ግራ የተጋቡበት ጥያቄ | 22፥23-33 | 12፥18-27 | 20፥27-40 | |
| የፈሪሳውያን ሕጋዊ ጥያቄ | 22፥34-40 | 12፥28-34 | | |
| *ለጠላቶቹ ተግዳሮት ኢየሱስ የመለሰው መልስ* | | | | |
| እንደ ልጅና እንደ ጌትነቱ ኢየሱስ ከዳዊት ጋር የነበረው ግንኙነት | 22፥41-46 | 12፥35-37 | 20፥41-44 | |
| የሕግ መምህራንንና ፈሪሳውያንን በተመለከተ የቀረቡ ሰባት ወዮታዎች | 23፥1-36 | 12፥38-40 | 20፥45-47 | |
| ኢየሱስ ለኢየሩሳሌም ያዘነው ሐዘን | 23፥37-39 | | | |
| ድኻዋ መበለት ያላትን ሁሉ ሰጠች | | 12፥41-44 | 21፥1-4 | |
| **ስለ ክርስቶስ ሞት የተነገሩ ትንቢቶች** | | | | |
| *የደብረ ዘይት ተራራ ትምህርት:- ኢየሱስ ስለ ቤተ መቅደሱና ስለ ዳግም ምጽአቱ የተናገረው ትንቢት* | | | | |
| ትምህርቱ የተሰጠበት ቦታና ጊዜ (መቼት) | 24፥1-3 | 13፥1-4 | 21፥5-7 | |
| የምጥ ጣር መጀመሪያ | 24፥4-14 | 13፥5-13 | 21፥8-19 | |
| የጥፋት እርኩሰትና የጓለኛው ጭንቀት | 24፥15-28 | 13፥14-23 | 21፥20-24 | |
| የሰው ልጅ ምጽአት | 24፥29-31 | 13፥24-27 | 21፥25-27 | |
| የቀረቤታው ምልክቶች ነገር ግን የጊዜው አለመታወቅ | 24፥32-41 | 13፥28-32 | 21፥28-33 | |
| ነቅቶ ስለ መጠበቅና ስለ ታማኝነት የተሰጡ አምስት ምልክቶች | 24፥42-25፥30 | 13፥33-37 | 21፥34-36 | |
| የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ የሚሆነው ፍርድ | 25፥31-46 | | | |
| *አሳልፎ ለመስጠት የተደረገ ዝግጅት* | | | | |
| ኢየሱስን ለማሰርና ለመግደል የሸንጎው ሤራ | 26፥1-5 | 14፥1-2 | 22፥1-2 | |
| ማርያም ኢየሱስን ለሞቱ ሽቱ መቀባቷ | 26፥6-13 | 14፥3-9 | | 12፥2-8 |
| ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት መስማማቱ | 26፥14-16 | 14፥10-11 | 23፥3-6 | |
| *የመጨረሻው ራት* | | | | |
| የፋሲካ መብል ዝግጅት | 26፥17-19 | 14፥12-16 | 22፥7-13 | |
| የፋሲካው መብል ጅማሬና ታላቅነትን አስመልክቶ በደቀ መዛሙርት መካከል የተደረገ ክርክር | 26፥20 | 14፥17 | 22፥14-16፥24-30 | |
| የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ | | | | 13፥1-20 |
| አሳልፎ የሚሰጠው መታወቅ | 26፥21-25 | 14፥18-21 | 22፥21-23 | 13፥21-30 |

## የወንጌላት ስምምነት

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ |
|---|---|---|---|---|
| ጴጥሮስ እንደሚክድ የተነገረ ትንቢት | 26፥31-35 | 14፥27-31 | 22፥32-38 | 13፥31-38 |
| የማዕዱ ፍጻሜና የጌታ ራት መከበር (1ቆሮ11፥23-26) | 26፥26-29 | 14፥22-25 | 22፥17-20 | |
| ***የፋሲካ ራት ከተበላበት እስከ ጌቴሴማኒ የተደረገ ትምህርትና ጸሎት*** | | | | |
| ስለሚሄድበት፣ ስለ አብና ስለ መንፈስ ቅዱስ ለተጠየቁ ጥያቄዎች መልስ | | | | 14፥1-31 |
| የወይኑ ግንድና ቅርንጫፎቹ | | | | 15፥1-17 |
| የዓለም ተቃውሞ | | | | 15፥18-16፥4 |
| የመንፈስ ቅዱስ ምጸትና አገግሎቱ | | | | 16፥16-22 |
| ጸሎት እንደሚመለስና ሰላም እንደሚሰጠን የተነገረ ተስፋ | | | | 16፥23-33 |
| ኢየሱስ ለደቀ መቷሙርቱና ለሚያምኑት ሁሉ የጸለየው ጸሎት | | | | 17፥1-26 |
| ኢየሱስ በጌቴሴማኒ ሦስት ጊዜ የጸለየው የጣር ጸሎት | 26፥30:36-46 | 14፥26፤32-42 | 22፥39-46 | 18፥1 |
| **የክርስቶስ ሞት** | | | | |
| ***አልፎ መሰጠቱና መታሰሩ*** | | | | |
| ኢየሱስ አልፎ ተሰጠ፣ ታሰረ እንዲሁም ተተወ | 26፥47-56 | 14፥43-52 | 22፥47-53 | 18፥2-12 |
| ***ሥቃዩ*** | | | | |
| በመጀመሪያ ጊዜ የአይሁድ ክስ- በሐና ፊት | | | | 18፥13-14፤19-23 |
| ሁለተኛው ጊዜ የአይሁድ ክስ- በቀያፋና በሸንጎ ፊት | 26፥57:59-68 | 14፥53:55-65 | 22፥54:63-65 | 18፥24 |
| የጴጥሮስ ክህደት | 26፥58:59-75 | 14፥54:66-72 | 22፥54-62 | 18፥15-18:25-27 |
| የሦስተኛው የአይሁድ ክስ- በሸንጎ ፊት | 27፥1 | 15፥1 | 22፥66-71 | |
| የአስቆሮቱ ይሁዳ መጸጸትና ራሱን መግደሉ (ሐሥ1፥18-19) | 27፥3-10 | | | |
| የመጀመሪያው በሮማውያን ፊት- በጲላጦስ ፊት | 27፥2:11-14 | 15፥1-5 | 23፥1-5 | 18፥28-38 |
| የሁለተኛው በሮማውያን ፊት- በሄሮድስ አንቲጳስ ፊት | | | 23፥6-12 | |
| የሦስተኛው በሮማውያን ፊት- በጲላጦስ ፊት | 27፥15-26 | 15፥6-15 | 23፥13-25 | 18፥39-19፥16 |
| ***ስቅለቱ*** | | | | |
| የሮማውያን ወታደሮች ተሳለቁበት | 27፥27-30 | 15፥16-19 | | |
| ጉዞ ወደ ጎልጎታ | 27፥31-34 | 15፥20-23 | 22፥26-33 | 19፥16-17 |
| የስቅለቱ የመጀመሪያዎቹ ሦስት ሰዓታት | 27፥35-44 | 15፥24-32 | 23፥33-43 | 19፥18:23-24:19-22:25-27 |
| የስቅለቱ የመጨረሻዎቹ ሦስት ሰዓታት | 27፥45-50 | 15፥33-37 | 23፥44-45:46 | 19፥28-30 |
| የኢየሱስ ሞት ምስክሮች | 27፥51-56 | 15፥38-41 | 23፥45:47-49 | |
| ***መቀበሩ*** | | | | |
| የኢየሱስ መሞት መረጋገጡና በድኑን መቀበላቸው | 27፥57-58 | 15፥42-45 | 23፥50-52 | 19፥31-38 |
| የኢየሱስ በድን በመቃብር ዐረፈ | 27፥59-60 | 15፥46 | 23፥53-54 | 19፥39-42 |
| መቃብሩ በሴቶች መጎብኘቱና በወታደሮች መጠበቁ | 27፥61-66 | 15፥47 | 23፥55-56 | |
| **የክርስቶስ ትንሣኤና ዕርገት** | | | | |
| ***ባዶው መቃብር*** | | | | |
| መቃብሩ በሴቶች ተጎበኘ | 28፥1 | 16፥1 | | |
| የመቃብሩ ድንጋዩ ተንከባለለ | 28፥2-4 | | | |
| ሴቶቹ መቃብሩ ባዶ ሆኖ አገኙት | 28፥5-8 | 16፥2-8 | 24፥1-8 | 20፥1 |
| ጴጥሮስና ዮሐንስ መቃብሩ ባዶ ሆኖ አገኙት | | | 24፥9-12 | 20፥2-10 |
| ***ከትንሣኤው በኋላ መታየቱ*** | | | | |
| ለመግደላዊት ማርያም መታየቱ | | [16፥9-11] | | 20፥11-18 |
| ለሌሎች ሴቶች መታየቱ | 28፥9-10 | | | |
| ወታደሮች ለአይሁድ ባለ ሥልጣናት አመለከቱ | 28፥11-15 | | | |
| ወደ ኤማሁስ ለሚጓዙት ሁለት ደቀ መዛሙርት መታየቱ | | [16፥12-13] | 24፥13-32 | |
| ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ለሌሎቹ ይዘውት የመጡት የምሥራች (1ቆሮ 15፥5) | | | 24፥33-35 | |
| ዐሥሩ ደቀ መዛሙርት አብረው ሳሉ መታየቱ | | [16፥14] | 24፥36-43 | 20፥19-25 |
| ዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት አብረው ሳሉ መታየቱ (1ቆሮ 15፥5) | | | | 20፥26-31 |
| ዓሣ በማጥመድ ላይ ለነበሩት ሰባት ደቀ መዛሙርት መታየቱ | | | | 21፥1-25 |
| ለዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት በገሊላ መታየቱ (1ቆሮ 15፥6) | 28፥16-20 | [16፥15-18] | | |
| ለኢየሱስ ወንድም ለያዕቆብ መታየቱ (1ቆሮ 15፥7) | | | | |
| በኢየሩሳሌም ለነበሩት ደቀ መዛሙርት መታየቱ (ሐሥ 1፥3-8) | | | 24፥44-49 | |
| ***ዕርገቱ*** | | | | |
| የክርስቶስ ባርኮትና ዕርገት (ሐሥ 1፥9-12) | | [16፥19-20] | 24፥50-53 | |

# ተመሳሳዮቹ ወንጌላት

አራቱን ወንጌላት በጥንቃቄ ስናነጻጽር የማቴዎስ፣ የማርቆስና የሉቃስ ወንጌላት ተመሳሳይ ሆነው እናገኛቸዋለን:: የዮሐንስ ወንጌል ግን ከእነዚህ ሦስት ወንጌላት ይለያል:: በቋንቋቸው፣ በይዘታቸውና በቅደም ተከተላቸው (ኢየሱስ የተናገራቸውንና ያደረጋቸውን ነገሮች ሲያወሱ) ተመሳሳይ ናቸው:: በእርግጥ የታሪኩን ቅደም ተከተል ሲያወሱ ሦስቱም ወንጌላት ተመሳሳይ ናቸው ማለት አይቻልም:: ወንጌላቱ በእነዚህ ነገሮች ተመሳሳይ በመሆናቸው "ተመሳሳዮቹ ወንጌላት" የሚል ስም ተሰጥቶአቸዋል:: በይዘታቸው ምን ያህል እንደሚመሳሰሉ ማቴ9፥2-8፤ ማር2፥3-12፤ ሉቃ5፥18-26 ይመ:: በማቴ10፥22፤ ማር13፥13፤ ሉቃ2፥17 ላይ ቃል በቃል ተመሳሳይ የሆኑ ነገሮች ይገኛሉ:: የወንጌላቱ ተመሳሳይነት በስሌት ቢቀመጥ፣ 91 በመቶ የሚሆነው የማርቆስ ወንጌል በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ይገኛል፤ ደግሞም 53 በመቶ የሚሆነው የማርቆስ ወንጌል በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ይገኛል:: ይህም የተመሳሳይ ወንጌላቱ ምንጭ ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ያስነሣል:: የሚነሣውም ጥያቄ፣ የእነዚህ ወንጌላት ጸሓፊዎች የጋራ ምንጭ ነበራቸውን? ወይስ እያንዳንዳቸው የራሳቸው የሆነ ምንጭ ነበራቸው? የሚል ነው:: እንዲህ ዐይነቱ ጥያቄ "የተመሳሳዮቹ ወንጌላት ውዝግብ" ይባላል:: በዚህ ጉዳይ ላይ በርካታ መልሶች ተሰጥተዋል:-

1. የወንጌላቱ ምንጭ ሥነ ቃል ነው:- በጥንቱ ዓለም ሥነ ቃሎች ትልቅ ቦታ ስለ ነበራቸው ጸሓፊዎቹ በዚህ ረገድ የጋራ ምንጮችን ተጠቅመዋል::

2. የወንጌላቱ ምንጭ ከእነርሱ በፊት የተጻፈ ወንጌል ነው:- አንዳንድ ሰዎች እነዚህ ወንጌሎች ከመጻፋቸው በፊት አንድ ሌላ ወንጌል ነበር ይላሉ፤ ጸሓፊዎቹ ወንጌሎቻቸውን የጻፉት በአንድ ወቅት የነበረውን በኋላ ግን የጠፋውን ወንጌል መሠረት አድርገው ነው ይላሉ::

3. የወንጌላቱ ምንጭ እዚህም እዚያም ተበታትነው የሚገኙ ጽሑፎች ናቸው:- አንዳንድ ሰዎች የኢየሱስን ሕይወት የሚተርኩ ልዩ ልዩ ጽሑፎች ስለ ነበሩ፣ ጸሓፊዎቹ እነዚህን መሠረት በማድረግ ጽፈዋል ይላሉ::

4.የወንጌላቱ ምንጭ ጸሓፊዎቹ ራሳቸው ናቸው:- አንዳንድ ሰዎች የተመሳሳዮቹ ወንጌላት ጸሓፊዎች አንዳቸው ከሌላው እየወሰዱ ጽፈዋል ይላሉ፤ ከዚህም የተነሣ ወንጌላቱ ተመሳሳይ ሊሆኑ ችለዋል::

5. የወንጌላቱ ምንጭ ሁለት ዐበይት ምንጮች ናቸው:- በአሁኑ ጊዜ ብዙ ተቀባይነት ባለው አመለካከት መሠረት የወንጌላቱ ምንጭ የማርቆስ ወንጌልና አንድ ሌላ መላ ምታዊ ምንጭ ነው (ይህ ምንጭ በጀርመን ቋንቋ "ኩዌል" ይባላል፤ ትርጕሙም ምንጭ ማለት ነው):: ማቴዎስና ሉቃስ ወንጌላቸውን ሲጽፉ በስፋት የተጠቀሙት እነዚህን ምንጮች ነው::

6. የወንጌላቱ ቀዳማይ ምንጭ ማቴዎስ ነው:- ሌላው አመለካከት፣ ሌሎቹ ሁለት ተመሳሳይ ወንጌላት ዋና ምንጭ አድርገው የተጠቀሙት የማቴዎስን ወንጌል ነው::

7. የወንጌላቱ ምንጭ ከላይ የተጠቀሱትን አብዛኞቹን ምንጮች ያጣመረ ነው:- በዚህ አመለካከት መሠረት የተመሳሳዮቹ ወንጌላት ጸሓፊዎች ሥነ ቃልን፣ እዚህም እዚያም ተበታትነው የሚገኙ ጽሑፎችን፣ እነርሱ ራሳቸው የጻፏቸውን ጽሑፎች እንዲሁም የዐይን ምስክሮችን እማኝነት ተጠቅመዋል::

## ተመሳሳዮቹ ወንጌላት የተጻፉበት ጊዜ

| ማርቆስ → ማቴዎስ ሉቃስ | ማርቆስ \| ማቴዎስ \| ሉቃስ |
|---|---|
| **መላ ምት "ሀ"**<br>ማቴዎስና ሉቃስ የማርቆስ ወንጌልን ዋና ምንጭ አድርገው ተጠቅመዋል<br><br>**ፅንሰ ሐሳብ "1"**<br>ማርቆስ የተጻፈው በ50ዎቹ ወይም በ60ዎቹ መጀመሪያ ላይ ነው<br>(1) ማቴዎስ የተጻፈው በ50ዎቹ ወይም በ60ዎቹ መጨረሻ ላይ ነው<br>(2) ሉቃስ የተጻፈው ከ59–63 ነው<br><br>**ፅንሰ ሐሳብ 2**<br>ማርቆስ የተጻፈው ከ65–70 ነው<br>(1) ማቴዎስ የተጻፈው በ70ዎቹ ላይ ነው<br>(2) ሉቃስ የተጻፈው በ70ዎቹ ላይ ነው | **መላ ምት "ለ"**<br>ማቴዎስና ሉቃስ የማርቆስን ወንጌል ዋና ምንጭ አድርገው አልተጠቀሙም<br><br>**ፅንሰ ሐሳብ "1"**<br>ማርቆስ የተጻፈው ከ50–70 ባሉት ዓመታት በአንዱ ዓመት ሊሆን ይችላል<br><br>**ፅንሰ ሐሳብ "2"**<br>ማርቆስ የተጻፈው ከ65–70 ነው<br>(1) ማቴዎስ የተጻፈው በ50 ላይ ነው (በማቴዎስ መግቢያ ላይ "የተጻፈበት ጊዜና ቦታ" የሚለውን ይመ)::<br>(2) ሉቃስ የተጻፈው ከ59–63 ነው (በሉቃስ መግቢያ ላይ "የተጻፈበት ጊዜና ቦታ" የሚለውን ይመ):: |

# የማቴዎስ ወንጌል

## መግቢያ

### “ተመሳሳይ ወንጌላት” የሚለውን ይመ

### ጸሐፊው

የማቴዎስ ወንጌል ጸሐፊ ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መካከል የሆነው ማቴዎስ መሆኑን የጥንት ቤተ ክርስቲያን አባቶች ያለ ጥርጥር ተቀብለውታል:: ሆኖም ማቴዎስ የጻፈው የማርቆስን ወንጌል ተመርኩዞ ነው በሚሉ ሊቃውንት ዘንድ የዚህ ተቀባይነት አነስተኛ ነው:: ምክንያቱም፣ ማቴዎስ የጌታ ሕይወት የቅርብ ምስክር ሆኖ ሳለ፣ በማርቆስ ወንጌል ላይ ተመሥርቶ እንዴት ይጽፋል የሚል ጥያቄ ያነሣሉ:: ለዚህ የሚሰጠው ምላሽ ከማርቆስ ወንጌል ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ መቅረቡ ስለ ክርስቶስ የሚሰጥ የሐዋርያት ምስክርነት ተመሳሳይ ስለ ሆነ ነው የሚል ነው::

ማቴዎስ፣ የስሙ ትርጕም “የእግዚአብሔር ስጦታ” ማለት ሲሆን፣ ቀረጥ ሰብሳቢና ኢየሱስን ለመከተል ሥራውን የተወ ሐዋርያ ነበር (9፥9-13):: ማቴዎስ በማርቆስና በሉቃስ ወንጌሎች ውስጥ የሚጠራው ሌዊ በሚባል ሌላኛው ስሙ ነው::

### ወንጌሉ የተጻፈበት ጊዜና ቦታ

ብዙ ሰዎች የማቴዎስ ወንጌል የተጻፈው ሶርያ አገር፣ አንጾኪያ በተባለች ከተማ እንደ ሆነ ይናገራሉ፤ ሆኖም ወንጌሉ አይሁዳዊ ጕዳዮችን ስለሚያንጸባርቅ በፓሌስቲና ምድር እንደ ተጻፈ ግልጽ ነው:: ከዚህ ባሕርዩ የተነሣም አንዳንድ ሰዎች ይህ ወንጌል የተጻፈው፣ ወንጌል ለአይሁድ ብቻ ይሰበክ በነበረበትና የጥንታዊቷ የቤተ ክርስቲያን አባላትም በብዛት አይሁዳውያን በነበሩበት (ሐሥ 11፥19) በ50 ዓ.ም. ገደማ ነው ይላሉ:: ሌሎች ደግሞ ማቴዎስና ሉቃስ ወንጌላትን የጻፉት በማርቆስ ወንጌል ላይ ተመሥርተው ነው በማለት፣ የማቴዎስ ወንጌል የተጻፈው የማርቆስ ወንጌል በጥንት ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መስጠት ከጀመረ በኋላ ነው ይላሉ:: ከዚህ የተነሣም የማቴዎስ ወንጌል በ50ዎቹ መጨረሻ ወይም በ60 ዓ.ም. አካባቢ እንደ ተጻፈ ይገመታል:: የማርቆስ ወንጌል በ65 እና በ70 ዓ.ም. መካከል እንደ ተጻፈ የሚገምቱ ሰዎች ደግሞ የማቴዎስ ወንጌል የተጻፈው በ70 ዓ.ም. ወይም ከዚያ በኋላ ነው ይላሉ::

### የወንጌሉ ተደራስያን

የማቴዎስ ወንጌል የተጻፈው በግሪክ ቋንቋ ስለ ሆነ የወንጌሉ አንባብያን የግሪክ ቋንቋ ተናጋሪ መሆናቸው ግልጽ ነው:: ደግሞም አይሁድ የነበሩ ይመስላል:: በወንጌሉ ውስጥ የምናገኛቸው ብዙ ነጥቦች ከአይሁድ አንባብያን ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ይጠቁማሉ፤

1) ማቴዎስ፣ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች መፈጸማቸውን በትኩረት ከሌሎች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ይልቅ በርካታ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን እየጠቀሰ መጻፉ፣
2) የኢየሱስን የዘር ግንድ ከአብርሃም እንደ ሆነ መገለጹ (1፥1-17)፣
3) በተለይ ከማርቆስ ወንጌል ጋር ሲነጻጸር፣ ማቴዎስ የአይሁድን ልማድ ለአንባቢዎቹ ማብራራት አለመፈለጉ (ምክንያቱም ስለሚያውቁት)፤
4) በአይሁድ ዘንድ የተለመዱ ሐረጎችን መጠቀሙ (ለምሳሌ:- “መንግሥተ ሰማያት”፤ “የሰማዩ አባታችሁ”፤ አይሁድ የእግዚአብሔርን ስም ላለመጥራት “ሰማይ” የሚለውን መጠቀማቸው በወንጌሉ ውስጥ በተመሳሳይ መገለጹ)፣
5) ኢየሱስ “የዳዊት ልጅ” መሆኑ በአጽንዖት መጠቀሱ (1፥1፤ 9፥27፤ 12፥23፤ 15፥22፤ 20፥30-31፤ 21፥9:15፤ 22፥41-45):: ይሁን እንጂ ማቴዎስ ወንጌሉን የጻፈው ለአይሁድ ብቻ ነው ማለት አይቻልም:: ለሕፃኑ ሊሰግዱ ስለ መጡት ሰብአ ሰገል (አይሁድ አይደሉም) መጻፉ (2፥1-12)፤ በተጨማሪም ኢየሱስ “ዕርሻው ዓለም ነው” የሚለውን በወንጌሉ ማካተቱ (13፥38) እና ስለ ታላቁ ተልእኮ መጻፉ ይህንኑ ያረጋግጣል (28፥18-20)):: የማቴዎስ ወንጌል በመሠረቱ የተጻፈው ለአይሁድ ሕዝብ ቢሆንም፣ ከእነዚህ ክፍሎች እንደምናየው ወንጌሉ ዓለም አቀፋዊ ትኵረት እንዳለው ከዚህ መረዳት ይቻላል::

### ዐላማው

የማቴዎስ ዋነኛ ዐላማ ለአይሁድ አንባብያኑ ኢየሱስ ሲጠብቁት የነበረው መሲሕ ስለ መሆኑ ማስረጃ ማቅረብ ነው:: ይህን የሚያደርገውም ኢየሱስ በሕይወቱና በአገልግሎቱ ብሉይ ኪዳንን እንዴት እንደ ፈጸመ በማሳየት ነው:: ሁሉም የወንጌል ጸሐፊዎች ከብሉይ ኪዳን ጠቅሰው ቢጽፉም፣ ማቴዎስ በብሉይ ኪዳን ስለ መሲሕ የተነገረው ትንቢት የተፈጸመው ኢየሱስ ነው የሚለውን መሪ ሐሳብ ለማስጨበጥ ዘጠኝ ተጨማሪ ማስረጃዎችን ከብሉይ ኪዳን ጠቅሶአል (1፥22-23፤ 2፥15፤ 2፥17-18፤ 2፥23፤ 4፥14-16፤ 8፥17፤ 12፥17-21፤ 13፥35፤ 27፥9-10):: ደግሞም በብሉይ ኪዳን የነበረው የእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ በኢየሱስ ሕይወት እንደ ተፈጸመ የጻፈው ማቴዎስ ነው (ለምሳሌ:- በ2፥15 ላይ ከሆሴ 11፥1 የተጠቀሰውን ይመ):: በተጨማሪም ማቴዎስ ዐላማውን ከግቡ ለማድረስ የኢየሱስ የዘር ሐረግ ከዳዊት እንደ ሆነ በአጽንዖት ያስረዳል::

**ውቅሩ**

የወንጌሉ አጻጻፍ ሥነ ጽሑፋዊ የአወቃቀር ስልት የተከተለ ነው። ወንጌሉ በአምስት ታላላቅ የገላጻ ትምህርቶች ላይ የተመሠረተ ነው:- (1) ም5-7፣ (2) ም10፣ (3) ም13፣ (4) ም18፣ (5) ም24-25። ይህ ዐይነት መዋቅር ሆን ተብሎ የተቀነባበረ መሆኑ በየትምህርቱ መጨረሻ ላይ "ኢየሱስም ይህን ነገር በጨረሰ ጊዜ" የሚለው ዐረፍተ ነገር ወይም ተመሳሳይ ሐረግ መገኘቱ ግልጽ ያደርገዋል (7፥28፤ 11፥1፤ 13፥53፤ 19፥1፤ 26፥1)። ተራኪው ክፍል ተከትሎት ወደሚገኘው ትምህርት በሚገባ ይመራል። ወንጌሉ ተስማሚ መግቢያና (ም1-2) ብርቱ ጥሪ የሚያቀርብ መደምደሚያ አለው (28፥16-20)።

ወንጌሉ በአምስት መከፈሉ ማቴዎስ ከአምስቱ የሙሴ ሕግ መጻሕፍት ጋር አገናዝቦ ማቅረቡን ያመለክት ይሆናል። ምናልባትም ወንጌሉን እንደ አዲስ የሕግ መጽሐፍ (ቶራ)፣ ኢየሱስን ደግሞ እንደ አዲስና የተሻለ ሙሴ አድርጎ ማቅረቡ ይሆናል።

**አስተዋፅኦ**

1. የኢየሱስ ልደትና የሕፃንነቱ ዓመታት (ም1-2)
   ሀ. የትውልድ ሐረጉ (1፥1-17)
   ለ. ልደቱ (1፥18-2፥12)
   ሐ. ወደ ግብፅ መሰደዱ (2፥13-23)
2. የኢየሱስ አገልግሎት መጀመሪያ (3፥1-4፥11)
   ሀ. የእርሱ መንገድ ጠራጊ (3፥1-12)
   ለ. መጠመቁ 3፥13-17)
   ሐ. መፈተኑ (4፥1-11)
3. የኢየሱስ አገልግሎት በገሊላ (4፥12-14፥12)
   ሀ. የገሊላው አገልግሎት አጀማመር (4፥12-25)
   ለ. የተራራው ስብከት (ም5-7)
   ሐ. የሠራቸው ታምራት (ም8-9)
   መ. የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መሾም (ም10)
   ሠ. በገሊላ የነበረው አገልግሎት (ም11-12)
   ረ. ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የተሰጡ ምሳሌዎች (ም13)
   ሰ. ሄሮድስ ስለ ኢየሱስ አገልግሎት የነበረው አመለካከት (14፥1-12)
4. ኢየሱስ ከገሊላ ፈቀቅ ስለ ማለቱ (14፥13-17፥20)
   ሀ. ወደ ገሊላ ባሕር ምሥራቅ ዳርቻ (14፥13-15፥20)
   ለ. ወደ ፊንቂ አገር (15፥21-28)
   ሐ. ወደ 'ዐሥር ከተሞች' (15፥29-16፥12)
   መ. ወደ ፊልጶስ ቂሣርያ (16፥13-17፥20)
5. የኢየሱስ የመጨረሻው አገልግሎት በገሊላ (17፥22-18፥35)
   ሀ. ስለ ኢየሱስ ሞት አስቀድሞ መነገሩ (17፥22-23)
   ለ. ቀረጥ ስለ መክፈል (17፥24-27)
   ሐ. በእግዚአብሔር መንግሥት ስለሚኖረው ሕይወት የተሰጠ ገለጻ (ም18)
6. የኢየሱስ አገልግሎት በይሁዳና በፔርያ ምድር (ም19-20)
   ሀ. ስለ መፋታት የተሰጠ ትምህርት (19፥1-12)
   ለ. ስለ ሕፃናት የተሰጠ ትምህርት (19፥13-15)
   ሐ. ሀብታሙ ወጣት (19፥16-30)
   መ. የወይን ዕርሻ ሠራተኞች ምሳሌ (20፥1-16)
   ሠ. ስለ ኢየሱስ ሞት አስቀድሞ መነገሩ (20፥17-19)
   ረ. አንዲት እናት ያቀረበችው ልመና (20፥20-28)
   ሰ. በኢያሪኮ የአንድ ዐይን ስውር ዐይን በራ (20፥29-34)
7. ሰሞነ ሕማማት (ም21-27)
   ሀ. በክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ (21፥1-11)
   ለ. ቤተ መቅደስን ማንጻቱ (21፥12-17)
   ሐ. የመጨረሻው ጭቅጭቅ ከአይሁድ አለቆች ጋር (21፥18-23፥39)
   መ. በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ስለ መጨረሻው ዘመን የተሰጠ ገለጻ (ም24-25)
   ሠ. (በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ስለ ኢየሱስ እግር ሽቱ መቀባት አልተወሣም–ራሱ ላይ ነው ያፈሰሰችው) (26፥1-13)
   ረ. የኢየሱስ መያዝ፣ ፍርድ ፊት መቅረብና መሞት (26፥14-27፥66)
8. የኢየሱስ ትንሣኤ (ም 28)

## የኢየሱስ የትውልድ ሐረግ

1፥1-17 ተጓ ምብ - ሉቃ 3፥23-38
1፥3-6 ተጓ ምብ - ሩት 4፥18-22
1፥7-11 ተጓ ምብ - 1ዜና 3፥10-17

1 የዳዊት ልጅ፣ የአብርሃም ልጅ የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ የሚከተለው ነው፤

2 አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፤
ይስሐቅ ያዕቆብን ወለደ፤
ያዕቆብ ይሁዳንና ወንድሞቹን ወለደ፤
3 ይሁዳ ከትዕማር ፋሬስንና ዛራን ወለደ፤
ፋሬስ ኤስሮምን ወለደ፤
ኤስሮምም አራምን ወለደ፤
4 አራም አሚናዳብን ወለደ፤
አሚናዳብ ነአሶንን ወለደ፤
ነአሶን ሰልሞንን ወለደ፤
5 ሰልሞን በዔዝን ከረዓብ ወለደ፤
ቦዔዝ ከሩት ኢዮቤድን ወለደ፤
ኢዮቤድ እሴይን ወለደ፤
6 እሴይ ንጉሥ ዳዊትን ወለደ።

ዳዊት የኦርዮ ሚስት ከነበረችው
ሰሎሞንን ወለደ፤
7 ሰሎሞን ሮብዓምን ወለደ፤
ሮብዓም አቢያን ወለደ፤
አቢያም አሣፍን ወለደ፤
8 አሣፍ ኢዮሣፍጥን ወለደ፤
ኢዮሣፍጥ ኢዮራምን ወለደ፤
ኢዮራም ዖዝያንን ወለደ፤
9 ዖዝያን ኢዮአታምን ወለደ፤
ኢዮአታም አካዝን ወለደ፤
አካዝ ሕዝቅያስን ወለደ፤
10 ሕዝቅያስ ምናሴን ወለደ፤
ምናሴ አሞንን ወለደ፤
አሞንም ኢዮስያስን ወለደ፤
11 ኢዮስያስ በባቢሎን ምርኮ ጊዜ፣
ኢኮንያንንና[ሀ] ወንድሞቹን ወለደ፤

12 ከባቢሎን ምርኮ በኋላ፣
ኢኮንያን ሰላትያልን ወለደ፤
ሰላትያልም ዘሩባቤልን ወለደ፤
13 ዘሩባቤል አብዩድን ወለደ፤
አብዩድ ኤልያቄምን ወለደ፤
ኤልያቄም አዛርን ወለደ፤
14 አዛር ሳዶቅን ወለደ፤
ሳዶቅ አኪምን ወለደ፤
አኪምም ኤልዩድን ወለደ፤
15 ኤልዩድ አልዓዛርን ወለደ፤
አልዓዛር ማታንን ወለደ፤
ማታን ያዕቆብን ወለደ፤
16 ያዕቆብ ዮሴፍን ወለደ፤
ዮሴፍም የኢየሱስ ክርስቶስ እናት
የማርያም እጮኛ ነበር።

17 እንግዲህ ከአብርሃም እስከ ዳዊት ዐሥራ አራት ትውልድ፣ ከዳዊት እስከ ባቢሎን ምርኮ ዐሥራ አራት ትውልድ፣ ከባቢሎን ምርኮ እስከ ክርስቶስ[ለ] ልደት ዐሥራ አራት ትውልድ ይሆናል።

## የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት

18 የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት ታሪክ እንዲህ ነው፤ እናቱ ማርያም ለዮሴፍ ታጭታ ሳይገናኙ፣ በመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች።

[ሀ] 11 ዮአኪን ማለት ነው፤ ቍ 12 ይመ
[ለ] 17 ወይም መሲሕ "ክርስቶስ" (በግሪክ) እና "መሲሕ" (በዕብራይስጥ) ሁለቱም "የተቀባ" የሚል ትርጕም አላቸው

1፥1 ዘፍ22፥18፤ 2ሳሙ7፥12-16፤ኢሳ 9፥6:7፤11፥1፤ኤር23፥5:6፤ማቴ9፥27፤ ሉቃ 1፥32:69፤ ገላ3፥16፤ ራእ22፥16
1፥2 ዘፍ21፥3:12፤ 25፥26፤29፥35፤ 49፥10
1፥3 ዘፍ38፥27-30
1፥5 ዕብ11፥31
1፥6 1ሳሙ16፥1፤ 17፥12፤2ሳሙ12፥24
1፥10 2ነገ20፥21
1፥11 2ነገ24፥14-16 ፤ኤር27፥20፤ 40፥1፤ዳን1፥1:2
1፥12 1ዜና3፥17: 19፤ዕዝ3፥2
1፥16 ማቴ27፥17፤ ሉቃ1፥27
1፥18 ሉቃ1፥35

*1፥1-16*፤ በማቴዎስ ወንጌል የተጻፈውን የትውልድ ሐረግ በሉቃስ ወንጌል ላይ ከተመለከተው ጋር ለማወዳደር የሉቃ 3፥23-38 ማብ ይመ። በዚህ የትውልድ ሐረግ የተካተቱት ሰዎች ሁሉ ማንነት እንደሚገልጸው የእግዚአብሔር ሕዝብ በመባል የሚታወቀውን ወገን ለመፍጠርና ስለ ኢየሱስ በሥጋ መወለድ ምክንያት የሆኑ ናቸው።

1፥1 ***የዳዊት ልጅ፤*** መሲሐዊ የማዕረግ ስም ሲሆን (የ9፥27 ማብ ይመ)፣ በዚህ ወንጌል ውስጥ በብዙ ቦታ ይገኛል (በ1፥20 ላይ የተመለከተው ግን መሲሐዊ የማዕረግ ስም አይደለም)። ***የአብርሃም ልጅ፤*** ማቴዎስ ወንጌሉን የጻፈው ለአይሁድ ስለ ነበር የኢየሱስን የትውልድ ሐረግ በዚህ መንገድ መግለጹ ተገቢ ነበር።

*1፥3፤* በወንጌላዊው ማቴዎስ የትውልድ ሐረግ ዝርዝር መሠረት በተለይ የአራት ሴቶች ስም ተገልጾአል። እነርሱም፦ ትዕማር፣ (በዚህ ቍጥር ላይ)፣ ረዓብ (በቍጥር 5) ሩት (በቍጥር 5) እና ቤርሳቤህ (በተለምዶ አገላለጽ "እናቱ የኦርዮን ሚስት የነበረች የዳዊት ልጅ የሰሎሞን እናት") ናቸው። በተለይ ከእነዚህ ሴቶች መካከል ሦስቱ ከአሕዛብ ወገን የነበሩ ናቸው (ትዕማር፣ ረዓብና ሩት)። ቤርሳቤህ በትውልዷ ሙሉ በሙሉ ከእስራኤል ወገን ሳትሆን አትቀርም። ሆኖም ከባሏ ከኦርዮን የተነሣ ከኬጢያውያን ጋር ዝምድና ነበራት። በማቴዎስ የኢየሱስ የትውልድ ሐረግ ዝርዝር ውስጥ እነዚህን ሴቶች ማካተቱ ነበር) የእግዚአብሔር ሥራ በወንዶች ብቻ አለመወሰኑንና አልፎ ተርፎም ከእስራኤላውያን ውጭ በሌሎች ወገኖች መገለጹን ያመለክታል።

1፥4 ***አሚናዳብ፤*** የአሮን አማት ነበር (ዘጸ6፥23)።

1፥5 ***ከረዓብ፤*** ኢያ2 ይመ። ምንም እንኳ በረዓብና በዳዊት መካከል አያሌ ዘመን ያለፈ ቢሆንም፣ ማቴዎስ ጽሑፉን በተቀ ናጀ ይዘት ለማዋቀር ስለ ፈለገ (የቍ17 ማብ ይመ)፣ በረዓብና በዳዊት መካከል ብዙ ትውልዶች እንደ ነበሩ እያወቀ ዝርዝራቸ ውን ለመግለጽ አልፈለገም።

1፥8 ***ኢዮራም... ወለደ፤*** ማቴዎስ ኢዮራምን "የዖዝያን አባት" ብሎታል፤ ነገር ግን ከ2ዜና21፥4-26፥23 እንደምንረዳው፣ አሁንም ብዙ ትውልዶች በመካከል እንዳሉ ተቈጥሮ ታልፎአል (አካዝያስ፣ ኢዮአስና አሜስያስ) "አባት" የሚለውም ቃል የገባው ከ"አበው" አንዱ መሆኑን ለመግለጽ ነው።

1፥11 ***ኢዮስያስ... ወለደ፤*** ኢዮስያስም በተመሳሳይ ሁኔታ የኢኮንያን አባት ተብሎአል (የቍ8 ማብ ይመ)፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ኢዮስያስ የኢዮአቄም አባት፣ የዮአኪን አያት ነበር (2ዜና 36፥1-9)።

1፥12 ***ሰላትያል ... ወለደ፤*** እንደ እውነቱ ከሆነ የዘሩባቤል አያት ነው (1ዜና3፥17-18 ይመ)።

*1፥16፤* ወንጌላዊው ማቴዎስ፣ ዮሴፍ የማርያም እጮኛ እንደ ሆነና፣ ኢየሱስ ከእርሷ እንደ ተወለደ እንጂ፣ ዮሴፍ የኢየሱስ አባት ነው ብሎ አልተናገረም። ነገር ግን ዮሴፍ የኢየሱስ የሥጋ አባት ባይሆንም እንደ ዘመኑ አባባል የሕግ አባት በመሆኑ፣ ማቴዎስ በዚህ የትውልድ አቈጣጠር ኢየሱስ ከዳዊት የትውልድ ሐረግ እንደ መጣ ያመለክታል።

1፥17 ***ዐሥራ አራት ትውልድ፤ ... ዐሥራ አራት ... ዐሥራ አራት፤*** እነዚህ ክፍፍሎች ሁለት የማቴዎስን ወንጌል ባሕርያት ያንጸባርቃሉ፤ (ሀ) በአኀዝ የመግለጽ ዝንባሌና (ለ) ሥርዐት የማስያዝ ፍላጎት። ዐሥራ አራት ቍጥር የተመረጠበት አንዱ ምክንያት፣ የፍጹምነት ምልክት የሆነው የሰባት ቍጥር እጥፍ በመሆኑ ሊሆን ይችላል። ይህ አቈጣጠር እንደ ማቴዎስ አገላለጽ ከዳዊት መንግሥት ዘመን አንሥቶ እስከ እስራኤላውያን የስደት ዘመን ዐሥራ አራት ትውልዶችን ብቻ ሲያካትት፣ ወንጌላዊው ሉቃስ ግን ከዳዊት አንሥቶ እስከ ስደት ዘመን ከነበሩት ትውልዶች ሃያ አንዱን ይጠቅሳል።

1፥18 ***ታጭታ...ሳይገናኙ፤*** በአይሁድ ባሕል መሠረት በሁለት እጮኛሞች መካከል የግብረ ሥጋ ግንኙነት አይፈቀድም ነበር፤ ይሁን እንጂ መተጫጨቱ በአሁኑ ዘመን ካለው መተጫጨት የበለጠ ጠንካራና ጥብቅ ስለ ነበር፣ በሕጋዊ ፍቺ ካልሆነ በቀር ማፍረስ አይቻልም ነበር (ቍ19ይመ)። በዘዳ22፥23 ላይ "ለታገባ

[19]እጮኛዋ ዮሴፍ ጻድቅ ሰው ስለ ነበርና
ማርያምን በሰው ፊት ሊያጋልጣት ስላል
ፈለገ በስውር ሊተዋት ወሰነ::
[20]በዚህ ሐሳብ ሳለ፣ የእግዚአብሔር
መልአክ በሕልም ተገለጠለት፤ እንዲህም
አለው፤ “የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፤ እጮ
ኛህን ማርያምን ወደ ቤትህ ለመውሰድ
አትፍራ፤ የፀነሰችው በመንፈስ ቅዱስ ነውና::
[21]ወንድ ልጅ ትወልዳለች፤ ስሙ ንም ኢየ
ሱስ[ሀ] ብለህ ትጠራዋለህ፤ ሕዝቡን ከኀጢአ
ታቸው ያድናቸዋልና::”
[22]ጌታ በነቢዩ (በኢሳይያስ) እንዲህ ሲል
የተናገረው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆነ፤
[23]“እነሆ፤ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም
ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል፤”
ትርጓሜውም፣ “እግዚአብሔር ከእኛ ጋር”
ማለት ነው::
[24]ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቃ፤ ከዚያም
የጌታ መልአክ እንዳዘዘው ማርያምን ወደ
ቤቱ ወሰዳት::[ለ] [25]ይሁን እንጂ የበኵር ልጇን
እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤ የተወለደ
ውንም ሕፃን፣ “ኢየሱስ” ብሎ ጠራው::

## የጠቢባን ከምሥራቅ መምጣት

**2** በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን፣ ኢየሱስ በቤተ
ልሔም ይሁዳ ከተወለደ በኋላ ጠቢባን
ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው፣
[2]“የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት
ነው? በምሥራቅ[ሐ] ኮከቡን አይተን ልንሰግ
ድለት መጥተናልና” ሲሉ ጠየቁ::
[3]ንጉሡ ሄሮድስ ይህን በሰማ ጊዜ ታወከ፤
እንዲሁም መላዪቱ ኢየሩሳሌም አብራ
ታወከች:: [4]እርሱም የካህናት አለቆችንና
የአይሁድ ሃይማኖት መምህራንን በሙሉ
ሰብስቦ፣ ክርስቶስ[መ] የት እንደሚወለድ ጠየ
ቃቸው:: [5]እነርሱም፣ “በይሁዳ ቤተ ልሔም፤
ነቢዩ እንዲህ ብሎ ጽፎአልና አሉ፤

[6]“ ‘በይሁዳ ምድር የምትገኚው አንቺ
ቤተልሔም፣
ከሌሎቹ የይሁዳ ገዢዎች በምንም
አታንሺም፤
የሕዝቤ የእስራኤል ጠባቂ የሚሆን፣
ከአንቺ ይወጣልና::’ ”

[7]ከዚያም ሄሮድስ ጠቢባኑን በምስጢር
አስጠርቶ በማነጋገር ኮከቡ የታየበትን ትክ
ክለኛ ጊዜ ተረዳ:: [8]ጠቢባኑንም ወደ ቤተ
ልሔም ልኮ፣ “ሂዱና ሕፃኑን ፈልጉ፤ እኔም
ደግሞ ሄጄ እንድሰግድለት፣ እንዳገኛችሁት

1፥19 ዘዳ24፥1
1፥20 ማቴ27፥19፤ ሐሥ5፥19
1፥21 መዝ130፥8፤ ሉቃ1፥31፤2፥11፤ ዮሐ3፥17፤ሐሥ5፥31፤ ሮሜ11፥14፤ቲቶ 2፥14
1፥22 ማቴ2፥15:17 :23፤4፥14፤8፥17፤12፥ 17፤21፥4፤26፥54:56፤ 27፥9፤ሉቃ4፥21፤21፥ 22፤24፥44፤ዮሐ13፥ 18፤19፥24:28:36
1፥23 ኢሳ7፥14፤ 8፥8:10
1፥24 ሐሥ5፥19
1፥25 ቍ21፤ ሉቃ 1፥31
2፥1 ሉቃ1፥5፤2፥4-7
2፥2 ዘኍ24፥17፤ ኤር23፥5፤ማቴ27፥ 11፤ማር15፥2፤ ሉቃ 23፥38፤ ዮሐ1፥49፤ 18፥33-37
2፥5 ዮሐ7፥42
2፥6 2ሳሙ5፥2፤ ሚክ5፥2

[ሀ]21 ኢየሱስ በግሪኩ ሲሆን በዕብራይስጡ ኢያሱ ነው፤ ትርጓሜውም እግዚአብሔር ያድናል ማለት ነው
[ለ]24 ወደ ቤቱ ወሰዳት የሚለው የግሪኩ ቃል *ሚስቱ እንድ ትሆን ወሰዳት* ይለዋል
[ሐ]2 ወይም *ኮከቡ ሲነሣ አይተን* [መ]4 ወይም *መሲሕ*

የታጨች” ያላትን ልጃገረድ በዚያው ምዕራፍ በቍ24 ላይ “ሚስቱን” ይላታል::

1፥19 ***ጻድቅ፤*** በአይሁድ ዘንድ ይህ ቃል ሕግን በጽኑ ፍላጎት ለመጠበቅ የሚተጋን ሰው ያመለክታል:: ***በስውር ሊተዋት፤*** ጉዳዩ አደባባይ ወጥቶ ሳይፈረድባትና በድንጋይ ሳትወገር፣ በሰላም ለመለያየት ተገቢውን የፍቺ ሥርዓት በመፈጸም ሊተዋት አስቦ እንደ ነበር ያሳያል (ዘዳ22፥23-24 *ይመ*)::

1፥20 ***በሕልም፤*** ይህ ቃል በማቴዎስ ወንጌል በመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች አምስት ጊዜ ተጽፎአል (በዚህ ቍጥርና በ2፥12-13:19:22 ላይ ይገኛል)፤ ይህም ጌታ ለዮሴፍ የተናገረበትን መንገድ ያመለክታል:: ***የዳዊት ልጅ፤*** መልአኩ ይህን ሲናገር ምናልባት ነገሩ ከሚጠበቀው መሲሕ ጋር እንደሚገናኝ ፍንጭ መስጠቱ ይሆናል:: ***የፀነሰችው በመንፈስ ቅዱስ ነውና፤*** ይህ ሐረግ በሉቃ1፥35 ለማርያም ከተነገረው ጋር አንድ ነው፤ በሉቃስ የተገለጸው ግን ይበልጥ በዝርዝር ያቀርባል (የሉቃ 1፥26-35 ማብ *ይመ*)::

1፥22 ***ይፈጸም ዘንድ፤*** በብሉይ ኪዳን የተተነበየው በአዲስ ኪዳን እንደ ተፈጸመ ማቴዎስ ዐሥራ ሁለት ጊዜ ጽፎአል (እዚህ ላይ የተጠቀሰውና 2፥15:23፤ 3፥15፤4፥14፤ 5፥17፤ 8፥17፤ 12፥17፤ 13፥14:35፤ 21፥4፤ 27፥9):: ይህም፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሠረቱ ከእግዚአብሔር እንደ ሆነና ዝርዝር ጉዳይ እንኳ ሳይቀር ትክክለኛ መሆኑን ያመለክታል:: በተጨማሪም “ይፈጸም ዘንድ” በሚለው አገላለጽ ወንጌላዊው ማቴዎስ ወንጌሉን ከብሉይ ኪዳን ጋር ለማገናኘት ያደረገውን ጥረት እንናስተውላለን::


*1፥23፤* የኢሳ7፥14 ማብ *ይመ*:: ማቴዎስ ከብሉይ ኪዳን ከጠቀሳቸው 47 ጥቅሶች ውስጥ ይህ የመጀመሪያው ነው፤ ከእነዚህም አብዛኛዎቹ ስለ መሲሑ የሚናገሩ ናቸው:: በኢሳ7፥14 ላይ የተነገረው ትንቢት ፍጻሜው የታወቀው በጌታ ኢየሱስ መወለድ ነው:: በተለይ ኢሳ9፥6-7 ያለውን *ይመ*::

2፥1 ***በቤተልሔም ይሁዳ፤*** ከኢየሩሳሌም በስተ ደቡብ ስምንት ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ የምትገኝ መንደር ናት:: በናዝሬት ከተማ ስለ ነበረው ሁኔታ ማቴዎስ የጻፈው ነገር የለም (ከሉቃ1፥26-56 ጋር *ያነጻጽሩ*):: ማቴዎስ ትረካውን ከዳዊት ከተማ መጀመሩ የኢየሱስ አመጣጥ ከዳዊት ወገን መሆኑን አበክሮ ለማሳየት ይሆናል:: ይህች ከተማ “የይሁዳ ቤተልሔም” ተብላ የተጠራችው ከናዝሬት ሰሜን ምዕራብ አሥራ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ከምትገኘው ተምሳሳይ ስም ካላት ከተማ ለመለየት ሳይሆን፣ ኢየሱስ የዳዊት ሥርወ መንግሥት መነሻ ከሆነው ነገድና አገር የመጣ መሆኑን በአጽንዖት ለማሳየት ነው:: አይሁድ፣ መሲሑ በቤተልሔም እንደሚወለድና ከዳዊትም ወገን እንደሚሆን ይጠባበቁ እንደ ነበር በዮሐ7፥42 በግልጽ ተጽፎአል:: ***በንጉሡ በሄሮድስ፤*** በመጽሐፍ ቅዱስ በዚሁ ስም ከሚጠሩት ከሌሎች ቤተ-ሄሮድስ ነገሥታት ተለይቶ እንዲታወቅ ያስፈልጋል፤ ይኸኛውም ታላቁ ሄሮድስ ሲሆን፣ ከ37-4 ዓ.ቅ.ክ. ነግሦ የነበረ ነው:: ኤዶማዊው ሄሮድስ ከአይሁድ ወገን አልነበረም፤ እርሱም የይሁዳ ንጉሥ ይሆን ዘንድ በ40 ዓ.ቅ.ክ. ከሮማውያን ምክር ቤት ሥልጣን ተቀብሎ በ 37 ዓ.ቅ.ክ.ግዛቱን ያጸና ንጉሥ ነበር:: በዘመኑ እንደ ነበሩት ብዙዎች ነገሥታት፣ አረመኔና ጨካኝ መሪ ነበር፤ የቤተልሔምን ሕፃናት ሳይጨምር (ቍ16) ሚስቱን፣ ሦስት ወንድ ልጆቹን፣ ሴት አማቱን፣ አማቹን፣ አጎቱንና ሌሎች ብዙዎችን የገደለ ንጉሥ ነበር:: በዘመኑ ያሠራቸውና የታ ደሱት ቲያትር ቤቶች፣ መካነ ትዕይንቶች፣ ሐውልቶች፣ የአረማውያን መሠዊያዎች፣ ምሽጎችና ሌሎችም ሕንፃዎች የንጉሡ ዘመን ታላቅ የጥበብ ዘመን እንደ ነበር ይመሰክራሉ፤ ይህም ከሁሉ በላይ ታላቅ የሆነውን ሥራ፣ በ20 ዓ.ቅ.ክ. ተጀምሮ እርሱ ከሞተ ከ68 ዓመት በኋላ የተጠናቀቀውን የኢየሩሳሌምን መቅደስ መታደስ ይጨምራል:: ***ጠቢባን፤*** ምናልባት ከዋክብትን በማየት መንፈሳዊ ምሥጢር የሚገልጹላቸው ሰዎች ሳይሆኑ አይቀሩም፤ እርሱም ከመካከለኛው ምሥራቅ በስተ ምሥራቅ ከሚገኙት ከፋርስ ወይም ከደቡብ ዓረቢያ የመጡ ሊሆኑ ይችላሉ:: ***ኢየሩሳሌም፤*** “የአይሁድን ንጉሥ” (ቍ2) ለማየት ይፈልጉ ስለ ነበር፣ የአይሁድ ዋና ከተማ ወደ ሆነችው ወደ ኢየሩሳሌም መጡ::

2፥2 ***የአይሁድ ንጉሥ፤*** ይህ ሐረግ ጠቢባኑ ከአሕዛብ ወገን እንደ ሆኑ ያመለክታል:: ከሕዝቦች ሁሉ የሆኑ ሰዎች ኢየሱስ “የአይሁድ ንጉሥ” መሆኑን በመቀበል ለጌትነቱ ሊሰግዱ መምጣታቸውን ማቴዎስ ይገልጻል:: ***ኮከቡን፤*** አንዳንድ ሊቃውንት ‘ጁፒተር’ና ‘ሳተርን’ ከሚባሉት ፕላኔቶች ጋር ቢያዛምዱትም ተራ ኮከብ ወይም ፕላኔት ወይም ተወርዋሪ ኮከብ ነው ማለት ያዳግታል::

2፥4 ***የካህናት አለቆችንና፤*** በኢየሩሳሌም በነበረው ቤተ መቅ ደስ የአምልኮ አገልግሎት ኀላፊዎች የነበሩ ሰዱቃውያን ናቸው (የ3፥7 ማብ *ይመ*):: ***የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን፤*** በዘመኑ የነበሩ የአይሁድ ሃይማኖት ምሁራን የብሉይ ኪዳን ሕግ አመ ጣጥ፣ ትምህርትና ተግባራዊነት እንዴት እንደ ሆነ በሙያ ደረጃ በሚገባ የሠለጠኑ ነበሩ:: ሆኖም በዚህ ረገድ የነበራቸው ሥልጣን በሰው ወግና ሥርዐት ላይ የተመሠረተ ነበር::

*2፥6፤* ይህ ትንቢት በነቢዩ ሚክያስ የተነገረው ከሰባት መቶ ዓመት በፊት ነበር::


የሄሮድስ
ቤተሰብ
የሜዲትራኒያን ባሕር
ገሊላ
ሰማርያ
ፔሪያ
ታላቁ
ሄሮድስ
ይሁዳ
ኢዱሚያ
1 ኛ
ትውልድ
ኢጡርያስ
ጥራኮኒየስ
ዳግማዊ
ሄሮድስ
ፊልጶስ
ሄሮድስ
አንቲጳስ
አርኬላዎስ
2 ኛ
ትውልድ
አቢላ
አውራኒጢስ
ሄሮድስ
አግሪጳ ቀዳማዊ
3 ኛ
ትውልድ
ጥራኮ
ኒየስ
አውራ
ኒጢስ
ዳግማዊ
ሄሮድስ አግሪጳ
በሮም ባለ
ሥልጣናት
የሚተዳደር
አቤላ
ይህ ስም ሁለት
ስፍራ ተጠቅሷል
4 ኛ
ትውልድ
ዳግማዊ ሄሮድስ ፊልጶስ
(እናቱ- ክሊዎፓትራ)
የኢጡርያስ እና የጥራኮኒዶስ
አገር አራተኛ ክፍል ገዥ
(4 ዓ.ቅ.ክ - 34 ዓ.ም)
(ሉቃ 3:1)
አርኬላዎስ
(እናቱ- ማልቴስ)
የይሁዳ፣ የኢዱሚያና የሰማርያ
አገረ ገዥ (4 ዓ.ቅ.ክ - 6 ዓ.ም)
ማርያምና ዮሴፍ ከግብፅ ከተመ
ለሱ በኋላ ይሁዳን ትተው
በናዝሬት ተቀመጡ
(ማቴ 2:19-23)
የከልቂሱ ሄሮድስ
አርስጦቡሉስ
(እናቱ- ማሪያም)
(10 ዓ.ቅ.ክ.) በመጽሐፍ
ቅዱስ ውስጥ አልተጠቀሰም።
ሄሮድስ
አግሪጳ ቀዳማዊ
የይሁዳ ንጉሥ
(ከ34 - 44 ዓ.ም.)
ያዕቆብን አስገደለ፤
ጴጥሮስን አሳሰረ፤
በመልአክ ተመትቶ
ሞተ (ሐሥ 12:1-24)
ፊልክስ- የይሁዳ ገዥ
ድሩሲላ
የይሁዳ ገዥ የሆነው
የፊልክስ ሚስት (52-59
ዓ.ም.) ፊልክስ ጳውሎስን
በፍርድ ቤት አቀመው
(ሐሥ 24:24)
ዳግማዊ
ሄሮድስ አግሪጳ
የይሁዳ ንጉሥ፤ ጳውሎስ
ሕጋዊ መከላከያውን ይግባኙን
በዚህ ንጉሥ ፊት አቀረበ
(ሐሥ 25:13-26፣32)
ታላቁ
ሄሮድስ
የይሁዳ፣ ገሊላ፣
ኢጡርያስ እና
ጥራኪኒየስ ንጉሥ
(37 - 4 ዓ.ቅ.ክ.)
የኢየሱስ ልደት
(ማቴ 2:1-19፤
ሉቃ 1:5)
ሄሮድስ አንቲጳስ
(እናቱ- ማልቴስ)
በገሊላ የአራተኛው ክፍል ገዥ
(ከ 4 ዓ.ቅ.ክ. - 39 ዓ.ም.)
(ሉቃ 3:1) የሄሮድያዳ ሁለተኛ
ባል:: መጥምቁ ዮሐንስን
ያስገደለ (ማቴ 14:1-12፤
ማር 6:14-29)፤ ጲላጦስ
ኢየሱስን ወደ እርሱ ላከ
(ሉቃ 23:7-12)
መፍቻ
ንጉሥ
አራተኛ
ክፍል ገዥ
ሄሮድያዳ
አጎቷን ቀዳማዊ ሄሮድስ
ፊልጶስን አገባች፤ በመቀ
ጠል ሌላኛውን አጎቷን
ሄሮድስ አንቲጳስን አገባች
(ማቴ 14:3፤ ማር 6:17)
በርኒቄ
ጳውሎስ ይግባኙን
ሲያቀርብ ከወንድሟ
ጋር የነበረች (ሐሥ
25:13)
ቀዳማዊ ሄሮድስ ፊልጶስ
(እናቱ- ማሪያም)
ገዥ አልነበረም፤ የሄሮድያዳ
የመጀመሪያ ባል (ማቴ 14:3፤
ማር 6:17) በ34 ዓ.ም. ገደማ
ሞተ።
. . . ሄሮድያዳ ሄሮድስ
አንቲጳስን ማግባቷን የሚያሳይ
መስመር
- - - ሄሮድያዳ ቀዳማዊ ሄሮድስ
ፊልጶስን ማግባቷን የሚያሳይ
መስመር
ሰሎሜ
የሄሮድያዳና የቀዳማዊ
ሄሮድስ ፊልጶስ ሴት ልጅ፤
የመጥምቁ ዮሐንስ ራስ
እንዲቆረጥ የዘፈነች
(ማቴ 14:1-12፤ ማር 6:14-29)
አንቲጳጠር
(እናቱ- ዶሪስ)

ወደ እኔ ተመልሳችሁ የት እንዳለ ንገሩኝ”
አላቸው::
9ጠቢባኑ ንጉሡ ያለውን ከሰሙ በኋላ
ጕዞአቸውን ቀጠሉ:: ይህም በምሥራቅ[a]
ያዩት ኮከብ እየመራቸው ሕፃኑ እስካለበት
ድረስ ወሰዳቸው:: 10ኮከቡንም ሲያዩ ከመጠን
በላይ ተደሰቱ:: 11ወደ ቤትም በገቡ ጊዜ ሕፃ
ኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩ፤ ተንበርክከ
ውም ሰገዱለት:: ሣጥኖቻቸውን ከፍተው
ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤም አቀረቡለት:: 12እግ
ዚአብሔርም ወደ ሄሮድስ እንዳይመለሱ
በሕልም ባስጠነቀቃቸው መሠረት፣ መንገድ
አሳብረው ወደ አገራቸው ተመለሱ::

## ወደ ግብፅ ሽሽት

13ጠቢባኑ ከሄዱ በኋላ የጌታ መልአክ
ለዮሴፍ በሕልም ተገለጠ፣ “ተነሥ! የምት
መለስበትን ጊዜ እስካስታውቅህ ድረስ ሕፃ
ኑንና እናቱን ይዘህ ወደ ግብፅ በመሸሽ
በዚያ ቈይ፤ ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይሻ
ልና” አለው::
14ስለዚህም ዮሴፍ ተነሣ፤ ሕፃኑንና እና
ቱን ይዞ በሌሊት ወደ ግብፅ ሄደ፤ 15በዚያም
ሄሮድስ እስከ ሞተበት ጊዜ ድረስ ኖረ::
በዚህም፣ “ልጄን ከግብፅ ምድር ጠራሁት” በማ
ለት እግዚአብሔር በነቢዩ አንደበት የተናገ
ረው ቃል ተፈጸመ::
16ሄሮድስ ጠቢባኑ እንዳታለሉት በተረዳ
ጊዜ በጣም ተናደደ:: ከጠቢባኑ በተነገረው
ጊዜ መሠረት ዕድሜያቸው ሁለት ዓመትና
ከዚያም በታች የሆኑትን የቤተ ልሔምንና
የአካባቢዋን መንደሮች ወንድ ልጆች ሁሉ
ልኮ አስገደለ:: 17በዚህም በነቢዩ በኤርምያስ
እንዲህ ተብሎ የተነገረው ተፈጸመ፤
18“የልቅሶና የታላቅ ዋይታ ድምጽ፣
በራማ ተሰማ፤
ራሔል ስለ ልጆቿ አለቀሰች፤
መጽናናትም አልቻለችም፤
ልጆቿ ሁሉ አልቀዋልና::”

## ከግብፅ ወደ ናዝሬት

19ሄሮድስ ከሞተ በኋላ የእግዚአብሔር
መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ተገለጠ፣ 20“ተነሣ፤
ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ እስራኤል
ምድር ተመለስ፤ ሕፃኑን ለመግደል የሚሹት
ሞተዋልና” አለው::
21ዮሴፍም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን
በመያዝ ወደ እስራኤል ምድር ተመለሰ፤
22ነገር ግን አርኬላዎስ በአባቱ በሄሮድስ
ቦታ በይሁዳ መንገሡን በሰማ ጊዜ ወደዚያ
መሄድ ፈራ:: ጌታ በሕልም ስላስጠነቀቀው፣
ወደ ገሊላ አውራጃ ሄደ፤ 23ናዝሬት ወደ
ምትባል ከተማም ሄዶ መኖር ጀመረ:: በዚ
ህም በነቢያት፣ “ናዝራዊ ይባላል” ተብሎ
የተነገረው ትንቢት ተፈጸመ::

## የመጥምቁ ዮሐንስ ስብከት

3፥1-12 ተጓ ምብ - ማር 1፥3-8፤ ሉቃ 3፥2-17

3በዚያን ወራት መጥምቁ ዮሐንስ በይ
ሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ::
2ስብከቱም፣ “መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና
ንስሓ ግቡ” የሚል ነበር:: 3በነቢዩ በኢሳይ

[a]9 ወይም ሲነሣ አይተው

2፥11 መዝ72፥10፤ ኢሳ60፥3
2፥12 ቍ 13:19:22 ፤ማቴ27፥19፤ዕብ 11፥7
2፥13 ቍ 12:19:22 ፤ማቴ27፥19፤ሐሥ 5፥19፤ራእ12፥4
2፥15 ቍ 17:23፤ዘፀ 4፥22:23፤ሆሴ11፥1፤ ማቴ1፥22
2፥17 ቍ 15:23፤ ማቴ1፥22
2፥18 ዘፍ35፥19፤ ኤር31፥15
2፥19 ቍ 12:13: 22፤ማቴ27፥19፤ሐሥ 5፥19
2፥20 ዘፀ4፥19
2፥22 ቍ 12:13:19 ፤ማቴ27፥19፤ሉቃ 2፥39
2፥23 ቍ 15:17፤ ማቴ1፥22፤ማር1፥9: 24፤6፥1፤ሉቃ1፥26፤ 2፥39:51፤4፥16:23፤ ዮሐ1፥45:46
3፥1 ቍ 13:14፤9፥ 14፤11፥2-14፤ 14፥ 1-12፤ሉቃ1፥13: 57-66፤3፥2-19፤ሐሥ 19፥3:4
3፥2 ዳን7፥14፤ማቴ 4፥17፤6፥10፤7፥21፤ 25፥34፤ሉቃ11፥20፤ 17፥20:21፤19፥11፤ 21፥31፤ዮሐ3፥3:5፤ ሐሥ1፥3:6

2፥11 *ቤትም፤* ጠቢባኑ ኢየሱስን ለማየት የመጡት፣ በዘል ማድ እንደሚነገረውና እረኞቹ እንዳደረጉት፣ ሕፃኑ በተወለደበት ምሽት በግርግም እያለ ሳይሆን፣ ጥቂት ወራት ካለፉ በኋላ በቤቱ ውስጥ ከእናቱ ጋር እንዳለ ነበር:: *ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር፤* በቍጥር 11:13-14:20-21 ላይ እንደምናየው፣ ሕፃኑ ኢየ ሱስና እናቱ ማርያም በአንድ ላይ በተጠሩ ቍጥር፣ በቅድሚያ የሚጠቀሰው ኢየሱስ ነው:: *ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤም፤* እነዚህ ሦስት ዓይነት ስጦታዎች፣ “ጠቢባኑ” ሦስት ነበሩ ለሚለው አፈ ታሪክ መነሻ ሳይሆን አይቀርም:: መጽሐፍ ቅዱስ የጠቢባኑ ቍጥር ስንት እንደ ነበረ አይገልጽም፤ ነገር ግን ነገሥታት እንዳ ልነበሩ የታወቀ ነው:: ከርቤ፤ የዘፍ37፥25 ማብ ይመ::

2፥15 *ሄሮድስ እስከ ሞተበት ጊዜ፤* ይህ የሆነው ጌታ ከተ ወለደ ጥቂት ጊዜያት በኋላ ነው፤ 4 ዓ.ቅ.ክ. ማለት ነው:: *ልጄን ከግብፅ ምድር ጠራሁት፤* በትንቢተ ሆሴዕ 11፥1 የሚገኘው ይህ ጥቅስ በመጀመሪያ በሙሴ ዘመን እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፅ ለማውጣት እንደ ጠራቸው የተነገረ ነው:: ይሁን እንጂ ማቴዎስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ይህንኑ ጥቅስ ለኢየሱስ ተጠቅሞአል:: የእግዚብሔር ልጆች የሆኑት፣ የእስራኤላውያን ታሪክ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ በሆነው በኢየሱስ ሕይወት እንደ ተጠቃለለ ማቴዎስ ያስተውላል:: የእስራኤል ሕዝብ እንደ መንግሥት ሳይበረታ ወደ ግብፅ ወርዶ እንደ ነበረ ሁሉ፣ ሕፃኑም ኢየሱስ ወደዚሁ አገር ወረደ፤ የእስራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር ምሪት ከግብፅ አገር እንደ ወጣ ሁሉ ኢየሱስም በእግዚአበሔር ምሪት ከግብፅ አገር ወጥቶአል:: ኢየሱስና ወላጆቹ በግብፅ አገር ምን ያህል ጊዜ እንደ ቆዩ ግን አይታወቅም::

2፥16 *ሁለት ዓመትና ከዚያም በታች ... ወንዶች ልጆች ሁሉ ልኮ አስገደለ፤* በዚህ ጊዜ የተገደሉት ሕፃናት ብዛት በሺህ እንደሚቈጠር ተጋንኖ ይነገራል፤ ግድያው የሚዘገንን ቢሆንም ቤተልሔምን በመሰለች ትንሽ መንደር ይቅርና የአካባቢዋ ሰፈሮች ቢጨመሩ እንኳ፣ የተገደሉት ሕፃናት ቍጥር በዘልማድ ተጋንኖ የሚወራውን ያህል ላይሆን ይችላል::

2፥18፤ የኤር31፥15 ማብ ይመ::

2፥22 *አርኬላዎስ፤* የታላቁ ሄሮድስ ልጅ ሲሆን፣ ይሁዳንና ሰማርያን የገዛው ለአሥር ዓመት ብቻ ነው (ከ4ዓ.ቅ.ክ. - 6ዓ.ም):: እጅግ በጣም ጨካኝና ፈላጭ ቈራጭ ስለ ነበር፣ ከሥልጣኑ እንዲወርድ ተደርጎአል:: ከዚያ በኋላ ይሁዳ ሥልጣኑን ከሮም መንግሥት በተቀበለ እንደ ራሴ የምትተዳደር የሮም ግዛት ሆነች:: *ገሊላ፤* ኢየሱስ በአካለ ሥጋ በምድር ላይ በነበረበት ዘመን በታሪክ “ፓለስቲይን” ወይም “መካከለኛው ምሥራቅ” ተብሎ በሚታወቀው ሰሜናዊ ክፍል ነበረች::

2፥23 *ናዝሬት፤* በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በየትኛውም ክፍል ያልተጠቀሰችና የማትታወቅ ከተማ ናት፤ ኢየሱስም የኖረ ባት ከተማ ነበረች (13፥54-57፤ ሉቃ2፥39፤ 4፥16-24፤ ዮሐ 1፥45-46 ይመ):: *ናዝራዊ ይባላል፤* ይህ አባባል በብሉይ ኪዳን ውስጥ ቃል በቃል አይገኝም፤ ምናልባት በብሉይ ኪዳን የሚገ ኙት ነቢያት መሲሑ እንደሚናቅ አስቀድመው የተናገሩትን ትንቢት ሊያመለክት ይችላል (መዝ22፥6፤ ኢሳ53፥3 ይመ):: ኢየ ሱስ በነበረበት ዘመን “ናዝራዊ” ወይም “የናዝሬት ሰው” የሚለው ቃል “የተናቀ” የሚል ትርጓሜ ይሰጠው ነበር (ዮሐ 1፥45-46):: አንዳንዶች፣ ማቴዎስ ኢየሱስን “ናዝራዊ” ነው ሲል፣ ምናልባት በኢሳ11፥1 ላይ እንደተጠቀሰው ማለትም “ቅርንጫፍ” የሚለውን ሐሳብ ለመግለጽ ይሆናል ይላሉ::

3፥1 *መጥምቁ ዮሐንስ፤* ለኢየሱስ አገልግሎት አስቀድሞ መንገድ የሚያዘጋጅ ሲሆን፣ በ7 ዓ.ቅ.ክ. ገደማ ከካህኑ ከዘካርያ ስና ከሚስቱ ከኤልሣቤጥ ተወለደ (ሉቃ1፥5-80 ይመ):: *የይሁዳ ምድረ በዳ፤* የኢየሩሳሌም ቤተ ልሔም አምባ ካለበት አንሥቶ እስከ ዮርዳኖስ ወንዝና እስከ ሙት ባሕር ድረስ 32 ኪ.ሜ. ርቀት ያለውን ቦታ የሚሸፍን ምድረ በዳ ነው፤ ምናልባትም ዮሐ ንስ የኖረበት አገር ሳይሆን አይቀርም (ከሉቃ1፥80 ጋር ያነጻጽሩ)::

3፥2 *ንስሐ ግቡ፤* በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ፍጹም የሆነ ለውጥ ማድረግን ያመለክታል:: *መንግሥተ ሰማያት፤* ይህ ሐረግ የሚገኘው በማቴዎስ ወንጌል ብቻ ሲሆን፣ 33 ጊዜ ተ ጽፎአል (በመግቢያው ላይ “ወንጌሉ የተጻፈላቸው ሰዎች” የሚ ለውን ይመ):: ማርቆስና ሉቃስ “የእግዚአብሔር መንግሥት”

ያስ እንዲህ ተብሎ የተነገረለት እርሱ ነው፤
"በምድረ በዳ፣
'የጌታን መንገድ አዘጋጁ፤
ጎዳናውንም አስተካክሉ' እያለ የሚጮህ
ድምፅ::"

4የዮሐንስ ልብስ የግመል ጠጕር ሲሆን፣
ወገቡንም በጠፍር ይታጠቅ ነበር:: ምግቡም
አንበጣና የበረሃ ማር ነበር:: 5ከኢየሩሳሌም፣
ከመላው ይሁዳና በዮርዳኖስ ዙሪያ ካለው
አገር ሁሉ ሰዎች ወደ ዮሐንስ ይጐርፉ፣
6ኀጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ
ወንዝ በእርሱ ይጠመቁ ነበር::
7ብዙ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ወደሚያ

3፥3 ኢሳ40፥3፤ ሚል3፥1፤ሉቃ1፥76 1ዮሐ1፥23
3፥4 ዘሌ11፥22፤ 2ነገ1፥8፤ማቴ3፥1
3፥6 ቍ11፤ማር1፥4
3፥7 ማቴ12፥34፤ 23፥33፤ሮሜ1፥18
3፥8 ሐሥ26፥20
3፥9 ሉቃ3፥8
3፥10 ማቴ7፥19፤ ሉቃ3፥9፤13፥6-9፤ ዮሐ15፥2፡6
3፥11 ቍ6፤ኢሳ 4፥4፤ማር1፥4፡8፤ ሐሥ 2፥3፡4

ጠምቅበት ስፍራ ሲመጡ ባየ ጊዜ እንዲህ
አላቸው፤ "እናንት የእፉኝት ልጆች! ለመሆኑ
ከሚመጣው ቍጣ እንድታመልጡ ማን መከ
ራችሁ! 8ለንስሓ የሚገባ ፍሬ አፍሩ፤ 9'አብ
ርሃም አባት አለን' በማለት ራሳችሁን አታ
ታሉ፤ እግዚአብሔር ከእነዚህ ድንጋዮች
ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣ ይችላል እላች
ኋለሁና:: 10እነሆ፤ ምሣር የዛፎችን ሥር
ሊቈርጥ ተዘጋጅቶአል፤ መልካም ፍሬ የማ
ያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል፤ ወደ እሳትም
ይጣላል::
11"እኔ ለንስሓ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤
ነገር ግን ጫማውን መሸከም የማይገባኝ፣
ከእኔ የሚበልጥ ኀያል ከእኔ በኋላ ይመ

ብለው የጻፉትን ሐረግ፣ ማቴዎስ አራት ጊዜ ብቻ ይጠቅሰዋል (የማር11፥30 ማብ ይመ):: *መንግሥተ ሰማያት* የእግዚአብሔር አገዛዝ ሲሆን፣ በአሁኑ ዘመን በእውን ያለና ወደ ፊትም በተስፋ የሚጠበቅ ነው:: የእግዚአብሔር *መንግሥት* የሚለው ሐሳብ የኢየሱስ ትምህርት ማእከላዊ ጕዳይ ሲሆን፣ በማቴዎስ ወንጌል ብቻ 50 ጊዜ ተጠቅሶአል::

*3፥3፤* ሉቃስ ሁለት ጥቅሶችን ያከለ ቢሆንም፤ ሦስቱም ወንጌሎች (ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ) ኢሳ40፥33 በመጥቀስ ከመጥምቁ ዮሐንስ ጋር ያያይዙታል:: *ጎዳናውንም አስተካክሉ፤* "የጌታን መንገድ አዘጋጁ" ከሚለው ሐረግ ጋር አቻ አባባል ነው (የሉቃ 3፥4 ማብ ይመ):: የተፈለገውም ዝግጅት ሞራላዊና መንፈሳዊ ገጽታ ነበረው::

3፥4 *አንበጣና የበረሓ ማር፤* በበረሃ የሚኖር ሰው ትናንሽ ነፍሳትንና አንበጣዎችን ለመብላት አያቅማማም፤ አንበጣም ለመብላት ከተፈቀዱት ምግቦች አንዱ ነበር (ዘሌ11፥21-22):: የዮሐንስ ተራ አመጋገብ፣ አለባበስና አኗኗር በራስ ወዳድነት ላይ የሚያተኵረውን የመንደላቀቅ ኑሮ በግልጽ የሚቃወም ነበር::


3፥6 *በዮርዳኖስ ወንዝ፤* የማር 1፥5 ማብ ይመ::

3፥7 *ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን፤ ፈሪሳውያን* (የማር 2፥16፤ የሉቃ 5፥17 ማብ ይመ) ለታይታ ያህል የሙሴን ሕግና በቃል "ሲነገር የኖረውን" የአባቶችን ወግ የሚጠብቁ (15፥2)፣ ሥርዓትን የሚያጠብቁና የማፈንገጥ ሐሳብ ያላቸው ወገን ነበሩ:: *ሰዱቃውያን* (የማር12፥18፤ የሉቃ20፥27፤ የሐሥ4፥1 ማብ ይመ) ዓለማዊ አመለካከትና የፖለቲካ ዝንባሌ የነበራቸው ሲሆኑ፣ ከትክክለኛው ትምህርተ መለኮት ያፈነገጡ፣ በተለይም የትንሣኤን፣ የመላእክትንና የመናፍስትን መኖር የሚክዱ ነበሩ (ሐሥ 23፥8)::

3፥9 *አብርሃም አባት አለን፤* ዮሐ 8፥39 ይመ:: ድኅነት (መዳን) በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኝ እንጂ (ሮሜ2፥28-29፤ ገላ3፥7፡9፡29)፣ ለአይሁድም ቢሆን ከዘር የሚወረስ ወይም በትውልድ የሚተላለፍ አይደለም::

3፥10 *ምሣር የዛፎችን ሥር ሊቈርጥ ተዘጋጅቶአል፤* ፍርድ መቃረቡን ያመለክታል::

3፥11 *ለንስሐ በውሃ፤* የዮሐንስ ጥምቀትና ንስሐ መግባት የተቈራኙ ነበሩ፤ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያንም ንስሐ ለመግባታቸው አንድም ማረጋገጫ ባለማሳየታቸው፣ ዮሐንስ እነርሱን



ጣል። እርሱም በመንፈስ ቅዱስና በእሳት
ያጠምቃችኋል። 12መንሹ በእጁ ነው፤ ዐው
ድማውን ያጠራል፤ ስንዴውን በጐተራ ይከ
ታል፤ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃ
ጥለዋል።"

## የኢየሱስ መጠመቅ

3፥13-17 ተጓ ምብ - ማር1፥9-11፤ ሉቃ3፥21፡22፤ ዮሐ1፥31-34

13በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ለመጠ
መቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ። 14ዮሐ
ንስ ግን፣ "ይህማ አይሆንም፤ እኔ ባንተ
መጠመቅ ሲያስፈልገኝ እንዴት አንተ ወደ
እኔ ትመጣለህ?" ብሎ ተከላከለ።
15ኢየሱስም፣ "ግድ የለም ፍቀድልኝ፤ ይህ
ን በማድረግ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባ
ናልና" አለው፤ ዮሐንስም በነገሩ ተስማማ።
16ኢየሱስም እንደ ተጠመቀ ከውሃው
ወጣ፤ ወዲያውኑም ሰማይ ተከፍቶ የእግዚአ
ብሔር መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድበት
አየ። 17እነሆ፣ "በእርሱ ደስ የሚለኝ የም
ወደው ልጄ ይህ ነው" የሚል ድምፅ ከሰ
ማይ ተሰማ።

3፥12 ማቴ13፥30፤ 25፥41
3፥13 ማቴ3፥1፤ ማር1፥4
3፥16 ኢሳ11፥2፤ 42፥1፤ሕዝ1፥1፤ ዮሐ 1፥51፤ ሐሥ7፥56፤ 10፥11፤ ራእ4፥1፤ 19፥11
3፥17 ዘዳ4፥12፤ መዝ2፥7፤ኢሳ42፥1፤ ማቴ12፥18፤17፥5፤ ማር1፥11፤9፥7፤ ሉቃ 3፥22፤9፥35፤ ዮሐ12፥28፤ ሐሥ 13፥33፤ ዕብ1፥1-5፤ 5፥5፤2ጴጥ1፥17፡18
4፥1 ዘፍ3፥1-7፤ ዕብ 4፥15
4፥2 ዘፀ34፥28፤ 1ነገ19፥8
4፥3 ማቴ3፥17፤ 14፥33፤16፥16፤ 27፥ 54፤ማር3፥11፤ ሉቃ 1፥35፤22፥70፤ ዮሐ 1፥34፡49፤ 5፥25፤11፥ 27፤20፥31፤ሐሥ 9፥20፤ሮሜ1፥4፤1ተሰ 3፥5፤1ዮሐ5፥10-13፡ 20፤ራእ2፥18
4፥4 ዘዳ8፥3፤ዮሐ 4፥34

## የኢየሱስ መፈተን

4፥1-11 ተጓ ምብ - ማር 1፥12፡13፤ ሉቃስ 4፥1-13

4 ከዚህ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን
በዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ ወደ ምድረ
በዳ ወሰደው። 2አርባ ቀንና አርባ ሌሊት
ከጾመ በኋላ ተራበ። 3ፈታኙም ወደ ኢየ
ሱስ ቀርቦ፣ "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እነዚ
ህን ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ እዘዝ" አለው።
4ኢየሱስም፣ " 'ሰው ከእግዚአብሔር አፍ
በሚወጣው ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ

ሊያጠምቅ አልፈለገም (ቍ7-8)። *በመንፈስ ቅዱስና በእሳት፤* እዚህ ላይ "እሳት" ወደ ፊት የሚመጣውን ፍርድ የሚያመለክት ቢሆንም (ቍ12)፣ በጰንጠቆስጤ ቀን አስደናቂ በሆነ መንገድ ታይቶአል (ሐሥ1፥5፡8፤ 2፥1-13፤11፥16)። መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ላይ እንደሚወርድ በኢል2፥28-29 ላይ ተስፋ ተሰቶጥ ነበር።

3፥12 *መንሹ፤* እህል ከተወቃ በኋላ እንዴት በመንሽ ለነፋስ እንደሚሰጥ የሩት1፥22 ማብ ይመ። እዚህ ላይ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት የሚሆነውን ፍርድ ለማመልከት የገባ ዘይቤአዊ አነጋገር ነው። አንዳንድ ጊዜ የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የክርስቶስን የመጀመሪያ ምጽአትና ዳግም ምጽአት ሲገልጹ አንድ ክስተት መስሎ ይታያል።

3፥15፤ ይህ ሁኔታ ክርስቶስ የመሲሕነት አገልግሎቱን እንደ ጀመረ ያመለክታል፤ ለመጠመቁም ብዙ ምክንያቶች ነበሩ፡- 1) በዚህ ላይ እንደ ተጠቀሰው የመጀመሪያው "ጽድቅን ሁሉ ለመፈጸም ነው" የሚል ነው፤ ጥምቀቱ ለአብ የተለየ መሆኑንና በእርሱም መሾሙን በግልጽ ያሳያል፤ ይህም፣ በተለይ መንፈስ ቅዱስ በላዩ በመውረዱና (ቍ16) አብ በተናገረው ቃል (ቍ17 ይመ፤ ከመዝ2፥7፤ ከኢሳ42፥1 ጋር ያነጻጽሩ) ታይቶአል። በእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ዕቅድ መሠረት በመሲሑ ሕይወት ላይ እንዲታይ የተፈለገው ፍጹም የሆነው መሻቱ በኢየሱስ ሕይወት ሙሉ በሙሉ ተገልጾአል። 2) ኢየሱስ በተጠመቀበት ጊዜ፣ ዮሐንስ የመሲሑን መምጣትና አገልግሎት መጀመሩን ይፋ አደረገ (ዮሐ1፥31-34)። 3) ኢየሱስ ንስሐ መግባትና ከኀጢአት መንጻት የማያስፈልገው ሆኖ ሳለ፣ የእኛ ምትክ በመሆን (2ቆሮ5፥21) በጥምቀቱ ራሱን ሙሉ በሙሉ ከሰው ኀጢአትና ውድቀት ጋር አንድ አድርጎአል። 4) የእርሱ ጥምቀት ለተከታዮቹ ምሳሌ ነበር።

3፥16-17፤ የሥላሴ አካላት እዚህ ላይ በግልጽ ታይተዋል።

3፥16 *የእግዚአብሔር መንፈስ፤* ኢየሱስ ኀጢአት የሌለበት እንደ መሆኑ፣ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ የወረደው ኀጢአትን ለማሸነፍ ሳይሆን፣ ሥጋ የለበሰውን (ትሥጉት) መለኮት በመሲሕነቱ ለአገልግሎት ለማዘጋጀት ነበር (የመሳ3፥10 ማብ ይመ)። በተጨማሪ የማር 1፥10 ማብ ይመ።

3፥17፤ ከመዝ2፥7 ና ከኢሳ42፥1 ጋር የሚዛመድ ነው።

4፥1-11፤ ኢየሱስ የይፋ አገልግሎቱን ከመጀመሩ አስቀድሞ፡- ያጋጠመው ፈተና ትኩረት የሚሰጠውና ስለ ሁኔታው በሚገባ ለመረዳት የሚቻለው በብሉይ ኪዳን ሲጠበቅ እንደ ነበረው መሲሕ ሆኖ በመገኘቱ ነው። ከሦስቱ ፈተናዎቹ በመጀመሪያው ሁኔታ ኢየሱስ መለኮታዊ ኀይሉን ለግል ፍላጎቱ ቢጠቀም ኖሮ፣ ደግሞም በሁለተኛው ፈተናው ብዙ ሰዎች እንዲከተሉት ኀይሉን በመጠቀም ታምራትንና ትንግርታዊ ነገሮችን ቢያደርግ ኖሮ፣ ወይም በሦስተኛው ፈተናው ከሰይጣን ሐሳብ ጋር ቢስማማ ኖሮ የመጣበትን ተልእኮ ሊፈጽም አይችልም ነበር። ኢየሱስ ኀጢአት ለማድረግ ፍላጎትም ሆነ ዝንባሌ አልነበረውም፤ እነዚህ የቀረቡለት ፈተናዎች በራሳቸው ኀጢአት ነበሩና (ማቴ 5፥22፡28)። ጌታ ኢየሱስ አምላክ እንደ መሆኑ መጠን በተግባሩም ሆነ በንግግሩ፣ ወይም በውስጣዊ ፍላጎቱ ኀጢአት አልፈጸመም (2ቆሮ5፥21፤ ዕብ7፥26፤ 1ጴጥ2፥22፤ 1ዮሐ3፥5)። ይሁን እንጂ የኢየሱስ መፈተን ለሌሎች አርአያ ለመሆን ብቻ የቀረበ የይምሰል ፈተና ሳይሆን፣ በእርግጠኝነት በእውን ተፈትኖአል። "እርሱ እንደ እኛ በማንኛውም ሁኔታ የተፈተነ፣ ነገር ግን ኀጢአትን ያልሠራ" ነበር (ዕብ4፥15)። ፈታኙ ወደ ኀጢአት የገፋፋው አመቺ ሁኔታ ጠብቆ ነበር። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ቢሆንም፣ ማንኛውም አማኝ ሊጠቀምበት የሚችለውን የመንፈስን ሰይፍ፣ ይኸውም የእግዚአብሔርን ቃል፣ በመጠቀም ሰይጣንን ድል አደረገ (ኤፌ6፥17)። ሦስቱንም ፈተናዎች (ቍ4፡7፡10) የተቋቋመው በዘዳግም የሚገኘውን የእውነት ቃል መሣሪያ በማድረግ ነበር።

4፥1 *መንፈስ ... ይፈተን ዘንድ ... ወሰደው፤* በመለኮት ታቅዶ የቀረበው ይህ ፈተና በዘዳ8፥1-5 ያለውን ሐሳብ መሠረት በማድረግ ነው፤ ኢየሱስ ለዲያብሎስ በመጀመሪያ የሰጠው መልስም ከዚሁ ክፍል የተጠቀሰ ነው (ቍ4 ይመ)። በዚያ ክፍል ላይ ሙሴ፣ "ትእዛዞቹን ስለ መጠበቅህና ስላለመጠበቅህ በልቡናህ ያለውን ለማወቅ ሲል፣ ዝቅ ዝቅ እንድትልና እንድትፈተን" በማለት እግዚአብሔር እስራኤላውያንን አርባ ዓመት ሙሉ በምድረ በዳ እንዴት እንደ መራቸው ያስታውሳል። በዚህም ላይ ኢየሱስ ገና በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ ወደ ተመሳሳይ ፈተና እንዲገባ ግድ ሆኖበት እንደ ነበርና፤ "ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል" መሠረት የሚመላለስ እውነተኛው እስራኤላዊ መሆኑን አስመስክሮአል። ምንም እንኳ አዳም የቀረበለትን ትልቅ ፈተና ማለፍ አቅቶት መላውን የሰው ዘር ኀጢአት ውስጥ ቢከትም (ዘፍ3)፣ ኢየሱስ ታማኝ ሆኖ በመገኘት የተቀበሉትን ሁሉ ለማዳን ብቃት ያለው አዳኝ መሆኑን አሳየ። ደግሞም ኢየሱስ ለእኛ "ርኅሩኅና ታማኝ ሊቀ ካህናት" (ዕብ2፥17) በመሆን፣ "የሚፈተኑትን ሊረዳቸው እንዲችል" (ዕብ2፥15፤ 4፥15-16 ይመ)፣ እንደ እስራኤላዊና እንደ ማንኛውም ሰው ሆኖ ፈተና መቀበሉ አስፈላጊ ነበር። በፈተናም ጊዜ እስከ መጨረሻው ታማኝ ሆኖ በመጽናቱ፣ ፈተና ለሚገጥማቸው አማኞች ሁሉ አርአያ ሆኖአል። *በዲያቢሎስ ይፈተን ዘንድ፤* በእርግጥ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይፈትናል፤ የሚፈትናቸውም እምነታቸውን ለማጽናት ነው (ያዕ 1፥2-4)፤ በክፋ የሚፈትነው ግን ዲያቢሎስ ነው (የዘፍ22፥1 ማብ፤ 1ዮሐ3፥8፤ ራእ2፥9-10 እና ማብ፤ ራእ12፥9-10 ይመ)። በዕብራይስጥ ቋንቋ 'ሰይጣን' በግሪኩ ደግሞ 'ዲያብሎስ' የሚባለው በከሳሽነቱና በሐሰት አባትነቱ ይታወቃል። ዲያብሎስ አካላዊ ፍጥረት እንጂ የሌላ አካል ወይም የኀይል ተቀጽላ አይደለም። በመሆኑም እስከ ጊዜው (ይሁ6 ይመ) የእግዚአብሔርና የመንግሥቱ ሥራ ቀንደኛ ጠላትና የጨለማው ሠራዊት መሪ እንደ ሆነ ይታወቃል።

4፥2 *አርባ ቀንና አርባ ሌሊት፤* ይህ ቍጥር ሙሴ (ዘፀ 24፥18፤ 34፥28) እና ኤልያስ (1ነገ19፥8) ያለፉበትን ልምምድ ወደ ትውስታ ያመጣል፤ እስራኤላውያን በምድረ በዳ ለአርባ ዓመት የተፈተኑትን ፈተና ያሳስባል (ዘዳ8፥2-3)።

4፥3 *የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፤* "የእግዚአብሔር ልጅ ነህና" ማለት ነው። ዲያብሎስ ኢየሱስን የፈተነው የእግዚአብሔር ልጅነቱን እንዲጠራጠር ለማድረግ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ መሆኑ መለኮታዊ ኀይሉን ለራሱ ክብር እንዲያውለው ለመገፋፋት ነበር።

*4፥4፤* እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በታምር መና እንዳ

አይኖርም’ ተብሎ ተጽፎአል” ሲል መለ
ሰለት::
[5]ቀጥሎም ዲያብሎስ ኢየሱስን ወደ
ቅድስት ከተማ በመውሰድ በቤተ መቅደ
ሱም ዐናት ላይ አውጥቶ፣ [6]“የእግዚአብሔር
ልጅ ከሆንህ ራስህን ወደ መሬት ወርውር፤
እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤

“ ‘እግርህ በድንጋይ እንዳይሰናከል፣
በእጃቸው ያነሡህ ዘንድ፣
መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል::’ ”

[7]ኢየሱስም፣ “እንደዚሁም በመጻሕፍት፣
‘እግዚአብሔር አምላክህን አትፈታተነው’
ተብሎ ተጽፎአል” በማለት መለሰለት::
[8]እንደ ገናም ዲያብሎስ ኢየሱስን እጅግ
ከፍ ወዳለ ተራራ አወጣው፤ የዓለምንም መን
ግሥታት ከነክብራቸው አሳየውና፣ [9]“ወድቀህ
ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ” አለው::
[10]ኢየሱስም፣ “አንተ ሰይጣን ከፊቴ ራቅ!
‘ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ስገድ፤ እርሱንም
ብቻ አምልክ’ ተብሎ ተጽፎአልና” አለው::

4፥5 ነህ11፥1፤ዳን 9፥24፤ማቴ27፥53
4፥6 ቍ3፤ መዝ 91፥11:12
4፥7 ዘዳ6፥16
4፥10 ዘዳ6፥13፤ 1ዜና21፥1፤ኢዮ1፥6-9 ፤ማቴ16፥23፤ማር 4፥15፤ሉቃ10፥18፤ 13፥16፤22፥3:31፤ ሮሜ16፥20፤2ቆሮ 2፥11፤11፥14፤2ተሰ 2፥9፤ራእ12፥9
4፥11 ማቴ26፥53፤ ሉቃ22፥43፤ዕብ1፥14 ፤ያዕ4፥7
4፥12 ማቴ14፥3፤ ማር1፥14
4፥13 ማር1፥21፤9፥33፤ ሉቃ4፥23:31፤ ዮሐ2፥12፤4፥46:47
4፥14 ማቴ1፥22
4፥16 ኢሳ9፥1:2፤ ሉቃ2፥32፤ ዮሐ 1፥4:5:9
4፥17 ማቴ3፥2

[11]ከዚያም ዲያብሎስ ትቶት ሄደ፤ መላእ
ክትም መጥተው አገለገሉት::

### ኢየሱስ ስብከት መጀመሩ

[12]ኢየሱስ የዮሐንስን መታሰር በሰማ ጊዜ
ወደ ገሊላ ተመለሰ:: [13]የናዝሬትንም ከተማ
ትቶ፣ በዛብሎንና በንፍታሌም አካባቢ በባ
ሕሩ አጠገብ በምትገኘው በቅፍርናሆም
ከተማ መኖር ጀመረ:: [14]በዚህም በነቢዩ ኢሳ
ይያስ እንዲህ ተብሎ የተነገረው ትንቢት
ተፈጸመ፤
[15]“የዛብሎን ምድር፣ የንፍታሌም ምድር፣
ከዮርዳኖስ ማዶ በባሕር መንገድ አጠገብ፣
ያለው የአሕዛብ ገሊላ፣
[16]በጨለማ የሚኖር ሕዝብ፣
ታላቅ ብርሃን አየ፤
በሞት ጥላ ምድር ላለው፣
ብርሃን ወጣለት::”
[17]ከዚያ ጊዜ አንሥቶ ኢየሱስ፣ “ንስሐ
ግቡ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለ
ችና” እያለ መስበክ ጀመረ::

ወረደላቸው ሁሉ (ዘጸ8፥3)፣ ማንም ሰው ለመንፈሳዊ ምግቡ በእግዚአብሔር ላይ እምነቱን መጣል አለበት:: ኢየሱስ ለሚያስ ፈልገው ምግብ በአባቱ ታመነ እንጂ፣ በራሱ የታምር ሠራነት ችሎታ ለማግኘት አልፈለገም::


4፥5፤ የሉቃ4፥2 ማብ ይመ:: *ከቤተ መቅደሱም ዐናት፤* የሉቃ4፥9 ማብ ይመ:: *ቤተ መቅደስ፤* ቤተ መቅደስና የቤተ መቅደሱ ዙሪያ በታላቁ ሄሮድስ እንደ ገና ታንጾ ነበር (የ2፥1 ማብና ዮሐ2፥20. ይመ):: የቤተ መቅደሱ አደባባይ 300 ሜትር በ457 ሜትር የሚያህል ስፋት ነበረው፤ በደቡባዊ ምሥራቅ በኩል የነበረውን ተዳፋት ለማስተካከል ትልቅ መድረክ ተሠርቶለት ነበር:: መድረኩም እንዳይናጋ በትላልቅ ድንጋይ የተገነባ ድጋፍ ተደርጎለት ነበር:: በመድረኩም ላይ የቤተ መቅደሱ ሕንጻ፣ አደ ባባዮችና መግቢያዎች በተዋቡ ዓምዶች ተደግፈው ቆመዋል::

4፥12፤ *የዮሐንስን መታሰር፤* ማር1፥14 እና የሉቃ3፥20 ማብ ይመ:: ዮሐንስ በምን ምክንያት እንደ ታሰረ፣ በ14፥3-4 ተገልጾአል::

4፥13 *ቅፍርናሆም፤* በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ባትጠቀስም ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ዘመን ሰፋ ያለች ከተማ ነበረች፤ ጌታ ኢየሱስ በገሊላ ያገለግል በነበረበት ወቅት የጴጥሮስን ቤት እንደ ዋና ማረፊያ አድርጎ ይጠቀም ነበር (ማር 2፥1፤ 9፥33 ይመ):: የጴጥሮስ ቤት ተሠርቶበት ነበር በተባለው ስፍራ በአ ምስተኛው ምዕተ ዓመት የታነጸ፣ እንደ ቤተ መንግሥት ያለ ትልቅ አዳራሽ በአሁኑ ጊዜ ይታያል፤ ከዚያም ትንሽ ራቅ ብሎ በአራተኛው ምዕተ ዓመት የተሠራ ምኵራብ ይገኛል::

4፥15-16፤ *መሲሑን በተመለከተ ኢሳይያስ የተነበየው* ሌላው ትንቢት ነው፤ ኢየሱስ አብዛኛውን የአደባባይ አገልግሎቱን የፈጸመው ከገሊላ በስተ ሰሜንና በስተ ምዕራብ በሚገኘው “በዛብሎንና በንፍታሌም አካባቢ” ነበር (ቍ13)::

4፥17 *ከዚያ ጊዜ አንሥቶ፤* ይህ አባባል ለጌታ ኢየሱስ የአገልግሎት ምዕራፍ ትልቅ ቦታ እንደ ተሰጠው የሚገልጽ ሲሆን፣ በተለይ በማቴዎስ ወንጌል ሦስት ጊዜ ተጠቅሶአል (ማቴ16፥21፤ 26፥16 ይመ):: እንዲያውም አንዳንዶች ከዚያ ጊዜ አንሥቶ የሚለውን ሐረግ ማቴዎስ የኢየሱስን የአገልግሎት ምዕራፎች



## የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት መጠራት

4፥18-22 ተጓ ምብ - ማር1፥16-20፤ ሉቃ5፥2-11፤ ዮሐ1፥35-42

18ኢየሱስ በገሊላ ባሕር አጠገብ ሲያ
ልፍ፣ ሁለት ወንድማማቾች ማለትም ጴጥ
ሮስ የተባለውን ስምዖንንና ወንድሙን እን
ድርያስን አያቸው:: ዓሣ አጥማጆች ነበሩና
መረባቸውን ወደ ባሕሩ ይጥሉ ነበር:: 19ኢየ
ሱስም፣ "ኑ፣ ተከተሉኝ፤ ሰዎችን አጥማጆች
አደርጋችኋለሁ" አላቸው:: 20ወዲያው መረ
ባቸውን ትተው ተከተሉት::
21አለፍ እንዳለም፣ ሌሎች ሁለት ወንድ
ማማቾች፣ የዘብዴዎስን ልጅ ያዕቆብንና
ወንድሙን ዮሐንስን አየ:: ከአባታቸው ከዘ
ብዴዎስ ጋር በጀልባ ውስጥ መረባቸውን
ያበጁ ነበር:: ኢየሱስም ጠራቸው፤ 22ወዲያ
ውኑ ጀልባቸውንም ሆነ አባታቸውን ትተው
ተከተሉት::

4፥18 ማቴ15፥29፤ 16፥17:18፤ማር7፥31፤ዮሐ6፥1
4፥19 ቍ20:22፤ ማቴ8፥22፤ማር10፥21:28:52፤ሉቃ5፥28፤ ዮሐ1፥43፤21፥19:22
4፥20 ቍ19
4፥21 ማቴ17፥1፤ 20፥20፤26፥37፤ማር 3፥17፤13፥3፤ሉቃ 8፥51፤ዮሐ21፥2
4፥22 ቍ19
4፥23 ማቴ3፥2፤ 8፥16፤9፥35፤13፥54፤ 14፥14፤15፥30፤ማር 1፥14:21:39፤3፥10፤ ሉቃ4፥15:44፤7፥22፤ ዮሐ6፥59፤18፥20፤ ሐሥ10፥38፤20፥25፤ 28፥23:31
4፥24 ማቴ8፥6:16: 28፤9፥2:32፤12፥22፤ 15፥22፤17፥15፤ማር 1፥32፤2፥3፤5፥15:16:18፤ሉቃ2፥2
4፥25 ማር 3፥7:8፤ ሉቃ6፥17

## የበሽተኞች መፈወስ

23ኢየሱስም በምኵራቦቻቸው እያስተማረ፣
የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራች
ቃል እየሰበከ፣ በሕዝቡ መካከል ማንኛው
ንም ደዌና ሕመም እየፈወሰ በመላው ገሊላ
ይዘዋወር ነበር::
24ከዚህም የተነሣ ዝናው በመላዋ ሶርያ
ተሰማ፤ ሕዝቡም በተለያዩ በሽታዎች የታ
መሙትን፣ በክፉ ደዌ የሚሠቃዩትን፣ አጋ
ንንት ያደሩባቸውን፣ የሚጥል በሽታ ያለባ
ቸውን፣ ሽባዎችን ሁሉ ወደ እርሱ አመጡ፤
ፈወሳቸውም::
25ከዚህም የተነሣ ከገሊላ፣ ከ'ዐሥሩ ከተ
ሞች'፣ ከኢየሩሳሌም፣ ከይሁዳና ከዮርዳ
ኖስ ማዶ የመጡ ብዙ ሰዎች ተከተሉት::

በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች በመክፈል የተጠቀመበት ነበር ይላሉ:: *ንስሐ ግቡ፤* ኢየሱስ ይፋ አገልግሎቱን የጀመረው እንደ መጥምቁ ዮሐንስ፣ "ንስሐ ግቡ" በማለት ነበር (3፥2):: የእግዚአብሔር መንግሥት በራሱ በኢየሱስ ክርስቶስና በአገልግሎቱ በኩል ወደ ሰው በመቅረብ ላይ ስለ ነበረች፣ ሰዎች ንስሐ መግባት ነበረባቸው::

4፥18 *በገሊላ ባሕር፤* የማር1፥16 ማብ ይመ:: *መረባቸውን፤* በጀልባ ላይ ወይም ጥልቀት በሌለው ውሃ ውስጥ በመሆን ዓሣ ለማጥመድ የሚጣል ክብ መረብ ነው

4፥20፤ የማር 1፥17 ማብ ይመ::

4፥21 *መረባቸውን ያበጁ ነበር፤* ለሚቀጥለው ቀን የማጥመድ ተግባር ለማዘጋጀት መረብን ማጠብ፣ መጠገንና እንዲደርቅ ማስጣት ማለት ነው::


4፥23 *እያስተማረ ... እየሰበከ ... እየፈወሰ፤* የጌታ አገልግሎት ሦስት ገጽታ ነበረው:: ምኵራቦች (የማር1፥21 ማብ ይመ) በየሰንበቱ የሚያስተምርባቸው ሲሆኑ፣ በተቀሩት የሳምንቱ ቀናት ግን አያሌ ሕዝብን በመስክ ላይ ይሰብክ ነበር::

4፥24 *ሶርያ፤* ከገሊላ በስተ ሰሜን፣ በደማስቆና በሚድትራኒያን ባሕር መካከል ይገኝ የነበረ ምድር ነው:: *የሚጥል በሽታ ያለባቸውን፤* ይህ በሽታ በግሪክ ቋንቋ "የጨረቃ ምታት" ይባል ነበር፤ ይህም የሚጥል በሽታ መንሥኤው ከጨረቃ መለዋወጥ ጋር የተያያዘ ነው የሚለውን የጥንት እምነት ያንጸባርቃል::

4፥25 *ዐሥሩ ከተሞች፤* የግሪክ የሥልጣኔ ባህል ጐልቶ የሚታይባቸው በአንድ ላይ ያሉ ዐሥር ከተሞች ናቸው:: ከአንዱ ጥንታዊ ከተማ በቀር (ቤት ሻን)፣ ሁሉም ከገሊላ ባሕርና ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ ይገኙ ነበር:: እነዚያ የተያያዙ ከተሞች ከገሊላ ባሕር ሰሜን ምሥራቅ አንሥቶ ወደ ደቡብ እስከ ፊላደልፊያ (የዛሬዋ አማን) ድረስ የሚዘልቅ የቆዳ ስፋት ይሸፍኑ ነበረ::

## የሄሮድስ ቤተ መቅደስ

ከ20 ዓ.ቅ.ክ - 70 ዓ.ም



## የተራራው ስብከት

5፥3-12 ተጓ ምብ - ሉቃ 6፥20-23

5 ብዙ ሕዝብ እንደ ተሰበሰበ ባየ ጊዜ፣
ወደ ተራራ ወጣና ተቀመጠ፤ ደቀ መዛ
ሙርቱም ወደ እርሱ መጡ። [2]እንዲህም
እያለ ያስተምራቸው ጀመር፤
[3]በመንፈስ ድኾች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፤
መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ናትና።
[4]የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፤
መጽናናትን ያገኛሉና።
[5]የዋሆች ብፁዓን ናቸው፤
ምድርን ይወርሳሉና።
[6]ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን
ናቸው፤
ይጠግባሉና።
[7]ምሕረት የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው፤
ምሕረትን ያገኛሉና።
[8]ልባቸው ንጹሕ የሆነ ብፁዓን ናቸው፤
እግዚአብሔርን ያዩታልና።
[9]ሰላምን የሚያወርዱ ብፁዓን ናቸው፤
የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው
ይጠራሉና።
[10]ስለ ጽድቅ ብለው የሚሰደዱ ብፁዓን
ናቸው፤
መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ናትና።
[11]ሰዎች በእኔ ምክንያት ቢሰድቧችሁ፣
ቢያሳድዷችሁና ክፉውን ሁሉ በሐሰት ቢ
ያስወሩባችሁ፤ ብፁዓን ናችሁ። [12]በሰማይ
የምትቀበሉት ዋጋ ታላቅ ስለ ሆነ ደስ ይበ
ላችሁ፤ ሐሤት አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት
የነበሩትን ነቢያት እንደዚሁ አሳደዋቸዋልና።

### ጨውና ብርሃን

[13]"እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው
የጨውነት ጣዕሙን ቢያጣ ጣዕሙን መልሶ
ሊያገኝ ይችላልን? ወደ ውጪ ተጥሎ
በሰው ከመረገጥ በቀር ጥቅም አይኖረውም።
[14]"እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ፤ በተራራ
ላይ ያለች ከተማ ልትደበቅ አትችልም፤
[15]ሰዎችም መብራት አብርተው ከዕንቅብ
ሥር አያስቀምጡትም፤ በቤት ውስጥ ላሉት
ሁሉ እንዲያበራ በመቅረዝ ላይ ያስቀምጡ
ታል እንጂ። [16]እንደዚሁም ሰዎች ሥራችሁን
አይተው በሰማይ ያለውን አባታችሁን እንዲ
ያከብሩ ብርሃናችሁ በሰዎች ፊት ይብራ።

### የሕግ ፍጻሜ

[17]"ሕግንና የነቢያትን ቃል ለመሻር የመ

5፥3 ቆላ10:19፤ ማቴ25፥34
5፥4 ኢሳ61፥2:3፤ ራእ7፥17
5፥5 መዝ37፥11፤ ሮሜ4፥13
5፥6 ኢሳ55፥1:2
5፥7 ያዕ2፥13
5፥8 መዝ17፥15፤ 24፥3:4፤42፥2፤73፥1፤ ዕብ12፥14፤ራእ22፥4
5፥9 ቆላ44:45፤ ሮሜ8፥14፤14፥19፤ ያዕ 3፥18
5፥10 ቆላ3:19፤ ማቴ 25፥34፤ 1ጴጥ3፥14
5፥11 ኢሳ51፥7፤ ዮሐ15፥21
5፥12 2ዜና36፥16፤ መዝ9፥2፤ማቴ23፥31:37፤ ሐሥ5፥41፤7፥52፤ 2ቆሮ6፥10፤12፥10፤ ቆላ1፥24፤1ተሰ2፥15 ፤ዕብ11፥32-38፤ ያዕ 1፥2፤1ጴጥ1፥6፤ 4፥13:16
5፥13 ማር9፥50፤ ሉቃ14፥34:35
5፥14 ዮሐ8፥12
5፥15 ማር4፥21፤ ሉቃ8፥16፤11፥33
1ቆሮ10፥31፤ፊል 1፥11፤ቲቶ2፥14፤5፥16 ማቴ9፥8፤ 5፥17ዮሐ10፥34:35፤ሮሜ3፥31

*5፥1-7፥29፤* 'የተራራው ስብከት' በመባል የሚታወቀው በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ከሚገኙት አምስት ታላላቅ ትምህርቶች የመጀመሪያው ነው (ም5-7፤ 10፤ 13፤ 18፤ 24-25)። ይህም የሚከተሉትን ሦስት ዐበይት ጉዳዮችን የያዘ ነው፤ 1) መባረክ፤ ይህም ስለ ቡሩካን የተነገረ ነው (5፥1-12)፤ 2) ሥነ ምግባርን በተመለከተ የቀረበ ተግሣጽ ነው (5፥13-20፤ 6፥1-7፥23)፤ 3) በኢየሱስ የሥነ ምግባር ትምህርትና በአይሁድ ወግ መካከል ያለውን ንጽጽር የሚያመለክት ነው (5፥21-48)። ስብከቱ የተደመደመው የተሰጠውን ትምህርት ተግባር ላይ ማዋል ምን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ ለማሳየት በቀረበ ምሳሌና (7፥24-27)፣ ኢየሱስ እንዴት ባለ ሥልጣን ያስተምር እንደ ነበር በመገረም ለማድመጥ የተሰበሰበው ሕዝብ በሰጠው አስተያየት ነው (7፥28-29)።

ይህ ትምህርት ኢየሱስ በአንድ ወቅት ካስተማረው ውስጥ ተጨምቆ የቀረበ ይሁን፣ ወይም በተለያየ ወቅት ከሰጠው ትምህርት የተውጣጣ ለመሆኑ የጋራ የሆነ አመለካከት የለም። ምናልባት ማቴዎስ፣ ኢየሱስ ከአስተማረው ትምህርት አንዱን በመውሰድ በተለያየ ወቅት ቀርቦ ከነበረው ተመሳሳይነት ካለው የጌታ ትምህርት ጋር በማዛመድ አስፋፍቶ ሳያቀርብ አልቀረም። በማቴዎስ ወንጌል ከተጠቀሰው የተራራው ስብከት ውስጥ ሠለሳ አራቱ ጥቅሶች፣ በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ተጓዳኝ ከሚመስለው ከ"መስክ ስብከት" ይልቅ (ሉቃ6፥17-49)፣ በተለያየ ዐውድ በየቦታው (በሉቃስ ወንጌል) ውስጥ ተጠቅሰው ይገኛሉ

የተራራው ስብከት ላቅ ያለ ግብረ ገባዊና ሥነ ምግባራዊ ሕይወት ስለሚጠይቅ፣ አንዳንዶች ተግባራዊነት የሌለው ነው በማለት ትተውታል፤ ወይም የዚህ ዓይነት ሕይወት ወደ ፊት ሊመጣ ባለው መንግሥት የሚፈጸም ነው ይላሉ። ነገር ግን ኢየሱስ (ማቴዎስም) ስብከቱን ሲያቀርብ ለክርስቲያኖች የአኗኗር መለኪያ ሚዛን እንዲሆናቸው ብሎ እንጂ፣ በሰው ጥረት መፈጸም እንደማይቻል ያውቅ ነበር። ደግሞም ኢየሱስ ትምህርቱ ለሰው ግልጽ እንዲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ አንድን ነገር አጉልቶ የሚያሳይበት የአነጋገር ማከሉ አይካድም (ለምሳሌም የ5፥29-30 ማብ ይመ)።

5፥1 *ወደ ተራራ፤* የትኛው ተራራ እንደ ሆነ በግልጽ ባይታወቅም፣ ከቅፍርናሆም ብዙ ሳይርቅ ከገሊላ ባሕር በሰሜን ምዕራብ ጫፍ በኩል ካለው ተዳፋትነት በሌለው ተረተር ላይ ሊሆን ይችላል (የሉቃ6፥20-49 ማብ ይመ)። አዲሱም ሕግ እንደ ቀድሞው ሕግ (ዘጸ19፥3) የተሰጠው ከተራራ ላይ ነው። *ተቀመጠ፤* ተቀምጦ ማስተማር የአይሁድ መምህራን ልማድ ነበር (ማር4፥1፤ 9፥35፤ ሉቃ4፥20፤ 5፥3፤ ዮሐ8፥2 ይመ)። *ደቀ መዛሙርቱም፤* ቀጥታ ትርጉሙ "ተማሪዎች" ማለት ነው።

5፥3 *ብፁዓን፤* ይህ ቃል ከ"መደሰት" የላቀ ትርጉም አለው፤ ምክንያቱም ደስታ በውጫዊ ባለ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ስሜት ነው። "ብፁዓን" የሚለው ቃል በዚህ ላይ የሚያመ ለክተው በእግዚአብሔር መንግሥት የመዳን ተካፋዮች የሆኑት የሚያገኙትን የኋላ ኋላ በጎ ሁኔታና ልዩ መንፈሳዊ ደስታን ነው (የመዝ 1፥1 እና የራእ1፥3 ማብ ይመ)። *በመንፈስ ድኾች፤* በመንፈስ ከመታበይና በራስ ብቃት ከመተማመን ጋር በተቃራኒነት የሚታይ ነው። *መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ናትና፤* ይህች መንግሥት በግል ጥረት የማትገኝ የእግዚአብሔር ስጦታ ናት እንጂ ለበጎ ሥራችን ወሮታ የምትሰጥ አይደለችም ።

5፥5 *የዋሆች፤* ይህ ሐሳብ ከመዝ37፥11 የተወሰደ ነው፤ የሚያመለክተውም ከሰው ጋር ባለን ግንኙነት የምናሳየውን አክብሮት ብቻ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ፊት በተሰበረ ልብና በትሕትና መቅረብን ነው። *ምድር፤* አዲሲቷ የተስፋይቱን ምድር ማለቱ ነው (ራእ21፥1)።

5፥8 *ልባቸው፤* አእምሮን፣ ፈቃድንና ስሜትን የሚያካትት የሕልውና ማእከል ማለት ነው (የመዝ4፥7 ማብ ይመ)።

5፥9 *ሰላምን የሚያወርዱ፤* እነርሱ በተማሩበት ምሕረት ሌሎችን የሚምሩ፣ የእግዚአብሔር ቃል በእኛ የማስታረቅን ቃል አኖረ እንደሚል (2ቆሮ5፥18-20 ይመ) ለሌሎችም የእግዚአብሔር የሆነ ሰላም እንዲመጣ ምክንያት የሚሆኑ ማለቱ ነው። ይኸንንም በማድረጋቸው የእግዚአብሔር የእምላካቸውን በጎ ባሕርይ ያንጸባርቃሉ፤ ስለዚህም ደግሞ "የእግዚአብሔር ልጆች" ይባላሉ።

5፥10 *መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ናትና፤* ይኸንን ሲልም በአሁኑ ዓለም በየዕለት የዕለት ሁኔታ የሚገለጽና ለወዲያኛውም ከሞት በኋላ ለሆነ በዘለዓለማዊ ሕይወት የሚገለጽ ተስፋ ነው።

5፥13 *ጨው፤* ምግብን ለማጣፈጥና ሳይበላሽ ረዘም ላለ ጊዜ እንዲቆይ ለማድረግ ያገለግላል።

5፥15 *መብራት፤* ኢየሱስ በምድር ላይ በአካለ ሥጋ በነበረበት ዘመን፣ ሰዎች ብርሃን ለማግኘት በወይራ ዘይት የሚነድድ የተገመደ ፈትል ከሸክላ በተሠራ ኩራዝ መሳይ ዕቃ ውስጥ በማድረግ ይጠቀሙ ነበር (የዘፀ25፥37 ማብ ይመ)። *ዕንቅብ፤* ዱቄት ወይም ጥራጥሬ ለመያዝ የሚያገለግል ጉድጉድ ያለ ሰፊድ መሳይ ዕቃ ነው።

5፥16 *በሰማይ ያለውን አባታችሁን፤* ማቴዎስ "የሰማይ አባታችሁ" ወይም "በሰማይ የሚኖር አባት" የሚለውን አባባል ዐሥራ ስባት ጊዜ ሲጠቅሰው፣ ማርቆስና ሉቃስ ደግሞ አንድ አንድ ጊዜ ብቻ ጽፈውታል፤ ዮሐንስ ግን ይህን ሐረግ ፈጽሞ አልተጠቀመም።

5፥17 *ሕግንና፤* የመጀመሪያዎቹ አምስት የአይሁድ መጻሕፍት ናቸው (እነዚህም በእኛ ብሉይ ኪዳን ውስጥ ይገኛሉ)። *የነቢያትን፤* ዐበይት ነቢያት የምንላቸውን "የኋለኞቹን ነቢያት":-

ባሁ አይምሰላችሁ፤ ለመፈጸም እንጂ ለመ
ሻር አልመጣሁም:: 18እውነት እላችኋለሁ፤
ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ሕግ
ሁሉ ይፈጸማል እንጂ ከሕግ አንዲት ፊደል
ወይም አንዲት ነጥብ እንኳ አትሻርም::
19ስለዚህ ማንም ከእነዚህ ትእዛዛት አነስተ
ኛዪቱን እንኳን ቢተላለፍ፣ ሌሎችንም እን
ዲተላለፉ ቢያስተምር በመንግሥተ ሰማይ
ታናሽ ተብሎ ይጠራል፤ ነገር ግን እነዚህን
ትእዛዛት እየፈጸመ ሌሎችም እንዲፈጽሙ
የሚያስተምር በመንግሥተ ሰማይ ታላቅ
ይባላል:: 20ጽድቃችሁ ከፈሪሳውያንና ከኦ
ሪት ሕግ መምህራን ጽድቅ ልቆ ካልተገኘ
መንግሥተ ሰማይ መግባት አትችሉም::

## ነፍስ መግደል አይገባም

5፥25:26 ተጓ ምብ - ሉቃ 12፥58:59

21"ለቀደሙት ሰዎች፣ 'አትግደል፤ የገደለ
ይፈረድበታል' እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤
22እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ወንድሙን ያለ አግ
ባብ የሚቈጣ ይፈረድበታል፤ ማንም ወንድ
ሙን 'ጅል' የሚል በሸንጎ ፊት ይጠየቅበ
ታል፤ 'ደደብ' የሚለው ደግሞ የገሃነመ እሳት
ፍርድ ይጠብቀዋል::
23"ስለዚህ መባህን በመሠዊያው ላይ ለእ
ግዚአብሔር በምታቀርብበት ጊዜ ወንድምህ
የተቀየመብህ ነገር መኖሩ ትዝ ቢልህ፣
24መባህን በዚያው በመሠዊያው ፊት ተወው፤
በመጀመሪያ ሂደህ ከወንድምህ ጋር ተስማማ፤
ከዚያም ተመልሰህ መባህን ለእግዚአብሔር
አቅርብ::
25"የከሰሰህ ባላጋራህ እንዳያስፈርድብህ፣
ዳኛውም ለአሳሪ አሳልፎ እንዳይሰጥህ፣ በወ
ህኒም እንዳትጣል፣ በመንገድ ላይ ሳለህ
ከባላጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ:: 26እውነት
እልሃለሁ፤ ካስፈረደብህ ግን የመጨረሻዋን
ሳንቲም[ሀ] እስክትከፍል ድረስ ከዚያ አትወ
ጣም::

## ማመንዘር አይገባም

27" 'አታመንዝር' እንደ ተባለ ሰምታች
ኋል:: 28እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ሴትን በም
ኞት ዓይን የተመለከተ ሁሉ በልቡ ከእርሷ
ጋር አመንዝሮአል:: 29ቀኝ ዓይንህ የኀጢአት
ሰበብ ቢሆንብህ፣ አውጥተህ ወዲያ ጣለው፤
ሰውነትህ በሙሉ ወደ ገሃነም ከሚጣል ከሰ
ውነትህ አንዱን ክፍል ብታጣ ይሻልሃል::
30ቀኝ እጅህ የኀጢአት ሰበብ ቢሆን ብህ
ቈርጠህ ወዲያ ጣለው፤ ሰውነትህ በሙሉ
ወደ ገሃነም ከሚጣል ከሰውነትህ አንዱን
ክፍል ብታጣ ይሻልሃል::
31" 'ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ የፍቺ ወረ
ቀት መስጠት አለበት' እንደተባለ ሰምታ
ችኋል:: 32እኔ ግን እላችኋለሁ፤ በላዩ ላይ
ስታመነዝር ካላገኛት በስተቀር፣ ሚስቱን
የሚፈታ ሁሉ እንድታመነዝር ያደርጋታል፤
በዚህ ሁኔታ የተፈታችውን ሴት ያገባም
እንዳመነዘረ ይቈጠራል::

## ስለ መሐላ

33"ለቀደሙት ሰዎች፣ 'በሐሰት አትማል፤
በእግዚአብሔር ፊት የማልኸውንም ጠብቅ'
እንደ ተባለ ሰምታችኋል:: 34እኔ ግን ፈጽሞ
አትማሉ እላችኋለሁ፤ በሰማይም ቢሆን አት
ማሉ፤ የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና፤ 35በም

[ሀ]26 ግሪኩ ኮድራንቴስ ይላል

5፥18 መዝ119፥89፤ ኢሳ40፥8፤55፥11፤ ማቴ24፥35፤ ማር13፥31፤ ሉቃ16፥17፤ 21፥33
5፥19 ያዕ2፥10
5፥20 ኢሳ26፥2፤ ማቴ18፥3፤ዮሐ3፥5
5፥21 ዘፀ20፥13፤ 21፥12፤ዘዳ5፥17
5፥22 መክ7፥9፤ ማቴ18፥9፤26፥59፤ ማር9፥43:48፤ ሉቃ16፥24፤ ዮሐ11፥47፤ ሐሥ 5፥21:27: 34:41፤ 6፥12፤ 1ቆሮ13፥5፤ ኤፌ4፥26፤ያዕ1፥19: 20፤3፥6፤1ዮሐ3፥15
5፥27 ዘፀ20፥14፤ ዘዳ5፥18
5፥28 ምሳ6፥25፤2ጴጥ2፥14
5፥29 ቍ30፤ማቴ 18፥6:8:9፤ማር9፥42-47፤ሉቃ17፥2፤ሮሜ 14፥21፤1ቆሮ8፥13፤ 2ቆሮ6፥3፤11፥29
5፥30 ቍ29
5፥31 ዘዳ24፥1-4
5፥32 ሉቃ16፥18
5፥33 ዘሌ19፥12፤ ዘኍ30፥2፤ዘዳ23፥21፤ ማቴ23፥16-22

(ኢሳይያስን፣ ኤርምያስንና ሕዝቅኤልን) እንዲሁም በአይሁድ ዘንድ በአንድ ላይ "የዐሥራ ሁለቱ መጻሕፍት" የሚባሉትን ዐሥራ ሁለቱን ደቂቅ ነቢያት ብቻ ሳይሆን፣ "የቀድሞ ነቢያት" የሚባሉትንም (ኢያሱን፣ መሳፍንትን፣ ሳሙኤልንና ነገሥትን) ያካትታል:: "ሕግና" "ነቢያት" ተብሎ በአንድነት ሲነገር፣ ብሉይ ኪዳንን በሙሉና "ጽሑፎች" የሚባለውን የዕብራውያን መጽሐፍ ቅዱስ ሦስተኛውን ክፍል ጭምር ያመለክታል:: ማቴዎስ "ጽሑፎች" ከተባለው ክፍል በ13፥35 ላይ "በነቢዩ...ይተነገረው" (መዝ 78፥2)በማለት የተጠቀሰውን ይመ:: *ለመፈጸም፤* ኢየሱስ በአኗኗሩ ሙሉ በሙሉ ሕግን ጠብቆ በመገኘቱ፣ በትምህርቱ የሕግ ፍጻሜ የሆነውን በፍቅር ላይ የተመሠረተ ሥነ ምግባር (ሮሜ13፥10) በአጽንዖት በመግለጹ፣ እንዲሁም ሕግ የሚጠይቀውን በሞቱ በመክፈሉ ሕግን ፈጽሞአል::

*5፥18-20፤* ኢየሱስ፣ ግብዝነት ያለበትን የፈሪሳውያንን የሕግ አፈጻጸም በመቃወም፣ ሕግን በአግባቡ እንድንጠብቅ ያበረታታል:: እንዲህ ያለው የፈሪሳውያን የሕግ አፈጻጸም ሕግን ሙሉ በሙሉ መፈጸም ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ ለማግኘት ሲባል በውጫዊ ሁኔታ ሕግን ፈጻሚ በመምሰል በልብ ውስጥ ግን ሕግን ተላላፊ ሆኖ መገኘት ነው:: ይህ ዓይነቱ የሕግ አፈጻጸም የሕጉን መንፈስ ችላ በማለት ለጥሬ ትርጕሙ ትኵረት ይሰጣል:: ኢየሱስ የፈሪሳውያንን የሕግ አተረጓጐምና በሥራቸው ለመጽደቅ ያላቸውን አመለካከት አጥብቆ ተቃውሞአል:: አበክሮ ያስተማረውም በእርሱና በፈጸመው ሥራ ብቻ በማመን የሚገኘውን ጽድቅ ነው:: ከእነዚህ ቀጥለው ባሉት ቍጥሮችም ስለ ፈሪሳውያን የታይታ ተግባር ስድስት ምሳሌዎችን አቅርቦአል::

5፥18 ***አንዲት ፊደል ... አንዲት ነጥብ፤*** የእግዚአብሔር መንፈስ ያረፈባት አንዲቷ ቅንጣት ቃል፣ ትንሽ ብትሆንም መፈጸሟ አይቀርም ለማለት ነው::

5፥21 ***እንደ ተባለ፤*** ኢየሱስ የብሉይ ኪዳንን ሕግ ትክክል መሆን አጽድቆአልና፣ በብሉይ ኪዳንና በእርሱ ትምህርት መካከል ንጽጽር ማድረጉ አይደለም (ቍ21:27:31:33:38:43):: ነገር ግን የእርሱ ንጽጽር ያተኰረው ሲወርድ ሲዋረድ በመጣውና ውጫዊ በሆነው በአይሁድ መምህራን የሕግ አተረጓጐምና በእርሱ ትክክለኛ የሕግ አተረጓጐም መካከል ባለው ልዩነት ላይ ነው:: ***አትግደል፤*** አያሌ የዕብራይስጥና የግሪክ አገባብ የዚህ ግስ ትርጕም በጥቅሉ "መግደል" ማለት ሲሆን፣ እዚህ ላይና በዘፀ 20፥13 ያለው ግን "ሰውን መግደል" እንደ ሆነ ልይቶ ያመለክታል::

5፥22 ***ጅል፤*** "የማይገባው" የማለት ያህል ነው:: ***በሸንጎ፤*** የማር14፥55 ማብ ይመ:: ***ገሃነመ እሳት፤*** ይህ ስያሜ የተወሰደው ከኢየሩሳሌም በስተደቡብ ይገኝ ከነበር፣ "የሄኖም ሸለቆ" ከተባለው ነው:: ክፉ ነገሥታት በነበሩት በአካዝና በምናሴ ዘመነ መንግሥት ሞሎክ ለተባለ ለአሞናውያን ጣዖት ሰዎች መሥዋዕት ተደርገው በዚህ ሸለቆ ይቀርቡ ነበር:: ይደረግ ከነበረው ባዕድ አምልኮ የተነሣ፣ ኢዮስያስ ይህን ሸለቆ ርኩስ ሆኖ እንዲቈጠር አደረገ (2ነገ23፥10፤ ኤር7፥31-32፤ 19፥6 ይመ):: ይህም ስፍራ ለዘመናት የከተማው ቈሻሻ መጣያና ማቃጠያ ቦታ ሆነ፤ በኋላም የመጨረሻው የፍርድ ቅጣት ስፍራ ምሳሌ ሆነ::

5፥26 ***ሳንቲም፤*** ከመዳብ የተሠራች የሮም መንግሥት ገንዘብ አነስተኛዋ ክፍልፋይ ነበረች::

5፥28 ***ሴትን በምኞት ዓይን የተመለከተ፤*** ከቃሉ እንደምንረዳው በምኞት መመልከት ከመፈለግና እንዲሁ ደግሞ በድንገት ወደ ሴቶች ከማየት መካከል ልዩነት እንዳለውና ይህም በጌታ ትምህርት መሠረት ገና ከልቡ እያለ እንዳመነዘረ ይቈጠራል::

5፥29-30፤ ዓይን ስውር እንኳ መጕምጀት ስለሚችል፣ ኢየሱስ እዚህ ላይ የሚያስተምረው ማንም ሰው አካላቱን እንዲቈራርጥ አይደለም፤ ነገር ግን የትምህርቱ ፍሬ ሐሳብ የኀጢአትን ምንጭ ከመሠረቱ ማድረቅ እንዳለብን የሚያመለክት ነው::

5፥32 ***በላዩ ላይ ስታመነዝር ካላገኛት በስተቀር፤*** የ19፥3 ማብ ይመ:: ይህ የተለየ ሐሳብ በማር 10፥11-12 ሆነ፣ በሉቃ 16፥18 ላይ አልተጠቀሰም::

ድርም ቢሆን አትማሉ፤ የእግዚአብሔር የእ
ግሩ ማረፊያ ናትና፤ በኢየሩሳሌምም አት
ማሉ፤ የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና 36በራሳ
ችሁም ቢሆን አትማሉ፤ ከጠጉራችሁ መካ
ከል አንዲቷን እንኳ ነጭ ወይም ጥቍር
ማድረግ አትችሉምና:: 37ስለዚህ ስትነጋገሩ
ቃላችሁ፣ 'አዎን' ከሆነ፣ 'አዎን'፤ አይ
ደለም፣ ከሆነ 'አይደለም' ይሁን፤ ከዚህ ውጭ
የሆነ ሁሉ ከክፉው የሚመጣ ነውና::

## ስለ መበቀል

38" 'ዓይን ስለ ዓይን፣ ጥርስ ስለ ጥርስ'
እንደ ተባለ ሰምታችኋል:: 39እኔ ግን እላች
ኋለሁ፤ 'ክፉ አድራጊውን ሰው አትቃወ
ሙት'፤ ነገር ግን ቀኝ ጒንጭህን ለሚመታህ
ሌላውን ጒንጭህን ደግሞ አዙርለት:: 40አንድ
ሰው እጀ ጠባብህን ሊወስድ ቢከስህ ካባህን
ጨምረህ ስጠው:: 41አንድ ሰው አንድ ኪሎ
ሜትር ተኩል የሚያህል ርቀት እንድት
ሄድ ቢያስገድድህ ዕጥፉን መንገድ አብረኸው
ሂድ:: 42ለሚለምንህ ስጥ፤ ከአንተም ሊበ
ደር የሚሻውን ፊት አትንሣው::
43" 'ወዳጅህን ውደድ፤ ጠላትህን ጥላ'
እንደ ተባለ ሰምታችኋል:: 44እኔ ግን ጠላቶ
ቻችሁን ውደዱ*፤ ለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ
እላችኋለሁ:: 45እንደዚህም በማድረጋችሁ
በሰማይ ላለው አባታችሁ ልጆች ትሆናላ
ችሁ፤ እርሱ ፀሐዩን ለክፉዎችና ለደጎች
ያወጣል፤ ዝናቡንም ለኀጢአተኞችና ለጻ
ድቃን ያዘንባል:: 46የሚወዷችሁን ብቻ የም
ትወዱ ከሆነ ምን ዋጋ ታገኛላችሁ? ቀረ
ጮችስ ይህንኑ ያደርጉ የለምን? 47ወንድ
ሞቻችሁን ብቻ እጅ የምትነሡ ከሆነ ከሌ
ሎች በምን ትሻላላችሁ? አሕዛብስ ይህንኑ
ያደርጉ የለምን? 48ስለዚህ የሰማይ አባታችሁ
ፍጹም እንደ ሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ::"

## ስለ ምጽዋት አሰጣጥ

6 "ሰዎች እንዲያዩላችሁ፣ መልካም ሥራ
ችሁን በፊታቸው ከማድረግ ተጠንቀቁ፤
እንዲህ ካደረጋችሁ ከሰማዩ አባታችሁ ዋጋ
አታገኙም::
2"በሰዎች ዘንድ ለመከበር ብለው በየ
ጎዳናውና በየምኵራቡ ጥሩምባ እንደሚያ
ስነፉ ግብዞች፣ እናንተም ለድኾች ምጽዋት
በምትሰጡበት ጊዜ ይታይልኝ ብላችሁ
አታድርጉ፤ እውነት እላችኋለሁ እንዲህ
የሚያደርጉ ዋጋቸውን በሙሉ ተቀብለዋል::
3እናንተ ግን ለድኾች ስትሰጡ ቀኝ እጃችሁ
የሚያደርገውን ግራ እጃችሁ አይወቅ፤ 4ምጽ
ዋታችሁ በስውር ይሁን፤ በስውር የተደረገ
ውን የሚያይ አባታችሁም ዋጋችሁን ይከፍ
ላችኋል::

## ስለ ጸሎት

6፥9-13 ተጓ ምብ - ሉቃ 11፥2-4

5"ስትጸልዩ እንደ ግብዞች አትሁኑ፤ እነ
ርሱ ለሰዎች ለመታየት ሲሉ በየምኵራቡና
በየመንገዱ ማእዘን ላይ ቆመው መጸለይ
ይወዳሉና:: እውነት እላችኋለሁ፤ ሙሉ
ዋጋቸውን ተቀብለዋል:: 6አንተ ግን ስትጸልይ
ወደ ክፍልህ ግባ፤ በሩንም ዘግተህ በስውር ወዳ
ለው አባትህ ጸልይ፤ በስውር የተደረገውን
የሚያይ አባትህም ዋጋህን ይከፍልሃል:: 7ስት
ጸልዩ፣ ከንቱ ቃላት በመደጋገም ጸሎታቸው
የሚሰማላቸው እንደሚመስላቸው አሕዛብ ነገራ
ችሁን አታስረዝሙ:: 8እነርሱን አትምሰ
ሏቸው፤ አባታችሁ ከመለመናችሁ በፊት ምን

*44 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *የሚረግሟችሁን መርቁ፤ ለሚጠ ሏችሁ መልካም አድርጉ* ይላሉ

5፥34 ኢሳ66፥1፤ ማቴ23፥22፤ያዕ5፥12
5፥35 መዝ48፥2
5፥37 ማቴ6፥13፤ 13፥19:38፤ዮሐ17፥15፤ኤፌ6፥16፤ 2ተሰ 3፥3፤ያዕ5፥12፤ 1ዮሐ 2፥13:14፤ 3፥12፤ 5፥18:19
5፥38 ዘፀ21፥24፤ ዘሌ24፥20፤ዘዳ19፥21
5፥39 ሉቃ6፥29፤ ሮሜ12፥17:19፤ 1ጴጥ3፥9
5፥42 ዘዳ15፥8፤ ሉቃ6፥30
5፥43 ዘሌ19፥18፤ ዘዳ23፥6፤መዝ139፥21:22፤ማቴ19፥19፤ 22፥39፤ማር12፥31፤ ሉቃ10፥27፤ሮሜ13፥9፤ገላ5፥14፤ያዕ2፥8
5፥44 ሉቃ6፥27:28፤23፥34፤ዮሐ15፥20፤ ሐሥ7፥60፤ ሮሜ8፥35፤12፥14፤ 1ቆሮ 4፥12፤ 1ጴጥ2፥23
5፥45 ቍ9፤ኢዮ25፥3፤ሉቃ6፥35፤ ሮሜ8፥14
5፥46 ሉቃ6፥32
5፥48 ዘሌ19፥2፤ 1ጴጥ1፥16
6፥1 ማቴ5፥16፤ 23፥5
6፥4 ቍ6፥18፤ ቈላ 3፥23:24
6፥5 ማር11፥25፤ ሉቃ18፥10-14
6፥6 2ነገ4፥33
6፥7 1ነገ18፥26-29፤መክ5፥2
6፥8 ቍ32

5፥38፤ የዘፀ21፥23-25 እና የዘሌ24፥20 ማብ ይመ::

5፥40 *እጀ ጠባብህን ... ካባህን፤* የመጀመሪያው ከሥር የሚለበስ ሲሆን ሁለተኛው ከላይ የሚደረብ ነው::

5፥41 *ቢያስገድድህ፤* የግሪኩ ግስ የተገኘው ከፋርስ ቋንቋ ሲሆን ትርጕሙ፣ "ለአገልግሎት ማስገደድ" ማለት ነው፤ ይህ ቃል በ27፥32 ላይ የሮም ወታደሮች ስምዖን የተባለውን ሰው የኢየሱስን መስቀል እንዲሸከም ማስገደዳቸውን ለመግለጽ ገብቶአል::

5፥42 *ለሚለምንህ ስጥ፤* ይህ መቼም ሳይቸገር ለሚለምንህ ሁሉ ስጥ ማለቱ ሳይሆን ለድኻና ለሚለምንህ ስጥ ማለቱ ነው (በተለይ ዘዳ15፥7-11፤ መዝ112፥5:9 ይመ)::

5፥43 *ጠላትህን ጥላ፤* ይህ ጥቅስ በብሉይ ኪዳን ቀጥታ ተጓዳኝ የለውም:: ሆኖም ጌታ በምድር በነበረበት ዘመን ይህ ዓይነቱ ሞራላዊ ሚዛን የተለመደ ነበር:: ለሚጠላው ሁሉ ሌላውም በአፀፋው ጥላቻን ማሳየት ነበረበት:: ምናልባት በሙት ባሕር አካባቢ በዋሻ ይኖሩ የነበሩ የአይሁዳውያን ወገን የሆኑት ኤሲይንስ የሚባሉ ወገኖች ያስተምሩ ከነበረው ትምህርት የተወሰደ ሊሆን ይችላል:: እነርሱ በትምህርታቸው "የብርሃን ልጆች" እና "የጨለማ ልጆች" በማለት የሰውን ልጆች ለሁለት ይከፍሉ ስለ ነበር ብርሃን ጨለማን እንደሚጠላ ሁሉ የብርሃን ልጆች የሆኑት የጨለማ ልጆች ናቸው የሚሏቸውን ሁሉ ይጠሉ ነበር:: ደግሞም ተግባራቸውን ብቻ ሳይሆን ሰዎቹንም ጭምር ይጠሉ ነበር::

5፥44 *ጸልዩ፤* በዚህ ስፍራ በተለይ የተገለጸው ጸሎት ሰዎች ስለ ፍቅር ሲሉ ተግባራዊነት ባለው መልክ የሚገልጹበት አንዱ መንገድ ነው:: አንዳንድ የጥንት ቅጂዎች "የሚረግሟቸውችሁን መርቁ፤ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ" ይላሉ::

5፥45 *በሰማይ ላለው አባታችሁ ልጆች ትሆናላችሁ፤* በእርግጥ አንድ ሰው ጠላቱን ስለ ወደደ ብቻ የእግዚአብሔር (የሰማዩ አባታችን) ልጅ ይሆናል ማለት አይደለም፤ ግን አንድ ልጅ የሚኖረውን መልካም ባሕርይ ያንጸባርቃል ለማለት ነው:: *ለክፉዎችና ለደጎች፤* እግዚአብሔር ፍቅሩን ለሰው ልጆች ሁሉ እኩል ይገልጻል ለማለት ነው::

5፥46 *ቀራጮችስ፤* እነዚህ ሰዎች ቀረጥን በሚመለከት ኀላፊነትን በወሰዱ ሮማውያን ውል ፈጻሚዎች ቀረጥ ለመ ሰብሰብ የተቀጠሩ የሀገሬው ተወላጆች የነበሩና በተለምዶ "የመሸታ ሰዎች" በመባል ይታወቃሉ:: እነዚህ ቀረጥ ሰብሳቢዎች ለሮም መንግሥት በመሥራታቸውና ከሚገባው በላይም ቀረጥ እንዲከፈል በማስገደዳቸው መጥፎ ስም ያላቸው፣ በብዙ ረገድ የተጠሉና እንደ ከሀዲ የተቈጠሩ ነበሩ::

5፥48 *ፍጹማን ሁኑ፤* በምድራዊ ኑሮአችን ሙሉ በሙሉ ልንደርስበት ባንችልም፣ ክርስቶስ ለፍጹም ፍቅር አርአያ የሚሆነውን መሠረት ጥሎልናል (ቍ43-47 ይመ)፤ በእግዚአብሔርም ፊት የምንመዘንበት መለኪያ ይኸው ነው::

6፥1 *መልካም ሥራችሁን፤* ይህ ጥቅስ ቀጥለው ለሚገለጹት ሦስት የጽድቅ ሥራዎች መግቢያ ነው፤ እነርሱም 1) መስጠት (ቍ2-4)፣ 2) መጸለይ (ቍ5-15)፣ እና 3) መጾም (ቍ16-18) ናቸው::

6፥2 *ግብዞች፤* በግሪኩ ቃል "ኒፖክራት" በመባል ሲታወቅ ቀጥታ ትርጕሙም ቲያትረኛ ወይም የመድረክ ተዋናይ ማለት ነው:: ስለዚህም ማቴዎስ በማስመሰል ሃይማኖተኞች ነን የሚሉትን "ግብዞች" ይላቸዋል::

6፥3 *ቀኝ እጃችሁ የሚያደርገውን ግራ እጃችሁ አይወቅ፤* ይህ መቼም በቀጥታ ትርጕሙ አልተወሰደም:: ወንጌላዊው ሰዎች ስለሚሰጡት ስጦታ ወይም በጎ ተግባር መቍጠር የለባቸውም ማለቱ ነው:: በተለይ የራስን ዋጋ ከፍ ከፍ ማድረግ አደገኛ አመለካከት መሆኑን ያሳያል::

6፥7 *ከንቱ ቃላት በመደጋገም ... የሚሰማላቸው፤* ጌታ ኢየሱስ ሊያወግዝ የፈለገው ትርጕም የለሽን፣ የድግግሞሽ ጸሎት ነው:: በተለይ አሕዛብ ወደ ጸሎት በሚሄዱበት ጊዜ ረዥም የሆነውን የአማልክታቸውን ዝርዝር ሐተታ ይዘው ስለ ሆነ፣

እንደሚያስፈልጋችሁ ያውቃልና።
9“እናንተ ግን እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ፤
“ ‘በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፤
ስምህ ይቀደስ፤
10መንግሥትህ ትምጣ፤
ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች፣
እንዲሁ በምድር ትሁን።
11የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን።
12እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር
እንደምንል፣
በደላችንን ይቅር በለን።
13ወደ ፈተናም አታግባን
ከክፉው አድነን እንጂ፣
(መንግሥት፣ ኃይል፣ ክብርም፣
ለዘለዓለሙ ያንተ ነውና፤ አሜን።)[a]

14እናንተ የበደሏችሁን ይቅር ብትሉ የሰ
ማዩ አባታችሁ ደግሞ እናንተን ይቅር ይላ
ችኋል። 15ነገር ግን የሰዎችን ኀጢአት
ይቅር የማትሉ ከሆነ፣ አባታችሁም ኀጢአ
ታችሁን ይቅር አይልላችሁም።

## ስለ ጾም

16“ስትጾሙ እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፤
እነርሱ መጾማቸው እንዲታወቅላቸው ሆን
ብለው በፊታቸው ላይ የሐዘን ምልክት ያሳ
ያሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፤ እንዲህ የሚያ
ደርጉ ዋጋቸውን በሙሉ ተቀብለዋል።
17አንተ ግን በምትጾምበት ጊዜ ፊትህን
ታጠብ፤ ራስህንም ተቀባ፤ 18በዚህም መጾምህ
በስውር ያለው አባትህ ብቻ የሚያውቀው፣
ከሰዎች ግን የተሰወረ ይሆናል፤ በስውር
የተደረገውን የሚያይ አባትህም ዋጋህን
ይከፍልሃል።

## ሰማያዊ ሀብት

6፥22፡23 ተጓ ምብ - ሉቃ 11፥34-36

19“ብል ሊበላው፣ ዝገት ሊያበላሸው፣
ሌባም ቈፍሮ ሊሰርቀው በሚችልበት በዚህ
ምድር ላይ ለራሳችሁ ሀብት አታከማቹ።
20ነገር ግን ብል ሊበላው፣ ዝገት ሊያበላሸው፣
ሌባም ቈፍሮ ሊሰርቀው በማይችልበት በዚያ
በሰማይ ለራሳችሁ ሀብት አከማቹ፤ 21ሀብ
ትህ ባለበት ልብህም በዚያው ይሆናልና።
22“ዐይን የሰውነት መብራት ነው፤ ስለዚህ
ዐይንህ ጤናማ ከሆነ መላው ሰውነትህ በብ
ርሃን የተሞላ ይሆናል። 23ዐይንህ ታማሚ
ከሆነ ግን መላው ሰውነትህ በጨለማ የተ
ሞላ ይሆናል። እንግዲህ በአንተ ውስጥ
ያለው ብርሃን ጨለማ ከሆነ፣ ጨለማው

6፥9 ኢር3፥19፤ ሚል 2፥10፤ 1ጴጥ1፥17
6፥10 ማቴ3፥2፤ 26፥39
6፥11 ምሳ30፥8
6፥12 ማቴ18፥21-35
6፥13 ማቴ5፥37፤ ያዕ1፥13
6፥14 ማቴ18፥21-35፤ ማር11፥25፡26፤ ኤፌ 4፥32፤ ቈላ3፥13
6፥15 ማቴ18፥35
6፥16 ዘሌ16፥29፡31፤23፥27-32፤ ዘኍ 29፥7፤ ኢሳ58፥5፤ ዘካ 7፥5፤8፥19
6፥18 ቍ4፡6
ምሳ23፥4፤ ሉቃ12፥16-21፤ ዕብ 13፥5፤ያዕ5፥2፡3
6፥20 ማቴ19፥21፤ ሉቃ12፥33፤16፥9፤ 18፥22፤1ጢሞ6፥19
6፥21 ሉቃ12፥34
6፥24 ሉቃ16፥13
6፥25 ቍ27፡28፡31፡34፤ሉቃ10፥41፤ 12፥11፡22
6፥26 ኢዮ38፥41፤ መዝ 104፥21፤136፥25፤145፥15፤147፥9፤ ማቴ10፥29-31
6፥27 መዝ39፥5
6፥29 1ነ10፥4-7
6፥30 ማቴ8፥26፤ 14፥31፥16፥8፤ ሉቃ 12፥28
6፥32 ቍ8
6፥33 መዝ37፥4፤ ማቴ3፥2፤19፥29
7፥1 ሉቃ6፥37፤ ሮሜ14፥4፡10፡13፤ 1ቆሮ4፥5፤5፥12፤ ያዕ 4፥11፡12
7፥2 ሕዝ35፥11፤ ማር4፥24፤ ሉቃ6፥38፤ሮሜ2፥1

እንዴት ድቅድቅ ይሆን?
24“አንድ ሰው ሁለት ጌቶችን ማገልገል
አይችልም፤ አንዱን ጠልቶ ሌላውን ይወዳል፤
ወይም አንዱን አክብሮ ሌላውን ይንቃል።
እግዚአብሔርንና ገንዘብን በአንድነት ማገ
ልገል አይቻልም።

## አለመጨነቅ

6፥25-33 ተጓ ምብ - ሉቃ 12፥22-31

25ስለዚህ እላችኋለሁ፣ ስለ ኑሮአችሁ ምን
እንበላለን? ምን እንጠጣለን? ምንስ እንለብ
ሳለን? በማለት አትጨነቁ። ሕይወት ከም
ግብ፣ ሰውነትስ ከልብስ አይበልጥምን?
26እስቲ የሰማይ ወፎችን ተመልከቱ፤ አይ
ዘሩም፤ አያጭዱም፤ በጐተራም አያከማቹም፤
ይሁን እንጂ የሰማዩ አባታችሁ ይመግባ
ቸዋል። እናንተ ከእነርሱ እጅግ አትበልጡ
ምን? 27ለመሆኑ ከእናንተ መካከል ተጨንቆ
በዕድሜው ላይ አንዲት ሰዓት[+] መጨመር
የሚችል አለን?
28“ደግሞስ ስለ ልብስ ለምን ትጨነቃላ
ችሁ? እስቲ የሜዳ አበቦችን ተመልከቱ፤
አይለፉም፤ ወይም አይፈትሉም። 29ስለዚህ
እላችኋለሁ፤ ያን ያህል ክብር የነበረው
ንጉሥ ሰሎሞን እንኳ ከእነዚህ አበቦች እንደ
አንዲቱ አልለበሰም። 30እናንተ እምነት የጐ
ደላችሁ! እግዚአብሔር ዛሬ ታይቶ በነጋ
ታው እሳት ውስጥ የሚጣለውን የሜዳ ሣር
ይህን ያህል ካለበሰ እናንተንማ እንዴት አብ
ልጦ አያለብሳችሁ? 31ስለዚህ፣ ‘ምን እንበላ
ለን? ምን እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን?’
ብላችሁ አትጨነቁ፤ 32አሕዛብ እነዚህን ነገ
ሮች ሁሉ ለማግኘት ይጨነቃሉና፤ የሰማዩ
አባታችሁም እነዚህ ሁሉ ለእናንተ እንደሚ
ያስፈልጓችሁ ያውቃል። 33ከሁሉ አስቀድ
ማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና
ጽድቁን እሹ፤ እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላች
ኋል። 34ስለዚህ ለነገ በማሰብ አትጨነቁ፤
የነገ ጭንቀት ለነገ ይደር፤ እያንዳንዱ ዕለት
የራሱ የሆነ በቂ ችግር አለውና”።

## በሌሎች ላይ አለ መፍረድ

7፥3-5 ተጓ ምብ - ሉቃ 6፥41፡42

7 “እንዳይፈረድባችሁ በማንም ሰው ላይ
አትፍረዱ፤ 2በምትፈርዱበትም ዐይነት
ይፈረድባችኋል፤ በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ
ይሰፈርላችኋል።

[a]13 በግሪኩ ይህ የለም፤ ሆኖም በሌሎቹ የጥንት ትርጒሞች ይገኛል
[+]27 ወይም *በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ*

ሳያቋርጡ እነዚያን ስሞች በመጥራታቸው ብዛት ጸሎታቸው የሚሰማ ስለሚመስላቸው፣ ጌታም እውነተኛውን የእስራኤልን አምላክ የሚያመልኩትን እንደነዚህ አሕዛብ እንዳይሆኑ ሲያስጠነቅቅ እንደ ተናገረ ያመለክታል።

6፥10 *መንግሥትህ ትምጣ፤* የጌታ መንግሥት ወደ ፊት ሙሉ በሙሉ እንደሚሰፍን ያመለክታል።

6፥11 *እንጀራችንን፤* ለቅንጦት ሳይሆን፣ ለመኖር አስፈላጊ የሆነውን መሠረታዊ ነገር ያመለክታል።

6፥12 *በደላችንን፤* የሥነ ምግባር ጕድለት፣ ኀጢአት ማለት ነው (የሉቃ11፥4 ማብ ይመ)።

6፥17 *ፊትህን ታጠብ፤ ራስህንም ተቀባ፤* አይሁድ ሲጾሙ በራሳቸው ላይ አመድ ይነሰንሱ ነበር፤ ፊት መታጠብና ራስን መቀባት ግን በደስታ ጊዜ የሚደረጉ ናቸው።

6፥19 *ብል…ዝገት፤* እነዚህ ምድራዊ ሀብትን ሊያጠፉ የሚችሉ ሁኔታዎችንና መንገዶችን ሁሉ የሚወክሉ ናቸው።

6፥20 *በሰማይ … ሀብት፤* ዘላለማዊነት ያለው ሆኖ በዚህ ምድር የተሠራ ማንኛውንም ዓይነት መልካም ሥራን ያመለክታል። በተለይ በሉቃ12፥21 እንደ ተጠቀሰው በእግዚአብሔር ዘንድ ባለጠጋ ስለ መሆን ያመለክታል።

6፥30 *እሳት ውስጥ የሚጣለውን፤* በመካከለኛው ምሥራቅ ሣር የሸክላ ምጣድ ለማሞቅ ለማገዶነት ያገለግል ነበር።

*7፥1፤* ከዐውዱ እንደምንረዳው (ቍ5)፣ አንድ ክርስቲያን

3“በዐይንህ ውስጥ ያለውን ግንድ ሳትመለ
ከት፣ በወንድምህ ዐይን ያለውን ጉድፍ ለምን
ታያለህ? 4በዐይንህ ውስጥ ግንድ እያለ ወን
ድምህን፣ ‘ዐይንህ ውስጥ ያለውን ጉድፍ
ላውጣልህ’ ማለት እንዴት ትችላለህ? 5አንተ
ግብዝ፤ አስቀድመህ በዐይንህ ውስጥ ያለውን
ግንድ አውጣ፤ ከዚያም በወንድምህ ዐይን
ውስጥ ያለውን ጉድፍ ለማውጣት አጥርተህ
ታያለህ።
6“በእግራቸው እንዳይረግጡት፣ ተመልሰ
ውም ነክሰው እንዳይበጫጭቋችሁ፣ የተቀደሰ
ነገር ለውሾች አትስጡ፤ ዕንቁቻችሁንም
በእሪያ ፊት አትጣሉ።

## ለምኑ፤ ፈልጉ፤ አንኳኩ

7፥7-11 ተጓ ምብ - ሉቃ 11፥9-13

7“ ‘ለምኑ፣ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ፣ ታገኛላ
ችሁ፤ አንኳኩ፣ በሩም ይከፈትላችኋል።
8የሚለምን ሁሉ ይሰጠዋል፤ የሚፈልግም
ያገኛል፤ ለሚያንኳኳም በሩ ይከፈትለታል።
9“ከእናንተ መካከል ልጁ ዳቦ ቢለምነው፣
ድንጋይ የሚሰጥ አባት አለ? 10ወይንም ዓሣ
ቢለምነው እባብ የሚሰጥ ይኖራልን? 11ታዲያ
እናንተ ክፉዎች ሳላችሁ ለልጆቻችሁ መል
ካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፣ የሰማዩ
አባታችሁማ ለሚለምኑት መልካም ስጦታን
እንዴት አብልጦ አይሰጣቸውም? 12ሌሎች
እንዲያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን ነገር እና
ንተም አድርጉላቸው፤ ኦሪትም ነቢያትም
በዚህ ይጠቃለላሉና።

## ጠባቡና ሰፊው በር

13“በጠባቡ በር ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወ
ስደው መንገድ ትልቅ፣ በሩም ሰፊ ነውና፤
ብዙዎችም በዚያ ይገባሉ። 14ወደ ሕይወት
የሚያደርሰው ግን መንገዱ ቀጭን፣ በሩም
ጠባብ ነው፤ የሚገቡበትም ጥቂቶች ብቻ
ናቸው።

## ሐሰተኛ ነቢያት

15“በውስጣቸው ነጣቂ ተኵላዎች ሆነው
ሳሉ የበግ ለምድ ለብሰው መካከላችሁ በመ
ግባት ከሚያሸምቁ ሐሰተኛ ነቢያት ተጠን

7፥7 1ነገ3፥5፤ማቴ 18፥19፤21፥22፤ ዮሐ 14፥13፡14፤ 15፥7፡16፤16፥23፡24፤ ያዕ1፥5-8፤ 4፥2፡3፤5፥16፤ 1ዮሐ 3፥22፤ 5፥14፡15
7፥8 ምሳ8፥17፤ ኤር 29፥12፡13
7፥11 ያዕ1፥17
7፥12 ሉቃ6፥31፤ ሮሜ13፥8-10፤ገላ5፥14
7፥13 ሉቃ13፥24፤ ዮሐ10፥7፡9
7፥15 ኤር23፥16፤ ሕዝ22፥27፤ማቴ24፥24፤ሉቃ6፥26፤ሐሥ 20፥29፤2ጴጥ2፥1፤ 1ዮሐ4፥1፤ራእ16፥13
7፥16 ማቴ12፥33፤ ሉቃ6፥44፤ያዕ3፥12
7፥18 ሉቃ6፥43
7፥19 ማቴ3፥10
7፥21 ሆሴ8፥2፤ ማቴ3፥2፤12፥50፤25፥11፤ዮሐ13፥13፤ሮሜ 2፥13፤1ቆሮ12፥3፤ያዕ 1፥22፤1ዮሐ3፥18
7፥22 ማቴ10፥15፤ ሉቃ10፥20፤ሐሥ 19፥13፤1ቆሮ13፥1-3
7፥23 መዝ6፥8፤ ማቴ25፥12፡41፤ሉቃ 13፥25-27
7፥24 ቍ21፤ ያዕ 1፥22-25
7፥28 ማቴ11፥1፤ 13፥53፡54፤19፥1፤ 22፥33፤26፥1፤ማር 1፥22፤ 6፥2፤11፥18፤ ሉቃ4፥32፤ዮሐ7፥46
8፥2 ዘሌ13፥45፤ ማቴ9፥18፤10፥8፤ 11፥5፤15፥25፤18፥26 ፤20፥20፤26፥6፤ ሉቃ 5፥12፤17፥12

ቀቁ። 16ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፤ ከእ
ሾህ ቍጥቋጦ ወይን፣ ከኵርንችትስ በለስ
ይለቀማልን? 17እንዲሁም ጥሩ ዛፍ ሁሉ ጥሩ
ፍሬ፣ መጥፎ ዛፍ ግን መጥፎ ፍሬ ያፈራል።
18ጥሩ ዛፍ መጥፎ ፍሬ፣ መጥፎም ዛፍ
ጥሩ ፍሬ ማፍራት አይችልም። 19ጥሩ ፍሬ
የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል፤ ወደ እሳ
ትም ይጣላል። 20ስለዚህ በፍሬአቸው ታው
ቋቸዋላችሁ።
21“በሰማይ ያለውን ያባቴን ፈቃድ ሳይፈ
ጽም ‘ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤’ የሚለኝ ሁሉ
ወደ መንግሥተ ሰማይ አይገባም። 22በዚያ
ቀን ብዙዎች፣ ‘ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ በስ
ምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህ
አጋንንት አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ
ታምራት አላደረግንምን?’ ይሉኛል። 23በዚያ
ጊዜ፣‘ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ክፉዎች፤
ከእኔ ራቁ!’ ብዬ በግልጽ እነግራቸዋለሁ።

## ብልኁና ሞኙ ቤት ሠሪ

7፥24-27 ተጓ ምብ - ሉቃ 6፥47-49

24“እንግዲህ ይህን ቃሌን ሰምቶ በተግባር
የሚያውል፣ ቤቱን በዐለት ላይ የሠራን
ብልኅ ሰው ይመስላል። 25ዶፍ ወረደ፤ ጐር
ፍም ጐረፈ፤ ነፋስም ነፈሰ፤ ያንን ቤት
መታው፤ በዐለት መሠረትም ላይ ስለ ተመ
ሠረተ አልወደቀም። 26ይህን ቃሌን ሰምቶ
በተግባር የማያውለው ግን ቤቱን በአሸዋ
ላይ የሠራን ሞኝ ሰው ይመስላል። 27ዶፍ
ወረደ፤ ጐርፍም ጐረፈ፤ ነፋስም ነፈሰ፤
ያንን ቤት መታው፤ ቤቱም ወደቀ፤
አወዳደቁም የከፋ ነበር።”
28ኢየሱስ ማስተማሩን በፈጸመ ጊዜ፣
ሕዝቡ በትምህርቱ ተደነቁ፤ 29ምክንያቱም
እንደ አይሁድ ሃይማኖት መምህራናቸው
ሳይሆን እንደ ባለ ሥልጣን አስተምሮአቸው
ስለ ነበር ነው።

## የለምጻሙ መንጻት

8፥2-4 ተጓ ምብ - ማር 1፥40-44፤ ሉቃ 5፥12-14

8 ከተራራው በወረደ ጊዜም ብዙ ሕዝብ
ተከተለው። 2እነሆ፤ አንድ ለምጻም* ሰው

*2 የግሪኩ ቃል የግድ ከለምጽ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን የተለያዩ የቆዳ በሽታዎችንም ያመለክታል

በግብዝነት ወይም በመመጻደቅ በሌላው ላይ መፍረድ የለበ ትም። ከዚሁ ጋር የተመሳሰለ ሐሳብ በ23፥13-39 ተገልጾአል (ከሮሜ 2፥1 ጋር ያነጻጽሩ)። በዚህ ምዕራፍ የተመለከተውን የክ ርስቶስን ትእዛዝ ለመፈጸም፣ ማንም “ውሾ” ይሁን (ቍ6)፣ ሐሰ ተኛ ነቢይ (ቍ15) ይሁን፣ ወይም ሕይወቱ ፍሬ የሚታይበት ሰው (ቍ16) ይሁን፣ ፍርድ ከመስጠታችን በፊት በቅድሚያ የሰ ውየውን ጠባይ መመዘን ይኖርብናል። ክርስቲያኖች በጎ ሰዎ ችንና ነገሮችን ክፉ ከሆኑት እንዲለዩና በጥንቃቄ እንዲመዝኑ ቅዱሳት መጻሕፍት በተደጋጋሚ ይመክራሉ (አመንዝራነት የሥጋ ግብር ያላቸውን 1ቆሮ5፥9፤ የብርሃን መልአክ መስለው ለመታየት የሚሞክሩትን 2ቆሮ11፥15፤ ውሾችን ፊል 3፥2፤ ሐሰ ተኛ ነቢያትን 1ዮሐ4፥1)። ክርስቲያን “ሁሉን ነገር መፈተን” አለበት (1ተሰ5፥21)።

*7፥6፤* መንፈሳዊ ትምህርት መቅረብ የሚገባው የሰሚዎቹ መንፈሳዊ ዐቅም ወይም ሁኔታ እየተመዘነና የእግዚአብሔር ፈቃድ እየተጠበቀ መሆን አለበት። *ውሾች፤* በመንገድ ላይ ይልከሰከሱ የነበሩት ውሾች በዚያን ጊዜም ይናቁ ነበር። እዚህ ላይ አገባቡ ግን የመቀደስ ፍላጎት የሌላቸውን ሰዎች ለማመልከት ነው።

7፥7 *ለምኑ፣ ... ፈልጉ፣ ... አንኳኩ፤* በዚህ ላይ እንደ ተጠቀሰው እንደ ትእዛዝ ያለማቋረጥ ሊፈጸሙ የሚገባቸው ነገሮ ችን ያመለክታል።

*7፥12፤* ይህ “ወርቃማው ሕግ” በመባል የሚታወቀው አባ ባል በተለያዩ እምነቶች፣ ማለትም በአይሁድ እምነት፣ የሒንዱ፣ በቡድሐ፣ እንዲሁም በኮንፉሺያን እምነት በአሉታዊ መልኩ ይገ ኛል፤ ይኸውም “በሌሎች ላይ ክፉ አታድርግ” በሚል ማለት ነው። በግሪክና በሮም የግብረ ገብ ትምህርትም በተለያየ መልክ ይገኛል። ጌታ ኢየሱስ ግን ይህንኑ ሕግ በአዎንታ መልኩ አቀ ረበው። *ኦሪትም፣ ነቢያትም፤* የ 5፥17 ማብ ይመ።

7፥22 *በዚያ ቀን፤* ይህ የመጨረሻውን የፍርድ ቀን ያመ ለክታል (ሚል3-4 ይመ)። *ትንቢት፤* በአዲስ ኪዳን የዚህ ቃል ዋና ትርጕም ወደ ፊት የሚሆነውን ነገር መናገር ብቻ ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን መልእክት ማስተላለፍ ነው። *አጋን ንት፤* የማር1፥23 ማብ ይመ።

7፥29 *ሥልጣን፤* የኦሪት ሕግ መምህራን ትምህርታቸው ይበልጥ ተቀባይነት እንዲያገኝ፣ ሌሎች የታወቁ መምህራንን በማረጋገጫነት በመጥቀስ ያስተምሩ ነበር (የ2፥4 ማብ ይመ)፤ ጌታ ኢየሱስ ግን በመለኮት ሥልጣኑ አስተማረ።

8፥2 *ለምጻም፤* ለዚህ ቃል የገባው የግሪኩ አቻ ቃል የተለያዩ

ወደ ኢየሱስ ቀረበና ከፊቱ ተንበርክኮ እየሰ
ገደለት፣ “ጌታ ሆይ፤ ብትፈቅድስ ልታነ
ጻኝ ትችላለህ” አለው።
3ኢየሱስም እጁን ዘርግቶ ዳሰሰውና፣ “ፈ
ቃዴ ነው፤ ንጻ!” አለው። ሰውየውም ወዲያ
ውኑ ከለምጹ ነጻ። 4ከዚያም ኢየሱስ፣
“መፈወስህን ለማንም አታውራ፤ ነገር ግን
ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ፤ ሙሴ ያዘዘው
ንም መባ አቅርብ፤ ይህም ምስክር ይሆንላ
ቸዋል” አለው።

## የመቶ አለቃው እምነት

8፥5-13 ተጓ ምብ - ሉቃ 7፥1-10

5ኢየሱስ ቅፍርናሆም እንደ ደረሰ አንድ
የመቶ አለቃ ቀርቦ፣ እንዲህ ሲል ለመነው፤
6“ጌታ ሆይ፤ አገልጋዬ ሽባ ሆኖ እጅግ በመ
ሠቃየት ከቤት ተኝቶአል” አለው።
7ኢየሱስም፣ “እኔ መጥቼ እፈውሰዋለሁ”
አለው።
8የመቶ አለቃው ግን መልሶ እንዲህ አለ፤
“ጌታ ሆይ፤ ወደ ቤቴ እንድትገባ የሚገባኝ
አይደለሁም፤ ነገር ግን ከዚሁ ሆነህ አንዲት
ቃል ብቻ ተናገር፤ አገልጋዬም ይፈወሳል፤
9እኔ ራሴ የምታዘዛቸው አለቆች፣ ለእኔም
የሚታዘዙ የበታቾች አሉኝ፤ ከእነርሱ አን
ዱን፣ ‘ሂድ!’ ስለው ይሄዳል፤ ሌላውን፣
‘ና!’ ስለው ይመጣል፤ አገልጋዬንም፣ ‘ይህን
አድርግ’ ስለው ያደርጋል።”
10ኢየሱስም በመልሱ ተደንቆ ይከተሉት
ለነበሩት እንዲህ አላቸው፤ “እውነት እላች
ኋለሁ፣ ከእስራኤል መካከል እንኳ እንዲህ
ያለ እምነት ያለው አንድ ሰው አላገኘሁም፤
11እላችኋለሁ፣ ብዙዎች ከምሥራቅና ከምዕ
ራብ ይመጣሉ፤ በመንግሥተ ሰማይ ማእድ
ዙሪያ ከአብርሃም፣ ከይስሐቅና ከያዕቆብ
ጋር ይቀመጣሉ፤ 12መንግሥተ ሰማይ ተዘጋ
ጅቶላቸው የነበሩት ግን ወደ ውጭ ወደ
ጨለማው ይጣላሉ። በዚያም ልቅሶና ጥርስ
ማፋጨት ይሆናል።”
13ኢየሱስም መቶ አለቃውን፣ “ሂድ እንደ

8፥4 ዘሌ14፥2-32፤ ማቴ9፥30፤12፥16፤ ማር5፥43፤7፥36፤ 8፥ 30፤ሉቃ4፥41፤ 17፥14
8፥6 ማቴ4፥24
8፥8 መዝ107፥20
8፥10 ማቴ15፥28
8፥11 መዝ107፥3፤ ኢሳ49፥12፤59፥19፤ ሚል1፥11፤ ሉቃ 13፥29
8፥12 ማቴ13፥38፡42፡50፤22፥13፤ 24፥51፤25፥30፤ ሉቃ 13፥28
8፥13 ማቴ9፥22
8፥16 ማቴ4፥23፡24
8፥17 ኢሳ53፥4፤ ማቴ1፥22
8፥18 ማር4፥35
8፥20 ዳን7፥13፤ ማቴ12፥8፡32፡40፤ 16፥13፡27፡28፤17፥9፤ 19፥28፤ ማር2፥10፤8፥31
8፥22 ማቴ4፥19

እምነትህ ይሁንልህ” አለው። አገልጋዩም
በዚያች ቅጽበት ተፈወሰ።

## ኢየሱስ ብዙዎችን መፈወሱ

8፥14-16 ተጓ ምብ - ማር 1፥29-34፤ ሉቃ 4፥38-41

14ኢየሱስ ወደ ጴጥሮስ ቤት ጎራ ሲል የጴ
ጥሮስ ዐማት በትኵሳት ታማ ተኝታ አገ
ኛት። 15እጇን ዳሰሳት፤ ትኵሳቱም ለቀቃት፤
ተነሥታም አገለገለችው።
16በዚያ ምሽት በአጋንንት የተያዙ ብዙ
ሰዎችን ወደ ኢየሱስ አመጡ፤ እርሱም
መናፍስትን በቃሉ አስወጣ፤ በሽተኞችንም
ሁሉ ፈወሰ። 17በዚህም ኢሳይያስ እንዲህ
ብሎ የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ፤

“እርሱ ደዌያችንን ተቀበለ፤
 ሕመማችንንም ተሸከመ።”

## የኢየሱስ ተከታይ ለመሆን ውሳኔ ይጠይቃል

8፥19-22 ተጓ ምብ - ሉቃ 9፥57-60

18ኢየሱስ ብዙ ሰዎች በዙሪያው ተሰብስ
በው ባየ ጊዜ ወደ ባሕሩ ማዶ እንዲሻገሩ
አዘዛቸው። 19በዚህ ጊዜ አንድ የአይሁድ
ሃይማኖት መምህር ወደ እርሱ ቀርቦ፣ “መም
ህር ሆይ፤ ወደምትሄድበት ሁሉ እከተልሃ
ለሁ” አለው።
20ኢየሱስም፣ “ቀበሮዎች ጕድጓድ፣ የሰ
ማይ ወፎችም ጎጆ አላቸው፤ የሰው ልጅ ግን
ራሱን የሚያስጠጋበት ቦታ የለውም” ሲል
መለሰ ለት።
21ደቀ መዝሙር የሆነ አንድ ሌላ ሰው
ደግሞ፣ “ጌታ ሆይ፤ መጀመሪያ ሄጄ አባቴን
እንድቀብር ፍቀድልኝ” አለው።
22ኢየሱስ ግን፣ “ሙታን ሙታናቸውን
ይቀበሩ፤ አንተ ተከተለኝ” አለው።

## ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ አደረገ

8፥23-27 ተጓ ምብ - ማር 4፥36-41፤ ሉቃ 8፥22-25
8፥23-27 ግመ - ማቴ 14፥22-23

23ከዚያም ኢየሱስ ወደ ጀልባ ገባ፤ ደቀ
መዛሙርቱም ተከትለውት ገብተው ሄዱ።
24ድንገት ኀይለኛ ማዕበል ተነሥቶ ጀልባዪ

---

የቈዳ በሽታዎችን ያመለክታል (ዘሌ13-14 ይመ)። *ልታነጻኝ፤* ለምጽ አንድን ሰው በመንጻት ሥርዓት መሠረት በማኅበረ ሰቡ ዘንድ እንደ ርኩስ ከማስቈጠሩም በላይ፣ በሽታውም ይጐዳዋል (የሉቃ5፥12-16 ማብ ይመ)።

8፥4 *ለማንም አታውራ፤* ኢየሱስ ይህን ያለበት ምክንያት የተለያየ ሊሆን ይችላል፤ 1) ኢየሱስ በሕዝቡ ዘንድ ታምር ሠሪ ብቻ ሆኖ እንዲታወቅ አልፈለገም፤ 2) ሰዎች ለፈውስ ታምራቱ አድናቆትን በመስጠት የማስተማር ተግባሩን እንዲያስተጓጕሉ በት አልፈለገም፤ 3) አገልግሎቱን ከግቡ ከማድረሱ በፊት፣ ጊዜው ገና ሳይደርስ ለመሞት አልፈለገም። 9፥30፤ 12፥16፤ ማር1፥44፤ 5፥43፤ 7፥36፤ ሉቃ8፥56 ይመ። *ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ፤* የሉቃ5፥14 ማብ ይመ። *ይሆንላቸዋል፤* ካህናቱ ማለት ነው።

8፥5 *የመቶ አለቃ፤* መቶ ወታደሮችን የሚያዝዝ የሮማውያን የጦር መኰንን ነው። ሉቃስ እንደ ዘገበው (ሉቃ7፥1-5) የአይሁድ ሽማግሌዎችና የመቶ አለቃው ወዳጆች ስለ መቶ አለቃው ጕዳይ ሲሉ ወደ ኢየሱስ መጥተዋል፤ ማቴዎስ ግን ስለ እነዚህ አማላጅ ሆነው ስለ መጡት ሰዎች አልጠቀሰም። ደግሞም ማቴዎስ በ27፥26 ላይ ጲላጦስ “ኢየሱስን ገረፈው” ይላል፤ ይሁን እንጂ ግርፋቱ የተፈጸመው በጲላጦስ ትእዛዝ በሮም ወታደሮች እንጂ በጲላጦስ በራሱ እጅ እንዳልሆነ ይታወቃል።

8፥8 *ወደ ቤቴ እንድትገባ የሚገባኝ አይደለሁም፤* በግሪክ ቋንቋ መሠረት ይህ አባባል፣ ማቴዎስ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ (ማቴ3፥11) እንደ ጻፈው፣ መጥምቁ ስለ ጌታ ኢየሱስ በትሕትና ከተናገረው ጋር አንድ ዓይነት ትርጓሜ ይሰጠዋል። ይህም አንድም መቶ አለቃው ለጌታ ኢየሱስ ማንነቱን ከመረዳት የተነሣ ከሰጠው ታላቅ አክብሮት፣ አንድም እርሱ ራሱ መቶ አለቃው ከነበረበት የኀጢአት ቀንበር የተነሣ ጌታ ኢየሱስ ዘንድ በመቅረቡ ኀጢአተ ኝነቱን በመቀበሉ እንደ ተናገረ ልንረዳ እንችላለን።

*8፥11፤* ከማቴዎስ ወንጌል ጭብጦች አንዱ የወንጌሉ ሁሉን አቀፍነት ነው (በተለይ 28፥19-20 ይመ)።

8፥18 *ማዶ፤* ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ ማለት ነው።

8፥20 *የሰው ልጅ፤* የማር 8፥31 ማብ ይመ።

8፥22 *ሙታን ሙታናቸውን ይቅበሩ፤* በመንፈስ ሙታን የሆኑት በሥጋ የሞቱትን ይቅበሩ ማለት ነው። ኢየሱስ በምድር በነበረበት ዘመን፣ የአገልግሎት ጊዜው አጭር ነበረ፤ በመሆኑም በሙሉ ሐሳብና በሙሉ ልብ ተሰጥቶ መከታተልን ይጠይቅበት ነበር። በአይሁድ ልማድ ልጆች ወላጆቻቸውን የመቅበር ኀላፊነትና ግዴታ አለባቸው፤ ስለዚህ ይህ የጌታ አባባል የእርሱ ደቀ መዝሙር መሆን ሥር ነቀል ለውጥ እንደሚጠይቅ ያመለክታል።

8፥24 *ኀይለኛ ማዕበል፤* የማር4፥37 ማብ ይመ። *ግን ኢየሱስ ተኝቶ ነበር፤* የሉቃ8፥23 ማብ ይመ።

ቱን እስኪሸፍን ድረስ አወካቸው፤ በዚህ ጊዜ
ግን ኢየሱስ ተኝቶ ነበር:: 25ደቀ መዛሙር
ቱም ቀርበው ቀሰቀሱትና፣ "ጌታ ሆይ!
ጠፋን፤ አድነን" አሉት::
26ኢየሱስም፣ "እናንተ እምነት የጐደላችሁ፤
ለምን ይህን ያህል ፈራችሁ!" አላቸው፤ ከዚ
ያም ተነሥቶ ነፋሱንና ማዕበሉን ገሠጸ፤
ወዲያውም ጸጥታ ሰፈነ::
27ሰዎቹም፣ "ነፋስና ባሕር እንኳ የሚታዘ
ዙለት፣ ይህ እንዴት ያለ ሰው ነው?" እያሉ
ተደነቁ::

## ከርኩሳን መናፍስት ስለ ተፈወሱ ሁለት ሰዎች

8፥28-34 ተጓ ምብ - ማር 5፥1-17፤ ሉቃ 8፥26-27

28ባሕሩን ተሻግሮ ጌርጌሴኖን[^1] ወደሚባል
አገር እንደ ደረሰ፣ አጋንንት ያደሩባቸው
ሁለት ሰዎች ከሚኖሩበት የመቃብር ቦታ
ወጥተው ተገናኙት:: በዚያ መንገድ ሰው
ማለፍ እስከማይችል ድረስ እጅግ አደገኞች
ነበሩ:: 29እነርሱም "የእግዚአብሔር ልጅ
ሆይ፤ ከእኛ ምን ጕዳይ አለህ? ጊዜው ሳይደ
ርስ ልታሠቃየን መጣህን?" እያሉ ጮኹ::
30ከእነርሱ ትንሽ ራቅ ብሎ፣ የብዙ ዐሣማ
መንጋ ተሰማርቶ ነበር:: 31አጋንንቱም ኢየ
ሱስን፣ "የምታስወጣን ከሆነ ዐሣማዎቹ
መንጋ ውስጥ እንድንገባ ፍቀድልን" ብለው
ለመኑት:: 32ኢየሱስም፣ 'ሂዱ!' አላቸው::
አጋንንቱም ከሰዎቹ ወጥተው ዐሣማዎቹ
ውስጥ ገቡ፤ ዐሣማዎቹም በሙሉ ከነበሩበት
አፋፍ እየተጣደፉ ባሕሩ ውስጥ በመ ግባት
ውሃው ውስጥ ሰጥመው ሞቱ:: 33የዐሣማ
ዎቹ ጠባቂዎችም ሸሽተው ወደ ከተማ
በመሄድ፣ የሆነውን ሁሉና በአጋንንት ተይ
ዘው በነበሩት ሰዎች ላይ የተደረገውን ነገር
አወሩ:: 34እነሆም፤ መላው የከተማ ነዋሪ ኢየሱ
ስን ለመገናኘት ወጣ፤ ባዩትም ጊዜ አገራቸ
ውን ለቅቆ እንዲሄድ ለመኑት::

## የሽባው ሰው መፈወስ

9፥2-8 ተጓ ምብ - ማር 2፥3-12፤ ሉቃ 5፥18-26

9 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ባሕሩን በጀልባ
ተሻግሮ ወደ ራሱ ከተማ መጣ:: 2በዚያም
ሰዎች አንድ ሽባ ሰው በቃሬዛ ተሸክመው
ወደ እርሱ አመጡ:: ኢየሱስም እምነታቸ
ውን አይቶ ሽባውን፣ "አይዞህ አንተ ልጅ፤
ኀጢአትህ ተሰርዮልሃል" አለው::
3በዚህን ጊዜ የአይሁድ ሃይማኖት መምህ
ራን፣ "ይህማ እግዚአብሔርን መሳደብ ነው"
በማለት በልባቸው አጕረመረሙ::
4ኢየሱስ ሐሳባቸውን ተረድቶ እንዲህ
አለ፤ "ክፉ ነገር በልባችሁ ለምን ታስባላችሁ?
5ለመሆኑ፣ 'ኀጢአትህ ይቅር ተብሎልሃል'
ከማለትና 'ተነሥተህ ሂድ' ከማለት የቱ
ይቀላል? 6ነገር ግን የሰው ልጅ በምድር
ላይ ኀጢአትን የማስተስረይ ሥልጣን እንዳ
ለው እንድታውቁ ነው' ብሎ፣ ሽባውን፣
'ተነሣ! ቃሬዛህን ይዘህ ወደ ቤትህ ሂድ'
አለው::" 7ሽባውም ተነሥቶ ወደ ቤቱ ሄደ::
8ሕዝቡም ይህን ባዩ ጊዜ በመደነቅ፣ በፍ
ርሃት ተሞልተው፣ እንደዚህ ያለ ሥል
ጣን ለሰው የሰጠውን እግዚአብሔርን አመ
ሰገኑ::

## የማቴዎስ መጠራት

9፥9-13 ተጓ ምብ - ማር 2፥14-17፤ ሉቃ 5፥27-32

9ኢየሱስ ከዚያ ተነሥቶ ሲሄድ ማቴዎስ
የሚባል አንድ ሰው በቀረጥ ማስከፈያ ኬላ
ተቀምጦ አየ፤ 'ተከተለኝ' አለው፤ እርሱም
ተነሥቶ ተከተለው::
10ኢየሱስ በማቴዎስ ቤት በማእድ ላይ
ሳለ፣ ብዙ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና ኀጢአተኞች
መጥተው ከእርሱና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር
አብረው ሊበሉ ተቀመጡ:: 11ፈሪሳውያንም
ይህን ባዩ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን፣ "መምህ
ራችሁ ከቀረጥ ሰብሳቢዎችና ከኀጢአተኞች
ጋር እንዴት አብሮ ይበላል?" ብለው ጠየ
ቋቸው::
12ኢየሱስም የተናገሩትን በመስማቱ እን
ዲህ አላቸው፤ "ሐኪም የሚያስፈልገው ለሕ
መምተኞች እንጂ ለጤነኞች አይደለም፤
13ሂዳችሁ፣ 'ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን
እወዳለሁ፤' ኀጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን
ልጠራ አልመጣሁምና የሚለውን ቃል ትር
ጕም አጢኑ::"

## የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ያልጾሙበት ምክንያት

9፥14-17 ተጓ ምብ - ማር 2፥18-22፤ ሉቃ 5፥33-39

14የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት
ወደ ኢየሱስ ቀርበው፣ "እኛና ፈሪሳውያን
ስንጾም፣ ያንተ ደቀ መዛሙርት ግን ለምን

[^1]: 28 አንዳንድ ቅጆች ጌራሴኖን ይላሉ

8፥26 መዝ65፥7፤ 89፥9፤107፥29፤ ማቴ6፥30
8፥28 ማቴ4፥24
8፥29 መሳ11፥12፤ 2ሳሙ16፥10፤1ነገ 17፥18፤ማር1፥24፤ ሉቃ4፥34፤ዮሐ2፥4፤ 2ጴጥ2፥4
8፥34 ሉቃ5፥8፤ ሐሥ16፥39
9፥1 ማቴ4፥13
9፥2 ቍ22፤ማቴ 4፥24፤ዮሐ16፥33፤ ሉቃ7፥48
9፥3 ማቴ26፥65፤ ዮሐ10፥33
9፥4 መዝ94፥11፤ ማቴ12፥25፤ሉቃ6፥8፤ 9፥47፤11፥17፤ ዮሐ 2፥25
9፥6 ማቴ8፥20
9፥8 ማቴ5፥16፤ 15፥31፤ሉቃ7፥16፤ 13፥13፤17፥15፤23፥ 47፤ዮሐ15፥8፤ሐሥ 4፥21፤11፥18፤21፥20
9፥9 ማቴ4፥19
9፥11 ማቴ11፥19፤ ሉቃ5፥30፤15፥2፤ 19፥7፤ገላ2፥15
9፥13 ሆሴ6፥6፤ ሚክ 6፥6-8፤ ማቴ12፥7፤ ሉቃ19፥10፤ 1ጢሞ 1፥15
9፥14 ማቴ3፥1፤11፥ 18፡19፤ሉቃ18፥12

8፥28 *ጌርጌሴኖን ወደሚባል አገር፤* ከገሊላ ባሕር በደቡብ ምሥራቅ በኩል 10 ኪ.ሜ. ያህል ርቆ ካለው ገዳራ ከሚባለው ከተማ አካባቢ የሚገኝ አገር ነው:: ማርቆስና ሉቃስ ይህንኑ ምድር ከባሕሩ በስተ ደቡብ ምሥራቅ 56 ኪ.ሜ. ያህል ርቆ በሚገኘው ጌራሳ በተባለው ዋና ከተማ ስም ይጠሩታል:: *ሁለት፤* ማርቆስና (5፥2) ሉቃስ (8፥27) ጋኔን ያደረበት አንድ ሰው ብቻ እንደ ሆነ ይናገራሉ::

8፥29 *ጊዜው፤* የሚፈረድባቸው ጊዜ ማለት ነው (የማር 5፥10 እና የሉቃ8፥31 ማብ ይመ)::

8፥30 *የ...ዐሣማ መንጋ፤* በብዙ የሚቈጠሩ አሕዛብ በገሊላ አውራጃ ይኖሩ ነበር:: በአይሁድ ዘንድ ዐሣማ ከእንስሳት ሁሉ እጅግ "ርኩስ" በመሆኑ፣ እነርሱ ዐሣማ እንደማያረቡ ይታወቃል::

*8፥32፤* ጌታ ኢየሱስ የአጋንንቱን ልመና የተቀበለ ቢመስልም፣ ዐሣማዎቹ አጋንንቱን ወደ ጥልቁ ባሕር ይዘዋቸው ገቡ፤ ይህም "ጥልቁ" የተባለውን የመጨረሻ መውደቂያቸውን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል (ሉቃ8፥31 እና ማብ ይመ)::

8፥34 *ለቅቆ እንዲሄድ ለመኑት፤* ጭንቀታቸው ለሀብት ንብረታቸው እንጂ፣ በአጋንንት ስለ ተያዙት ምስኪን ሰዎች ነጻ መውጣት አልነበረም::

9፥1 *ወደ ራሱ ከተማ፤* ወደ ቅፍርናሆም ከተማ ማለት ነው (የ4፥13 ማብ ይመ)::

9፥3 *መሳደብ፤* አይሁድ የኢየሱስን አምላክነት ባለመቀበላቸው፣ ኀጢአትን ይቅር በማለቱ የእግዚአብሔርን ሥልጣን እንደ ተጋፋ ቈጠሩት፤ ኀጢአት ይቅር የሚል አምላክ ብቻ ነውና::

9፥10 *ቀረጥ ሰብሳቢዎችና፤* የ5፥46 ማብ ይመ:: በተጨ

አይጾሙም?” ብለው ጠየቁት።
15ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “ሙሽራው
አብሮአቸው እያለ ሚዜዎቹ እንዴት ሊያ
ዝኑ ይችላሉ? ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድ
በት ጊዜ ይመጣል፤ በዚያን ጊዜ ይጾማሉ።
16በአሮጌ ልብስ ላይ አዲስ ዕራፊ የሚ
ጥፍ ሰው የለም፤ ይህ ከሆነ አዲሱ ዕራፊ
ካረጀው ልብስ ላይ ተቦጭቆ ቀዳዳውን የባሰ
ያሰፋዋል። 17በአሮጌ አቍማዳ አዲስ የወ
ይን ጠጅ ማንም አይጨምርም፤ ይህ ከሆነ
አቍማዳው ይፈነዳል፤ የወይን ጠጁም ይፈ
ስሳል፤ አቍማዳውም ከጥቅም ውጭ ይሆ
ናል። ነገር ግን አዲስ የወይን ጠጅ በአዲስ
አቍማዳ ይጨመራል፤ በዚህ ሁኔታ የወ
ይን ጠጁና አቍማዳው በደህና ተጠብቀው
ይቈያሉ።

## ከሞት የተነሣችው ልጅና ከደም መፍሰስ የተፈወሰችው ሴት

9፥18-26 ተጓ ምብ - ማር 5፥22-43፤ ሉቃ 8፥41-56

18ኢየሱስ ሰዎቹን በማናገር ላይ ሳለ፣
አንድ ሹም ከፊቱ ተደፍቶ፣ “ልጄ ልትሞት
ተቃርባለች፤ በሕይወት እንድትኖር መጥተህ
እጅህን ጫንባት” አለው። 19ኢየሱስም ተነ
ሥቶ አብሮት ሄደ፤ ደቀ መዛሙርቱም
ተከተሉት።
20ከዚያም ዐሥራ ሁለት ዓመት ሙሉ
ደም እየፈሰሳት ትሠቃይ የነበረች አንዲት
ሴት ከኋላው መጥታ የልብሱን ጫፍ ነካች።
21እርሷም በልቧ፣ “የልብሱን ጫፍ እንኳ
ብነካ እፈወሳለሁ” የሚል እምነት ነበራት።
22ኢየሱስም ወደ ኋላ ዘወር ብሎ ሴቲቱን
አያትና፣ “አይዞሽ፤ ልጄ ሆይ፤ እምነትሽ
አድኖሻል” አላት። ሴቲቱም ወዲያውኑ
ተፈወሰች።
23ኢየሱስ ወደ ምኵራብ አለቃው ቤት
እንደ ደረሰ የሐዘን እምቢልተኞችንና የሚ
ንጫጫውን ሕዝብ አይቶ፣ 24“ዞር በሉ፤
ልጅቱ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም” አላ
ቸው፤ እነርሱ ግን ሣቁበት። 25ሕዝቡም
ከወጣ በኋላ ወደ ውስጥ ገብቶ እጇን ያዘ፤
ልጅቱም ተነሥታ ቆመች። 26ወሬውም
በአካባቢው ሁሉ ተሰራጨ።

## የዐይነ ስውሮቹና የድዳው መፈወስ

27ኢየሱስም ከዚያ እንደ ሄደ ሁለት ዐይነ
ስውሮች፣ “የዳዊት ልጅ ሆይ፤ ማረን” በማ
ለት እየጮኹ ተከተሉት።
28ዐይነ ስውሮቹም ኢየሱስ ወደ ገባበት
ቤት ተከትለው ገቡ፤ ኢየሱስም፣ “ዐይናች
ሁን ላበራላችሁ እንደምችል ታምናላችሁ?”
ሲል ጠየቃቸው።
እነርሱም፣ “አዎን፣ ጌታ ሆይ፤” ብለው
መለሱለት።
29ከዚያም ኢየሱስ ዐይናቸውን ዳሰሰ፣
“እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ” አላቸው።
30ዐይናቸውም በራ፤ ኢየሱስም፣ “ይህን
ማንም እንዳያውቅ” ብሎ በጥብቅ አስጠነቀ
ቃቸው። 31እነርሱ ግን ወጥተው በአካባቢው
ሁሉ ስለ ኢየሱስ አወሩ።
32ከዚያም ሲወጡ፣ በጋኔን የተያዘ ድዳ
ሰው ወደ እርሱ አመጡ። 33ጋኔኑ ከወጣለት
በኋላ ድዳው መናገር ጀመረ፤ ሕዝቡም
ተደንቀው፣ “እንዲህ ያለ ነገር በእስራኤል
ምድር ታይቶ አያውቅም” አሉ።
34ፈሪሳውያን ግን፣ “አጋንንትን የሚያወ
ጣው፣ በአጋንንት አለቃ ነው” አሉ።

## ሠራተኞች ጥቂቶች ናቸው

35ኢየሱስ በምኵራቦቻቸው እያስተማረ፣
የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራች
እየሰበከ እንዲሁም ደዌንና ሕመምን ሁሉ
እየፈወሰ በከተሞቹና በመንደሮቹ ዞረ።
36ሕዝቡም እረኛ እንደሌለው በግ ተጨን
ቀውና ተመልካች የለሽ ሆነው ባየ ጊዜ
አዘነላቸው።
37ደቀ መዛሙርቱንም እንዲህ አላቸው፤
“መከሩ ብዙ ነው፤ የመከሩ ሠራተኞች ግን
ጥቂቶች ናቸው፤ 38ስለዚህ የመከሩ ጌታ፣
ወደ መከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ ለምኑት።”

## የዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት መላክ

10፥2-4 ተጓ ምብ - ማር3፥16-19፤ ሉቃ6፥14-16፤ የሐሥ1፥13
10፥9-15 ተጓ ምብ - ማር 6፥8-11፤ ሉቃ 9፥3-5፤ 10፥4-12
10፥19-22 ተጓ ምብ - ማር 13፥11-13፤ ሉቃ 21፥12-17
10፥26-33 ተጓ ምብ - ሉቃ 12፥2-9
10፥34-35 ተጓ ምብ - ሉቃ 12፥51-53

10 ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛ
ሙርት ወደ እርሱ ጠርቶ ርኵሳን
መናፍስትን እንዲያወጡ፣ ደዌንና ሕማምን
ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣንን ሰጣቸው።
2የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ስም የሚከተ
ለው ነው፦ መጀመሪያ ጴጥሮስ የተባለው
ስምዖንና ወንድሙ እንድርያስ፣ የዘብዴዎስ
ልጅ ያዕቆብና ወንድሙ ዮሐንስ፣ 3ፊልጶስና

9፥15 ዮሐ3፥29፤ ሐሥ13፥2፡3፤14፥23
9፥18 ማቴ8፥2፤ ማር5፥23
9፥20 ማቴ14፥36፤ ማር3፥10፤6፥56፤ ሉቃ6፥19
9፥22 ቍ2፥29፤ማቴ 8፥13፤15፥28፤ማር 10፥52፤ሉቃ7፥50፤ 17፥19፤18፥42፤ ዮሐ16፥33
9፥23 2ዜና35፥25፤ ኤር9፥17፡18
9፥24 መዝ76፥5፤ ዳን12፥2፤ ዮሐ11፥11-14፤ ሐሥ7፥60፤13፥36፤ 20፥10፤1ቆሮ11፥30፤ 15፥6፡18፡20፤ 1ተሰ 4፥13-16
9፥25 ሉቃ7፥14
9፥26 ቍ31፤ ማቴ4፥24፤14፥1፤ ማር1፥28፡45፤ሉቃ 4፥14፡37፤5፥15፤7፥17
9፥27 ማቴ1፥1፤ 12፥23፤15፥22፤ 20፥30፡31፤21፥9፡15፤ 22፥42፤ማር10፥47
9፥28 ሐሥ14፥9
9፥29 ቍ22
9፥30 ማቴ8፥4
9፥31 ቍ26፤ማር7፥36
9፥32 ማቴ4፥24፤ 12፥22-24
9፥33 ማር2፥12
9፥34 ማቴ12፥24
9፥35 ማቴ4፥23
9፥36 ዘኍ27፥17፤ 1ነገ22፥17፤ሕዝ 34፥5፡ 6፤ዘካ10፥2፤ ማቴ14፥ 14፤15፥32፤ ማር8፥2
9፥37 ሉቃ10፥2፤ ዮሐ4፥35
10፥1 ማቴ4፥23፤ ማር3፥13-15፤6፥7፤ ሉቃ4፥36፤9፥1

ማሪም ማር2፥16 ይመ።
9፥17 *በአዲስ አቍማዳ፤* በጥንት ዘመን ከፍየል ቈዳ የተሠራ ስልቻ የወይን ጠጅ ለመያዝ ያገለግል ነበር። አዲሱ የወይን ጭማቂ ሲፈላ የወይን ጠጁ መጠን እየጨመረ ይሄዳል፤ አዲሱ ቈዳም አብሮት ይወጠራል። አዲሱ የወይን ጭማቂ በአሮጌው አቍማዳ ቢጨመር ግን፣ አሮጌው አቍማዳ ይቀደዳል። አዲሱ የኢየሱስ ትምህርት ነባሩን የአምልኮ ሥርዓት መልክ እየለወጠና እየጣሰ የሚሄድ እንጂ፣ በአሮጌው ልማድ ተውጦ የሚቀር አልነበረም።
9፥18 *ሹም፤* ከማርቆስና ከሉቃስ ወንጌሎች እንደምንረዳው፣ ይህ ሰው ኢያኢሮስ የተባለ የምኵራብ አለቃ ነበረ (የማር 5፥22 ማብ ይመ)።
9፥20 *ዐሥራ ሁለት ዓመት ሙሉ ደም እየፈሰሳት፤* የማር 5፥25 ማብ ይመ።
9፥22 *አድኖሻል፤* የማር5፥34 ማብ ይመ።
9፥23 *እምቢልተኞችንና፤* በልቅሶ ጊዜ፣ በሙዚቃ መሣሪያ የሐዘን እንጕርጕሮ እንዲያሰሙ የሚቀጠሩ ባለ ሙያዎች ነበሩ። *የሚንጫጫውን ሕዝብ፤* ገንዘብ እየተከፈላቸው የሚያለቅሱና የሚያንጐራጕሩ አልቃሾች ነበሩ።
9፥24 *ተኝታለች እንጂ አልሞተችም፤* የሉቃ8፥52 ማብ ይመ።
9፥27 *የዳዊት ልጅ፤* ሊመጣ ላለው መሲሕ በአይሁድ ዘንድ የታወቀ መጠሪያ ነበር (ለምሳሌ፣ 12፥23፤ 20፥30፤ 21፥9፤ 22፥41-45፤ የ1፥1 ማብ ይመ)።
10፥2-4፤ የሉቃ6፥14-16 ማብ ይመ።
10፥2 *ሐዋርያት፤* የማር6፥30 ማብ ይመ።

በርቶሎሜዎስ፣ ቶማስና ቀረጥ ሰብሳቢው
ማቴዎስ፣ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብና ታዴ
ዎስ የተባለው ልብደዮስ፣ 4ቀነናዊው’ ስምዖ
ንና በኋላ ኢየሱስን አሳልፎ የሰጠው አስቆ
ሮቱ ይሁዳ::
5እነዚህን ዐሥራ ሁለቱን ኢየሱስ እንዲህ
ከሚል ትእዛዝ ጋር ላካቸው፤ "ወደ አሕዛብ
አትሂዱ፤ ወደ ሳምራውያንም ከተማ አት
ግቡ:: 6ይልቁንስ የእስራኤል ቤት ወደ ሆኑት
ወደ ጠፉት በጎች ሂዱ:: 7ሂዳችሁም፣ ‘መን
ግሥተ ሰማያት ቀርባለች’ ብላችሁ ስበኩ::
8በሽተኞችን ፈውሱ፤ ሙታንን አስነሡ፤
ለምጻሞችን[T] አንጹ፤ አጋንንትን አስወጡ፤
በነጻ የተቀበላችሁትንም በነጻ ስጡ:: 9በመ
ቀነታችሁ ወርቅም ሆነ ብር ወይም መዳብ
አትያዙ:: 10ለመንገዳችሁም ከረጢት፣ ትርፍ
እጀ ጠባብ ወይም ጫማ ወይም በትር አት
ያዙ፤ ለሠራተኛ የዕለት ጕርሱ ይገባዋልና::
11"ወደ አንድ ከተማ ወይም መንደር
ስትገቡ ሊቀበላችሁ ፈቃደኛ የሆነ ሰው
ፈልጋችሁ በቤቱ ዕረፉ፤ እስክትወጡም
ድረስ በዚያው ቈዩ:: 12ወደ ማንኛውም
ሰው ቤት ስትገቡ ሰላምታ አቅርቡ:: 13ቤቱም
የሚገባው ሆኖ ከተገኘ፣ ሰላማችሁ ይድረ
ሰው፤ የማይገባው ከሆነ ግን ሰላማችሁ ወደ
እናንተ ይመለስላችሁ:: 14ማንም ሰው ሊያስ
ተናግዳችሁ ወይም የምትናገሩትን ሊሰማ ፈቃ
ደኛ ካልሆነ፣ ከቤቱ ወይም ከከተማው ስት
ወጡ የእግራችሁን ትቢያ አራግፋችሁ
ውጡ:: 15እውነት እላችኋለሁ፤ በፍርድ ቀን
በዚያች ከተማ ከሚደርሰው ቅጣት ይልቅ
በሰዶምና በገሞራ የሚደርሰው ይቀላል::
16"እንደ በጎች በተኵላዎች መካከል እል
ካችኋለሁ፤ ስለዚህ እንደ እባብ ብልኆች
እንደ ርግብ የዋሃን ሁኑ:: 17ሰዎች ይዘው
ለፍርድ ወደ ሸንጎ ያቀርቧችኋል፤ በምኵራ
ቦቻቸውም ይገርፏችኋል፤ ስለዚህ ከእነርሱ
ተጠንቀቁ:: 18በእኔ ምክንያት ወደ ገዦ
ችና ወደ ነገሥታት ትወሰዳላችሁ፤ በእነ
ርሱና በአሕዛብም ፊት ምስክር ትሆናላ
ችሁ:: 19በምትያዙበትም ጊዜ ምን እንናገራ
ለን፣ ምንስ እንመልሳለን ብላችሁ አትጨ
ነቁ፤ በዚያን ጊዜ የምትናገሩት ይሰጣች
ኋል፤ 20በእናንተ የሚናገረው የሰማዩ አባታ
ችሁ መንፈስ እንጂ እናንተ አይደላችሁምና::
21"ወንድም ወንድሙን ለሞት አሳልፎ
ይሰጣል፤ አባትም ልጁን፤ ልጆች በወላጆቻ
ቸው ላይ ያምፃሉ፤ ያስገድሏቸዋልም:: 22ስለ
ስሜ ሰዎች ሁሉ ይጠሏችኋል፤ ነገር ግን
እስከ መጨረሻ የሚጸና እርሱ ይድናል::
23በአንድ ስፍራ ሲያሳድዷችሁ ወደ ሌላ
ሽሹ፤ እውነት እላችኋለሁ፣ የእስራኤልን
ከተሞች ሳታዳርሱ የሰው ልጅ ይመጣል::
24"ደቀ መዝሙር ከመምህሩ፣ ሎሌም
ከጌታው አይበልጥም፤ 25ደቀ መዝሙር መም
ህሩን፣ ሎሌም ጌታውን ከመሰለ ይበቃ
ዋል:: ባለቤቱን ‘ብዔልዜቡል’ ካሉት ቤተ
ሰዎቹንማ እንዴት አብልጠው አይሏቸውም!
26"ስለዚህ አትፍሯቸው፤ የተሸፈነ መገ
ለጡ፣ የተደበቀ መውጣቱ አይቀርምና:: 27በጨ
ለማ የምነግራችሁን በብርሃን አውሩት፤
በጆሮአችሁ የሰማችሁትን በአደባባይ አው
ጁት፤ 28ሥጋን መግደል እንጂ ነፍስን መግ
ደል የማይችሉትን አትፍሩ፤ ይልቁንስ ነፍ
ስንና ሥጋን በገሃነም ማጥፋት የሚቻለ
ውን ፍሩ:: 29በአንድ ሳንቲም[^] ከሚሸጡት
ሁለት ድንቢጦች አንዲቷ እንኳ ያለ አባታ
ችሁ ፈቃድ ምድር ላይ አትወድቅም::
30የራስ ጠጕራችሁ እንኳ አንድ ሳይቀር
የተቈጠረ ነው:: 31ስለዚህ አትፍሩ፤ ከብዙ
ድንቢጦች ይልቅ ዋጋችሁ የከበረ ነው::
32"በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ፣ እኔም
በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤
33ነገር ግን በሰው ፊት የሚክደኝን፣ እኔም
በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እክደዋለሁ::
34"እኔ የመጣሁት ሰላምን በምድር ለማ

10፥4 ማቴ26፥14-16:25:47፤27፥3፤ማር14፥10፤ዮሐ6፥71፤12፥4፤13፥2:26:27፤ሐሥ1፥16
10፥5 1ነገ16፥24፤2ነገ17፥24፤ሉቃ9፥52፤10፥33፤17፥16፥ዮሐ 4፤4-26:39:40፤8፥48፤ሐሥ8፥5:25
10፥6 ኤር50፥6፤ማቴ15፥24
10፥7 ማቴ3፥2
10፥9 ሉቃ22፥35
10፥10 1ጢሞ5፥18
10፥12 1ሳሙ25፥6
10፥14 ነህ5፥13፤ማር6፥11፤ሉቃ9፥5፤10፥11፤ሐሥ13፥51፤18፥6
10፥15 ዘፍ18፥20፤19፥24፤ማቴ11፥22:24፤12፥36፤ሐሥ17፥31፤2ጴጥ2፥6:9፤3፥7፤1ዮሐ4፥17፤ ይሁ6:7
10፥16 ሉቃ10፥3፤ሐሥ20፥29፤1ቆሮ14፥20
10፥17 ማቴ5፥22፤23፥34፤ማር13፥9፤ሐሥ5፥40፤22፥19፤26፥11
10፥18 ሐሥ25፥ 24-26
10፥19 ዘፀ4፥12
10፥20 ሉቃ12፥11:12፤ሐሥ4፥8
10፥21 ቍ35:36፤ሚክ7፥6፤ማር13፥12
10፥22 ማቴ24፥13፤ማር13፥13፤ሉቃ21፥19፤ዮሐ15፥21፤ራእ2፥10
10፥23 ሉቃ17፥30
10፥24 ዮሐ13፥16
10፥25 ማር3፥22
10፥26 ማር4፥22፤ሉቃ8፥17
10፥28 ኢሳ8፥12:13፤ዕብ10፥31
10፥30 1ሳሙ14፥45፤2ሳሙ14፥11፤1ነገ1፥52፤ሉቃ21፥18፤ሐሥ27፥34
10፥31 ማቴ6፥26፤ 12፥12 10፥32 ሮሜ10፥9
10፥33 ማር8፥38፤ 2ጢሞ2፥12

’4 ቀነናዊ የሚለው ቃል አራማይክ ሲሆን፣ ቀነናውያን የተባሉት በዚያን ጊዜ የሮምን መንግሥት የሚቃወሙ የፖለቲካ ቡድን አባላት ነበሩ
[T]8 የግሪኩ ቃል የግድ ከለምጽ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን የቆዳ በሽታዎችን ያመለክታል
[^]29 ግሪኩ አንድ አሳሪዮን ይላል

10፥4 *ቀነናዊ፤* አንድም ስምዖን ለሃይማኖቱ ምን ያህል ቀናተኛ እንደ ነበረ የሚያመለክት ቃል ሲሆን፣ በሌላም በኩል በዚህ ስም የሚጠራና በእስራኤል ምድር የነበረውን የሮማውያንን አገዛዝ የሚቃወም ተቀናቃኝ የአይሁድ የፖለቲካ ቡድን አባል እንደ ነበረ ያመለክታል:: "ቀነናዊ" የሚለው ቃል የአራማይክ ሲ ሆን፣ "ቀናተኛ" ወይም "ቃናዊ" (የቃና ሰው) የሚል ትርጕም አለው::

10፥5 *አትሂዱ፤* ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የምሥራቹ መሰበክ የነበረበት አስቀድሞ ለአይሁድ ሲሆን፣ ኢየሱስ ከሞቱና ከትንሣኤው በኋላ ወንጌሉ ለሕዝብ ሁሉ እንዲሰበክ አዝዞአል (28፥19፤ ከ21፥43 ጋር ያነጻጽሩ):: *ሳምራውያንም፤* የሰሜኑ መን ግሥት ሲሰደድ፣ ከስደት የቀሩት እስራኤላውያንና አሦራውያን በምድሪቱ ካሰፈሯቸው አሕዛብ ጋር ተጋብተው የተወለዱ ቅይጥ ወገኖች ናቸው (2ነገ17፥24):: ኢየሱስ በአካለ ሥጋ በምድር ላይ በነበረበት ዘመን፣ በአይሁድና በሳምራውያን መካከል ከፍተኛ ጥላቻ ነበረ (ዮሐ4፥9 ይመ)::

10፥14 *የእግራችሁን ትቢያ አራግፋችሁ፤* ፈሪሳውያን እንደ "ርኩስ" ከሚቈጥሩት ከአሕዛብ ምድር ለቀው ሲወጡ ያደ ርጉት የነበረ ልማድ ሲሆን፣ ይህም ድርጊት ከርኵሰት የመላቀቅ ምሳሌ ነበር:: እዚህ ላይ ግን የእግዚአብሔርን መልእክት አንቀበ ልም ላሉት እንደ ከባድ ማስጠንቀቂያ መሆኑ ነው (የሉቃ9፥5፤ የሐሥ 13፥51ማብ ይመ፤ ከሐሥ18፥6 ጋር ያነጻጽሩ)::

10፥15 *በሰዶምና በገሞራ፤* ዘፍ19፥ 23-29 ይመ::

10፥16 ሮሜ16፥19 ይመ::

10፥17 *ሸንጎ፤* ከዚህ ሥፍራ የተጠቀሰው ሸንጎ ከአጥቢያ ምኵራቦች ጋር ግንኙነት ያለው፣ መለስተኛ ጉዳዮችን የሚመለከ ትና ጥፋተኛ ሆነው የተገኙትን በግርፋት የሚቀጣ መለስተኛ ፍርድ ቤት ነው::

*10፥23፤* ይህ አባባል፣ ክርስቶስ ዳግመኛ እስከሚመጣ ድረስ ወንጌል ለአይሁድ እንደሚሰበክ የሚያስተምር ይመስላል::

10፥25 *ብዔልዜቡል፤* የአጋንንት አለቃ ነው (12፥24):: ይህ የግሪክ ቃል በዕብራይስጡ ቋንቋ በኣል ዜቡብ ሲሆን ("የዝ ንብ ጌታ" ፤ 2ነገ1፥2)፣ በኣል ዜቡል ("ክቡር በኣል" ወይም "ልዑል በኣል") የሚለውን ትክክለኛ የባሕርይ መግለጫ ስያሜ በድምፀቱ በማወራረስ ለማሽነፍ የተለወጠ አጠራር ነው::

10፥28 *በገሃነም፤* የ5፥22 ማብ ይመ:: አንዳንድ ትርጕ ሞች ‘ሲኦል’ ይሉታል::

*10፥34፤* ይህ አባባል ላይ ላዩን ሲታይ፣ ከኢሳ9፥6 ("የሰ

ስፈን አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ሰላምን
ለማውረድ አልመጣሁም። 35እኔ የመጣሁት
"'ልጅን ከአባቱ፣
ሴት ልጅን ከእናቷ
ምራቲንም ከዐማቷ ለመለያየት ነው፤
36የሰው ጠላቶቹ፣
የገዛ ቤተ ሰዎቹ ይሆናሉ።'
37"ከእኔ ይልቅ እናቱን ወይም አባቱን
የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባም፤ ከእኔ ይልቅ
ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ
ለእኔ ሊሆን አይገባም። 38መስቀሉን ተሸክሞ
የማይከተለኝ የእኔ ሊሆን አይገባውም።
39ሕይወቱን ሊያድን የሚፈልግ ያጠፋታል፤
ሕይወቱን ስለ እኔ አሳልፎ የሚሰጥ ግን
ያገኛታል።
40"እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤
እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል። 41ነቢ
ይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ
ያገኛል፤ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል
የጻድቅን ዋጋ ያገኛል። 42ስለዚህ እውነት
እላችኋለሁ፣ ማንም ሰው ከእነዚህ ከታናና
ሾች ለአንዱ ደቀ መዝሙሬ በመሆኑ አንድ
ጽዋ ቀዝቃዛ ውሃ ቢሰጠው ዋጋውን አያጣም።"

### መጥምቁ ዮሐንስ ወደ ኢየሱስ የላከው ጥያቄ

11፥2-19 ተጓ ምብ - ሉቃ 7፥18-35

11 ኢየሱስ ለዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙ
ርቱ ትእዛዙን ሰጥቶ ከጨረሰ በኋላ
ለማስተማርና ለመስበክ ወደ ገሊላ ከተሞች[ሀ]
ሄደ።
2ዮሐንስ በእስር ቤት ሆኖ ክርስቶስ በማ
ድረግ ላይ ያለውን ነገር በሰማ ጊዜ፣ ደቀ
መዛሙርቱን ወደ እርሱ ልኮ፣ 3"ይመጣል
ተብሎ የሚጠበቀው አንተ ነህ? ወይስ ሌላ
እንጠብቅ?" ሲል ጠየቀ።
4ኢየሱስም፣ እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፤
"ሄዳችሁ የምትሰሙትንና የምታዩትን ለዮሐ
ንስ ንገሩት፤ 5ዕውሮች ያያሉ፤ አንካሶች ይራ

10፥35 ሎ21
10፥36 ሚክ7፥6
10፥37ሉቃ፥14፥26
10፥38ማቴ16፥24፤ ሉቃ14፥27
10፥39 ዮሐ12፥25
10፥40 ዘፀ16፥8፤ ማቴ18፥5፤ሉቃ9፥48፤ 10፥16፤ዮሐ12፥44፤ 13፥20፤ገላ4፥14
10፥42 ምሳ14፥31፤ 19፥17፤ማቴ25፥40፤ ማር9፥41፤ ሐሥ10፥4፤ ዕብ6፥10
11፥1 ማቴ7፥28
11፥2ማቴ3፥1፤14፥3
11፥3 መዝ118፥26 ፤ዮሐ11፥27፤ ዕብ 10፥37
11፥5 ኢሳ35፥4-6፤ 61፥1፤ማቴ15፥31፤ ሉቃ4፥18፡19
11፥6 ማቴ13፥21፤ 26፥31
11፥7 ማቴ3፥1
11፥9 ማቴ14፥5፤ 21፥26፤ሉቃ1፥76፤ 7፥26
11፥10 ሚል3፥1፤ ማር1፥2፤ዮሐ3፥28፤ ሉቃ7፥27
11፥13 ሉቃ16፥16
11፥14 ሚል4፥5፤ ማቴ17፥10-13፤ማር 9፥11-13፤ሉቃ1፥17፤ ዮሐ1፥21
11፥15 ማቴ13፥9፡ 43፤ማር4፥23፤ሉቃ 14፥35፤ራእ2፥7

መዳሉ፤ ለምጻሞች[ሁ] ይነጻሉ፤ ደንቆሮዎች
ይሰማሉ፤ ሙታን ይነሣሉ፤ ለድኾችም
የምሥራች እየተሰበከ ነው፤ 6በእኔ የ
ማይሰናከልም ብፁዕ ነው።"
7የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ከሄዱ በኋላ፣
ኢየሱስ ለሕዝቡ ስለ ዮሐንስ እንዲህ ሲል
ተናገረ፤ "ወደ ምድረ በዳ ምን ልታዩ ወጣ
ችሁ? ሸምበቆ በነፋስ ሲወዛወዝ? 8ወይስ
ምን ልታዩ ወጣችሁ? ባማረ ልብስ ያጌጠ
ሰው? ባማረ ልብስ ያጌጡ በነገሥታት ቤት
አሉላችሁ! 9ታዲያ ምን ልታዩ ወጣችሁ?
ነቢይ ልታዩ? አዎን፤ ከነቢይም የሚበልጥ
ነው። 10እንዲህ ተብሎ የተጻፈለት እርሱ ነው፤
"'በፊትህ መንገድህን ያዘጋጅልህ ዘንድ፣
ከአንተ አስቀድሜ መልእክተኛዬን
እልካለሁ።'
11እውነት እላችኋለሁ፤ ከሴት ከተወለዱት
መካከል እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ያለ አል
ተነሣም፤ ሆኖም በመንግሥተ ሰማይ ከሁሉ
የሚያንሰው ይበልጠዋል። 12ከመጥምቁ
ዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ
መንግሥተ ሰማያት በብዙ ትገፋለች፤ የሚ
ያገኟትም ብርቱዎች ናቸው፤ 13ነቢያትም፣
የሙሴ ሕግም ሁሉ እስከ ዮሐንስ ድረስ
ትንቢት ተናግረዋልና። 14እንግዲህ ልትቀ
በሉት ከፈቀዳችሁ ይመጣል የተባለው ኤል
ያስ እርሱ ነው። 15ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ።
16"ይህን ትውልድ በምን ልመስለው? በገ
በያ ተቀምጠው ጓደኞቻቸውን እንዲህ እያሉ
የሚጣሩ ልጆችን ይመስላሉ፤
17"'ዋሽንት ነፋንላችሁ፤
አልጨፈራችሁም፤
ሙሾ አወረድንላችሁ፤
አላለቀሳችሁም'

[ሀ]1 ግሪኩ *ወደ ከተሞቻቸው* ይላል
[ሁ]5 የግሪኩ ቃል የግድ ከለምጽ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን የተለ ያዩ የቆዳ በሽታዎችንም ያመለክታል

ላም አለቃ")፣ ከሉቃ2፥14 ("ሰላም በምድር ላይ ለሰዎች ይሁን") እና ከዮሐ14፥27 ("ሰላምን እተውላችኋለሁ") ጋር የሚቃረን ይመስላል። በእርግጥ ክርስቶስ የመጣው ሰላም እንዲሰፍን ነው፤ በሰዎችና በእግዚአብሔር፣ በሰዎችና በሰዎችም መካከል ያለው የጥል ግድግዳ እንዲፈርስ ነው። ይሁን እንጂ የክርስቶስ መምጣት ጠላትነትን ማስከተሉ አልቀረም፤ ይኸውም በክርስቶስና በክርስቶስ ተቃዋሚ መካከል፣ በብርሃንና በጨለማ መካከል፣ በክርስቶስ ልጆችና በሰይጣን ልጆች መካከል ጠላትነት ተነሥቶአል። ይኸው ግጭት በቤተ ሰብ አባላት መካከል እንኳ ሳይቀር ሊነሣ ይችላል (ቍ35-36)።

10፥38 *መስቀሉን ተሸክሞ፤* በማቴዎስ ወንጌል "መስቀል" የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ እዚህ ቍጥር ላይ ተጠቀሰ። መስቀል ሰውን በሞት መቅጫ መሣሪያ ሲሆን፣ በዚህ ላይ በተም ሳሌት የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ሕይወታቸውን እስከ ሞት ድረስ እንኳን ቢሆን፣ አሳልፈው መስጠት እንዳለባቸው አመ ልካች ነው (የማር8፥34 ማብ ይመ)።

10፥41 *ነቢይ፤* መጥምቁ ዮሐንስ የብሉይ ኪዳን የመጨረ ሻው ነቢይ ነው።

*11፥11* ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት የመጀመሪያ ተልእኳቸ ውን ሲያከናውኑ በነበሩበት ጊዜ፣ ጌታ ኢየሱስ በገሊላ አውራጃ አገልግሎቱን ቀጠለ።

11፥3 *ይመጣል ተብሎ የሚጠበቀው፤* መሲሑን ማለት ነው። *ሌላ እንጠብቅ?* የሉቃ7፥19 ማብ ይመ።

11፥4 *የምትሰሙትንና የምታዩትን ለዮሐንስ ንገሩት፤* የሉቃ7፥22 ማብ ይመ።

11፥5 *ለድኾችም የምሥራች እየተሰበከ ነው፤* የሉቃ7፥22 ማብ ይመ።

11፥6 *የማይሰናከልም፤* የሉቃ7፥23 ማብ ይመ።

11፥11 *ይበልጠዋል፤* መጥምቁ ዮሐንስ የነበረበት ዘመን የብሉይ ኪዳን መገባደጃና የክርስቶስ መምጫ ዋዜማ ነበር። በአዲስ ኪዳን ውስጥ "ከሁሉ የሚያንስ" የተባለው ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ሙሽራ የሆነችው፣ የቤተ ክርስቲያን አካል በመሆኑ (ኤፌ5፥25-27፡32)፣ የሙሽራው ሚዜ ከሆነው (ዮሐ3፥29) ከመጥምቁ ከዮሐንስ ይበልጣል። ሌላው አመለካከት ደግሞ "ከሁሉ የሚያንሰው" በሚለው ሐሳብ ላይ በማተኰር፣ የዚህ አባባል ትርጕም የሚገኘው በ 18፥4 ላይ፣ "እንደዚህ ሕፃን ራሱን ዝቅ የሚያደርግ" በሚለው ሐረግ ላይ ነው ይላል። እንደዚህ ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ሰው "የሚያንስ" ቢሆንም፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ከመጥምቁ ዮሐንስ እንደሚበልጥ ይቈጠራል።

11፥12 *የሚያገኟአትም ብርቱዎች ናቸው፤* ወደ መንግሥቱ ገብተው የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ይሆናሉ፤ ይህን ለማድረግም ምን ጊዜም የማያቋርጥ ስደት ስላለ፣ ጽኑ መንፈሳዊነትን፣ ጥንካሬን፣ ብርታትንና ቈራጥነትን ይጠይቃል።

11፥17 *ዋሽንት ነፋንላችሁ፤* በሰርግ ጊዜ እንደሚደረገው ዓይነት ማለት ነው። *ሙሾ አወረድንላችሁ፤* በቀብር ጊዜ እንደሚደረገው ማለት ነው። ይኸኛው ሐረግ የመጥምቁ ዮሐንስን አገልግሎት የሚያመለክት ሲሆን፣ የመጀመሪያው ሐረግ ("ዋሽንት ነፋንላችሁ") ደግሞ የኢየሱስን ያሳያል። አይሁድ፣

18ዮሐንስ ከመብልና ከመጠጥ ተቈጥቦ
በመምጣቱ፣ ‘ጋኔን አለበት’ ይሉታልና።
19የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ መጣ፤ እነር
ሱም፣ ‘በልቶ የማይጠግብ፣ ጠጪ እንዲሁም
የቀረጥ ሰብሳቢዎችና የኀጢአተኞች ወዳጅ’
አሉት። ጥበብ ግን በሥራዋ ጸደቀች።”

## ንስሓ ስላልገቡ ከተሞች የተነገረ ወዮታ

11፥21-23 ተጓ ምብ - ሉቃ 10፥13-15

20ከዚያም ኢየሱስ ብዙውን ታምራት
ያደረገባቸው ከተሞች ንስሓ ባለመግባታ
ቸው እንዲህ ሲል ወቀሳቸው፤ 21“ወዮልሽ
ኮራዚን፤ ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ፤ በእናንተ የተ
ደረገው ታምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርጎ
ቢሆን ኖሮ፣ ገና ድሮ ማቅ ለብሰው፣ ዐመድ
ነስንሰው ንስሓ በገቡ ነበር። 22ስለዚህ እላ
ችኋለሁ፤ በፍርድ ቀን ከእናንተ ይልቅ ለጢ
ሮስና ለሲዶና ቅጣቱ ይቀልላቸዋል። 23አን
ቺም ቅፍርናሆም ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ ማለት
ፈለግሽ? ነገር ግን ወደ ሲኦል ትወርጃ
ለሽ፤ በአንቺ የተደረገው ታምራት በሰዶም
ቢደረግ ኖሮ፣ እስከዛሬ በቆየች ነበር።
24ስለዚህ እልሻለሁ፤ በፍርድ ቀን ከአንቺ
ይልቅ ቅጣቱ ለሰዶም ይቀልላታል።”

## ክርስቶስ የሚሰጠው ዕረፍት

11፥25-27 ተጓ ምብ - ሉቃ 10፥21-22

25በዚያን ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ “የሰ
ማይና የምድር ጌታ አባት ሆይ፤ ይህንን
ከጥበበኞችና ከዐዋቂዎች ሰውረህ ለሕፃናት
ስለ ገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ፤ 26አዎን
አባት ሆይ፤ ይህ በፊትህ በጎ ፈቃድህ ሆኖ
ተገኝቶአልና።
27“ሁሉ ነገር ከአባቴ ተሰጥቶኛል፤ ከአብ
ሌላ ወልድን የሚያውቅ የለም፤ ከወልድና
ወልድ ራሱ ፈቅዶ ከሚገልጥላቸው ሌላ
አብን የሚያውቅ የለም።
28“እናንተ ሸክም የከበዳችሁና የደከማችሁ
ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም ዕረፍት እሰጣች
ኋለሁ። 29ቀንበሬን ተሸከሙ፤ ከእኔም ተማሩ፤
እኔ በልቤ የዋህና ትሑት ነኝና፤ ለነፍሳች
ሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ 30ቀንበሬ ልዝብ
ሸክሜም ቀላል ነውና።

## ሰንበትን ስለ ማክበር

12፥1-8 ተጓ ምብ - ማር 2፥23-28፤ ሉቃ 6፥1-5
12፥9-14 ተጓ ምብ - ማር 3፥1-6፤ ሉቃ 6፥6-11

12 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በሰንበት ቀን
በእህል ዕርሻ ውስጥ አለፈ፤ ደቀ
መዛሙርቱም ስለ ራባቸው እሸት ቀጥፈው
ይበሉ ጀመር። 2ፈሪሳውያንም ይህን አይ
ተው፣ “እነሆ፣ደቀ መዛሙርትህ በሰንበት ቀን
መደረግ የሌለበትን እያደረጉ ነው” አሉት።
3እርሱም እንዲህ አላቸው፤ “ዳዊትና አብ
ረውት የነበሩት ሰዎች በተራቡ ጊዜ እርሱ
ምን እንዳደረገ አላነበባችሁምን? 4ወደ እግ
ዚአብሔር ቤት ገባ፤ ለካህናት እንጂ ለእር
ሱም ሆነ አብረውት ለነበሩት ያልተፈቀደ
ውን የተቀደሰ ኅብስት በላ። 5ወይስ ካህ
ናት ሰንበትን ሽረው በቤተ መቅደስ ውስጥ
ሥራ ቢሠሩ በደል እንደማይሆንባቸው ከኦ
ሪት ሕግ አላነበባችሁም? 6ነገር ግን እላች
ኋለሁ፤ ከቤተ መቅደስ የሚበልጥ[*] በዚህ
አለ። 7‘ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን እወ
ዳለሁ’ የሚለው ቃል ምን ማለት እንደ ሆነ
ብታውቁ ኖሮ፣ በንጹሐን ላይ ባልፈረዳ
ችሁ ነበር። 8የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነውና።”
9ከዚያ ስፍራ ዕልፍ ብሎ በመሄድ ወደ
ምኵራባቸው ገባ፤ 10በዚያም አንድ እጁ ሽባ
የሆነ ሰው ነበር፤ ኢየሱስን ሊከሱት ምክንያት
ፈልገው፣ “በሰንበት ቀን መፈወስ ተፈቅዶ
አል?” ብለው ጠየቁት።
11እርሱም፣ “ከእናንተ መካከል የአንዱ ሰው
በግ በሰንበት ቀን ጕድጓድ ቢገባበት በጉን
ከገባበት ጕድጓድ ጎትቶ አያወጣውምን?
12ታዲያ ሰው ከበግ እጅግ አይበልጥምን?
ስለዚህ በሰንበት ቀን በጎ ማድረግ ተፈቅዶ

[*]6 ወይም አንድ ነገር፤ ቍ 41 እና 42 ይመ

11፥18 ማቴ3፥4፤ ሉቃ1፥15
11፥19 ማቴ9፥11
11፥21 ኢል3፥4፤ አሞ1፥9፤ዮና3፥5-9፤ ማቴ15፥21፤ማር3፥8፤ 6፥45፤8፥22፤ ሉቃ6፥17፤9፥10፤ዮሐ1፥44፤ 12፥21፤ሐሥ12፥20
11፥22 ቍ 24፤ ማቴ 10፥15
11፥23 ኢሳ14፥13-15፤ማቴ4፥13
11፥24 ማቴ10፥15
11፥25 ማቴ13፥11፥16፥17፤ሉቃ22፥42፤ 23፥34፤ዮሐ11፥41፤ 12፥27፡28፤ 1ቆሮ 1፥26-29
11፥27 ማቴ28፥18፤ ዮሐ3፥35፤10፥15፤ 17፥25፡26
11፥28 ዘፀ33፥14፤ ዮሐ7፥37
11፥29 መዝ116፥7፤ ኤር6፥16፤ዮሐ13፥15፤ፊል2፥5፤1ጴጥ2፥21፤ 1ዮሐ2፥6
11፥30 1ዮሐ5፥3
12፥1 ዘዳ23፥25
12፥2 ቍ 10፤ዘፀ 20፥10፤23፥12፤ዘዳ 5፥14፤ሉቃ13፥14፤ 14፥3፤ዮሐ5፥10፤7፥23፤9፥16
12፥3 1ሳሙ21፥6
12፥4 ዘሌ24፥5፡9
12፥5 ዘኍ28፥9፡10፤ ዮሐ7፥22፡23
12፥6 ቍ41፡42
12፥7 ሆሴ6፥6፤ሚክ 6፥6-8፤ማቴ9፥13
12፥8 ማቴ8፥20
12፥10 ቍ 2፤ማር 3፥2፤12፥13፤ሉቃ 11፥54፤14፥1፤20፥20
12፥11 ሉቃ14፥5
12፥12 ማቴ6፥26፤ 10፥31

በሁለቱም አጋጣሚዎች እንደ እንቢተኛ ልጅ ሆነዋል።

11፥19 *ጥበብ በሥራዋ ጸደቀች፤* እግዚአብሔር (ጥበብ) ዮሐንስንና ኢየሱስን ለተለያየ የአገልግሎት ሚና ልኳቸዋል፤ ይህም በኢየሱስ ታምራዊ ሥራዎች ተረጋግጦአል (ቍ20 ይመ)፤ የሉቃ 7፥35 ማብ ይመ።

11፥21 *ኮራዚን፤* ይህች ከተማ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰችው ሁለት ጊዜ ብቻ ሲሆን (በዚህ ቦታና በሉቃ 10፥13)፣ ምናልባትም ከቅፍርናሆም በስተ ሰሜን ሦስት ኪ.ሜ. ያህል ራቅ ብላ፣ በገሊላ ባሕር አጠገብ ትገኝ ነበር። *ቤተ ሳይዳ፤* በገሊላ ባሕር ሰሜን ምሥራቅ ዳርቻ ላይ ትገኝ ነበር። የአራተ ኛው ክፍል ገዥ የነበረው ፊልጶስ ቤተ ሳይዳን መልሶ ከገነባት በኋላ፣ በአውግስጦስ ቄሣር ሴት ልጅ በዮሊያና ስም “ዩሊያናስ” ብሎ ሰየማት። *ጢሮስና ሲዶና፤* ከፓሌስቲና በስተ ሰሜን፣ በፊ ንቄ ምድር ዳርቻ በሜድትራኒያን ባሕር ጠረፍ ላይ የነበሩ ከተ ሞች ናቸው።

11፥23 *ቅፍርናሆም፤* የሉቃ10፥15 ማብ ይመ።

12፥1 *በሰንበት፤* ሳምንታዊው ሰንበት የሳምንቱ ሰባተኛ ቀን ሲሆን፣ አይሁድ ከዕለት ተግባራቸው ተቈጥበው እንዲያር ፉና እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ በሙሴ ሕግ ልዩ ቀን ተደር ጎአል (ዘፀ20፥10፤ ዘዳ5፥14 ይመ)። ዛሬም ቢሆን ክርስቲያኖች በሳምንት ውስጥ አንድ ቀን በመለየት የዕረፍትና እግዚአብሔርን የማምለኪያ ዕለት አድርገው ለመቍጠር በቂ ምክንያት አላቸው ይኸውም (ሀ) ‘የተባረከ የዕረፍት ቀን’ የሚለው ሐሳብ የመጣው ሕ ግ ለአይሁድ ከመሰጠቱ በፊት ነበር (የዘፍ2፥3 ማብ ይመ፤ ከዘፀ 20፥11 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (ለ) ጌታ ኢየሱስ ስለ ዕረፍት ቀን የተሰጠ ውን መመሪያ በአጥል መልክ የሚጠቀሙትን የአይሁድ መሪዎችን እንጂ፣ በመሠረቱ ይህን መመሪያ አልተቃወመም (ቍ1-8፤ ሉቃ13፥10-17፤ 14፥1-6፤ ማር2፥27 እና ማብ ይመ)። (ሐ) የቀደመው ሰንበት እስራኤላውያን የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ መሆናቸውን እንደሚገልጽ ሁሉ (ዘፀ31፥16-17)፣ ክርስ ቲያኖች እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት ቀንም (እሑድ)፣ የክ ርስቶስ መሆናቸውንና እርሱም ጌታቸው መሆኑን ለዓለም የሚገ ልጹበት ዕለት ነው። *በእህል እርሻ፤* የስንዴ ወይም የገብስ ሊሆን ይችላል፤ ገብስ የድኾች ምግብ ነበር።

12፥3 *እርሱ ምን እንዳደረገ፤* የማር2፥25 ማብ ይመ።

12፥4 *የተቀደሰ ኅብስት፤* በየሰንበቱ 12 ትኩስ ዳቦ በቅድ ስት ውስጥ በጠረጴዛ ላይ ይቀመጥ ነበር (ዘፀ25፥30፤ ዘሌ24፥5-9)፤ ካህናቱም የሰነበተውን ዳቦ ይበሉ ነበር።

12፥5 *ሰንበትን ሽረው፤* መሥዋዕት ከማቅረብ ጋር የተያያዘ ሥራን በመሥራት ማለት ነው።

12፥8 *የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነውና፤* የሉቃ6፥5 ማብ ይመ።

12፥10 *ሰንበት ቀን መፈወስ፤* አንድ በሽተኛ እስከሚቀ ጥለው ቀን መቈየቱ የሚያሠጋ ካልሆነ በቀር፣ በሰንበት ቀን የፈ ውስ ተግባር እንዳይፈጸም የአይሁድ መምህራን ከልክለው ነበር።

እል" አላቸው።
13ከዚያም ሰውየውን፣ "እጅህን ዘርጋ"
አለው፤ ሰውየውም እጁን ዘረጋ፤ እንደ ሌላ
ኛውም እጁ ደህና ሆነለት። 14ፈሪሳውያን
ግን ከዚያ ወጣ ብለው ኢየሱስን እንዴት
እንደሚገድሉት ተማከሩ።

## እግዚአብሔር የመረጠው አገልጋይ

15ኢየሱስ ሐሳባቸውን አውቆ ከዚያ ዘወር
አለ። ብዙ ሕዝብም ተከተለው፤ ሕመምተ
ኞችን ሁሉ ፈወሰ፤ 16ማንነቱን ለማንም እን
ዳይናገሩ አዘዛቸው። 17ይህም የሆነው በነቢዩ
በኢሳይያስ እንዲህ ተብሎ የተነገረው ትን
ቢት ይፈጸም ዘንድ ነው፤

18"እነሆ የመረጥሁት፣
የምወደውና በእርሱ ደስ የሚለኝ
አገልጋዬ፣
መንፈሴን በእርሱ ላይ አኖራለሁ፤
እርሱም ለአሕዛብ ፍትሕን ያውጃል።
19አይጨቃጨቅም ወይም አይጮኽም፤
ድምፁም በአደባባይ አይሰማም።
20ፍትሕን ለድል እስኪያበቃ ድረስ፣
የተቀጠቀጠውን ሸምበቆ አይሰብርም፤
የሚጤሰውንም የጧፍ ክር አያጠፋም።
21አሕዛብ በስሙ ተስፋ ያደርጋሉ።"

## ኢየሱስ በአጋንንት ሥልጣን አጋንንትን ያወጣል መባሉ

12፥25-29 ተጓ ምብ - ማር 3፥23-27፤ ሉቃ 11፥17-22

22ከዚህ በኋላ በጋኔን ተይዞ ማየትና መና
ገር የማይችል ሰው ወደ እርሱ አመጡ፤
ኢየሱስም ፈወሰው፤ ሰውየውም ማየትና
መናገር ቻለ። 23ሕዝቡም ሁሉ ተደንቀው፣
"ይህ ሰው የዳዊት ልጅ ይሆንን?" አሉ።
24ነገር ግን ፈሪሳውያን ይህን በሰሙ ጊዜ፣
"ይህ ሰው አጋንንትን የሚያወጣው በአጋንንት
አለቃ በብዔልዜቡል ብቻ መሆን አለበት" አሉ።
25ኢየሱስም ሐሳባቸውን ዐውቆ እንዲህ
አላቸው፤ "እርስ በርሱ የተከፋፈለ መንግ
ሥት ሁሉ ይወድቃል፤ እርስ በርሱም የተ
ከፋፈለ ከተማ ወይም ቤት አይጸናም።
26ሰይጣንም ሰይጣንን የሚያስወጣ ከሆነ፣
እርስ በርሱ ተለያይቷል ማለት ነው፤ እን
ዲህ ከሆነ ደግሞ መንግሥቱ እንዴት ጸንቶ
ሊቆም ይችላል? 27እኔ አጋንንትን የማስወ
ጣው በብዔልዜቡል ከሆነ፣ ልጆቻችሁ በምን
ሊያስወጧቸው ነው? ስለዚህ ልጆቻችሁ ይፈ

12፥14 ዘፍ37፥18፤ መዝ71፥10፤ ማቴ 26፥4፤27፥1፤ ማር3፥6፤ ሉቃ6፥11፤ ዮሐ5፥18፤ 7፥1፤19፤11፥53
12፥15 ማቴ4፥23
12፥16 ማቴ8፥4
12፥17 ማቴ1፥22
12፥18 ማቴ3፥17፤ ዮሐ3፥34
12፥21 ኢሳ42፥1-4
12፥22 ማቴ4፥24
12፥23 ማቴ9፥27
12፥24 ማቴ9፥34፤ ማር3፥22
12፥25 ማቴ9፥4
12፥26 ማቴ4፥10
12፥27 ቍ 24፤ሐሥ 19፥13
12፥28 ማቴ3፥2
12፥30 ማር9፥40፤ ሉቃ11፥23
12፥31 ማር3፥28፡ 29፤ሉቃ12፥10
12፥32 ማር10፥30፤ ሉቃ20፥34፡35፤ኤፌ 1፥21፤ቲቶ2፥12፤ ዕብ6፥5
12፥33 ማቴ7፥16፡ 17፤ሉቃ6፥43፡44
12፥34 ማቴ3፥7፤ 15፥18፤23፥33፤ሉቃ 6፥45
12፥37 ኢዮ15፥6፤ ምሳ10፥14፤18፥21፤ ያዕ3፥2
12፥38 ማቴ16፥1፤ ማር8፥11፡12፤ሉቃ11 ፥16፤ዮሐ2፥11፡18፤4፥ 48፤6፥30፤1ቆሮ1፥22
12፥39 ማቴ16፥4፤ ሉቃ11፥29
12፥40 ማቴ8፥20፤ 16፥21

ርዱባችኋል። 28ነገር ግን እኔ አጋንንትን
የማስወጣው በእግዚአብሔር መንፈስ ከሆነ፣
የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ
መጥታለች።
29"ወይስ አንድ ሰው ወደ ኀይለኛ ሰው
ቤት ገብቶ ንብረቱን ለመዝረፍ ቢፈልግ፣
አስቀድሞ ያንን ኀይለኛ ሰው ሳያስር እን
ዴት አድርጎ ይሳካለታል?
30"ከእኔ ጋር ያልሆነ ሁሉ ይቃወመኛል፤
ከእኔም ጋር የማይሰበስብ ሁሉ ይበትናል።
31ስለዚህ እላችኋለሁ፤ ኀጢአት መሥራትና
የስድብ ቃል ሁሉ መናገር ለሰዎች ይቅር
ይባልላቸዋል፤ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ
ላይ የሚነገር የስድብ ቃል ይቅር አይባልም።
32ማንም ሰው በሰው ልጅ ላይ የሚናገረው
ክፉ ቃል ይቅር ይባላል፤ በመንፈስ ቅዱስ
ላይ የሚናገረው ክፉ ቃል ግን በዚህም ሆነ
በወዲያኛው ዓለም ይቅር አይባልም።
33"ዛፍ ሁሉ በፍሬው ስለሚታወቅ፣ መል
ካም ፍሬ እንድታገኙ መልካም ዛፍ ይኑራ
ችሁ፤ መጥፎ ዛፍ ቢኖራችሁ ግን መጥፎ
ፍሬ ታገኛላችሁ። 34እናንት የእፉኝት ልጆች፤
እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ መልካም ነገር
መናገር እንዴት ትችላላችሁ? በልብ ውስጥ
የሞላውን አንደበት ይናገረዋልና። 35መል
ካም ሰው በልቡ ካከማቸው መልካም ነገር
በጎ ነገር ያወጣል፤ ክፉ ሰውም በልቡ ካከማ
ቸው ክፉ ነገር መጥፎ ነገር ያወጣል።
36ነገር ግን እላችኋለሁ፤ ሰዎች ስለ ተናገሩት
ከንቱ ቃል ሁሉ በፍርድ ቀን ይጠየቁበ
ታል። 37ምክንያቱም ከቃልህ የተነሣ ትጸድ
ቃለህ፤ ከቃልህም የተነሣ ይፈረድብሃልና።

## ማረጋገጫ ምልክት ስለ መሻት

12፥39-42 ተጓ ምብ - ሉቃ 11፥29-32
12፥43-45 ተጓ ምብ - ሉቃ 11፥24-26

38ከዚያም አንዳንድ የአይሁድ ሃይማኖት
መምህራንና ፈሪሳውያን፣ "መምህር ሆይ፤ ከአንተ
ታምራዊ ምልክት ማየት እንፈልጋለን" አሉት።
39እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አላቸው፤
"ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክትን ይጠ
ይቃል፤ ነገር ግን ከነቢዩ ዮናስ ምልክት
በስተቀር ሌላ ምልክት አይሰጠውም።
40ዮናስ በዓሣ ዐንበሪ ሆድ ውስጥ ሦስት
ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ቈየ፣ እንዲሁ
የሰው ልጅ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት

12፥16 *ማንነቱን . . . እንዳይናገሩ፤* የ 8፥4 ማብ ይመ።
12፥18 *አገልጋዬ፤* ጌታ ኢየሱስ በዚህ ክፍልና በሐዋርያት ሥራ (ሐሥ3፥13፡26፤ 4፥27፡30) ላይ "አገልጋዬ" ተብሎ ተጠርቶአል (የማቴ3፥17 ማብ ይመ)።
12፥20፤ ኢየሱስ የተሰበረውን ልብ ይጠግናል፤ የፈረሰውንም ሕይወት ያድሳል (ቍ15፤ ዮሐ4፥4-42፤ 8፥3-11 ይመ)።
12፥23 *የዳዊት ልጅ፤* የ9፥27 ማብ ይመ።
12፥24 *ብዔል ዜቡል፤* የ 10፥25 ማብ ይመ።
12፥31 *በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚነገር የስድብ ቃል ... ይቅር አይባልም፤* የቍ24፡28፡32 ዐውድ እንደሚያሳየው፣ "ይቅርታ የሌለው ኀጢአት" የተባለው፣ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል የተሠራው እውነተኛው የክርስቶስ ታምር በሰይጣን ኀይል እንደ ተደረገ መቈጠሩ ነው (የማር3፥29 ማብ ይመ)።
12፥38 *ታምራዊ ምልክት፤* ኢየሱስ መሲሕ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ፣ ፈሪሳውያን በሰማይ ላይ በጕልሕ የሚታይ (ሉቃ11፥16) ታምር ለማየት ፈለጉ፤ ኢየሱስ ግን ከታሪክ ውስጥ ስለ አንድ "ምልክት" ጠቀሰላቸው።
12፥39 *አመንዝራ፤* እዚህ ላይ ይህ ቃል የሚያመለክተው መንፈሳዊ ባል ለሆነው (ለእግዚአብሔር) የእነርሱ ትውልድ ታማኝ ሆኖ አለመገኘቱን እንጂ፣ በሥጋ ማመንዘርን አይደለም።
12፥40 *ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት፤* በአይሁድ የቀን አቈጣጠር ቢያንስ የመጀመሪያውን ቀን በከፊልና የሦስተኛውን ቀን በከፊል መጨመር የተለመደ ነው። የሉቃ24፥46 ማብ ይመ። *በዓሣ ዐንበሪ፤* የግሪኩ ቃል የሚያመለክተው "ዓሣ አንበሪ" ሳይሆን፣ "በባሕር ውስጥ የሚገኝ ትልቅ ፍጡርን" ነው፤ ይህም እጅግ

በምድር ሆድ ውስጥ ይቈያል:: 41የነነዌ
ሰዎች በፍርድ ዕለት ከዚህ ትውልድ ጋር
ተነሥተው ይፈርዱበታል፤ እነርሱ በዮናስ
ስብከት ንስሓ ገብተዋልና:: እነሆ፤ ከዮናስ
የሚበልጥ እዚህ አለ:: 42በፍርድ ዕለት
የደቡብ ንግሥት ከዚህ ትውልድ ጋር ተነ
ሥታ ትፈርድበታለች፤ የሰሎሞንን ጥበብ
ለመስማት ከምድር ዳርቻ መጥታለችና::
እነሆ፤ ከሰሎሞን የሚበልጥ እዚህ አለ::
43"ርኩስ መንፈስ ከሰው ከወጣ በኋላ ዕረ
ፍት ለማግኘት ውሃ በሌለበት ደረቅ ቦታ
ይንከራተታል፤ የሚሻውን ዕረፍት ግን አያ
ገኝም:: 44ከዚያም፣ 'ወደ ነበርሁበት ቤት
ተመልሼ ልሂድ' ይላል፤ ሲመለስም ቤቱ
ባዶ ሆኖ፣ ጸድቶና ተዘጋጅቶ ያገኘዋል::
45ከዚያም ይሄድና ከራሱ የባሱ ሌሎች ሰባት
ክፉ መናፍስት ይዞ ይመጣል፤ እነርሱም
ሰውየው ውስጥ ገብተው ይኖራሉ:: የዚያም
ሰው የኋለኛው ሁኔታ ከፊተኛው የከፋ
ይሆናል:: በዚህ ክፉ ትውልድም ላይ እን
ዲሁ ይሆንበታል::"

## የኢየሱስ እናትና ወንድሞች

12፥46-50 ተጓ ምብ - ማር 3፥31-35፤ ሉቃ 8፥19-21

46ኢየሱስ ለሕዝቡ ሲናገር ሳለ፣ እናቱና
ወንድሞቹ ሊያነጋግሩት ፈልገው በውጭ
ቆመው ነበር:: 47አንድ ሰውም፣ "እነሆ፣
እናትህና ወንድሞችህ ሊያነጋግሩህ ፈልገው
በውጭ ቆመዋል" አለው::[o]
48ኢየሱስም፣ "እናቴ ማን ናት? ወንድሞ
ቼስ እነማን ናቸው?" ሲል መለሰለት:: 49በእ
ጁም ወደ ደቀ መዛሙርቱ እያመለከተ እን
ዲህ አለ፤ "እናቴና ወንድሞቼ እነዚህ ናቸው፤
50በሰማይ ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያ
ደርግ ሁሉ፣ ወንድሜ፣ እኅቴና እናቴም ነው::"

## የዘሪው ምሳሌ

13፥1-15 ተጓ ምብ - ማር 4፥1-12፤ ሉቃ 8፥4-10
13፥16፡17 ተጓ ምብ - ሉቃ 10፥23፡24
13፥18-23 ተጓ ምብ - ማር 4፥13-20፤ ሉቃ 8፥11-15

13 በዚያኑ ቀን ኢየሱስ ከቤት ወጥቶ
በባሕሩ ዳር አጠገብ ተቀመጠ::
2ብዙ ሕዝብም ስለ ከበበው በባሕሩ ዳር ትቶ
አቸው ጀልባ ላይ ወጥቶ ተቀመጠ:: 3ብዙ
ነገሮችን በምሳሌ እንዲህ ሲል ነገራቸው፤
"አንድ ገበሬ ዘር ሊዘራ ወጣ:: 4ሲዘራም
ሳለ፣ አንዳንዱ ዘር መንገድ ዳር ወደቀ፤
ወፎችም መጥተው ለቀሙት በሉት:: 5አን
ዳንዱ ዘር ዐፈሩ ስስ በሆነ፣ ድንጋያማ
መሬት ላይ ወደቀ፤ ዐፈሩ ስስ ስለ ሆነም
ፈጥኖ በቀለ:: 6ነገር ግን ፀሓይ ሲመ
ታው ጠወለገ፤ ሥር ባለመስደዱም ደረቀ::
7አንዳንዱም ዘር በእሾኽ መካከል ወደቀ፤
እሾኹም አደገና ቡቃያውን አንቆ አስ
ቀረው፤ 8ሌላው ዘር ደግሞ በጥሩ መሬት
ላይ ወደቀ፤ ፍሬም አፈራ፤ አንዱ መቶ፣
አንዱ ሥልሳ፣ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ::
9ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ!"::
10ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ
ቀርበው፣ "ለምን ለሕዝቡ በምሳሌ ትናገራ
ለህ?" አሉት::
11እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "ለእናንተ
የመንግሥተ ሰማይን ምስጢር ማወቅ ተሰ
ጥቶአችኋል፤ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም::
12ላለው ይጨመርለታል፤ ይበዛለትማል፤ ከሌ
ለው ግን ያ ያለው እንኳ ይወሰድበታል::
13ስለዚህ እንዲህ በማለት በምሳሌ የምነግራ
ቸው ለዚህ ነው፤

"እያዩ ስለማያዩ፣
እየሰሙ ስለማይሰሙ ወይንም
ስለማያስተውሉ ነው::

14እንዲህ ተብሎ የተነገረው የኢሳይያስ ትን
ቢት በእነርሱ ይፈጸማል፤

" 'መስማትንስ ትሰማላችሁ፤ ነገር ግን
አታስተውሉም፤
ማየትንም ታያላችሁ፤ ነገር ግን ልብ
አትሉም::
15የሕዝቡ ልብ ደንድኖአልና፤
ጆሮአቸውም አይሰማም፤
እንዳያዩም ዐይናቸውን ጨፍነዋል፤
ይህ ባይሆን ኖሮ፣ በዐይናቸው
አይተው፣
በጆሮአችው ሰምተው፣
በልባቸውም አስተውለው፣
ወደ እኔ በተመለሱና በፈወስኋቸው
ነበር::'

16የእናንተ ዐይኖች ስለሚያዩ፣ ጆሮዎቻ
ችሁም ስለሚሰሙ ግን የተባረኩ ናቸው::
17እውነት እላችኋለሁ፤ ብዙ ነቢያትና ብዙ
ጻድቃን እናንተ የምታዩትን ለማየትና የም

[o]47 አንዳንድ ትርጒሞች ይህን ጥቅስ ይዘላሉ

12፥41 ዮና1፥2፤3፥5
12፥42 1ነገ10፥1፤ 2ዜና9፥1
12፥45 2ጴጥ2፥20
12፥46 ማቴ1፥18፤ 2፥11፡13፡14፡20፤ 13፥55፤ሉቃ1፥43፤ 2፥33፡34፡48፡51፤ዮሐ 2፥1፡5፡12፤7፥3፡5፤ 19፥25፡26፤ሐሥ1፥14 ፤1ቆሮ9፥5፤ገላ1፥19
12፥50 ማቴ6፥10፤ ዮሐ15፥14
13፥1 ቍ36፤ማቴ 9፥28
13፥2 ሉቃ5፥3
13፥8 ዘፍ26፥12
13፥9 ማቴ11፥15
13፥11 ማቴ3፥2፤ 11፥25፤16፥17፤19፥ 11፤ዮሐ6፥65፤1ቆሮ 2፥10፡14፤ቈላ1፥27፤1 ዮሐ2፥20፡27
13፥12 ማቴ25፥29
13፥13 ዘዳ29፥4፤ ኤር5፥21፤ሕዝ12፥2
13፥14 ቍ35፤ ማቴ1፥22
13፥15 ኢሳ6፥9፡10፤ ዮሐ12፥40፤ሐሥ28፥ 26፡27፤ሮሜ11፥8
13፥16 ማቴ16፥17
13፥17 ዮሐ8፥56፤ ዕብ11፥13፤ 1ጴጥ10-12

ትልቅ ዓሣ ነበር ማለቱ ነው (የዮና1፥17 ማብ ይመ)::

12፥41-42 *ከዮናስ የሚበልጥ ... ከሰሎሞን የሚበልጥ፤* የሉቃ11፥31-32 ማብ ይመ::

12፥42 *የደቡብ ንግሥት፤* በ 1ነገ10፥1 "የሳባ ንግሥት" ተብላለች፤ ይህ አገር በዐረብ ምድር በስተ ደቡብ ምዕራብ የሚገኝ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ የመን ተብሎ ይታወቃል:: በእኛ በኢትዮጵያው ያን ዘንድ ግን ከዚሁ ከምድራችን እንደ ሄደች ይታመናል::

12፥43-45፤ የሉቃ11፥24 ማብ ይመ::

12፥46 *እናቱና ወንድሞቹ፤* የሉቃ8፥19 ማብ ይመ::

12፥50 *የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፤* የማር3፥34 ማብ ይመ::

13፥3-9፤ የዚህን የመጀመሪያውን ምሳሌ ትርጒም ለማወቅ ቍ18-23 ይመ::

13፥3 *በምሳሌ፤* ቃሉ በግሪክ ቋንቋ፣ "ፓራቦል" ሲሆን፣ "በአጠገብ ወይም በጎን ማስቀመጥን" ያሳያል፤ በመሆኑም ማነጻ ጸርን ወይም በምሳሌ ማስረዳትን ያመለክታል:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተለመደ አገባቡም፣ ኢየሱስ ከተፈጥሮና ከሰው ሕይወት አንዳንድ ክሥተቶችን በመውሰድ፣ ለገላጭ ታሪኮቹ መጠቀሙ ነው:: የማቴዎስ፣ የማርቆስና የሉቃስ ወንጌሎች ወደ 30 የሚደርሱ እንዲህ ያሉ ገላጭ ታሪኮች ሲኖሯቸው፣ የዮሐንስ ወንጌል ግን አንድም ምሳሌ አይጠቀምም፤ ይሁን እንጂ በሌሎች ዘይቤአዊ አነጋገሮች ይጠቀማል (የማር 4፥2፤ የሉቃ 8፥4 ማብ ይመ)::

13፥5 *ድንጋያማ መሬት፤* በጠጠር የተሸፈነ መሬት ላይ ሆነ፣ ጥልቀት በሌለው ስስ ዐፈር የተሸፈነ ጠንካራ ዐለት ነው::

*13፥13-14፤* ኢየሱስ በምሳሌ የተናገረው የሕዝቡ መንፈሳዊ ሕይወት የደነዘዘ በመሆኑ ነው (የሉቃ8፥4 ማብ ይመ)::

ትሰሙትንም ለመስማት ተመኝተው ነበር፤
ግን አልሆነላቸውም::
18“እንግዲህ የዘሪውን ምሳሌ ስሙ፤ 19የእ
ግዚአብሔርን መንግሥት ቃል ሰምቶ ከማ
ያስተውል ከማንኛውም ሰው ልብ ውስጥ
ክፉው መጥቶ የተዘራውን ዘር ይነጥቃል::
ይህ እንግዲህ በመንገድ ዳር የተዘራው ዘር
ነው:: 20በድንጋያማ መሬት ላይ የተዘራው፣
ቃሉን ሰምቶ ወዲያውኑ በደስታ የሚቀበለ
ውን ሰው ይመስላል:: 21ነገር ግን ሥር
መስደድ ባለመቻሉ ብዙ አይቈይም፤ በቃሉ
ምክንያት መከራ ወይም ስደት ሲመጣ ወዲ
ያውኑ ይሰናከላል:: 22በእሾኽ መካከል የተዘ
ራው ዘር ቃሉን ሰምቶ ለዚህ ዓለም በመ
ጨነቅና በብልጽግና ሐሳብ በመታለል ታንቆ
ያላፈራውን ሰው ይመስላል:: 23በጥሩ መሬት
ላይ የተዘራው ዘር ግን ቃሉን ሰምቶ
የሚያስተውለውን ሰው ይመስላል፤ በእርግ
ጥም ፍሬ ያፈራል፤ አንዱ መቶ፣ አንዱ
ሥልሳ፣ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ::”

## የእንክርዳዱ ምሳሌ

24ኢየሱስም ሌላ ምሳሌ እንዲህ ሲል ነገ
ራቸው፤ “መንግሥተ ሰማይ በዕርሻው ቦታ
ጥሩ ዘር የዘራን ሰው ትመስላለች:: 25ነገር
ግን ሰው ሁሉ ተኝቶ ሳለ፣ ጠላቱ መጥቶ
በስንዴው መካከል እንክርዳድ ዘርቶ ሄደ::
26ስንዴው በቅሎ ማፍራት ሲጀምር እንክር
ዳዱም አብሮ ብቅ አለ::
27“የዕርሻው ባለቤት አገልጋዮችም ወደ
እርሱ ቀርበው፣ ‘ጌታ ሆይ፤ በዕርሻህ ቦታ
ጥሩ ዘር ዘርተህ አልነበረምን? እንክርዳዱ
ከየት መጣ?’ አሉት::
28“እርሱም፣ ‘የጠላት ሥራ ነው’ አላቸው::
አገልጋዮቹም፣ ‘እንክርዳዱን ሄደን እንድ
ንነቅለው ትፈልጋለህ?’ ብለው ጠየቁት::
29“እርሱ ግን፣ ‘አይሆንም፤ ምክንያቱም
እንክርዳዱን እንነቅላለን ስትሉ ስንዴውንም
አብራችሁ ልትነቅሉ ትችላላችሁ፤ 30ተዉአ
ቸው፤ እስከ መከር ጊዜ አብረው ይደጉ::
በዚያን ጊዜ አጫጆቹን እንክርዳዱን አስቀ
ድማችሁ ንቀሉ፤ በእሳትም እንዲቃጠል
በየነዶው እሰሩት፤ ስንዴውን ግን ሰብስባችሁ

13፥19 ማቴ4፥23፤ 5፥37
13፥21 ማቴ11፥6፤ 26፥31
13፥22 ማቴ19፥23፤ 1ጢሞ6፥9:10:17
13፥23 ቍ8
13፥24 ቍ31:33: 45:47፤ማቴ18፥23፤ 20፥1፤22፥2፤25፥1፤ ማር4፥26:30
13፥30 ማቴ3፥12
13፥31 ቍ24፤ማቴ 17፥20፤ሉቃ17፥6
13፥32 መዝ104፥12 ሕዝ17፥23፤31፥6፤ ዳን4፥12
13፥33 ቍ24፤ ዘፍ 18፥6፤ገላ5፥9
13፥34 ዮሐ16፥25
13፥35 ቍ14፤ መዝ 78፥2፤ ማቴ1፥22፤ ሮሜ 16፥25:26፤ 1ቆሮ 2፥7፤ኤፌ3፥9፤ ቈላ 1፥26
13፥36 ማቴ15፥15
13፥37 ማቴ8፥20
13፥38 ዮሐ8፥44: 45፤1ዮሐ3፥10
13፥39 ኢዩ3፥13፤ ማቴ24፥3፤28፥20፤ ራእ14፥15

በጐተራዬ ክተቱ እላቸዋለሁ’ ” አላቸው::

## የሰናፍጭና የእርሾ ምሳሌ

13፥31-32 ተጓ ምብ - ማር 4፥30-32፤
13፥31-33 ተጓ ምብ - ሉቃ 13፥18-21

31ሌላ ምሳሌ እንዲህ ሲል ነገራቸው፤
“መንግሥተ ሰማይ አንድ ሰው ወስዶ በዕ
ርሻው ቦታ የዘራትን የሰናፍጭ ዘር ትመስ
ላለች:: 32የሰናፍጭ ዘር ከሌሎች ዘሮች
ሁሉ ያነሰች ብትሆንም፣ ስታድግ ግን
ከቊጥቋጦዎች ሁሉ በልጣ፣ የሰማይ ወፎች
መጥተው በቅርንጫፎቿ ላይ እስኪያርፉ
ድረስ ዛፍ ትሆናለች::”
33አሁንም ሌላ ምሳሌ እንዲህ ሲል ነገራ
ቸው፤ “መንግሥተ ሰማይ ሴት ወስዳ ሊጡ
በሙሉ እስኪቦካ ድረስ በሦስት መስፈሪያ*
ዱቄት ውስጥ በመደባለቅ የሸሸገችውን
እርሾ ትመስላለች::”
34ኢየሱስ ለሕዝቡ ይህን ሁሉ በምሳሌ
ተናገረ፤ ምሳሌም ሳይጠቀም የነገራቸው
አንድም ነገር አልነበረም:: 35በዚህም በነቢዩ
እንዲህ ተብሎ የተነገረው ተፈጸመ፤

“አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ፤
ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተሰወረውንም
እናገራለሁ::”

## የእንክርዳዱ ምሳሌ ትርጕም

36ከዚያም ሕዝቡን ትቶ ወደ ቤት ገባ::
ደቀ መዛሙርቱም ወደ እርሱ ቀርበው፣
“በዕርሻው ውስጥ ስላለው እንክርዳድ የተና
ገርኸውን ምሳሌ ትርጕም ንገረን” አሉት::
37እርሱም እንዲህ ሲል መለሰ፤ “ጥሩውን
ዘር የዘራው የሰው ልጅ ነው፤ 38ዕርሻውም
ይህ ዓለም ነው፤ ጥሩው ዘር የእግዚአብሔርን
መንግሥት ልጆች ያመለክታል፤ እንክርዳ
ዱም የክፉው ልጆች ናቸው፤ 39ዘርቶት የሄ
ደው ጠላትም ዲያብሎስ ነው፤ መከሩ የዓ
ለም መጨረሻ ሲሆን፣ አጫጆቹም መላእክት
ናቸው::
40“እንክርዳዱ ተነቅሎ በእሳት እንደሚ
ቃጠል ሁሉ በዓለም መጨረሻም እንዲሁ
ይሆናል:: 41የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል፤

*33 ምናልባት 22 ሊትር ያህል

*13፥24-25፤* የስንዴውና የእንክርዳዱ ምሳሌ አበክሮ የሚያሳየው የወንጌል አገልጋዮች ወንጌል ሲያሰራጩ፣ ሰይጣንም በበኩሉ በዚያው ቦታ የሐሰት ትምህርት እንደሚነዛ ነው:: “እርሻው” ዓለምን ሲወክል፣ “መልካሙ ዘርም” ለጌታ መንግሥት ታማኝ የሆኑትን አገልጋዮች ያመለክታል::

*13፥24-30፤* ለትርጕሙ ቍ 36-43 ይመ::

13፥24 ***መንግሥተ ሰማይ ... ትመስላለች፤*** ይህ ሐረግ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከተጠቀሱት ሰባት ምሳሌዎች ለስድስቱ (ከዘሪው ምሳሌ በቀር) መግቢያ ሆኖ ቀርቦአል::

13፥25 ***እንክርዳድ፤*** እንክርዳድ ገና በቡቃያነቱ ስንዴ ይመስላል፤ ውሉ አድሮ ግን ምንነቱ ተለይቶ ይታወቃል:: እርሻ የተባለችው ዓለም እንደ መሆኗ (ቍ 38)፣ ይህ ምሳሌ “እውነተኛ አማኝ ነኝ” በምትለዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን አማኞች ብቻ ሳይሆን፣ ከመንግሥተ ሰማያት ዜጎች ጋር ጎን ለጎን በዚህ ዓለም የሚኖሩትን የክፉውን ወገን ሁሉ የሚያመለክት ነው::

*13፥31-32፤* ይህ መንግሥት የጐላ ጅማሬ ያለው ባይመስልም፣ በመጨረሻ ግን በመላው ዓለም ይስፋፋል::

13፥32 *ያነሰች ... በልጣ፤* በዚያን ዘመን የሰናፍጭ ቅንጣት በፓሌስቲና ለነበሩ ገበሬዎች አነስተኛዋ ዘር ትባል እንጂ፣ በአሁኑ ዘመን ካለው ዘር ሁሉ የመጨረሻ አነስተኛ ዘር የምትባል አይደለችም፤ ሁኔታዎች ከተመቻቹላትም ተክሏ ሦስት ሜትር ያህል ወደ ላይ ልታድግ ትችላለች:: ***በቅርንጫፎቿ...ዛፍ፤*** መንግሥተ ሰማይ በዓለም ግዛት ሁሉ ላይ እንደምትስፋፋና የዓለም ሕዝቦች ሁሉ በእርሷ እፎይታ እንደሚያገኙ በተዘዋዋሪ ከዳን4፥21 ጋር በማዛመድ የቀረበ ይመስላል (ከዳን2፥35:44-45፤ 7፥27፤ ከራእ11፥15 ጋር ያነጻጽሩ)::

*13፥33፤* በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እርሾ ብዙውን ጊዜ የክፋት ወይም የርኵሰት ምሳሌ ሆኖ ይቀርባል (የማር8፥15 ማብ ይመ):: በዚህ ላይ ግን እርሾ ዕድገትን ያሳያል፤ እርሾ ወደ ሊጡ ዘልቆ እንደሚገባ፣ መንግሥተ ሰማይ ወደ ሰው ሕይወት ውስጥ ገብታ ትነግሣለች:: በሌላም በኩል፣ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል በመጠቀም በሰው ልብ ውስጥ የሚሠራውን የእግዚአብሔርን መንግሥት የማሳደግ ሥራ ሊያመለክት ይችላል::

እነርሱም ለኀጢአት ምክንያት የሆኑትንና
ክፉ የሚያደርጉትን ሁሉ ለቅመው ከመን
ግሥቱ ያወጣሉ:: 42ልቅሶና ጥርስ ማፋ
ጨት ወዳለበት ወደ እቶን እሳት ይጥሏቸ
ዋል:: 43በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው
መንግሥት እንደ ፀሐይ ያበራሉ:: ሰሚ
ጆሮ ያለው ይስማ::

### የተደበቀ ሀብትና የዕንቍው ምሳሌ

44"መንግሥተ ሰማይ በዕርሻ ውስጥ የተ
ደበቀ ሀብት ትመስላለች፤ አንድ ሰው ባገ
ኘት ጊዜ መልሶ ሸሸጋት፤ ከመደሰቱም የተ
ነሣ ሄዶ፤ ያለውን ሁሉ በመሸጥ ያንን የዕ
ርሻ ቦታ ገዛ::

45"እንዲሁም መንግሥተ ሰማይ ውብ
ዕንቍ የሚፈልግ ነጋዴ ትመስላለች፤ 46እጅግ
ውድ የሆነ ዕንቍ ባገኘም ጊዜ ሄዶ ያለውን
ሁሉ ሸጦ ገዛው::

### የመረቡ ምሳሌ

47"ደግሞም መንግሥተ ሰማይ ወደ ባሕር
ተጥሎ የዓሣ ዓይነቶችን የያዘ መረብ ትመ
ስላለች፤ 48ዓሣ አጥማጆቹ መረቡ ሲሞላላ
ቸው ጎትተው ወደ ባሕሩ ዳር አወጡት፤
ከዚያም ተቀምጠው ጥሩ ጥሩውን እየለዩ
በቅርጫት ውስጥ ጨመሩ፤ መጥፎ መጥ
ፎውን ግን ጣሉት:: 49በዓለም መጨረሻም
ልክ እንደዚሁ ይሆናል፤ መላእክት መጥ
ተው ኀጢአተኞችን ከጻድቃን በመለየት፣
50ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት ወደ
እቶን እሳት ይጥሏቸዋል::"

51ኢየሱስ፣ "ይህ ሁሉ ገብቷችኋል?" አላ
ቸው::

እነርሱም፣ "አዎን" አሉት::

52እርሱም፣ "ስለዚህም የመንግሥተ ሰማ
ይን ምስጢር የተረዳ ማንኛውም የኦሪት
ሕግ መምህር፣ ከከበረ ሀብቱ ክምችት አዲ
ሱንም አሮጌውንም የሚያወጣ ባለንብረት
ይመስላል" አላቸው::

13፥41 ማቴ8፥20፤
24፥31
13፥42 ማቴ8፥12
13፥43 ዳን12፥3፤
ማቴ11፥15
13፥44 ቍ24፤
ኢሳ 55፥1፤
ማቴ19፥21፤
ፊል 3፥7:8
13፥45 ቍ24
13፥47 ቍ24፤ማቴ
22፥10
13፥49 ማቴ25፥32
13፥50 ማቴ8፥12
13፥53 ማቴ7፥28
13፥54 ማቴ4፥23፤
7፥28
13፥55
ማቴ12፥46፤
ሉቃ3፥23፤ዮሐ6፥42
13፥57 ሉቃ4፥24፤
ዮሐ4፥44፤6፥61
14፥1 ማር8፥15፤
ሉቃ3፥1:19፤9፥7-7፤
13፥31፤23፥7:8፤
ሐሥ4፥27፤12፥1
14፥2 ማቴ3፥1
14፥3 ማቴ4፥12፤
11፥2፤ሉቃ3፥19:20
14፥4 ዘሌ18፥16፤
20፥21
14፥5 ማቴ11፥9

### በገዛ አገሩ ያልተከበረው ነቢይ

13፥54-58 ተጓ ምብ - ማር 6፥1-6

53ኢየሱስ እነዚህን ምሳሌዎች እንደ
ጨረሰ፣ ከዚያ ስፍራ ተነሥቶ ሄደ፤ 54ወደ
ገዛ አገሩ መጣ፤ በምኵራባቸውም ሕዝቡን
ያስተምር ጀመር:: እነርሱም በመገረም እን
ዲህ አሉ፤ "ይህ ሰው ይህን ጥበብና እነዚህን
ታምራት የማድረግ ኀይል ከየት አገኘ?
55ይህ የአናጺው ልጅ አይደለምን? የእናቱስ
ስም ማርያም አይደለምን? ወንድሞቹስ ያዕ
ቆብ፣ ዮሴፍ፣ ስምዖንና ይሁዳ አይደሉ
ምን? 56እኅቶቹስ ከእኛው ጋር አይደሉ
ምን? ታዲያ ይህ ሰው ይህን ሁሉ ከወዴት
አገኘው?" 57ስለዚህም ሳይቀበሉት ቀሩ::

ኢየሱስ ግን፣ "ነቢይ የማይከበረው በራሱ
አገርና በራሱ ቤት ነው እንጂ በሌላ ቦታ
ይከበራል" አላቸው:: 58ባለማመናቸውም ምክ
ንያት ብዙ ታምራትን በዚያ አላደረገም::

### የመጥምቁ ዮሐንስ መሞት

14፥1-12 ተጓ ምብ - ማር 6፥14-29

14 በዚያን ጊዜ የአራተኛው ክፍል
ገዥ የነበረው፣ ሄሮድስ ስለ ኢየሱስ
ዝና ሰማ፤ 2ባለሟሎቹንም፣ "እንዲህ ከሆነ
መጥምቁ ዮሐንስ ከሞት ተነሥቶ መጥቶአል
ማለት ነው፤ ይህ ሁሉ ድንቅ ታምራት በእ
ርሱ የሚደረገውም ለዚህ ነው" አላቸው::

3ቀደም ሲል ሄሮድስ፣ በወንድሙ በፊ
ልጶስ ሚስት በሄሮድያዳ ምክንያት ዮሐን
ስን አስይዞ ወህኒ አስገብቶት ነበር:: 4ምክን
ያቱም ዮሐንስ፣ "እርሷን እንድታገባ ሕግ
አይፈቅድልህም" ይለው ነበር:: 5ሄሮድስም
ዮሐንስን ሊገድለው ፈልጎ፣ ሕዝቡ እንደ
ነቢይ ይመለከተው ስለ ነበር ፈራ::

6ሄሮድስ የልደቱን ቀን ሲያከብር፣ የሄሮ
ድያዳ ልጅ በዘፈን ደስ ስላሰኘችው፣ 7የም
ትጠይቀውን ሁሉ ሊሰጣት በመሐላ ቃል
ገባላት:: 8ልጅቷም በእናቷ ተመክራ፣

*13፥44-45፤* እነዚህ ሁለት ምሳሌዎች የሚያስተምሩት አንድ እውነት ነው፤ መንግሥተ ሰማይ እጅግ የከበረ ዋጋ ስላላት፣ ያገኛት ዘንድ ማንም ያለውን ሁሉ ለመተው ፈቃደኛ ሊሆን ይገባዋል:: ኢየሱስ እንዲህ ማለቱ ግን መንግሥተ ሰማያት በገንዘብ ኀይል ወይም በመልካም ሥራ ትገኛለች ለማለት አይደለም::

13፥44 *በዕርሻ ውስጥ የተደበቀ፤* በጥንት ዘመን "ገንዘብ ለዋጮች" የሚባሉ እንጂ (ማቴ25፥27)፣ ባንክ ባለመኖሩ ገንዘብን በመሬት ውስጥ ደብቆ ማስቀመጥ የተለመደ ነበር::

*13፥47-51፤* የመረቡ ምሳሌ እንደ እንክርዳዱ ምሳሌ አንድ አጠቃላይ ትምህርት ያስተምራል፤ ይኸውም ጻድቃንና ክፉዎች በመጨረሻ የሚለዩበት ጊዜ መኖሩን የሚያሳይ ነው:: የእንክርዳዱ ምሳሌ በአሁኑ ዘመን የመለየቱን ተግባር እኛ መሞከር እንደማይገባንና ኀላፊነቱ ሙሉ በሙሉ የጌታ እንደ ሆነ ያሳያል (ቍ28-30፡ 41-42)::

13፥54 *ወደ ገዛ አገሩ፤* ናዝሬት ማለት ነው::

13፥55 *የአናጺው ልጅ፤* "አናጺ" ተብሎ የተተረጐመው የግሪኩ ቃል፣ "ድንጋይ ጠራቢ" ማለትም ይሆናል:: በዚህ ጊዜ ዮሴፍ በሕይወት ያለ አይመስልም::

13፥58 *ባለማመናቸውም፤* በማመንና በታምራት መካከል ስላለው ግንኙነት በተለይ በማቴዎስ ወንጌል ተገልጧል (ማቴ 8፥10:13፤ 9፥2:22:28-29)::

14፥1 *የአራተኛው ክፍል ገዥ፤* የአንድ አውራጃ አንድ-አራተኛ ክፍል ገዥ ማለት ነው:: የአራተኛው ክፍለ ገዥ ሄሮድስ (ሄሮድስ አንቲጳስ) ከታላቁ ሄሮድስ ብዙ ልጆች አንዱ ነበር:: ታላቁ ሄሮድስ በሞተ ጊዜ፣ ግዛቱ ለአራት ልጆቹ ተከፋፈለ:: ሄሮድስ አንቲጳስ ገሊላንና ፖርያን ይገዛ ነበር (ዓ.ቅ.ክ. 4-39):: ሉቃስ አዘውትሮ እንደ ጠቀሰው፣ ማቴዎስም እዚህ ላይ በትክክል የአራተኛው ክፍል ገዥ ይለዋል (ሉቃ3፥19፤ 9፥7፤ ሐሥ 13፥1):: በቍ9 ላይ ግን ማቴዎስ እንደ ማርቆስ "ንጉሥ" ይለዋል (ማር6፥14)፤ በገሊላና በሮም ሰዎች ዘንድ በይፋ ይታወቅ የነበረው ማዕረጉ ይኸው ነበርና::

14፥3 *በሄሮድያዳ፤* የታላቁ ሄሮድስ የልጅ ልጅ ናት:: በመ ጀመሪያ በሮም ይኖር የነበረውን አጎቷን ሄሮድስ ፊልጶስን አገ ባች (ታላቁ ሄሮድስ፣ ፊልጶስ የተባለ ሌላም ልጅ ነበረው):: ሄሮ ድስ አንቲጳስ በቤታቸው በእንግድነት ሳለ፣ ሄሮድያዳ ባሏን ትታ የእርሱ እንድትሆን አባብሎ አገባት:: በሙሴ ሕግ መሠረት አንድ ሰው ወንድሙ በሕይወት እያለ የወንድሙን ሚስት ማግ ባት የተከለከለ ነበር (ዘሌ18፥16):: *በፊልጶስ፤* ከታላቁ ሄሮድስና ከሊቀ ካህናቱ ከስምዖን ልጅ፣ ከማርያም የተወለደ ሲሆን፣ ለታ ላቁ ሄሮድስ ከማልታኬ ለተወለደው ለሄሮድስ አንቲጳስ በአባቱ በኩል ወንድሙ ነው::

14፥6 *የሄሮድያዳ ልጅ፤* ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን የተባለ ታሪክ ጸሓፊ እንደ ጻፈው ከሆነ የልጂቱ ስም ሰሎሜ ነበር:: በኋላም የሰሜኑ ክፍል ገዥ የነበረውን የታላቁን ሄሮድስ ልጅ፣ ሌላውን ፊልጶስ አገባች (ሉቃ3፥1):: በዚህ ጊዜ ሰሎሜ ለትዳር የደረሰች ወጣት ልጅ ነበረች፤ አዘፋፈኗና እንቅስቃሴዋ የፍትወት

“የመጥምቁ ዮሐንስን ራስ በሳሕን ላይ አድ
ርገህ አሁኑኑ ስጠኝ” አለችው:: 9በዚህ ጊዜ
ንጉሡ አዘነ፤ ይሁን እንጂ ስለ መሐላውና
ከእርሱ ጋር ስለነበሩ እንግዶች ሲል ጥያቄዋ
እንዲፈጸምላት አዘዘ:: 10ልኮም በወህኒ ውስጥ
እንዳለ የዮሐንስን ራስ አስቈረጠ:: 11የተቈ
ረጠውንም ራስ በሳሕን ላይ አድርገው ለል
ጅቱ ሰጧት፤ ልጅቱም ወስዳ ለእናቷ ሰጠች::
12የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትም አስከሬኑን
ወስደው ቀበሩት፤ ከዚያም ሄደው የሆነውን
ለኢየሱስ ነገሩት::

## ኢየሱስም አምስት ሺህ ሰዎችን በታምር መገበ

14፥13-21 ተጓ ምብ - ማር6፥32-44፤ሉቃ9፥10-17፤ዮሐ6፥1-13
14፥13-21 ማመ - ማቴ 15፥32-38

13ኢየሱስ የሆነውን ነገር በሰማ ጊዜ፣ ከነ
በረበት ተነሥቶ ወደ አንድ ገለልተኛ ስፍራ
በጀልባ ሄደ:: ሕዝቡም ይህን ሰምተው፣
ከየከተማው በእግር ተከተሉት:: 14ኢየሱስም
ከጀልባው ሲወርድ ብዙ ሕዝብ አይቶ ራራ
ላቸው፤ ሕመምተኞቻቸውንም ፈወሰላቸው::
15እየመሸ በመሄዱም ደቀ መዛሙርቱ
ወደ እርሱ ቀርበው፣ “ይህ ስፍራ ምንም የማ
ይገኝበት ምድረ በዳ ነው፤ ጊዜው እየመሸ
ስለሆነ፣ ወደ መንደሮች ሄደው የሚበሉት
ምግብ እንዲገዙ ሕዝቡን አሰናብት” አሉት::
16ኢየሱስ ግን፣ “መሄድ አያስፈልጋቸውም፤
የሚበሉትን እናንተ ስጧቸው” አላቸው::
17እነርሱም፣ “በዚህ ያለን አምስት እንጀ
ራና ሁለት ዓሣ ብቻ ነው” አሉት::
18እርሱም፣ “እስቲ ያለውን ወደ እኔ
አምጡት” አላቸው:: 19ከዚያም ሕዝቡ በሣሩ
ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ፤ አምስቱን እንጀራና
ሁለቱን ዓሣ ይዞ ዓይኑን ወደ ሰማይ በማ
ቅናት አመስግኖና ባርኮ እንጀራውን ቈረሰ፤
ለደቀ መዛሙርቱም ሰጠ፤ እነርሱም ለሕ
ዝቡ ሰጡ:: 20ሁሉም በልተው ጠገቡ፤ ከዚ
ያም ደቀ መዛሙርቱ የተረፈውን ቍርስራሽ
ዐሥራ ሁለት መሶብ ሙሉ አነሡ:: 21የበሉ
ትም ከሴቶችና ከሕፃናት ሌላ አምስት ሺህ
ወንዶች ያህሉ ነበር::

14፥10 ማቴ17፥12
14፥12 ሐሥ8፥2
14፥14 ማቴ4፥23፤ 9፥36
14፥17 ማቴ16፥9
14፥19 1ሳሙ9፥13፤ ማቴ26፥26፤ ማር8፥6፤ ሉቃ9፥16፤24፥30፤ ሐሥ2፥42፤20፥7:11፤ 27፥35፤1ቆሮ10፥16፤ 1ጢሞ4፥4

## ኢየሱስ በባሕር ላይ በእግሩ ሄደ

14፥22-33 ተጓ ምብ - ማር 6፥45-51፤ ዮሐ 6፥15-21፤
14፥34-36 ተጓ ምብ - ማር 6፥53-56

22ወዲያውኑ ደቀ መዛሙርቱ በጀልባ
ተሳፍረው ወደ ማዶ እንዲቀድሙት አዘዛ
ቸውና እርሱ ሕዝቡን ለማሰናበት ወደ ኋላ
ቀረት አለ:: 23ሕዝቡን ካሰናበተ በኋላም
ለመጸለይ ብቻውን ወደ ተራራ ወጣ፤ በጨ
ለመም ጊዜ ብቻውን በዚያው ነበር፤ 24በዚያ
ጊዜ ጀልባዋ ባሕሩን ዘልቃ* እየተንገዘች ሳለች
ነፋስ ተነሥቶ በማዕበል ትንገላታ ጀመር::
25ከሌሊቱ በአራተኛው ክፍል ኢየሱስ
በባሕሩ ላይ እየተራመደ ደቀ መዛሙርቱ
ወዳሉበት መጣ:: 26ደቀ መዛሙርቱም
በባሕሩ ላይ እየተራመደ ሲመጣ ባዩት ጊዜ
ፈሩ፤ እነርሱም፣ “ምትሀት ነው!” በማለት
በፍርሃት ጮኹ::
27ኢየሱስም ወዲያውኑ፣ “አይዞአችሁ፤ እኔ
ነኝ አትፍሩ” አላቸው::
28ጴጥሮስም፣ “ጌታ ሆይ፤ አንተ ከሆንህስ፣
በውሃው ላይ እየተራመድሁ ወደ አንተ እን
ድመጣ እዘዘኝ” አለው::
29እርሱም፣ “ና” አለው::
ጴጥሮስም፣ ከጀልባው ወርዶ በውሃው
እየተራመደ ወደ ኢየሱስ አመራ:: 30ነገር
ግን የነፋሱን ኀይል ባየ ጊዜ ፈራ፤ መስጠ
ምም ሲጀምር፣ “ጌታ ሆይ፤ አድነኝ!” ብሎ
ጮኸ::
31ኢየሱስም ወዲያውኑ እጁን ዘርግቶ ያዘ
ውና፣ “አንተ እምነት የጎደለህ፤ ለምን
ተጠራጠርህ?” አለው::
32ጴጥሮስና ኢየሱስ ጀልባው ላይ እንደ
ወጡ ነፋሱ ጸጥ አለ:: 33ከዚያም በጀልባው
ውስጥ የነበሩት፣ “በእውነት አንተ የእግዚ
አብሔር ልጅ ነህ” ብለው ሰገዱለት::

## ፈውስ በጌንሴሬጥ

34ባሕሩን ከተሻገሩ በኋላ ጌንሴሬጥ ወደ
ተባለ ቦታ ደረሱ:: 35ነዋሪዎቹም ኢየሱስ
መሆኑን ባወቁ ጊዜ፣ በዙሪያው ወዳለ አካ
ባቢ ሁሉ መልእክት ላኩ፤ የታመሙትን
ሁሉ ወደ እርሱ በማስመጣት፣ 36በሽተኞቹ
የልብሱን ጫፍ ብቻ ይነኩ ዘንድ እንዲፈቅ
ድላቸው ለመኑት፤ የነኩትም ሁሉ ተፈወሱ::

14፥23 ሉቃ3፥21
14፥26 ሉቃ24፥37
14፥27 ዳን10፥12፤ ማቴ9፥2፤17፥7፤ 28፥10፤ሉቃ1፥13:30 12፥10፤ሐሥ18፥9፤ 23፥11፤ራእ1፥17
14፥31 ማቴ6፥30
14፥33 መዝ2፥7፤ ማቴ4፥3
14፥36 ማቴ9፥20

*24 ግሪኩ *ብዙ ምዕራፍ* ይላል

ስሜት ቀስቃሽ እንደ ነበር ጥያቄ የለውም፤ ሄሮድስና እንግዶቹም በዚህ ደስ ተሰኝተዋል::

14፥13-21፤ ማር6፥32-44፤ ሉቃ9፥10-17፤ ዮሐ6፥1-13 እና ማብ ይመ::

14፥19 *እንጀራ ... ዓሣ፤* አምስት ሺህ ሕዝብ እንዲመገቡ የተደረገበት ታምር በአራቱም ወንጌሎች ተጽፎ ይገኛል (ማር 6፥34-44፤ ሉቃ9፥10-17፤ ዮሐ6፥1-14):: ታምሩ ለምን አስፈላጊ እንደ ሆነም ከሚከተሉት ዝርዝሮች መረዳት ይቻላል፡-

1) ኢየሱስ የሕይወት እንጀራ እንደ ሆነ ያመለክታል፤

2) ጌታ ታምር ሠሪ አምላክ እንደ ሆነ ያረጋግጣል፤

3) ኢየሱስ ለራብተኞች ርኅሩኅ መሆኑን የሚገልጽ አንድ ምሳሌ ነው (ቍ14 ይመ፤ ዘፀ34፥6፤ ከሚክ7፥18 ጋር ያነጻጽሩ)::

14፥21 *ከሴቶችና ከሕፃናት ሌላ፤* ይህን ገልጾ የጻፈው ማቴዎስ ብቻ ነው፤ የጻፈውም ሴቶችና ልጆች ከዐዋቂ ወንዶች ጋር በአደባባይ በማዕድ ላይ እንዲሳተፉ ለማይፈቅደው ለአይሁድ ኅብረተ ሰብ ነበር::

14፥25 *ከሌሊቱ በአራተኛው ክፍል፤* ከሌሊቱ 9:00 ሰዓት እስከ ንጋቱ 12:00 ሰዓት ማለት ነው:: በሮማውያን የሰዓት አቈጣጠር መሠረት የሌሊቱ ጊዜ ለአራት ተከፍሎ ነበር፡- 1) ከምሽቱ 12:00 እስከ ምሽቱ 3:00፤ 2) ከምሽቱ 3:00 ሰዓት እስከ እኩለ ሌሊት፤ 3) ከእኩለ ሌሊት እስከ ሌሊቱ 9 ሰዓት፤ 4) ከሌሊቱ 9:00 ሰዓት እስከ ንጋቱ 12:00 ሰዓት (የማር 13፥35 ማብ ይመ):: አይሁድ ግን የሌሊቱን ጊዜ ለሦስት ብቻ ይከፍሉታል፡- 1)ከፀሐይ መግቢያ እስከ ምሽቱ 4:00 ሰዓት፤ 2) ከምሽቱ 4:00 ሰዓት እስከ ሌሊቱ 8:00 ሰዓት፤ 3) ከሌሊት 8:00 ሰዓት እስከ ንጋት (መሳ7፥19፤ 1ሳሙ 11፥11 ይመ)::

14፥34 *ጌንሴሬጥ፤* ከገሊላ ባሕር በስተ ምዕራብ፣ ከማግደላ በስሜን ጫፍ በኩል የሚገኝ ርዝመቱ ከስድስት ኪ.ሜ. በላይና ስፋቱ ሦስት ኪ.ሜ. የሚያህል ጠባብ ሜዳ፣ ወይም በዚሁ በሜዳ ላይ የነበረ ከተማ ሊሆን ይችላል:: ሜዳውም ለምና በቂ ውሃ ያለው ስለ ነበር፣ “የፖለስቲና ገነት” ይባል ነበር::

## የፈሪሳውያን ወግ

15፥1-20 ተጓ ምብ - ማር 7፥1-23

15 ከዚያም ከኢየሩሳሌም የመጡ
ፈሪሳውያንና የኦሪት ሕግ መምህራን
ወደ ኢየሱስ ቀርበው፣ 2“ደቀ መዛሙርትህ
የአባቶችን ወግ የሚሽሩት ለምንድነው?
ምግብ ሲበሉኮ እጃቸውን አይታጠቡም”
አሉት።
3ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
“እናንተስ ለወጋችሁ ስትሉ የእግዚአብሔ
ርን ትእዛዝ ለምን ትሽራላችሁ? 4እግዚአ
ብሔር፣ ‘አባትህንና እናትህን አክብር፤ በአ
ባቱ ወይም በእናቱ ላይ ክፉ ቃል የሚና
ገር ይገደል’ ብሎ ሲያዝ፣ 5እናንተ ግን፣
ማንም ሰው አባቱን ወይም እናቱን፣ ‘ላደር
ግላችሁ የሚገባውን ማንኛውንም ነገር ለእ
ግዚአብሔር መባ አድርጌ አቅርቤአለሁ’
ቢላቸው፣ 6‘አንድ ሰው ይህን ካደረገ ዘንድ
አባቱን ወይም እናቱን አክብሮአል’ ትላላ
ችሁ። ስለዚህ ለወጋችሁ ብላችሁ የእግዚአ
ብሔርን ቃል ትሽራላችሁ። 7እናንተ ግብ
ዞች፤ ኢሳይያስ ስለ እናንተ እንዲህ ብሎ
በትንቢት የተናገረው ትክክል ነው፤

8‘ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፤
 ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው፤
9በከንቱ ያመልኩኛል፣
 ትምህርታቸውም የሰው ሥርዓት ነው።’”

10ሕዝቡን ወደ እርሱ ቀረብ እንዲሉ አድ
ርጎ እንዲህ አላቸው፤ “ስሙ አስተውሉም፤
11ሰውን የሚያረክሰው ከአፉ የሚወጣው
እንጂ ወደ አፉ የሚገባው አይደለም።”
12ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው፣ “ፈሪ
ሳውያን ያልኸውን ሰምተው እንደ ተቈጡ
አወቅህ?” አሉት።
13እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፤ “የሰማዩ
አባቴ ያልተከለው ተክል ሁሉ ይነቀላል።
14ተዉአቸው፣ እነርሱ ዕውሮችን የሚ
መሩ ዕውር መሪዎች ናቸው፤ ዕውር ዕውርን
ቢመራ ሁለቱም ተያይዘው ገደል ይገባሉ።”
15ጴጥሮስም፣ “ምሳሌውን አስረዳን” አለው።
16እርሱም እንዲህ አላቸው፤ “እናንተም
እስካሁን አላስተዋላችሁም ማለት ነውን?
17በአፍ የሚገባ ሁሉ ወደ ሆድ ዘልቆ፣ ከዚ
ያም ወደ ውጪ እንደሚወጣ አታውቁ
ምን? 18ከአፍ የሚወጣ ግን ከልብ ይመነ
ጫል፤ ሰውንም የሚያረክሰው ይህ ነው፤
19ክፉ ሐሳብ፣ ነፍስ ምግደል፣ ማመንዘር፣
ዝሙት፣ መስረቅ፣ በሐሰት መመስከርና
ስም ማጥፋት ከልብ ይመነጫልና። 20ሰውን
የሚያረክሱ እነዚህ ናቸው እንጂ እጅን
ሳይታጠቡ መብላት ሰውን አያረክስም።”

## የከነዓናዊቷ ሴት እምነት

15፥21-28 ተጓ ምብ - ማር 7፥24-30

21ኢየሱስም ከዚያ ወጥቶ ወደ ጢሮስና
ወደ ሲዶና አገር ሄደ። 22አንዲት ከነዓና
ዊት ሴት ከዚያ አካባቢ በመውጣት ወደ
ኢየሱስ መጥታ፣ “ጌታ ሆይ፤ የዳዊት ልጅ፤
ራራልኝ፤ ልጄ በርኩስ መንፈስ ተይዛ በጣም
ትሠቃያለች” ብላ ጮኸች።
23እርሱ ግን አንድም ቃል አልመለሰላ
ትም፤ በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ
እርሱ ቀርበው፣ “እየተከተለችን ትጮኻለ
ችና ብታሰናብታትስ?” ብለው ጠየቁት።
24እርሱም፣ “የተላክሁት ከእስራኤል ቤት
ሆነው ወደ ጠፉት በጎች ብቻ ነው” አለ።
25ሴትዮዋም እግሩ ላይ ወድቃ፣ “ጌታ
ሆይ፤ ርዳኝ” አለች።
26እርሱም መልሶ፣ “የልጆችን እንጀራ
ወስዶ ለውሾች መወርወር አይገባም” አላት።
27እርሷም፣ “አዎን ጌታ ሆይ፤ ውሾችም
እኮ ከጌታቸው ማዕድ የወዳደቀውን ፍርፋሪ
ይበላሉ” አለችው።
28በዚህ ጊዜ ኢየሱስ፣ “አንቺ ሴት እምነ
ትሽ ታላቅ ነው፤እንደ ፈለግሽው ይሁንልሽ”
አላት። ልጇም ከዚያ ሰዓት ጀምሮ ተፈ
ወሰች።
29ኢየሱስ ከዚያ ተነሥቶ በገሊላ ባሕር
አጠገብ ወዳለው ስፍራ በመሄድ ወደ ተራራ
ወጥቶ ተቀመጠ። 30ቍጥሩ ብዙ የሆነ ሕዝ
ብም አንካሶችን፣ ዐይነ ስውሮችን፣ ሽባዎ
ችን፣ ዲዳዎችን እንዲሁም ሌሎች ብዙዎ
ችን ሕመምተኞች ይዘው ወደ እርሱ በማ
ምጣት በእግሩ ሥር አስቀመጧቸው፤ እር
ሱም ፈወሳቸው። 31ሕዝቡም ዲዳው ሲናገር፣
ሽባው ደህና ሲሆን፣ አንካሳው ቀጥ ብሎ
ሲሄድ፣ ዐይነ ስውሩም ሲያይ ተመልክተው
ተደነቁ፤ የእስራኤልንም አምላክ አመሰገኑ።

## ኢየሱስ አራት ሺህ ሰዎች በታምር መገበ

15፥29-31 ተጓ ምብ - ማር 7፥31-37
15፥32-39 ተጓ ምብ - ማር 8፥1-10
15፥32-39 ማመ - ማቴ 14፥13-21

32ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ፣ “ሕዝቡ

15፥2 ሉቃ11፥38
15፥4 ዘፀ20፥12፤ 21፥17፤ዘሌ20፥9፤ ዘዳ5፥16፤ኤፌ6፥2
15፥9 ኢሳ29፥13፤ ሚል2፥2፤ቈላ2፥ 20-22
15፥11 ቍ18፤ ሐሥ 10፥14:15
15፥13 ኢሳ60፥21፤ 61፥3
15፥14 ማቴ23፥16: 24፤ሉቃ6፥39፤ሮሜ 2፥19
15፥15 ማቴ13፥36
15፥16 ማቴ16፥9
15፥18 ማቴ12፥34 ፤ሉቃ6፥45፤ያዕ3፥6
15፥19 ገላ5፥19-21
15፥20 ሮሜ14፥14
15፥21 ማቴ11፥21
15፥22 ማቴ4፥24፤ 9፥27
15፥24 ማቴ10፥6: 23፤ሮሜ15፥8
15፥25 ማቴ8፥2
15፥28 ማቴ9፥22
15፥30 ማቴ4፥23
15፥31 ማቴ9፥8
15፥32 ማቴ9፥36

15፥2 *የአባቶችን ወግ፤* ከባቢሎን ምርኮ በኋላ፣ የአይሁድ መምህራን የሕዝቡን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚቈጣጠሩበት ከጅማት የከረሩ ደንቦችንና ሕጎችን አወጡ። እነዚህ ድንጋጌዎችም የሙሴ ሕግ እንዴት በሥራ ላይ እንደሚውል የሚያብራሩና ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ የኖሩ ናቸው። ኢየሱስ በምድር ላይ በአካለ ሥጋ በነበረበት ዘመን እነዚህ “የአባቶች ወግ” የተባሉት በአፈ-ታሪክ ብቻ የሚነገሩ ነበሩ። ነገር ግን በ200 ዓ.ም ገደማ እነዚህን “የአባቶች ወግ” በመባል የታወቁትን የቃል ትምህርቶች ተጽፈውና በአንድ ላይ ተጠርዘው በአይሁድ ዘንድ “ምሽናህ” የሚል መጠሪያ ተሰጣቸው። *አይታጠቡም፤* ማር 7፥1-4 ይመ።

*15፥5-6፤* የማር7፥11:13 ማብ ይመ።

*15፥7-20፤* ማር7፥6-23 እና ማብ ይመ።

15፥26 *የልጆችን፤* “ከእስራኤል ቤት ... የጠፉት በጎች” (ቍ24) የተባሉት ናቸው። *ለውሾች፤* የግሪኩ “ቡችሎች” ይላል። በዚህም መሠረት፣ ኢየሱስ የተናገረው ሐሳብ ወንጌል አስቀድሞ ለአይሁድ መድረስ እንዳለበት ያመለክታል። ሴትዮዋም ኢየሱስ ምን ማለቱ እንደ ሆነ ስለ ገባት “ፍርፋሪውን” እንኳ ለማግኘት ፈቃደኛ ነበረች። ኢየሱስም እምነቷን አይቶ የለመነችውን ፈጸመላት (ቍ28)።

15፥28 *እምነትሽ ታላቅ ነው፤* በእውነተኛ እምነት መጽናት ማለት በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ በእግዚአብሔር መታመንና ለእርሱ ታማኝ ሆኖ መገኘት ነው (ሉቃ18፥1-7፤ 1ጴጥ1፥7)።

*15፥29-39፤* ማር 7፥31-8፥10 እና ማብ ይመ።

ከእኔ ጋር ሦስት ቀን ስለ ሆናቸውና የሚበ
ሉት ስለሌላቸው አዝንላቸዋለሁ፤ በመን
ገድ ላይ በራብ ዝለው እንዳይወድቁ ጦማ
ቸውን ልሰዳቸው አልፈቅድም” አለ።
33ደቀ መዛሙርቱም፣ “በዚህ ምንም በሌ
ለበት ምድረ በዳ ይህንን ሁሉ ሕዝብ ለማ
ብላት በቂ እንጀራ ከየት እናገኛለን?” በማ
ለት መለሱለት።
34ኢየሱስም፣ “ለመሆኑ ስንት እንጀራ
አላችሁ?” ሲል ጠየቀ።
እነርሱም፣ “ሰባት እንጀራና ጥቂት ትና
ንሽ ዓሣ” አሉት።
35እርሱም ሕዝቡን መሬት ላይ እንዲቀ
መጡ አዘዛቸው፤ 36ሰባቱን እንጀራና ዓሣውን
ይዞ ካመሰገነ በኋላ ቈርሶ ለደቀ መዛሙ
ርቱ ሰጣቸው፤ እነርሱም ለሕዝቡ አከፋ
ፈሉ። 37ሁሉም በልተው ጠገቡ፤ ደቀ መዛ
ሙርቱም የተረፈውን ቍርስራሽ ሰባት
መሶብ ሙሉ አነሡ። 38የበሉትም ከሴቶችና
ከሕፃናት ሌላ አራት ሺህ ወንዶች ነበሩ።
39ኢየሱስ ሕዝቡን ካሰናበተ በኋላ በጀልባ
ወደ መጌዶል ሄደ።

## ኢየሱስ ከሰማይ ምልክት እንዲያሳይ መጠየቁ

16፥1-12 ተጓ ምብ - ማር 8፥11-21

16 ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ወደ ኢየ
ሱስ ቀርበው ሊፈትኑት በመሻት
ከሰማይ ምልክት እንዲያሳያቸው ጠየቁት።
2እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፦['] “ምሽት
ላይ፣ ‘ሰማዩ ስለ ቀላ ብራ ይሆናል’ ትላላችሁ፤
3ንጋት ላይም፣ ‘ሰማዩ ቀልቶአል፣ ከብዶአ
ልም፤ ስለዚህ ዝናብ ይዘንባል’ ትላላችሁ።
የሰማዩን ገጽታ ትለያላችሁ፤ ነገር ግን የዘ
መኑን ምልክት መለየት አትችሉም።
4ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይፈ
ልጋል፤ ነገር ግን ከዮናስ ምልክት በስተቀር
ሌላ ምልክት አይሰጠውም።” ከዚያም ኢየ
ሱስ ትቶአቸው ሄደ።

## የፈሪሳውያንና የሰዱቃውያን እርሾ

5ባሕሩን እንደ ተሻገሩም፣ ደቀ መዛሙ
ርቱ እንጀራ መያዝ ረስተው ነበር። 6ኢየ
ሱስም፣ “ልብ በሉ፤ ከፈሪሳውያንና ከሰ
ዱቃውያን እርሾ ተጠበቁ” አላቸው።
7እነርሱ ግን እርስ በርሳቸው፣ “እንጀራ
ስላልያዝን ይሆናል” ተባባሉ።
8ኢየሱስም ሐሳባቸውን አውቆ እንዲህ አላ
ቸው፤ “እናንተ እምነት የጐደላችሁ፣ እርስ
በርሳችሁ እንጀራ ስለ አለመያዛችሁ ለምን
ትነጋገራላችሁ? 9አምስቱ እንጀራ ለአምስት
ሺህ ሰው በቅቶ ስንት መሶብ ተርፎ እንዳነ
ሣችሁ አታስተውሉምን? 10እንዲሁም ሰባቱ
እንጀራ ለአራት ሺህ ሰው በቅቶ ስንት
መሶብ ተርፎ እንዳነሣችሁ ልብ አላላችሁም
ማለት ነውን? 11ታዲያ የነገርኋችሁ ስለ እን
ጀራ እንዳልሆነ እንዴት አታስተውሉም?
አሁንም ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ
ተጠንቀቁ።” 12በዚህ ጊዜ ያስጠነቀቃቸው
እንጀራ ውስጥ ስለሚጨመረው እርሾ ሳይ
ሆን፣ ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ትምህ
ርት መሆኑ ገባቸው።

## ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ማንነት መናገሩ

16፥13-16 ተጓ ምብ - ማር 8፥27-29፤ ሉቃ 9፥18-20

13ኢየሱስ ፊልጶስ ቂሣርያ ወደተባለው
አገር በደረሰ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን፣
“ለመሆኑ ሰዎች፣ የሰውን ልጅ ማን ነው
ይላሉ?” ብሎ ጠየቃቸው።
14እነርሱም፣ “አንዳንዶቹ መጥምቁ ዮሐ
ንስ፣ ሌሎች ኤልያስ፣ ሌሎች ደግሞ ኤር
ምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ”
አሉት።
15እርሱም፣ “እናንተስ እኔን ማን ትሉኛላ
ችሁ?” አላቸው።
16ስምዖን ጴጥሮስም፣ “አንተ ክርስቶስ[*]
የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ” በማለት
መለሰ።

## ኢየሱስ ስለሚደርስበት መከራ ተናገረ

16፥21-28 ተጓ ምብ - ማር 8፥31- 9፥1፤ ሉቃ 9፥22-27

17ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ “የዮና ልጅ
ስምዖን ሆይ፣ ብፁዕ ነህ፤ ይህን የገለጠልህ
በሰማይ ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም
አይደለም። 18አንተ ጴጥሮስ[z] ነህ፤ በዚህ
ዐለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገ

15፥36 ማቴ14፥19
15፥37 ማቴ16፥10
16፥1 ማቴ12፥38፤ ሐሥ4፥1
16፥3 ሉቃ12፥54-56
16፥4 ማቴ12፥39
16፥6 ሉቃ12፥1
16፥8 ማቴ6፥30
16፥9 ማቴ14፥17-21
16፥10 ማቴ15፥34-38
16፥12 ሐሥ4፥1
16፥14 ማቴ3፥1፤ ማር6፥15፤ዮሐ21
16፥16 መዝ42፥2፤ ኤር10፥10፤ማቴ4፥3፤ ሐሥ14፥15፤2ቆሮ 6፥16፤1ተሰ1፥9፤ 1ጢሞ3፥15፤ዕብ 10፥31፤12፥22
16፥17 ማቴ13፥11 ፤1ቆሮ15፥50፤ኤፌ 6፥12፤ዕብ2፥14
16፥18 ዮሐ1፥42፤ ኤፌ2፥20

['] 2 አንዳንድ የጥንት ቅጆች የቍጥር 2 ከፊልና ቍጥር 3 በሙሉ የላቸውም
[*] 16 ወይም መሲሕ፤ ቍ 20 ይመ
[z] 18 ጴጥሮስ ትርጕሙ ዐለት ማለት ነው
[t] 18 ወይም ሊቋቋሟት አይችሉም

*15፥37፤* ስለ 5000 ሰዎች መመገብ በአራቱም ወንጌላት ተጽፎ እናገኛለን፤ ሆኖም ስለ 4000 ሕዝብ መመገብ የዘገቡት ማቴዎስና ማርቆስ ብቻ ናቸው። 5000 ሕዝብ በተመገበ ጊዜ የተጠቀሱት ዐሥራ ሁለቱ መሶቦች የዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት የምሳ መያዣ ዕቃ ሊሆኑ ይችላሉ። እዚህ ላይ የተጠቀሱት ሰባቱ መሶቦች ምናልባት መጠናቸው ከእነዚያ ላቅ ያለ ሊሆን ይችላል።

15፥39 *መጌዶል፤* የመግደላዊት ማርያም አገር ሲሆን፣ “መግደላ” ተብሎም ይጠራል። ይኸውም በማርቆስ ወንጌል “ዳልማኑታ” ተብሎአል (ማር8፥10)።

16፥4 *ከዮናስ ምልክት፤* 12፥39-40 እና የሉቃ11፥30 ማብ ይመ።

16፥6 *ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ፤* ቍ12 ይመ። እዚህ ላይ “እርሾ” የክፋትና የብልሽት ምሳሌ ሲሆን፣ የፈሪሳውያንንና የሰዱቃውያንን ትምህርት የሚመለከት ነው። ክርስቶስ የእነርሱን ትምህርት “እርሾ” ያለበት ምክንያት፣ ግምት ውስጥ አይገባም የተባለ ትንሽ ነገር እንኳ ሥር ሰድዶ፣ በብዙዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በማሳደር ስሕተት የሆነ ነገር እንኳ እንዲታመን ስለሚያደርግ ነው።

*16፥12፤* ማቴዎስ ብዙ ጊዜ ኢየሱስ የተናገረውን ቃል በመተርጐም ያብራራል (ከ17፥13 ጋር ያነጻጽሩ)።

16፥13 *ፊልጶስ ቂሣርያ፤* ይህች ከተማ ታላቁ ሄሮድስ በሚድትራኒያን ባሕር ዳርቻ ከቈረቈራት ቂሣርያ ከተባለች ውብ ከተማ የምትለይ ናት። ይህችኛዋ ፊልጶስ ቂሣርያ የተባ ለችው፣ በሄሮድስ ልጅ በፊልጶስ እንደ ገና ታንጻ በራሱ በጢባርዮስ ቄሣር ስም የሰየማት ሳትሆን፣ ከገሊላ ባሕር በስተ ሰሜን ከሔርሞን ተራራ ተዳፋት ሥር ነበረች። ጥንት ግን “ፓኒያስ” ተብላ ትጠራ ነበር፤ ይህ የጥንት ስሟም ዛሬ “በናያስ” በሚል ይታወቃል፤ ስሙም የመጣው “ፓን” ከተባለ የግሪክ ባዕድ አምላክ ስም ሲሆን፣ ቤተ ጣዖቱም በዚሁ ቦታ ቆሞ ነበር። ይህ ቦታ በተለይ የአረማውያን አካባቢ ነበር።

16፥18 *ጴጥሮስ ... ዐለት ... ቤተ ክርስቲያን፤* “ጴጥሮስ”

ሃነም ደጆችም አያሸንፏትም::[ን] 19የመንግ
ሥተ ሰማይን መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤
በምድር ያሰርኸው ሁሉ በሰማይ የታሰረ
ይሆናል፤ በምድርም የፈታኸው ሁሉ በሰ
ማይ የተፈታ ይሆናል::" 20ቀጥሎም እርሱ
ክርስቶስ መሆኑን ለማንም እንዳይናገሩ ደቀ
መዛሙርቱን አስጠነቀቃቸው::
21ኢየሱስ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ወደ ኢየሩሳ
ሌም ይሄድ ዘንድ፣ በዚያም በሽማግሌ
ዎች፣ በካህናት አለቆችና በኦሪት ሕግ
መምህራን እጅ መከራን ይቀበልና ይገደል
ዘንድ፣ በሦስተኛው ቀን ከሞት ይነሣ ዘንድ
እንደሚገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገል
ጽላቸው ጀመር::

## ኢየሱስ ስለሚደርስበት መከራ ለሁለተኛ ጊዜ ተናገረ

22ጴጥሮስም ኢየሱስን ወደ ጐን ሳብ አድ
ርጎ፣ "ጌታ ሆይ፤ እንዲህ ያለ ነገር ፈጽሞ
አይድረስብህ" እያለ ይገሥጸው ጀመር::
23ኢየሱስም ወደ ጴጥሮስ ዘወር ብሎ፣
"አንተ ሰይጣን፣ ሂድ ከዚህ! የሰው እንጂ
የእግዚአብሔር ነገር በሐሳብህ ስለ ሌለ
መሰናከል ሆንህብኛል!" አለው::

16፥19 ኢሳ22፥22፤ ማቴ18፥18፤ዮሐ20፥23፤ራእ3፥7
16፥20 ማር8፥30
16፥21 መዝ22፥6፤ ኢሳ53፥3፤ሆሴ6፥2፤ ማቴ12፥40፤17፥22፡23፤26፥67፡68፤27፥1፡2፡63፤ማር9፥31፤10፥34፤ሉቃ9፥22፡51፤17፥25፤18፥31-33፤24፥6፡7፡21፡46፤ዮሐ2፥19፤18፥22፡23፤19፥3፤ ሐሥ2፥23፤3፥13፤ 1ቆሮ15፥3፡4
16፥23 ማቴ4፥10
16፥24ማቴ10፥38፤ ሉቃ14፥27
16፥25 ዮሐ12፥25
16፥27 2ዜና6፥23፤ ኢዮ34፥11፤መዝ62፥12፤ኤር17፥10፤ሕዝ18፥20፤ማቴ8፥20፤ ሉቃ17፥30፤ ዮሐ14፥3፤ ሐሥ1፥11፤ 1ቆሮ 1፥7፤3፥12-15፤ 2ቆሮ 5፥10፤ 1ተሰ2፥19፤ 4፥16፤ ራእ1፥7፤22፥7፡12፡20
17፥1 ማቴ4፥21

24ከዚያም ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እን
ዲህ አላቸው፤ "ሊከተለኝ የሚወድ ራሱን
ይካድ፣ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ፤
25ነፍሱን[ም] ሊያድን የሚፈልግ ሁሉ ያጠፋ
ታል፤ ነገር ግን ነፍሱን ስለ እኔ የሚያጠ
ፋት ያድናታል:: 26ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያ
ተርፍ፣ ነፍሱን ግን ቢያጣ ምን ይጠቅ
መዋል? ወይስ ሰው በነፍሱ ምትክ ሊከ
ፍለው የሚችለው ዋጋ ምንድን ነው?
27የሰው ልጅ በአባቱ ክብር ከመላእክት ጋር
ይመጣል፤ ለእያንዳንዱም ሰው እንደ ሥራው
ዋጋውን ይከፍለዋል:: 28እውነት እላችኋለሁ፣
እዚህ ከቆሙት ሰዎች መካከል የሰው ልጅ
በመንግሥቱ ሲመጣ እስከሚያዩ ድረስ
ሞትን የማይቀምሱ አሉ::"

## የኢየሱስ መልክ በቅጽበት መቀየር

17፥1-8 ተጓ ምብ - ሉቃ 9፥28-36
17፥1-13 ተጓ ምብ - ማር 9፥2-13

**17** ከስድስት ቀን በኋላ ኢየሱስ፣ ጴጥ
ሮስንና ያዕቆብን እንዲሁም የያዕ
ቆብን ወንድም ዮሐንስን ወደ አንድ ከፍ
ያለ ተራራ ብቻቸውን ይዞአቸው ወጣ::
2በዚያም በፊታቸው መልኩ ተቀየረ፤ ፊቱ

[ም]25 የግሪኩ ቃል ትርጉም ሕይወት ወይም ነፍስ ነው፤ ቍ26 ይመ

የሚለው ስም ግሪክኛ ሲሆን፣ በዚሁ ቋንቋ "ፔትራ" ማለት ዐለት ማለት ነው:: ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችበት ዐለት ጴጥሮስ፣ እግዚአብሔር ብርሃን ሰጥቶት፣ የኢየሱስን መሲሕነት በመቀበል፣ "አንተ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ" (ቍ 17) ባለው ቃሉ ላይ ሊሆን ይችላል፤ በሌላም በኩል በኤፌ2፥20 ላይ፣ "በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል" ስለሚል፣ በራሱ በጴጥሮስ ላይ የተባለ ይመስላል:: በግልጽ እንደምንረዳው የቤተ ክርስቲያን መሠረት ክርስቶስ ነው (1ቆሮ3፥11 ይመ):: *ቤተ ክርስቲያን፤* ከወንጌሎች ውስጥ ይህ ቃል የሚገኘው በማቴዎስ ወንጌል ብቻ ነው (ይኸውም በዚህ ቦታና በ18፥17 ላይ ሁለት ጊዜ ተጠቅሶአል):: ይህ ቃል በሰብዓ ሊቃናት ትርጕም የእስራኤልን ጉባኤ ለመግለጽ ገብቶ ይገኛል:: ኢየሱስ በአካል ሥጋ በምድር ላይ በነበረበት ዘመን፣ በግሪክ ኅብረተ ሰብ ዘንድ "ኢክሊሲያ" የሚለው የግሪክ ቃል የመምረጥ መብት የነበራቸውን የነጻ ዜጎችን ጉባኤ ያመለክት ነበር (ከሐሥ19፥32፡38፡41 ጋር ያነጻጽሩ):: *ገሃነም፤* በግሪክ የሙታን መናፍስት ቦታ ማለት ነው፤ ይህም በዕብራይስጡ "ሲኦል" ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይነት አለው (የዘፍ37፥35 ማብ ይመ):: "የገሃነም ደጆች" ሲባል "የሞት ኀይላት" እንደ ማለት ሲሆን ክርስቶስንና መንግሥቱን የሚቃወሙትን ኀይላት ሁሉ ያመለክታል (የኢዮ17፥16 ማብ ይመ):: ይህም ሰይጣንንና የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ለማጥፋት የሚጥረውን በዓለም ዙሪያ ተሰልፎ ያለውን ክፋት ሁሉ ይጠቀልላል:: *አያሸንፏትም፤* ይህ ማለት ክርስቲያን፣ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወይም የአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ወደ ከንቱ የስሕተት ትምህርት ወይም ክህደት ውስጥ አይገባም ማለት አይደለም:: እዚህ ላይ የክርስቶስ ቃል የሚያመለክተው ሰይጣን በተለያየ መንገድ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ቢጥርም፣ ከሃዲዎች በክርስ ቲያኖች መካከል ቢኖሩም፣ ቤተ ክርስቲያን ለብ ብትልም፣ የሐሰት አስተማሪዎች ወደ ቅዱሳን ኅብረት ሾልከው ቢገቡም፣ ቤተ ክርስቲያን ከቶ እንደማትጠፋ ነው::

16፥19 *መክፈቻች፤* መክፈቻ ቍልፍ የሥልጣን ምሳሌ ነው (ራእ1፥18፤ 3፥7 ይመ):: ጴጥሮስ ይህን ቍልፍ የተጠቀመው የመንግሥተ ሰማያት በር ለአይሁድና ወደ ይሁዲነት ለገቡት በተከፈተበት በጰንጠቆስጤ ቀን (ሐሥ2)፣ በኋላም ለአሕዛብም መክፈቱን ባስታወቀበት ጊዜ ሊሆን ይችላል (ሐሥ10):: *ያሰርኸው ... የፈታኸው፤* የአንዳንዶች ዕጣ ፈንታን ለመወሰን ሥልጣን አገኘ ማለት ሳይሆን፣ አንድን ሰው ከበደል ነጻ ነው ወይም አይደለም ብሎ የመግለጽ ሥልጣን ተሰጠው ማለት ነው ይላሉ (18፥18 እና ዐውዱን ይመ፤ ከሐሥ5፥3፡9 ጋር ያነጻጽሩ)::

16፥20 *እንዳይናገሩ፤* ይህን ያለበት ምክንያት አይሁድ ብሔራዊ ስሜትና የፖለቲካ ተልእኮ ያለው መሲሕ ብቻ ይጠብቁ ስለ ነበር፣ ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ የገለጸውን ደቀ መዛሙርቱ ይፋ እንዳያደርጉትና ይህም በሮም መንግሥት ላይ ዐመፅ እንዳያስነሣ ነው (የ 8፥4 ማብ ይመ)::

16፥21 *ጀመር፤* ቃሉ በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ አዲስ ትኵረት መጀመሩን ያመለክታል:: ሕዝቡን በምሳሌ በማስተማር ፈንታ፣ ወደፊት ስለሚደርስበት መከራና ሞት ደቀ መዛሙርቱን ወደማዘጋጀት እያደላ ሄደ::

16፥23 *ሰይጣን፤* ከዕብራይስጥ የተወረሰ ቃል ሲሆን፣ ትርጕሙ "ተቃዋሚ" ወይም "ከሳሽ" ማለት ነው (የራእ2፥9፤ የኢዮ1፥6 ማብ ይመ)::

16፥24 *መስቀሉንም ተሸክሞ፤* የ 10፥38 ማብ ይመ::

*16፥28፤* ይህ ጥቅስ ሁለት ዋና ዋና ትርጕሞች አሉት:- 1) ከሳምንት በኋላ ሊሆን ያለውን በታቦር ተራራ ላይ የታየውን የክብሩን መገለጥ (17፥1)፤ ይኸውም ኢየሱስ በአባቱ ክብር ዳግም እንደሚመለስ የሚያመለክት ነው (16፥27)፤ (2) በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተገለጸውን የጰንጠቆስጤ ቀንና በፍጥነት የተሠራጨውን የወንጌል መዳረስ ያመለክታል:: ዐውደ ንባቡ ግን ወደ መጀመሪያው ትርጓሜ የሚያደላ ይመስላል:: የ2ጴጥ1፥16 ማብ ይመ::

17፥1-9፤ የጌታ የክብር መገለጥ ሲባል:- (1) አሁን ያልተገለጠው፣ ነገር ግን በዳግም ምጻቱ ሙሉ በሙሉ የሚታየው የእግዚአብሔር ልጅ ክብር መገለጥ ማለት ነው፤ (2) በፊልጶስ ቂሣርያ ለደቀ መዛሙርት ለተሰጠው ከባድ ትምህርት ማረጋገጫ ነው (16፥13-20)፤ (3) ኢየሱስ መከራ እንደሚቀበልና እንደሚሞት (16፥21)፤ በቅርቡ ተነግሮአቸው፣ ተስፋ ቈርጠው ለነበሩት ደቀ መዛሙርት የክብሩን መገለጥ ማየታቸው የሚያበረታታቸው ነው:: የማር9፥2-7፤ የሉቃ9፥28-35 ማብ ይመ::

17፥1 *ከስድስት ቀን፤* ማርቆስም "ስድስት ቀን" ይላል (ማር9፥2)፤ ይኸውም ጴጥሮስ ምስክርነት ከሰጠበት ቀን ጀምሮ እስከ ኢየሱስ የክብር መገለጥ ድረስ ያለውን ቀን በመቍጠር ነው:: ሉቃስ ግን በሁኔታው ውስጥ የተካተቱትን ቀናት በሙሉ በመቁጠር፣ "ስምንት ቀን ያህል" ይላል (ሉቃ9፥28):: *ጴጥሮስንና ያዕቆብን ... ዮሐንስን፤* እነዚህ ሦስት ደቀ መዛሙርት ለኢየሱስ የተለየ ቅርበት ነበራቸው (26፥37፤ ማር5፥37 ይመ):: *ከፍ ያለ ተራራ፤* የትኛው ተራራ እንደ ሆነ በትክክል ባይታወቅም፣ ፊልጶስ ቂሣርያ መጠቀሱ (16፥13)፣ ከፊልጶስ ቂሣርያ በሰሜን ምሥራቅ በኩል የሚገኘውን የአርሞንዔም ተራራን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል፤ በልማድ ግን የታቦር ተራራ (ደብረ ታቦር) እንደ ሆነ ይነገራል (የሉቃ9፥28 ማብ ይመ):: *ብቻቸውን፤* ሉቃስ "ለመጸለይ" የሚለውን ቃል ይጨምራል (ሉቃ9፥28)::

17፥2 *መልኩ ተቀየረ፤* ሦስቱ ደቀ መዛሙርት የኢየሱስ

እንደ ፀሐይ አበራ፤ ልብሱም እንደ ብርሃን
አንጸባረቀ። 3ወዲያውም ሙሴና ኤልያስ
ከኢየሱስ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው።
4ጴጥሮስም ኢየሱስን፣ "ጌታ ሆይ፤ በዚህ
ብንሆን ለእኛ መልካም ነው፤ ፈቃድህ ከሆነ፣
አንድ ለአንተ፣ አንድ ለሙሴ፣ አንድ ለኤል
ያስ ሦስት ዳሶች ልሥራ" አለው።
5እርሱ እየተናገረ ሳለ፣ ብሩህ ደመና
ሸፈናቸው፤ ከደመናውም ውስጥ፣ "በእርሱ
ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እር
ሱን ስሙት" የሚል ድምፅ ተሰማ።
6ደቀ መዛሙርቱም ይህን ሲሰሙ ደን
ግጠው በግንባራቸው መሬት ላይ ተደፉ።
7ኢየሱስም ቀርቦ ነካቸውና፣ "ተነሡ፤ አት
ፍሩ" አላቸው። 8ቀና ብለው ሲመለከቱም
ከኢየሱስ በስተቀር ሌላ ማንንም አላዩም።
9ከተራራው በመውረድ ላይ ሳሉ ኢየሱስ፣
"የሰው ልጅ ከሞት እስኪነሣ ድረስ ያያችሁ
ትን ለማንም እንዳትናገሩ" ብሎ አዘዛቸው።
10ደቀ መዛሙርቱም፣ "ታዲያ የኦሪት ሕግ
መምህራን፣ ኤልያስ አስቀድሞ መምጣት
አለበት የሚሉት ለምንድን ነው?" ብለው
ጠየቁት።
11እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ "ኤል
ያስ በእርግጥ መጥቶ ሁሉንም ነገር ያስተ
ካክላል፤ 12ነገር ግን እላችኋለሁ፤ ኤልያስ
መጥቶአል፤ ሆኖም የፈለጉትን ነገር አደረ
ጉበት እንጂ አላወቁትም። እንዲሁም የሰው
ልጅ በእጃቸው መከራን ይቀበላል።" 13በዚህ
ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ የነገራቸው
ስለ መጥምቁ ዮሐንስ መሆኑን ተረዱ።

### ኢየሱስ የሚጥል በሽታ ያለበትን ልጅ ፈወሰ

14ወደ ሕዝቡ እንደ ተመለሱ፣ አንድ
ሰው ወደ ኢየሱስ ቀርቦ በፊቱ ተንበረከከና
እንዲህ አለ፤ 15"ጌታ ሆይ፤ እባክህ ልጄን
ማርልኝ፤ በሚጥል በሽታ እጅግ እየተሠቃየ
ነው፤ ብዙ ጊዜ እሳት ውስጥ ይወድቃል፤

17፥5 ማቴ3፥17፤ ሐሥ3፥22:23
17፥7 ማቴ14፥27
17፥9 ማቴ8፥20፤ 16፥21፤ማር8፥30
17፥11 ሚል4፥6፤ ሉቃ1፥16:17
17፥12 ማቴ11፥14፤ 14፥3:10፤16፥21
17፥13 ማቴ3፥1
17፥15 ማቴ4፥24
17፥20 ማቴ13፥31፤ 21፥21፤ሉቃ17፥6፤ 1ቆሮ13፥2
17፥22 ማቴ8፥20
17፥23 ማቴ16፥21 ፤ሐሥ2፥23፤3፥13
17፥24 ዘፀ30፥13
17፥25 ማቴ22፥17-21፤ሮሜ13፥7
17፥27 ዮሐ6፥61

ውሃ ውስጥም ይገባል፤ 16ወደ ደቀ መዛሙ
ርትህ አመጣሁት፤ ነገር ግን ሊፈውሱት
አልቻሉም።" 17ኢየሱስም፣ "አንት የማታ
ምን ጠማማ ትውልድ፤ እስከ መቼ ከእናንተ
ጋር እኖራለሁ፤ እስከ መቼስ እታገሣችኋ
ለሁ። ልጁን ወደዚህ አምጡት" አለ።
18ከዚያም ኢየሱስ ጋኔኑን ገሠጸውና ከልጁ
ወጣ፤ ልጁም ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ዳነ።
19ደቀ መዛሙርቱም ለብቻቸው ወደ ኢየ
ሱስ ቀርበው፣ "እኛ ጋኔኑን ማስወጣት ያል
ቻልነው ለምንድነው?" ብለው ጠየቁት።
20እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "እምነታችሁ
በማነሱ ምክንያት ነው፤ እላችኋለሁ፤ የሰና
ፍጭ ቅንጣት የምታህል እምነት ቢኖራችሁ፣
ይህንን ተራራ፣ 'ከዚህ ተነሥተህ ወደዚያ
ሂድ' ብትሉት ይሄዳል፤ የሚሳናችሁም ነገር
አይኖርም፤ 21የዚህ ዓይነቱ ግን በጸሎትና በጾም
ካልሆነ በስተቀር አይወጣም።"
22በገሊላ ተሰባስበው ሳሉ ኢየሱስ እንዲህ
አላቸው፤ "የሰውን ልጅ አሳልፈው ለሰዎች
ይሰጡታል፤ 23ይገድሉታልም፤ እርሱም በሦ
ስተኛው ቀን ይነሣል።" ደቀ መዛሙርቱም
እጅግ አዘኑ።

### ስለ ቤተ መቅደስ ግብር ክፍያ

24ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ቅፍርናሆም
ከደረሱ በኋላ፣ የቤተ መቅደሱ ግብር ተቀ
ባዮች ወደ ጴጥሮስ ቀርበው "መምህራችሁ
ሁለቱን ዲናር የቤተ መቅደስ ግብር አይ
ከፍልምን?" አሉት።
25እርሱም፣ "ይከፍላል እንጂ" አላቸው።
ጴጥሮስ ወደ ቤት እንደ ገባ ኢየሱስ በቅ
ድሚያ፣ "ስምዖን፤ የምድር ነገሥታት ግብር
ወይም ቀረጥ የሚቀበሉት ከራሳቸው ልጆች
ወይስ ከሌሎች ይመስልሃል?" አለው።
26ጴጥሮስም፣ "ከሌሎች ነው የሚቀበሉት"
አለው።
ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ "እንግዲያውስ
ልጆች ነጻ ናቸው፤ 27ሆኖም እንዳናስቀይማ

---

መልክ ተለውጦ፣ በክብር ደምቆ አዩት (ዮሐ17፥5፤ 2ጴጥ1፥17 ይመ)።

17፥3 *ሙሴና ኤልያስ፤* ሙሴ የብሉይ ኪዳንና በቅርብ ጊዜ በኢየሱስ ሞት የሚፈጸመው የመዳን ተስፋ ተወካይ ሆኖ ሲቀርብ፣ ኤልያስ ደግሞ ለመሲሑ መመጣት ሁኔታዎችን የሚያመቻች ሆኖ መጣ (ሚል4፥5-6 እና ማብ፤ ማር9፥11-13 ይመ)። ሉቃ9፥31 ሙሴና ኤልያስ ስለ ክርስቶስ ሞት እንደ ተነጋገሩ ይገልጻል፤ የሉቃ9፥30 ማብ ይመ።

17፥4 *ሦስት ዳሶች፤* የማር9፥5 እና የሉቃ9፥33 ማብ ይመ።

17፥5 *ሸፈናቸው፤* ኢየሱስን፣ ሙሴንና ኤልያስን ማለት ነው። *በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤* ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ ከሰማይ ከተነገረው ቃል ጋር አንድ ነው (3፥17)። መልኩ በክብር የተለወጠው ተራ ሰው ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ነበረ።

17፥6 *ደንግጠው፤* በዚያ ስፍራ በነበረው ህልዎተ እግዚአብሔርና በግርማ ሞገሱ አክብሮት ያለበት ፍርሃት እንደ ተሰማቸው ያሳያል።

*17፥10፤* የኦሪት ሕግ መምህራን በሚል 4፥5-6 ያለውን ክፍል መሠረት በማድረግ፣ በመጨረሻው ዘመን ከመሲሑ አስቀድሞ ኤልያስ መምጣት እንዳለበት ያምኑ ነበር። ደቀ መዛሙርቱም በተራራው ላይ የተከሠተው የጌታ ክብር መገለጥ እንዳረጋገጠው፣ ኢየሱስ እውነተኛው መሲሕ ከሆነ፣ ታዲያ ኤልያስ አስቀድሞ ለምን አልመጣም? የሚል ጥያቄ ነበራቸው።

17፥12 *እንዲሁም፤* መጥምቁ ዮሐንስ ተቀባይነት አጥቶ እንደ ተገደለ ሁሉ፣ ኢየሱስንም አይቀበሉትም፤ ይገድሉታልም።

*17፥13፤* የ16፥12 ማብ ይመ።

17፥15 *በሚጥል በሽታ፤* የ4፥24 ማብ ይመ።

17፥17 *የማታምን ጠማማ ትውልድ፤* አጋንንትን ለማስወጣት ወይም አስፈላጊ የጸሎት መልስ ለማግኘት እምነት አስፈላጊ መሆኑን ጌታ በግልጽ ያሳያል (ቍ 20-21 ይመ)።

*17፥18፤* ማንኛውም የሚጥል በሽታ መንሥኤው ርኩስ መንፈስ ነው ማለት አይቻልም፤ ይህኛው ግን ከርኩስ መንፈስ የመጣ ነው።

17፥20 *የሰናፍጭ ቅንጣት፤* 13፥31-32 እና ማብ ይመ።

*17፥22፤* ስለ ክርስቶስ ሞት ለሁለተኛ ጊዜ መነገሩ ነው፤ አንደኛው በ16፥21 ላይ ተመልክቶአል።

17፥24 *የቤተ መቅደሱ ግብር፤* ሀያ ዓመት ከሞላውና ከዚያም በላይ ከሆነ አይሁዳዊ ሁሉ በየዓመቱ የሚሰበሰብ የቤተ መቅደስ ግብር ነበር (ዘፀ30፥13፤ 2ዜና24፥9፤ ነህ10፥32)። የግብሩም መጠን በዚያን ዘመን የሁለት ቀን ያህል የሠራተኛ ክፍያ ሲሆን፤ የሚውለውም የቤተ መቅደሱን ይዞታ ለመንከባከብ ነበር።

17፥26 *ልጆች ነጻ ናቸው፤* ይህ አባባል ጴጥሮስና ሌሎቹ

ቸው ሄደህ መንጠቆህን ወደ ባሕር ጣል፤
መጀመሪያ የምትይዘውን ዓሣ አፉን ስትከ
ፍት የምታገኘውን አንድ እስታቴር በእኔና
በአንተ ስም ክፈል።"

## በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው?

18፥1-5 ተጓ ምብ - ማር 9፥33-37፤ ሉቃ 9፥46-48

18 በዚያ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየ
ሱስ ቀርበው፣ "በመንግሥተ ሰማይ
ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው?" ብለው ጠየቁት።
2ኢየሱስ አንድ ሕፃን ጠርቶ በመካከላ
ቸው አቆመና እንዲህ አላቸው፤ 3"እውነት
እላችኋለሁ፣ ካልተለወጣችሁ እንደ ሕፃናት
ካልሆናችሁ ፈጽሞ ወደ መንግሥተ ሰማይ
አትገ ቡም። 4ስለዚህ በመንግሥተ ሰማይ
ከሁሉ የሚበልጥ እንደዚህ ሕፃን ራሱን ዝቅ
የሚ ያደርግ ነው፤

5"እንደዚህ ያለውንም ሕፃን በስሜ የሚ
ቀበል እኔን ይቀበላል። 6ነገር ግን በእኔ
ከሚያምኑት ከእነዚህ ከታናናሾቼ አንዱን
የሚያሰናክል ሰው፣ ከባድ የወፍጮ ድንጋይ
በዐንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር ተጥሎ
ቢሰጥም ይሻለዋል። 7ይህች ዓለም የመሰና
ክል ምክንያት በመሆኗ ወዮላት! መሰናክል
መምጣቱ አይቀርምና፤ ነገር ግን የመሰናክሉ
ምክንያት ለሚሆነው ሰው ወዮለት። 8እጅህ
ወይም እግርህ ለመሰናክል ምክንያት ቢሆን
ብህ፣ ቈርጠህ ጣለው፤ ሁለት እጅ ወይም
ሁለት እግር ኖሮህ ወደ ዘለዓለም እሳት
ከምትጣል፣ አንካሳ ወይም ሽባ ሆነህ ወደ
ሕይወት መግባት ይሻልሃል። 9እንዲሁም ዐይ
ንህ ለመሰናክል ምክንያት ቢሆንብህ፣ አው
ጥተህ ጣለው፤ ሁለት ዐይን ኖሮህ ወደ ገሃ
ነመ እሳት ከምትጣል፣ አንድ ዐይን ኖሮህ
ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃል። 10"ከእነ
ዚህ ከታናናሾች መካከል አንዱን እንዳት
ንቁ ተጠንቀቁ፤ እላችኋለሁና፤ በሰማይ ያሉት
መላእክታቸው በሰማይ ያለውን የአባቴን
ፊት ሁልጊዜ ያያሉ፤ 11የሰው ልጅ የጠፉትን
ለማዳን መጥቶአልና።

## የጠፋው በግ ምሳሌ

12"እስቲ ንገሩኝ፤ አንድ ሰው መቶ በጎች
ቢኖሩትና ከእነርሱም አንዱ ቢጠፋበት ዘጠና
ዘጠኙን በተራራ ላይ ትቶ የጠፋውን ለመ
ፈለግ አይሄድምን? 13እውነት እላችኋለሁ፣
የጠፋውን በግ ሲያገኝ፣ ካልጠፉት ከዘጠና
ዘጠኙ ይልቅ በዚያ በተገኘው ደስ ይለዋል።
14እንደዚሁም ከእነዚህ ከታናናሾቼ መካከል
አንዱ እንኳ እንዲጠፋ በሰማያት ያለው
አባታችሁ ፈቃድ አይደለም።

## ስለ መቀያየም

15"ወንድምህ ቢበድልህሙ ሄደህ አንተና
እርሱ ብቻ ሆናችሁ ጥፋቱን ንገረው። ቢሰ
ማህ፣ ወንድምህን እንደ ገና የራስህ ታደር
ገዋለህ። 16ባይሰማህ ግን ቃል ሁሉ በሁለት
ወይም በሦስት ምስክሮች ፊት ስለሚጸና፣
አንድ ወይም ሁለት ሰው ይዘህ እነጋግረው።
17እነርሱን ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገር፤
ቤተ ክርስቲያንንም ባይሰማ እንደ አሕዛ
ብና እንደ ቀረጥ ሰብሳቢ ቍጠረው።

18"እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር ያሰራች
ሁት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድ
ርም የፈታችሁት ሁሉ በሰማይ የተፈታ
ይሆናል።

19"ደግሞም እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር
ላይ ሁለት ሆናችሁ ስለ ምንም ነገር በመስ
ማማት ብትጠይቁ በሰማይ ያለው አባቴ
ያደርግላችኋል፤ 20ሁለት ወይም ሦስት ሆነው
በስሜ በሚሰበሰቡበት መካከል በዚያ እገኛ
ለሁና።"

## ይቅርታ ስለ ማድረግ

21በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ ወደ ኢየሱስ ቀርቦ፣
"ጌታ ሆይ፤ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ
ይቅር ልበለው? እስከ ሰባት ጊዜ ነውን?
አለው። 22ኢየሱስም "እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት
እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ ብቻ አልልህም" አለው።

23"ስለዚህ መንግሥተ ሰማይ፣ በአገልጋ
ዮቹ እጅ የነበረውን ሂሳብ ለመተሳሰብ
የፈለገን ንጉሥ ትመስላለች። 24ሂሳቡን
ማጣራት እንደ ጀመረም ዐሥር ሺህ ታላ
ንት* ዕዳ ያለበትን አንድ አገልጋይ አቀረ
ቡለት። 25አገልጋዩም ያለበትን ዕዳ መክ
ፈል ስላቃተው እርሱ ራሱ፣ ሚስቱ፣ ልጆ

ሙ15 አንዳንድ ቅጆች *ቢበድል/ኃጢአት ቢሠራ* ይላሉ
*24 በሚሊዮን የሚቆጠር ብር የሚያህል ነው

18፥3 ማቴ3፥2፤ 19፥14፤1ጴጥ2፥2
18፥4 ማር9፥35
18፥5 ማቴ10፥40
18፥6 ማቴ5፥29፤ ማር9፥42፤ሉቃ17፥2
18፥7 ሉቃ17፥1
18፥8 ማቴ5፥29
18፥9 ማቴ5፥22፡29
18፥10 ዘፍ48፥16፤ መዝ34፥7፤ ሐሥ12፥11፡15፤ ዕብ1፥14
18፥15 ዘሌ19፥17፤ ሉቃ17፥3፤ገላ6፥1፤ ያዕ5፥19፡20
18፥16 ዘኍ35፥30፤ ዘዳ17፥6፤19፥15፤ ዮሐ8፥17፤ 2ቆሮ13፥1፤1ጢ ሞ5፥19፤ዕብ10፥ 28
18፥17ሮሜ16፥17፤ 1ቆሮ6፥1-6
18፥18 ማቴ16፥19 ፤ዮሐ20፥23
18፥19 ማቴ7፥7
18፥20 ማቴ28፥20
18፥21 ማቴ6፥14፤ ሉቃ17፥4
18፥22 ዘፍ4፥24
18፥23 ማቴ13፥24 ፤25፥19
18፥25 ዘሌ25፥39፤ 2ነገ4፥1፤ነህ5፥5፡8፤ ሉቃ7፥42

ደቀ መዛሙርት ከእግዚአብሔር ንጉሣዊ ቤተ ሰብ ወገን መሆ
ናቸውን ነው፤ ያላመኑት አይሁድ ግን ከዚህ ቤተ ሰብ ውጭ ናቸው
(21፥43 ይመ)።

18፥1 *ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው?* እዚህ ላይ ደቀ መዛ
ሙርት ትልቅነትን በምድራዊ መስፈርት ያዩ ይመስላል። ሆኖም
ጌታ ኢየሱስ በመንግሥተ ሰማይ ያለው ትልቅነት የሚገኘው
በተለየ አመለካከት እንደ ሆነና እንዲያውም ትልቅነት ማለት
እንደ ታናሽ ለሁሉም አገልጋይ በመሆን እንደ ሆነ አበክሮ አስተ
ማረ።

18፥3 *እንደ ሕፃናት፤* አንድ ሰው ክርስቲያን ሲሆን የሚፈ
ለግበት የመጀመሪያው የባሕርይ ለውጥ እንደ ሕፃን መሆን ነው፤
ይኸውም ትሑት፣ የማያስመስል፣ በእግዚአብሔር እንጂ በራሱ
የማይመካ መሆን ማለት ነው።

18፥6 *ከባድ የወፍጮ ድንጋይ፤* ዕብራይስጡ ቃል በቃል
ሲተረጐም "የአህያ ወፍጮ" ማለት ሲሆን፣ በአህያ የሚገፋ መሆ
ኑን ያመለክታል፤ ይኸውም ሴቶች በየቤታቸው ጠዋት ጠዋት
ከሚፈጩበት ወፍጮ (24፥41) እጅግ ትልቅና ከባድ ነው። አን
ድን ሕፃን ወይም እንደ ሕፃን ያለን አማኝ በመንፈሳዊ ሕይወቱ
ያሰናከለ ሰው፣ ታላቁን የክርስቶስን ቍጣ በራሱ ላይ ያመጣል።

18፥10 *መላእክታቸው፤* ጠባቂ መላእክት የተባሉት ሲሆኑ፣
አገልግሎታቸው በሕፃናት ብቻ ሳይወሰን ለአጠቃላይ የእግዚ
አብሔር ሕዝቦች ሁሉ ነው (መዝ34፥7፤ 91፥11፤ ዕብ1፥14)።

18፥15 *ወንድምህ፤* ክርስቲያን የሆነውን አማኝ ማለት ነው።

18፥17 *ለቤተ ክርስቲያን፤* በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን
የሚገኝ የምእመናን ጉባኤ ማለት ነው። ወንጌሎች "ቤተ ክርስ
ቲያን" የሚለውን ቃል የተጠቀሙት በዚህ ክፍልና በ16፥18 ላይ
ብቻ ነው። *አሕዛብ፤* በአይሁድ ዘንድ ከእነርሱ ነገድ ውጭ የሆነ
ማንኛውም ሰው አሕዛብ ይባላል። *ቀረጥ ሰብሳቢ፤* የ5፥16 ማብ
ይመ። ጥፋቱ በቂ ሆኖ ከተገኘ፣ ቤተ ክርስቲያን አንድን ምእ
መን ከማኅበረ ምእመናን መካከል ለማግለል ሥልጣን እንዳላት
ይህ ጥቅስ አንድ መሠረታዊ መነሻ የሚሆን ነው።

*18፥18፤* የ16፥19 ማብ ይመ።

18፥22 *ሰባ ጊዜ ሰባት፤* ይቅርታው በቍጥር የሚወሰን
ወይም ገደብ ያለው ነው ማለት አይደለም። ይህንኑ ቍጥር "ሰባ

ቹና ንብረቱ ሁሉ ተሸጠው ዕዳው እንዲከ
ፈል ጌታው አዘዘ::
26"በዚህ ጊዜ አገልጋዩ እግሩ ላይ ወድቆ፣
'ታገሰኝ፣ ያለብኝን ዕዳ ሁሉ እከፍልሃለሁ'
ሲል ለመነው:: 27ጌታውም አዘነለትና ማረው፤
ዕዳውንም ትቶለት አሰናበተው::
28"ያ አገልጋይ ከጌታው ፊት እንደ ወጣ
አንድ መቶ ዲናር* የእርሱ ዕዳ ያለበትን
አገልጋይ ባልንጀራውን አግኝቶ እንቅ አድ
ርጎ በመያዝ፣ 'ያለብህን ዕዳ ክፈለኝ!' አለው::
29"ባልንጀራው አገልጋይም ከፊቱ ወድቆ፣
'ታገሠኝ እከፍልሃለሁ' ብሎ ለመነው::
30"ነገር ግን ሊታገሠው ፈቃደኛ ስላልነበረ፣
ያለበትን ዕዳ እስኪከፍለው ድረስ ወህኒ
ቤት አስገባው:: 31የሆነውን ነገር ያዩ
ሌሎች አገልጋዮችም በጣም አዘኑ፤ ሄደ
ውም ሁኔታውን በሙሉ ለጌታቸው ነገሩት::
32"በዚህ ጊዜ ጌታው አገልጋዩን አስጠርቶ
እንዲህ አለው፤ 'አንተ ክፉ አገልጋይ፤ ስለ
ለመንኸኝ ያን ሁሉ ዕዳ ተውሁልህ፤ 33እኔ
እንደ ማርሁህ አንተም ባልንጀራህን ልት
ምረው አይገባህም ነበርን?' 34በቍጣም ያለ
በትን ዕዳ ከፍሎ እስኪጨርስ ድረስ ለአሳ
ሪዎች አሳልፎ ሰጠው::
35"ስለዚህ እያንዳንዳችሁ ወንድሞቻችሁን
ከልባችሁ ይቅር ካላላችሁ፣ የሰማዩ አባቴም
እንደዚሁ ያደርግባችኋል::"

## ስለ መፋታት የቀረበ ጥያቄ

19፥1-9 ተጓ ምብ-ማር10፥1-12

19 ኢየሱስ ይህን ተናግሮ ከጨረሰ
በኋላ፣ ገሊላን ትቶ ከዮርዳኖስ ማዶ
ወዳለው ወደ ይሁዳ አውራጃ ሄደ:: 2ብዙ
ሕዝብም ተከተለው፤ በዚያም ፈወሳቸው::
3ፈሪሳውያንም ሊፈትኑት ቀርበው፣ "ለመሆኑ
አንድ ሰው በማንኛውም ምክንያት ሚስቱን
መፍታት ተፈቅዶአልን?" ሲሉ ጠየቁት::
4እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ "ፈጣሪ
በመጀመሪያ ወንድና ሴት አድርጎ እንደ
ፈጠራቸው አላነበባችሁምን? 5እንዲህም
አለ፤ 'ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ከሚስ
ቱም ጋር ይጣመራል፣ ሁለቱም አንድ ሥጋ
ይሆናሉ' የተባለው በዚህ ምክንያት አይደ

18፥26 ማቴ8፥2
18፥35 ማቴ6፥14፤ ያዕ2፥13
19፥1 ማቴ7፥28
19፥2 ማቴ4፥23
19፥3 ማቴ5፥31
19፥4 ዘፍ1፥27፤5፥2
19፥5 ዘፍ2፥24፤ 1ቆሮ6፥16፤ኤፌ5፥31
19፥7 ዘዳ24፥1-4፤ ማቴ5፥31
19፥9 ሉቃ16፥18
19፥11 ማቴ13፥11፤ 1ቆሮ7፥7-9:17
19፥13 ማር5፥23
19፥14 ማቴ18፥3፤ 25፥34፤1ጴጥ2፥2
19፥16 ማቴ25፥46 ፤ሉቃ10፥25

ለምን? 6ከእንግዲህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ
ሁለት አይደሉም፤ ስለዚህ እግዚአብሔር
ያጣመረውን ሰው አይለየው::"
7እነርሱም፣ "ታዲያ፣ ሙሴ አንድ ወንድ
የፍቺውን የምስክር ወረቀት ሰጥቶ ሚስቱን
እንዲያሰናብት ለምን አዘዘ?" አሉት::
8ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "ሙሴ የል
ባችሁን ጥንካሬ አይቶ ሚስቶቻችሁን እን
ድትፈቱ ፈቀደላችሁ እንጂ ከመጀመሪያው
እንዲህ አልነበረም፤ 9እላችኋለሁ፤ በትዳሯ
ላይ ዝሙት ፈጽማ እስካልተገኘች ድረስ
ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ሴት የሚያገባ ሁሉ
አመንዝራ ይሆናል፤ እርሷንም አመንዝራ
ያደርጋታል፣ የተፈታችውንም ሴት የሚያ
ገባ ያመነዝራል::"
10ደቀ መዛሙርቱም፣ "የባልና የሚስት
ጉዳይ እንዲህ ከሆነ አለማግባት ይሻላል"
አሉት::
11ኢየሱስ ግን እንዲህ አላቸው፤ "ከተሰ
ጣቸው በስተቀር ይህንን ትምህርት ማንም
ሊቀበል አይችልም፤ 12ምክንያቱም አንዳን
ዶች ጃንደረባ ሆነው ይወለዳሉ፤ ሌሎች
በሰው እጅ ተሰልበው ጃንደረባ ይሆናሉ፤
ደግሞም ለመንግሥተ ሰማይ ሲሉ ራሳቸ
ውን ጃንደረባ የሚያደርጉ አሉ:: ይህን መቀ
በል የሚችል ይቀበል::"

## ኢየሱስ ሕፃናትን ባረካቸው

19፥13-15 ተጓ ምብ - ማር 10፥13-16፤ ሉቃ 18፥15-17

13ከዚያም እጆቹን በላያቸው ላይ ጭኖ
እንዲጸልይላቸው ሕፃናትን ወደ እርሱ አቀ
ረቧቸው:: ደቀ መዛሙርቱ ግን ሕፃናቱን
ያመጡትን ሰዎች ገሠጿቸው::
14ኢየሱስም፣ "ሕፃናት ወደ እኔ ይምጡ፤
አትከልክሏቸው፤ መንግሥተ ሰማይ እንደ
እነርሱ ላሉት ናትና" አላቸው:: 15እጁንም
ጭኖ ከባረካቸው በኋላ ከዚያ ስፍራ ተነሥቶ
ሄደ::

## የሀብታሙ ጥያቄ

19፥16-29 ተጓ ምብ - ማር 10፥17-30፤ ሉቃ 18፥18-30

16ከዚያም አንድ ሰው ወደ ኢየሱስ ቀርቦ፣
"መምህር ሆይ፤ የዘላለምን ሕይወት አገኝ

*28 ጥቂት ብር ያህል ነው

ሰባት ጊዜ" ብለው የሚሉ ትርጉሞች አሉ::

*18፥25፤* አንድ ሰው በባርነት እንዴት ይሸጥ እንደ ነበር ለመገንዘብ ዘፀ21፥2፤ ዘሌ25፥39፤ 2ነገ4፥1፤ ነህ5፥5፤ ኢሳ50፥1 ይመ::

18፥35 *ይቅር ካላላችሁ፤* የምሳሌው ዐቢይ ትምህርት ይቅርታ ማድረግ ነው:: ጌታ ኢየሱስ በዚህ ምሳሌ ንስሓ ለሚገቡ ኀጢአተኞች ሁሉ የእግዚአብሔር ይቅርታ እንዲሁ የሚሰጥ ቢሆንም፣ ይህ ይቅርታ ከኀጢአተኛው ይቅርባይነት ጋር የተሳሰረ መሆኑን ያስተምራል:: አንድ ሰው የሙጥኝ ብሎ በልቡ ቂምን ቢይዝ፣ እግዚአብሔር የሚሰጠውን ይቅርታ አያገኝም (6፥14-15)::

19፥1 *ከዮርዳኖስ ማዶ ወዳለው፤* በምሥራቅ በኩል ማለት ነው፤ ኋላም ይኸው አካባቢ "ከዮርዳኖስ ማዶ ያለ አገር" ወይም ፓርያ ተባለ፤ በአሁኑ ዘመን ግን ዮርዳኖስ በመባል ይታወቃል:: በዚህ ጥቅስ መሠረት፣ ኢየሱስ በዚህ ስፍራ ማገልገል የጀመረው በዚህ ጊዜ ነው (የሉቃ13፥22 ማብ ይመ)::

19፥3 *በማንኛውም ምክንያት፤* የጥያቄው አካል የሆነው ይህ ሐረግ በማርቆስ ወንጌል (10፥2) ከሚገኘው ተመሳሳይ ክፍል አልተጠቀሰም:: ምናልባት ማቴዎስ ይህን ሐረግ የጨመረው በዘዳ24፥ 1-4 ባለው ትርጓሜ ላይ በሸማይና በሂለል ተከታዮች መካከል የነበረውን ክርክር ለሚያውቁ ለአይሁድ በመጻፉ ሊሆን ይችላል:: በሸማይ አመለካከት "ነውር" ማለት "በጋብቻ ውስጥ ታማኝ ሆኖ አለመገኘት" ነው፤ ይህም ለመፋታት ተቀባይነት ያለው ብቸኛ ምክንያት ነበር:: ሂለል (ከዓ.ቅ.ክ. 60-20 ዓ.ም. አካባቢ) አጽንዖት የሰጠው በጥቅሱ (ዘዳ24 1-4) ውስጥ "ደስ ባታሰኘው" ለሚለው ሐረግ ነው:: እንደ ሂለል አመለካከት አንዲት ሚስት ባሏ ቅር የሚሰኝበትን አንዳች ነገር ብትፈጽም (ወጥ ስትሠራ ቢጎረናባት ወይም እንጀራ ስትጋግር ቢያርባት እንኳ)፣ ባሏ እርሷን የመፍታት መብት ነበረው:: ኢየሱስ፣ እግዚአብሔር ስለ ጋብቻ በዘፍ1፥27፤ 2፥24 ላይ የተናገረውን የመጀመሪያና ዐይነተኛ ሐሳብ አስቀድሞ በመጥቀስ የሸማይን አመለካከት ደግፎአል (ቍ9 ይመ)::

19፥10-12፤ 1ቆሮ7፥7-8:26:32-35 ይመ::

ዘንድ ምን መልካም ነገር ልሥራ” ሲል ጠየ
ቀው።
[17]ኢየሱስም፣ “ስለ መልካም ነገር ለምን
ትጠይቀኛለህ? መልካም የሆነ አንዱ ብቻ
ነው፤ ወደ ሕይወት ለመግባት ከፈለግህ
ግን ትእዛዛቱን ጠብቅ” አለው።
[18]ሰውየውም፣ “የትኞቹን ትእዛዛት?” ሲል
ጠየቀ።
ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ “አትግደል፣
አታመንዝር፤ አትስረቅ፤ በሐሰት አትመስ
ክር፤ [19]አባትህንና እናትህን አክብር፤ ጎረቤ
ትህን እንደ ራስህ ውደድ።”
[20]ጕልማሳውም ሰውዬ፣ “እነዚህንማ ጠብ
ቄአለሁ፤ ከዚህ ሌላ የሚጐድለኝ ምን አለ?”
አለው።
[21]ኢየሱስም፣ “ፍጹም ለመሆን ከፈለግህ፣
ሄደህ ንብረትህን ሁሉ ሸጠህ፣ ገንዘቡን
ለድኾች ስጥ፤ በሰማይም ሀብት ታገኛለህ።
ከዚያም መጥተህ ተከተለኝ” አለው።
[22]ጕልማሳው ሰውዬም ይህን ሲሰማ ብዙ
ሀብት ስለ ነበረው እያዘነ ሄደ።
[23]ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አለ፤
“እውነት እላችኋለሁ፣ ለሀብታም ወደ መን
ግሥተ ሰማይ መግባት እጅግ አስቸጋሪ
ነው። [24]ደግሜ እላችኋለሁ፤ ሀብታም ወደ
እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ግመል
በመርፌ ቀዳዳ ቢሾልክ ይቀላል።”
[25]ይህን ሲሰሙ፣ ደቀ መዛሙርቱ እጅግ
በመገረም፣ “እንግዲያስ ማን ሊድን ይች
ላል?” ሲሉ ጠየቁ።
[26]ኢየሱስም እየተመለከታቸው፣ “ይህ በሰው
ዘንድ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን
ሁሉም ነገር ይቻላል” አላቸው።
[27]ጴጥሮስም መልሶ፣ “እኛ ሁሉን ትተን
ተከትለንሃል፤ ታዲያ ምን እናገኝ ይሆን?”
አለው።
[28]ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ “እውነት
እላችኋለሁ፤ በሚመጣው አዲስ ዓለም የሰው
ልጅ በክብሩ ዙፋን ላይ በሚቀመጥበት ጊዜ፣
እናንተም የተከተላችሁኝ በዐሥራ ሁለት

19፥17 ዘሌ 18፥5
19፥18 ያዕ 2፥11
19፥19 ዘፀ 20፥12-16፤ ዘሌ 19፥18፤ ዘዳ 5፥16-20፤ ማቴ 5፥43
19፥21 ማቴ 5፥48፤ 6፥20፤ ሐሥ 2፥45
19፥23 ማቴ 13፥22፤ 1ጢሞ 6፥9፡10
19፥26 ዘፍ 18፥14፤ ኢዮ 42፥2፤ ኤር 32፥17፤ ሉቃ 1፥37፤ 18፥27፤ ሮሜ 4፥21
19፥27 ማቴ 4፥19
19፥28 ማቴ 20፥21፤ 25፥31፤ ሉቃ 22፥28-30፤ ራእ 3፥21፤ 4፥4፤ 20፥4
19፥29 ማቴ 6፥33፤ 25፥46
19፥30 ማቴ 20፥16፤ ማር 10፥31፤ ሉቃ 13፥30
20፥1 ማቴ 13፥24፤ 21፥28:33
20፥8 ዘሌ 19፥13፤ ዘዳ 24፥15

ዙፋን ላይ ተቀምጣችሁ በዐሥራ ሁለቱ የእ
ስራኤል ነገድ ላይ ትፈርዳላችሁ። [29]ስለ
ስሜ ብሎ ቤቶችን፣ ወንድሞችን፣ እኅቶ
ችን፣ አባትን፣ እናትን*፣ ልጆችን ወይም
ዕርሻን የሚተው ሁሉ መቶ ዕጥፍ ይቀበ
ላል፤ የዘላለምንም ሕይወት ይወርሳል።
[30]ነገር ግን ብዙ ፊተኞች ኋለኞች፣ ብዙ
ኋለኞችም ፊተኞች ይሆናሉ።”

### የወይን ቦታው ሠራተኞች ምሳሌ

20 “መንግሥተ ሰማይ ለወይኑ ቦታ ሠራ
ተኞችን ለመቅጠር ማልዶ የወ
ጣን የአትክልት ስፍራ ባለቤት ትመስላለች።
[2]በቀን አንዳንድ ዲናር ሊከፍላቸው ከተስ
ማማ በኋላ ሠራተኞቹን በወይኑ ቦታ አሰ
ማራቸው።
[3]“ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ላይ በመውጣት
ሥራ ፈትተው በገበያ ቦታ የቆሙትን
ሌሎች ሰዎች አግኝቶ፣ [4]‘እናንተም ሂዱና
በወይኔ ቦታ ሥሩ፤ ተገቢውን ክፍያ እሰጣ
ችኋለሁ’ አላቸው፤ [5]እነርሱም ሄዱ።
“ከቀኑ በስድስት ሰዓትና በዘጠኝ ሰዓት
ላይ ወጥቶ ሌሎች የቀን ሠራተኞችን ቀጠረ።
[6]ከሰዓት በኋላ በዐሥራ አንድ ሰዓት ገደማ
ወጥቶ ቆመው የነበሩ ሌሎች ሰዎች አገኘና፣
‘ቀኑን ሙሉ ያለ ሥራ እዚህ ለምን ትቆማ
ላችሁ?’ በማለት ጠየቃቸው። [7]“እነርሱም፣
‘የሚቀጥረን ሰው ስለ አጣን ነው’ አሉት።
እርሱም፣ ‘እናንተም ሂዱና በወይኔ ቦታ
ሥሩ’ አላቸው።
[8]“በመሸም ጊዜ የወይኑ አትክልት ባለቤት
የሠራተኞቹን ተቈጣጣሪ፣ ‘ኋላ ከመጡት
ጀምረህ መጀመሪያ እስከመጡት ድረስ
ያሉትን ሠራተኞች በሙሉ ጥራና ደመ
ወዛቸውን ክፈላቸው’ አለው።
[9]“በዐሥራ አንደኛው ሰዓት ገደማ የተ
ቀጠሩት ሠራተኞች ቀርበው፣ እያንዳንዳቸው
አንዳንድ ዲናር ተቀበሉ። [10]በመጀመሪያ
የተቀጠሩት ሲቀርቡ ብልጫ ያለው ክፍያ
የሚያገኙ መስሎአቸው ነበር፤ ነገር ግን እነ

*29 አንዳንድ ቅጆች *እናትን ወይም ሚስትን* ይላሉ

19፥16 *ምን መልካም ነገር ልሥራ?* ሀብታሙ ሰው ጽድቅ በመልካም ሥራ ይገኛል ብሎ ያስብ ነበር። ኢየሱስ ጥያቄውን ሙሉ በሙሉ ከመመለሱ በፊት፣ የጠያቂውን የተሳሳተ ግንዛቤ ማስተካከል ነበረበት። *የዘላለምን ሕይወት፤* ይህ ሐረግ በማቴዎስ ወንጌል ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው እዚህ ላይ ነው (ቍ 29፤ 25፥46 ይመ)። ዮሐንስ በተቀሩት ሦስት ወንጌሎች ውስጥ “የእግዚአብሔር መንግሥት (ወይም መንግሥተ ሰማይ)” ተብሎ የተጻፈውን ሐረግ በመተካት፣ ይህንኑ ሐረግ ደጋግሞ ይጠቅሳል፤ ይህም አቀራረብ የሚከተሉትን የተለያዩ ሦስት አገላለጾች ተመሳሳይ ያደርጋቸዋል፦ 1) የዘላለም ሕይወት (ቍ 16፤ ማር 10፥17፤ ሉቃ 18፥18)፤ 2) ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት (ቍ 23፤ ማር 10፥24፤ ሉቃ 18፥24) እና 3) መዳን (ቍ 25-26፤ ማር 10፥26-27፤ ሉቃ 18፥26-27)።

19፥17 *መልካም የሆነ አንዱ ብቻ ነው፤* በጎ ሥራ ሲሠራ፣ በራሱ ፍጹም መልካምነት ያለው ነው በማለት የሚደረግ አይደለም። መልካም እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ በጎነትም ሁሉ የሚመነጨው ከእርሱ ዘንድ ነው፤ ኢየሱስ የዘረዘራቸውንም ትእዛዛት (ቍ 18-20) መፈጸም የሚቻለው ከእርሱ በሚገኝ ኀይል ነው። *ወደ ሕይወት ለመግባት ከፈለግህ ግን ትእዛዛቱን ጠብቅ፤* “ወደ ሕይወት መግባት” ሲባል “የዘላለምን ሕይወት ማግኘት” ከሚለው ሐረግ ጋር አንድ ነው (ቍ 16)። “ትእዛዛቱን መጠበቅ” ያስፈለገበት ምክንያት አንድን ሰው በእግዚአብሔር ፊት እንደ መልካም ለማስቈጠር ሳይሆን፣ የእውነተኛ እምነት መግለጫ እንዲሆነው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ መዳን በእምነት የሚገኝ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ እንደ ሆነ ደጋግሞ ይናገራል (ኤፌ 2፥8 ይመ)።

19፥21 *ሄደህ ንብረትህን ሁሉ ሸጠህ፤* ይህ ሰው ጠብቄአለሁ የሚላቸውን ትእዛዛት (ቍ 18-20)፣ በተለይም “ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ” የሚለውን ጠብቆ ቢሆን ኖሮ፣ ያለውን ሀብት ሸጦ ለድኾች ማካፈል በቻለ ነበር።

19፥24 *ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢሾልክ፤* የማር 10፥25 ማብ ይመ።

19፥28 *ትፈርዳላችሁ፤* ታስተዳድራላችሁ ወይም ትመራላችሁ ማለት ነው። እግዚአብሔር ወደ መንግሥቱ ለጠራቸው የመፍረድ መብት ቢሰጣቸውም እንኳ፣ ዋነኛው ዳኛና ከእስራት ነጻ አውጪ እርሱ ራሱ ነው (መሳ 8፥23፤ 11፥27 ይመ)።

20፥2 *ዲናር፤* ለቀን ሠራተኛ የሚከፈል የአንድ ቀን ዋጋ ነበር። አንድ የሮም ወታደርም በቀን አንድ ዲናር ይከፈለው ነበር።

ርሱም አንዳንድ ዲናር ተከፈላቸው:: 11ክፍ
ያውን ሲቀበሉ በባለቤቱ ላይ በማጕረምረም፣
12‘እነዚህ በመጨረሻ የተቀጠሩት አንድ
ሰዓት ብቻ ሲሠሩ፣ ቀኑን ሙሉ በሥራ
ስንደክምና በፀሐይ ስንንቃቃ ከዋልነው
ጋር እንዴት እኩል ትከፍለናለህ?’ አሉት::
13“እርሱም አንደኛውን ሠራተኛ እንዲህ
አለው፤ ‘ወዳጄ ሆይ፤ በደል አላደረስሁብ
ህም፤ በአንድ ዲናር ለመሥራት ከእኔ ጋር
ተስማምተህ አልነበረምን? 14በል ድርሻህን
ይዘህ ሂድ፤ ለአንተ የሰጠሁትን ያህል በመ
ጨረሻ ለመጣውም ሰው መስጠት እፈልጋ
ለሁ:: 15ታዲያ በራሴ ገንዘብ የፈለግሁትን
ማድረግ አልችልምን? ወይስ ቸር በመሆኔ
ምቀኝነት ያዘህን?’
16“ስለዚህ ኋለኞች ፊተኞች፣ ፊተኞችም
ኋለኞች ይሆናሉ::”

## ኢየሱስ ስለሚደርስበት መከራ ለሦስተኛ ጊዜ ተናገረ

20፥17-19 ተጓ ምብ - ማር 10፥32-34፤ ሉቃ 18፥31-33

17ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ላይ
ሳለ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ለብቻ
ቸው ወስዶ እንዲህ አላቸው፤ 18“እንግዲህ
ወደ ኢየሩሳሌም መሄዳችን ነው፤ የሰው ልጅ
ለካህናት አለቆችና ለአሪት ሕግ መምህራን
አልፎ ይሰጣል፤ እነርሱም እንዲሞት ይፈር
ዱበታል፤ 19እንዲያላግጡበት፣ እንዲገርፉ
ትና እንዲሰቅሉት ለአሕዛብ አሳልፈው
ይሰጡታል፤ በሦስተኛውም ቀን ከሞት ይነሣል::”

## በጌታ መንግሥት ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ የማግኘት ጥያቄ

20፥20-28 ተጓ ምብ - ማር 10፥35-45

20ከዚያም፣ የዘብዴዎስ ልጆች እናት ከል
ጆቿ ጋር ወደ ኢየሱስ ቀርባ በጕልበቷ
በፊቱ በመንበርከክ፣ አንድ ነገር እንዲያደ
ርግላት ለመነችው::
21እርሱም፣ “ምን ትፈልጊያለሽ?” አላት::
እርሷም፣ “እነዚህ ሁለት ልጆቼ፣ በመ
ንግሥትህ አንዱ በቀኝህ፣ አንዱ በግራህ
እንዲቀመጡ ፍቀድ” አለችው::
22ኢየሱስም፣ “የምትለምኑትን አታውቁም፤
እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ ትችላላች
ሁን?” አላቸው::
እነርሱም፣ “እንችላለን” አሉት::
23እርሱም፣ “ከጽዋዬ በእርግጥ ትጠጣላ
ችሁ፤ ነገር ግን በቀኜና በግራዬ መቀመጥ
አባቴ ላዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምፈ
ቅደው ነገር አይደለም” አላቸው::
24ዐሥሩም ይህንን በሰሙ ጊዜ፣ ሁለቱን
ወንድማማቾች ተቈጧቸው:: 25ኢየሱስም
አንድ ላይ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ “የአሕ
ዛብ ገዢዎች በሕዝባቸው ላይ ጌቶች እንደ
ሚሆኑ፣ ባለ ሥልጣኖቻቸውም በኀይል እን
ደሚገዟቸው ታውቃላችሁ፤ 26በእናንተ መካ
ከል ግን እንዲህ መሆን የለበትም:: ከእናንተ
ትልቅ መሆን የሚፈልግ አገልጋያችሁ ይሁን፤
27የበላይ ለመሆን የሚሻም የእናንተ የበታች
ይሁን፤ 28የሰው ልጅ እንዲያገለግሉት ሳይሆን፣
ለማገልገልና ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ
ለመስጠት መጥቶአልና::”

## የሁለት ዐይነ ስውሮች መፈወስ

20፥29-34 ተጓ ምብ - ማር 10፥46-52፤ ሉቃ 18፥35-43

29ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ከኢያሪኮ
ወጥተው ሲሄዱ ብዙ ሕዝብ ተከተለው::
30በዚያም ሁለት ዐይነ ስውሮች በመንገድ
ዳር ተቀምጠው ነበር፤ ኢየሱስም በዚያ
ማለፉን ሲሰሙ፣ “ጌታ ሆይ፤ የዳዊት ልጅ
ማረን!” በማለት ጮኹ:: 31ሕዝቡም በግሣጼ
ቃል ዝም እንዲሉ ነገሯቸው፤ እነርሱ ግን
አምርረው በመጮኽ፣ “ጌታ ሆይ፤ የዳዊት
ልጅ ማረን!” አሉ::
32ኢየሱስም ቆም ብሎ ጠራቸውና፣ “ምን
እንዳደርግላችሁ ትፈልጋላችሁ?” አላቸው::
33እነርሱም፣ “ዐይኖቻችን እንዲያዩ እንፈ
ልጋለን” አሉት::
34ኢየሱስም ራራላቸው፤ ዐይኖቻቸውንም
ዳሰሰ፣ ወዲያው አዩ፤ ተከተሉትም::

## ኢየሱስ በታላቅ ክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ

21፥1-9 ተጓ ምብ - ማር 11፥1-10፤ ሉቃ 19፥29-38
21፥4-9 ተጓ ምብ - ዮሐ 12፥12-15

21 ኢየሩሳሌም መቃረቢያ ደብረዘይት
ተራራ ላይ ወደምትገኘው ቤተ ፋጌ
ወደ ተባለችው ስፍራ እንደ ደረሱ፣ ኢየ

20፥11 ዮና4፥1
20፥12 ዮና4፥8፤ ሉቃ12፥55፤ያዕ1፥11
20፥13 ማቴ22፥12 ፤26፥50
20፥15 ዘዳ15፥9፤ ማር7፥22
20፥16 ማቴ19፥30
20፥18 ማቴ8፥20፤ 27፥1፡2፤ሉቃ9፥51
20፥19 ማቴ16፥21፤ ሐሥ2፥23
20፥20 ማቴ4፥21፤ 8፥2
20፥21 ማቴ19፥28
20፥22 ኢሳ51፥17፡ 22፤ኤር49፥12፤ማቴ 26፥39፡42፤ማር14፥ 36፤ሉቃ22፥42፤ ዮሐ18፥11
20፥23 ሐሥ12፥2፤ ራእ1፥9
20፥24 ሉቃ22፥24፡25
20፥26 ማር9፥35
20፥28 ዘፀ30፥12፤ ኢሳ42፥1፤44፥22፤ 53፥10፤ማቴ8፥20፤ 26፥28፤ሉቃ12፥37፤ 22፥27፤ዮሐ13፥13-16፤ 2ቆሮ8፥9፤ ፊል 2፥7፤1ጢሞ2፥6፤ ቲቶ 2፥14፤ ዕብ9፥28፤ 1ጴጥ 1፥18፡19
20፥30 ማቴ9፥27
21፥1 ማቴ24፥3፤ 26፥30፤ማር14፥26፤ ሉቃ19፥37፤21፥37፤ 22፥39፤ዮሐ8፥1፤ ሐሥ1፥12

*20፥17-19፤* ማር10፥32-34፤ ሉቃ18፥31-33 እና ማብ ይመ::

20፥19 *እንዲያላግጡበት፣ እንዲገርፉትና እንዲሰቅሉት ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታል፤* በዚህ ለሦስተኛ ጊዜ አስቀድሞ ስለ ሕማማቱ በተነገረው ላይ የተጨመረ ገለጻ ነው:: ኢየሱስ በድንጋይ ተወግሮ ይሞት ዘንድ አልፎ በአይሁድ እጅ አልተሰጠም፤ ነገር ግን በሮማውያን እጅ በመስቀል ላይ መሞት ይጠብቀው ነበር:: በሦስቱም ትንበያ በሦስተኛው ቀን እንደሚነሣ ተጠቅሶ አል (16፥21፤ 17፥23)::

20፥20 *የዘብዴዎስ ልጆች እናት፤* ማርቆስ በወንጌሉ፣ “የዘብዴዎስ ልጆች፣ ያዕቆብና ዮሐንስ” ይህን ጥያቄ እንዳቀረቡ ይናገራል (ማር10፥35-37)፤ ይሁን እንጂ በሁለቱ አገላለጽ መካከል ቅራኔ የለም፤ ሦስቱም ጥያቄውን አንድ ላይ በመሆን ማቅረብ ይችላሉና::

20፥22 *የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ፤* ዘይቤአዊ አነጋገር ሲሆን፣ የሚያመለክተውም በአንድ ሁኔታ ውስጥ ማለፍን ወይም አንድን ነገር መለማመድ ነው:: እዚህ ላይ የሚያመለክተውም መከራን መቀበል ነው (ከ26፥39 ጋር ያነጻጽሩ):: ይኸው ዘይቤ በኤር 25፥15፤ በሕዝ23፥32፤ በዕን2፥16፤ በራእ14፥10፤ 16፥19፤ 18፥6 ላይ የመለኮትን ቍጣ ወይም ፍርድ ለመግለጽ ገብቶ ይገኛል::

20፥28 *ቤዛ፤* ለዚህ ቃል አቻ ሆኖ በግሪኩ የገባው ቃል ብዙውን ጊዜ የሚያመለክተው ባሪያን ለመዋጀት የሚከፈለውን ዋጋ ነው:: ክርስቶስም እኛን ከኀጢአት ባርነት ነጻ ለማውጣት የገዛ ሕይወቱን ቤዛ አድርጎ ከፈለ:: *ለብዙዎች፤* በዚህ ቦታ የግሪኩ መስተዋድድ የክርስቶስ ሞት በሰዎች ምትክ መሆኑን በአጽንኦት ይገልጻል:: *ብዙዎች፤* ክርስቶስ “ራሱን ለሁሉ ሰው ቤዛ አድርጎ ሰጠ” (1ጢሞ2፥6):: ይህም ድኅነት የቀረበው ለሰው ሁሉ እንደ ሆነ ያመለክታል::

20፥29 *ከኢያሪኮ፤* የማር10፥46 ማብ ይመ::

20፥30 *ሁለት ዐይነ ስውሮች፤* ማርቆስና ሉቃስ የጠቀሱት አንድ ዐይነ ስውር ብቻ ነው (የ8፥28 ማብ ይመ):: *የዳዊት ልጅ፤* ለመሲሑ የተሰጠ መጠሪያ ነው (የ9፥27 ማብ ይመ)::

21፥1 *ኢየሩሳሌም፤* የሰላም ከተማ ማለት ነው:: የዮርዳኖስ

ሱስ ሁለት ደቀ መዛሙርት ላከ፤ 2እንዲህ
አላቸው "ባቅራቢያችሁ ወዳለው መንደር
ሂዱ፤ እንደ ደረሳችሁም አንዲት አህያ ከነ
ውርንጫዋ ታስራ ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁም
ወደ እኔ አምጧቸው:: 3ማንም ሰው ለምን
እንዲህ ታደርጋላችሁ ቢላችሁ፣ 'ጌታ ይፈ
ልጋቸዋል' በሉት፤ ወዲያውኑ ይሰዳቸዋል::"
4ይህ የሆነውም በነቢዩ እንዲህ በማለት
የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ነው::

5"ለጽዮን ልጅ እንዲህ በሏት፤
'እነሆ፤ ንጉሥሽ ትሑት ሆኖ፣
በአህያዪቱና በግልገሏ፣
በውርንጫዪቱም ላይ ተቀምጦ ወደ
አንቺ ይመጣል::' "

6ደቀ መዛሙርቱም ሄደው ኢየሱስ እንዳ
ዘዛቸው አደረጉ:: 7አህያዪቱንና ውርንጫ
ዋን አምጥተው ልብሶቻቸውን በላያቸው
ላይ አኖሩ፤ እርሱም ተቀመጠባቸው:: 8ከሕ
ዝቡም አብዛኛው ልብሶቻቸውን፣ በመንገድ
ላይ አነጠፉ፤ ሌሎቹም ከዛፎች ቅርንጫፍ
እየዘነጠፉ በመንገዱ ላይ ባል ባል አደ
ረጉ:: 9ቀድሞት ከፊቱ የሚሄደውና ከኋ
ላው ይከተለው የነበረው ሕዝብም እንዲህ
እያለ ይጮኽ ነበር፣

"ሆሣዕና* ለዳዊት ልጅ፤"
"በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤"
"ሆሣዕና በአርያም!"

10ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜም ከተማዋ በመላ፣
"ይህ ማነው?" በማለት ታወከች::
11አጅቦት የመጣው ሕዝብም፣ "ይህ በገ
ሊላ ከምትገኘው ከናዝሬት የመጣው ነቢዩ
ኢየሱስ ነው" አሉ::

## ኢየሱስ በቤተ መቅደስ ሲነግዱ ያገኛቸውን አስወጣቸው

21፥12-16 ተጓ ምብ - ማር 11፥15-18፤ ሉቃ 19፥45-47

12ከዚያም ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ
ገብቶ በቤተ መቅደስ ውስጥ ይሸጡና ይገዙ
የነበሩትን አባረራቸው፤ የገንዘብ ለዋጮችን
ጠረጴዛና የርግብ ሻጮችን መቀመጫ በመ
ገለባበጥ፣ 13"'ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል'
ተብሎ ተጽፎአል፤ እናንተ ግን፣ 'የዘራፊ
ዎች ዋሻ' አደረጋችሁት" አላቸው::
14በቤተ መቅደሱም ውስጥ ዐይነ ስውሮ
ችና ሽባዎች ወደ እርሱ ቀረቡ፤ እርሱም
ፈወሳቸው:: 15ነገር ግን የካህናት አለቆችና
የኦሪት ሕግ መምህራን ያደረጋቸውን ታም
ራትና፣ "ሆሣዕና ፤ለዳዊት ልጅ" እያሉ የሚ
ጮኹትን ሕፃናት ባዩ ጊዜ በቍጣ ተሞሉ::
16እነርሱም፣ "እነዚህ ሕፃናት የሚሉትን
ትሰማለህ" አሉት::
ኢየሱስም፣ "አዎን እሰማለሁ፤ እንዲህ
የሚለውን ከቶ አላነበባችሁምን?"

" 'ከልጆችና ጡት ከሚጠቡ፣
ሕፃናት አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ::' "

17ትቶአቸው ከከተማው ወጣ፤ ወደ ቢታ
ንያም ሄዶ በዚያው አደረ::

21፥4 ማቴ1፥22
21፥5 ኢሳ62፥11፤ ዘካ9፥9
21፥8 2ነገ9፥13
21፥9 ቍ15፤መዝ 118፥26፤ማቴ9፥27፤ 23፥39፤ሉቃ2፥14
21፥11 ዘዳ18፥15፤ ሉቃ7፥16:39፤ 24፥19፤ዮሐ1፥21:25፤ 6፥14፤7፥40
21፥12 ዘፀ30፥13፤ ዘሌ1፥14፤ዘዳ14፥26
21፥13 ኢሳ56፥7፤ ኤር7፥11
21፥14 ማቴ4፥23
21፥15 ቍ9፤ማቴ 9፥27፤ሉቃ19፥39
21፥16 መዝ8፥2
21፥17 ማቴ26፥6፤ ማር11፥1፤ሉቃ24፥50፤ ዮሐ11፥1:18፤12፥1

*9 በዕብራይስጡ አገላለጽ *አሁን አድን!* ማለት ሲሆን የምስጋና አገላለጽ ነው፤ ቍ15 ይመ

ወንዝ ወደ ጨው ባሕር ከሚገባበት በምዕራብ 30 ኪ.ሜ.፣ ከታላቁ ባሕር 50 ኪ.ሜ. ርቃ በተራራማው አገር የምትገኝ ከተማ ናት:: የኢየሩሳሌም ጥንታዊ ስም ሳሌም ነበር (ዘፍ14፥18)፤ ቀጥሎም ኢያቡስ (ኢያ15፥63፤18፥16)፤ *ደፌር* (2ዜና27፥3፤ 33፥14)፤ ጽዮን (መዝ136፥1) ተብላ ነበር፤ ቅድስት ከተማም ተብላለች (ነህ11፥1):: ዳዊት ኢየሩሳሌምን ከኢያቡሳውያን እጅ ከወሰደ በኋላ የእስራኤል ሁሉ፣ በተለይም የይሁዳ ዋና ከተማና እግዚአብሔርን የማምለኪያ ከተማ አደረጋት (2ሳሙ5፥6-10):: *ቤተ ፋጌ፤* የስሙ ትርጉም "የበለስ ቤት" ማለት ነው:: በብሉይ ኪዳን አልተጠቀሰችም፤ በአዲስ ኪዳን የተጠቀሰችው እንኳ ስለ ጌታ ኢየሱስ ከቤተ ፋጌ ወደ ኢየሩሳሌም "በክብር ከመግባት" ጋር በተያያዘ መልክ ነው:: 'ታልሙድ' በተባለው የአይሁድ መጽሐፍ ኢየሩሳሌም አጠገብ እንደ ሆነች ተጠቅሶአል::

21፥2 *አህያ፤* የትሕትና፣ የሰላም፣ እንዲሁም የዳዊት ንጉሣዊ ቤተ ሰብ ምሳሌ የሆነች እንስሳ ናት (የዘካ9፥9፤ የሉቃ 19፥30፤ የማር11፥2 ማብ ይመ)::

21፥7 *እርሱም ተቀመጠባቸው፤* ከሉቃ19፥20 እና ከማር 11፥2 እንደምንረዳው የተቀመጠው በውርንጫዋ ላይ ነው:: እናትየዋ አህያ ውርንጫዋን ተከትላ መሄዷ ያለ ነገር ነው:: ማቴዎስ ሁለት አህዮች እንደ ነበሩ ሲጠቅስ፣ ሌሎቹ የወንጌል ጸሐፊዎች ግን አንድ አህያ ብቻ እንደ ሆነ ይናገራሉ (የ8፥28 ማብ ይመ)::

21፥8 *ልብሶቻቸውን፣ በመንገድ ላይ አነጠፉ፤* ለንጉሥ የሚገባውን ዐይነት አክብሮት መግለጻቸው ነው (2ነገ9፥13 ይመ)::

*21፥9፤* እነዚህ ሦስት የተለያዩ ጥቅሶች ናቸው፤ ሦስቱም በአንድ ጊዜ የተነገሩ ናቸው ማለትም አይቻልም:: *ሆሣዕና፤* የመዝ118፥25-26 ማብ ይመ:: ሆሣዕና ሲባል ልመናም ምስጋናም ይሆናል:: *ለዳዊት ልጅ፤* የ 9፥27 ማብ ይመ:: *በአርያም፤* በሰማይ ያሉትም "ሆሣዕና" እያሉ ይዘምሩ ለማለት ነው (መዝ148፥1-2፤ ሉቃ2፥14 ይመ)::

*21፥12-17፤* ቤተ መቅደስን የማንጻቱ ጉዳይ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ወንጌሎች የተገለጸው በኢየሱስ አገልግሎት የመጨረሻ ሳምንት ውስጥ እንደ ተፈጸመ ነው፤ በዮሐንስ ወንጌል ግን የማንጻቱ ተግባር የተከናወነው ጌታ አገልግሎቱን በጀመረ በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራት ውስጥ ነበር (ዮሐ2፥12-16):: ለዚህም ሁለት ማብራሪያዎች ማቅረብ ይቻላል፤ 1) ሁለት ጊዜ ማንጻት ተከናውኖአል፤ አንደኛው በኢየሱስ አገልግሎት መጀመሪያ ላይ፣ ሁለተኛው ደግሞ በይፋ አገልግሎቱ መጨረሻ ላይ፤ 2) በሕማማት ሳምንት የተከናወነው አንድ የማንጻት ተግባር ብቻ ሲሆን፣ ሐዋርያው ዮሐንስ ትምህርተ መለኮታዊ ምክንያት ስላለው በወንጌሉ መጀመሪያ ላይ አስቀምጦታል፤ ይኸውም መሲሑ ገና አገልግሎቱን እንደ ጀመረ፣ የእግዚአብሔር ፍርድ በእርሱ እጅ እውን መሆኑን ለመግለጽ ነው:: ይሁን እንጂ በሁለቱም ትረካ ውስጥ ያሉ ዝርዝር ጉዳዮች ይለያያሉ፤ ለምሳሌ:- የበሬዎችና የበጎች መሸጥ (ዮሐ2፥14)፣ የጅራፉ ጉዳይ (ዮሐ2፥15)፣ ኢየሱስ የተናገረው ቃል (ማቴ21፥13፤ ዮሐ2፥16):: ከማቴዎስና ከሉቃስ ወንጌሎች ትረካ መገመት እንደሚቻለው የቤተ መቅደሱ መንጻት የተከናወነው "በክብር መግባት" ከተባለው ቀን ቀጥሎ ባለው እሑድ ነው (21፥1-11):: በማርቆስ ወንጌል ላይ ግን የማንጻቱ ተግባር የተከናወነው በሰኞ ቀን መሆኑ በግልጽ ይታወቃል (11፥ 15-19):: ማቴዎስ ታሪኮችን ጨምቆ የማቅረብ ልማድ አለው::

21፥12 *ቤተ መቅደስ፤* "ሽያጩና ግዢው" የተከናወነው በቤተ መቅደሱ ግቢ ውስጥ "የአሕዛብ አደባባይ" በመባል በተመደበው ሰፊ ቦታ ላይ ነበር (የማር11፥15 ማብ ይመ)::

21፥13 *የጸሎት ቤት፤* የማር11፥17 ማብ ይመ::

21፥17 *ቢታንያም፤* ደብረ ዘይት በተባለው ተራራ፣ በምሥራቅ በኩል ባለው ተዳፋቱ ላይ፤ ከኢየሩሳሌም 3 ኪ.ሜ. ያህል ራቅ ብላ የምትገኝ፣ ከኢያሪኮ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ መዳረሻው ያለች መንደር ነበረች::

### ፍሬ አልባ የ[illegible]ነችው በለስ

21፥18-22 ተጓ ምብ - ማር 11፥12-14፡20-24

18ኢየሱስ በማግስቱ ማለዳ ወደ ከተማ
ዪቱ በመመለስ ላይ ሳለ ተራበ፤ 19በመን
ገድ ዳርም አንድ የበለስ ዛፍ አይቶ ወደ
እርሷ ሲሄድ ከቅጠል በስተቀር ምንም ስላ
ላገኘባት፣ "ከእንግዲህ ፍሬ አይኑርብሽ!"
አላት፤ የበለሷ ዛፍ ወዲያውኑ ደረቀች::
20ደቀ መዛሙርቱም የሆነውን አይተው
በመደነቅ፣ "የበለሷ ዛፍ እንዴት ባንዴ
ልትደርቅ ቻለች?" አሉ::
21ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "እውነት እላ
ችኋለሁ፤ እምነት ቢኖራችሁ ባትጠራጠሩ፣ በበ
ለሷ ዛፍ ላይ የሆነውን ማድረግ ብቻ ሳይ
ሆን፣ ይህንን ተራራ፣ 'ከዚህ ተነቅለህ ባሕር
ውስጥ ግባ' ብትሉት እንኳ ይሆናል፤ 22እም
ነት ካላችሁ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ
ትቀበላላችሁ::"

### በኢየሱስ ሥልጣን ላይ የቀረበ ጥያቄ

21፥23-27 ተጓ ምብ - ማር 11፥27-33፤ ሉቃ 20፥1-8

23ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ በማስ
ተማር ላይ ሳለ፣ የካህናት አለቆችና የሕ
ዝብ ሽማግሌዎች ቀርበው፣ "ይህን ሁሉ
ነገር የምታደርገው በምን ሥልጣን ነው?
ሥልጣኑንስ የሰጠህ ማን ነው?" ብለው ጠየ
ቁት::
24ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
"እኔም አንድ ጥያቄ እጠይቃችኋለሁ፤
መልሱን ብትነግሩኝ፣ እኔም እነዚህን ነገ
ሮች በምን ሥልጣን እንደማደርግ እነግራች
ኋለሁ፤ 25የዮሐንስ ጥምቀት የመጣው ከየት
ነበር? ከሰማይ ወይስ ከሰዎች?"

እነርሱም እርስ በርስ በመነጋገር እንዲህ
ተባባሉ፤ 'ከሰማይ ነው?' ካልን 'ታዲያ ለምን
አላመናችሁበትም?' ይለናል፤ 26'ከሰዎች ነው'
ካልን ደግሞ፣ 'ሕዝቡ ዮሐንስን ነቢይ ነው'
ብሎ ስለሚያምን እንፈራለን::"
27ስለዚህ፣ "አናውቅም" ብለው ለኢየሱስ
መለሱለት::

እርሱም፣ "እኔም እነዚህን ነገሮች በምን ሥልጣን እንደማደርግ አልነግራችሁም" አላቸው::

### የመታዘዝ ትርጕም

28ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "ምን ይመ
ስላችኋል? ሁለት ወንዶች ልጆች ያሉት
አንድ ሰው ነበረ፤ ወደ መጀመሪያው ልጁ
ሄዶ፣ 'ልጄ ሆይ፤ ዛሬ ወደ ወይኑ ቦታ ሄደህ
ሥራ' አለው::
29"ልጁም፣ 'አልሄድም' አለው፤ ኋላ ግን
ተጸጽቶ ሄደ::
30"ወደ ሁለተኛው ልጁ ሄዶ እንደዚያው
አለው፤ ልጁም 'እሺ እሄዳለሁ' አለው፤
ነገር ግን ሳይሄድ ቀረ::
31"ከሁለቱ የአባቱን ፈቃድ የፈጸመው
የትኛው ነው?"

እነርሱም፣ "የመጀመሪያው ልጅ" አሉት::

ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "እውነት
እላችኋለሁ፣ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና አመንዝራ
ዎች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በመ
ግባት ይቀድሟችኋል፤ 32መጥምቁ ዮሐንስ
የጽድቅን መንገድ ሊያሳያችሁ ወደ እናንተ
መጣ፤ እናንተ አላመናችሁትም፤ ቀረጥ ሰብ
ሳቢዎችና አመንዝራዎች ግን አመኑት::
የሆነውን ካያችሁ በኋላ እንኳ ንስሓ ገብ
ታችሁ አላመናችሁትም::

### የወይን ዕርሻ ገበሬዎች ምሳሌ

21፥33-46 ተጓ ምብ - ማር 12፥1-12፤ ሉቃ 20፥9-19

33"ሌላም ምሳሌ ስሙ፤ አንድ የወይን ዕርሻ
ባለቤት ነበረ፤ በዕርሻው ዙሪያ አጥር አጠረ፤
ለወይኑ መጭመቂያ ጕድጓድ ቈፈረ፤
ለጥበቃ የሚሆን ማማ ሠራ፤ ከዚያም ዕር
ሻውን ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሌላ አገር
ሄደ:: 34የመከር ወራት ሲደርስ፣ ፍሬውን
ለመቀበል አገልጋዮቹን ወደ ገበሬዎቹ
ላካቸው::
35"ገበሬዎቹም አገልጋዮቹን ይዘው አን
ዱን ደበደቡት፤ ሌላውን ገደሉት፤ ሌላውን
ደግሞ በድንጋይ ወገሩት:: 36እርሱም ከፊ
ተኞቹ የሚበልጡ ሌሎች አገልጋዮቹን ላከ፤
ገበሬዎቹም ተመሳሳይ ድርጊት ፈጸሙ
ባቸው:: 37በመጨረሻም፣ 'ልጄን ያከብሩታል'
በማለት ልጁን ላከ::
38"ነገር ግን ገበሬዎቹ ልጁን ባዩት ጊዜ፣
'ይህማ ወራሹ ነው፤ ኑ፣ እንግደለውና ርስ
ቱን እንውረስ' ተባባሉ:: 39ይዘውም ከወይኑ
ዕርሻ ውጭ አውጥተው ገደሉት::
40"ታዲያ የወይኑ ዕርሻ ባለቤት ሲመጣ
እነዚያን ገበሬዎች ምን የሚያደርጋቸው
ይመስላችኋል?"
41እነርሱም፣ "እነዚያን ክፉዎች በአሰቃቂ
ሁኔታ ገድሎ ከወይኑ ዕርሻ ተገቢውን ፍሬ
በወቅቱ ለሚያስረክቡት ለሌሎች ገበሬዎች

21፥19 ኢሳ34፥4፤ ኤር8፥13
21፥21 ማቴ17፥20፤ሉቃ17፥6፤1ቆሮ 13፥2፤ያዕ1፥6
21፥22 ማቴ7፥7
21፥23 ሐሥ4፥7፤ 7፥27
21፥26 ማቴ11፥9
21፥28 ቍ33፤ ማቴ20፥1
21፥31 ሉቃ7፥29፡50
21፥32 ማቴ3፥1-12 ፤ሉቃ3፥12፡13፤7፥29፡ 30፡36-50
21፥33 መዝ80፥8፤ ኢሳ5፥1-7፤ማቴ25፥ 14፡15
21፥34 ማቴ22፥3
21፥35 2ዜና24፥21 ፤ማቴ23፥34፡37፤ዕብ 11፥36፡37
21፥36 ማቴ22፥4
21፥38 መዝ2፥8፤ ማቴ12፥14፤ዕብ1፥2
21፥41 ማቴ8፥11፡ 12፤ሐሥ13፥46

21፥18-22፤ የቍ 12-17 ማብ ይመ፤ ይህ ክፍል ማቴዎስ ትረካን ጨምቆ ስለ ማቅረቡ ሌላው ማስረጃ ነው:: ማርቆስ በለሷ ሰኞ ዕለት እንደ ተረገመችና ደቀ መዛሙርቱ ማክሰኞ ጠውልጋ እንዳገኟት ጽፎአል (ማር11፥12-14፡20-25):: ማቴዎስ ግን ኢየ ሱስ በለሷን እንደ ረገማት ወዲውያኑ መጠውለጓን በመጻፍ፣ ፍርዱ ምን ያህል ቅጽበታዊ እንደ ሆነ በአጽንዖት ገልጾአል:: የዚህ ሁኔታ ነገረ መለኮታዊ ትርጕም ምን እንደ ሆነ ለማወቅ የማር 11፥14 ማብ ይመ::

21፥23 *በምን ሥልጣን ...?* የሉቃ20፥2 ማብ ይመ::

21፥25 *ከሰማይ ወይስ ከሰዎች?* የማር11፥30፤ የሉቃ 20፥3 ማብ ይመ::

21፥33 ማማ፤ የወይን አትክልት ስፍራ፣ በተለይ ወይኑ በሚጐመራበት ጊዜ ለመጠበቅ የሚሠራ ሲሆን፣ እንደ መጠለያም ያገለግላል:: የአንድ ማማ ከፍታው 5 ሜትር ያህል፣ የጠባቂው መቆሚያ ደግሞ 1 ሜትር ካሬ ያህል ሆኖ ከጣውላ መሠራት እንዳለበት የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን ልኩን አይተው አስቀ ምጠዋል::

*21፥35-37፤* ገበሬዎች የተባሉት አይሁድ ወይም አለቆቻ ቸው ናቸው፤ አገልጋዮች የተባሉትም የተገደሉትን ብዙዎቹን የብሉይ ኪዳን ነቢያት ይወክላሉ:: ልጅ የተባለውም የአይሁድ ሃይ ማኖት መሪዎች ለሞት አሳልፈው የሰጡት፣ የክርስቶስ ምሳሌ ነው::

21፥41 *ለሌሎች ገበሬዎች፤* ብዙዎቹ አይሁድ ወንጌልን

ያከራያል” አሉት::
42ኢየሱስም እንዲህ ተብሎ በቅዱሳት
መጻሕፍት የተጻፈውን አላነበባችሁምን?አላ
ቸው፤

“ ‘ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣
  የማእዘን ራስ[ፐ] ሆነ፤
እግዚአብሔር ይህን አድርጎአል፤
  ሥራውም ለዐይናችን ድንቅ ነው::’

43“ስለዚህ እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔር
መንግሥት ከእናንተ ተወስዳ ፍሬዋን ለሚ
ያፈራ ሕዝብ ትሰጣለች፤ 44በዚህ ድንጋይ
ላይ የሚወድቅ ይሰባበራል፤ ድንጋዩ የሚወ
ድቅበት ሰው ግን ይደቅቃል::”[ሀ]
45የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ምሳሌዎ
ቹን በሰሙ ጊዜ፣ ስለ እነርሱ የሚናገር
መሆኑን ዐወቁ:: 46ነገር ግን ይዘው ሊያስሩት
ቢፈልጉም ሕዝቡ ኢየሱስን እንደ ነቢይ
አድርጎ ይመለከት ስለ ነበር ፈሩ::

### በሰርግ ድግስ ላይ የተጠሩ ሰዎች ምሳሌ

22፥2-14 ተጓ ምብ - ሉቃ 14፥16-24

**22** ኢየሱስም እንደ ገና እንዲህ የሚል
ምሳሌ ነገራቸው፤ 2“መንግሥተ ሰማይ
ለልጁ ሰርግ የደገሰ ንጉሥ ትመስላለች፤
3ንጉሡም የተጋበዙትን ሰዎች እንዲጠሩ አገ
ልጋዮቹን ላከ፤ እነርሱ ግን አንመጣም አሉ::
4“እንደገናም ሌሎች አገልጋዮች ልኮ፣
‘የተጋበዙትን፣ እነሆ፣ በሬዎችንና የሠቡ
ከብቶቼን አርጄ ድግሱን አዘጋጅቻለሁ፤
ሁሉም ነገር ዝግጁ ስለሆነ ወደ ሰርጉ ኑ በሏ
ቸው’ አለ::
5“ተጋባዦቹ ግን ጥሪውን ችላ ብለው፣ አንዱ
ወደ እርሻው ሌላው ወደ ንግዱ ሄደ፤ 6የቀሩ
ትም አገልጋዮቹን በመያዝ አጕላልተው
ገደሏቸው:: 7ንጉሡም በመቈጣት ሠራዊቱን
ልኮ ገዳዮቻቸውን አጠፋ፤ ከተማቸውንም
አቃጠለ::
8“ከዚያም አገልጋዮቹን እንዲህ አላቸው፤
‘የሰርጉ ድግስ ዝግጁ ነው፤ ነገር ግን የተጋ
በዙት የሚገባቸው ሆነው ስላልተገኙ፣ 9ወደ
መንገድ መተላለፊያ ወጥታችሁ ያገኛችሁ
ትን ሁሉ ወደ ሰርጉ ድግስ ጥሩ::’ 10አገል
ጋዮቹም ወደ መንገድ ወጥተው ያገኙትን
መልካሙንም ክፉውንም ሁሉ ሰብስበው
የሰርጉን አዳራሽ በእንግዶች ሞሉት::
11“ንጉሡም የተጋበዙትን እንግዶች ለማ
የት ሲገባ፣ አንድ የሰርግ ልብስ ያልለበሰ
ሰው አየ፤ 12እንዲህም አለው፤ ‘ወዳጄ ሆይ፤
የሰርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት እዚህ ልት
ገባ ቻልህ?’ ሰውየው ግን የሚመልሰው
ቃል አልነበረውም::
13“ንጉሡም አገልጋዮቹን፣ ‘እጅና እግሩን
አስራችሁ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጥ
ታችሁ ጣሉት፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋ
ጨት ይሆናል’ አላቸው፤ 14የተጠሩት ብዙ
ዎች፣ የተመረጡት ግን ጥቂቶች ናቸውና::”

### ግብር ስለ መክፈል

22፥15-22 ተጓ ምብ - ማር 12፥13-17፤ ሉቃ 20፥20-26

15ከዚህ በኋላ ፈሪሳውያን ወጥተው በመ
ሄድ በአፍ እላፊ እንዴት እንደሚያጠምዱት
ተማከሩ:: 16ደቀ መዛሙርታቸውን ከሄሮ
ድስ ወገኖች ጋር ወደ እርሱ ልከው እንዲህ
አሉት፤ “መምህር ሆይ፤ አንተ እውነተኛና
የእግዚአብሔርንም መንገድ በእውነት የም
ታስተምር እንደ ሆንህ፣ ለማንም ሳታዳላ
ሁሉን በእኩልነት እንደምትመለከት እናው
ቃለን፤ 17ንገረን፤ ምን ይመስልሃል? ለመ
ሆኑ ለቄሣር ግብር መክፈል ይገባል ወይስ
አይገባም?”
18ኢየሱስ ግን ተንኰላቸውን በመረዳት
እንዲህ አላቸው፤ “እናንተ ግብዞች ለምን
በነገር ልታጠምዱኝ ትሻላችሁ? 19ለግብር
የሚከፈለውን ገንዘብ እስቲ አሳዩኝ” እነር
ሱም አንድ ዲናር አመጡለት:: 20እርሱም፣
“በዚህ ገንዘብ ላይ የሚታየው መልክ የማን

ፐ42 ወይም *የማእዘን ድንጋይ*
ሀ44 አንዳንድ ቅጆች ቍጥር 44 የላቸውም

21፥42 መዝ118፥22:23፤ሐሥ4፥11
21፥43 ማቴ8፥12
21፥44 ሉቃ2፥34
21፥46 ቍ11:26
22፥2 ማቴ13፥24
22፥3 ማቴ21፥34
22፥4 ማቴ21፥36
22፥7 ሉቃ19፥27
22፥9 ሕዝ21፥21
22፥10 ማቴ13፥4 7:48
22፥12 ማቴ20፥13፤ 26፥50
22፥13 ማቴ8፥12
22፥14 ራእ17፥14
22፥16 ማር3፥6
22፥17 ማቴ17፥25

አንቀበልም ባሉ ጊዜ፣ ጳውሎስ እነዚህን ትቶ ወንጌልን የሰበከላቸው አሕዛብ ናቸው (ሐሥ13፥46፤ 18፥6):: ሁለተኛው ምዕተ ዓመት ላይ፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት አሕዛብ ብቻ ነበሩ ማለት ይቻላል::

21፥44 *ይሰባበራል፤* የሉቃ20፥18 ማብ ይመ:: አንዳንድ ቅጂዎች ይህ ጥቅስ (ቍ44) የላቸውም::

22፥7 *ከተማቸውንም አቃጠለ፤* ወታደሮች የጠላትን ከተማም አቃጥለው መሄድ ልማዳቸው ነበር፤ እዚህ ላይ ኢየሩሳሌም በ70 ዓ.ም. እንደምትጠፋ በስላች መጠቈሙ ሊሆን ይችላል::

22፥11 *የሰርግ ልብስ ያልለበሰ፤* ዕድምተኞችን የሚያስተናግድ ሰው ተጋባዦቹን የሰርግ ልብስ ማልበሱ የተለመደ ነበር የሚል ግምት አለ:: በዚህ ግብዣ ላይ የነበሩትም ከየጎዳናው የተጠሩ ስለ ነበር (ቍ9-10)፣ እነዚህን ሰዎች በተለይ በዚህ ጊዜ የሰርግ ልብስ ማልበሱ አስፈላጊ ነበር:: በዚህ ምሳሌ ላይ የተጠቀሰው ሰው የተዘጋጀለትን የሰርግ ልብስ አለመልበሱም፣ የጋባዡን ክብር የሚነካ ነበር:: የሰርግ ልብስ የልብን መዘጋጀት ያመለክታል፤ ይኸውም በክርስቶስ ማመንና ከእርሱም ጋ የተነሣ ዘወትር መታዘዝን ያሳያል:: ሁላችንም ራሳችንን እንድንመረምር፣ ክርስቶስ የሠርግን ልብስ ያልለበሰውን ሰው ማስረጃ በማድረግ አቅርቦአል::

22፥13 *በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጥታችሁ ጣሉት ... ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት፤* የቅጣቱን ክብደት የሚያመለክት አገላለጽ ነው:: የምሳሌው የመጀመሪያ ክፍል (ቍ2-10) እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ እንደ ናቀ ይናገራል (ከ21፥43-45 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ (ቍ 11-13) የግለሰቡን ኀላፊነት ይገልጻል:: የሰርጉ ልብስ፣ የጸጋ ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር ጥሪውን በእምነት ለሚቀበሉት ስለሚሰጣቸው ጽድቅ እንደሚናገር ግልጽ ነው:: እግዚአብሔር ክቡር ጥሪውን ጸጋውን ለመቀበል ብቃት ለሌላቸው ሰዎች ያቀርባል፤ በተጨማሪም ለጥሪው ብቁ የሚያደርገውን ጽድቅ ይሰጣል::

22፥15-17፤ ፈሪሳውያን የሮማውያንን አገዛዝን የሚቃወሙ ጠንካራ ብሔረተኞች ነበሩ፤ በአንጻሩ የሄሮድስ ወገኖች የተባሉትና ጥላቻን ያተረፉት፣ የሄሮድስን ሮማዊ አገዛዝ ይደግፉ ነበር:: በዚህ ጊዜ ግን ፈሪሳውያን ኢየሱስን በሚናገረው ጠልፈው ለመያዝ የሄሮድስ ወገኖችን እርዳታ ፈለጉ፤ በሸንገላቸው ወደ ወጥመዳቸው እንዲገባ ካመቻቹም በኋላ፣ “ለቄሣር ግብር መክፈል ይገባል ወይስ አይገባም?” በማለት ጥያቄያቸውን ድንገት ሰነዘሩበት (ቍ17):: “መክፈል አይገባም”ብሎ ቢመልስ ኖሮ፣ የሄሮድስ ወገኖች በሮማዊው እንደራሴ ፊት ከሰውት፣ በመንግሥት ተቃዋሚነት የሞት ፍርድ ባሰበየኑበት ነበር፤ “መክፈል ይገባል” ብሎ ቢመልስ ኖሮም፣ ለገዛ ወገኑ ታማኝ እንዳልሆነ በመቍጠር በሕዝቡ ዘንድ ሊያጥላሉት ምክንያት ባገኙበት ነበር::

22፥19 *ዲናር፤* በዚያ ዘመን በሮም መንግሥት ግዛት መገ

ነው? ጽሕፈቱስ የማን ነው?" አላቸው።
21እነርሱም፣ "የቄሣር ነው" አሉት።
እርሱም መልሶ፣ "እንግዲያውስ የቄሣርን
ለቄሣር፣ የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር
ስጡ" አላቸው።
22ይህን ሲሰሙ ተደነቁ፤ ትተውትም ሄዱ።

## ስለ ሙታን ትንሣኤ

22፥23-33 ተጓ ምብ - ማር 12፥18-27፤ ሉቃ 20፥27-40

23የሙታን ትንሣኤ የለም ብለው የሚያ
ምኑ ሰዱቃውያን በዚያኑ ቀን ወደ ኢየሱስ
ቀርበው እንዲህ ብለው ጠየቁት፤ 24"መም
ህር ሆይ፤ ሙሴ፣ 'አንድ ሰው ከሚስቱ
ልጅ ሳይወልድ ቢሞት ወንድሙ የሚቱን
ሚስት አግብቶ ለእርሱ ዘር ይተካለት'
ብሎአል። 25በእኛ ዘንድ ሰባት ወንድማማ
ቾች ነበሩ፤ የመጀመሪያው ሚስት አግብቶ
ልጅ ሳይወልድ በመሞቱ፣ ሚስቱን ወን
ድሙ አገባት፤ 26ሁለተኛውም ለመጀመሪያ
ወንድሙ እንዲሁ ልጅ ሳያፈራ ሞተ፤ በዚህ
ሁኔታ ሴትዮዋ ለሰባተኛው ወንድሙ ደረ
ሰችው። 27በመጨረሻ ሴትዮዋ ራሷ ሞተች።
28ስለዚህ ሁሉም ስላገቧት በትንሣኤ ቀን ከሰ
ባቱ ለየትኛው ሚስት ትሆናለች?"
29ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰ፤ "ቅዱ
ሳት መጻሕፍትንና የእግዚአሔርን ኀይል
ስለማታውቁ ትስታላችሁ፤ 30ከትንሣኤ
በኋላ ሰዎች እንደ ሰማይ መላእክት ይሆ
ናሉ እንጂ አያገቡም፤ አይጋቡም። 31ስለ
ሙታን ትንሣኤ ግን እግዚአብሔር እንዲህ
ብሎ የተናገራችሁን አላነበባችሁምን? 32'እኔ
የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣
የያዕቆብ አምላክ ነኝ።' እግዚአብሔር የሕያ
ዋን እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም።
33ሕዝቡም ይህን በሰሙ ጊዜ በትምህርቱ
ተደነቁ።

## ታላቁ ትእዛዝ

22፥34-40 ተጓ ምብ - ማር 12፥28-31

34ኢየሱስ ሰዱቃውያንን ዝም እንዳሰኛ
ቸው ሰምተው፣ ፈሪሳውያን በአንድነት ተሰ
በሰቡ፤ 35ከእነርሱም አንድ የኦሪት ሕግ
አዋቂ፣ ሊፈትነው ፈልጎ እንዲህ አለው፤
36"መምህር ሆይ፤ ከሕግ ሁሉ የሚበልጠው

22፥21 ሮሜ13፥7
22፥22 ማር12፥12
22፥23 ሐሥ4፥1፤
23፥8፤1ቆሮ15፥12
22፥24 ዘዳ25፥5-6
22፥29 ማቴ24፥38
22፥32 ዘፀ3፥6፤
ሐሥ7፥32
22፥33 ማቴ7፥28
22፥34 ሐሥ4፥1
22፥35 ሉቃ7፥30፤
10፥25፤11፥45፤14፥3
22፥37 ዘዳ6፥5
22፥39 ዘሌ19፥18፤
ማቴ5፥43
22፥40 ማቴ7፥12፤
ሉቃ10፥25-28
22፥42 ማቴ9፥27
22፥44 1ነገ5፥3፤
መዝ110፥1፤ሐሥ
2፥34፡35፤1ቆሮ15፥
25፤ዕብ1፥13፤10፥13
22፥46 ማር12፥34፤
ሉቃ20፥40
23፥2 ዕዝ7፥6፡25
23፥4 ሉቃ11፥46፤
ሐሥ15፥10፤ገላ6፥13

የትኛው ትእዛዝ ነው?"
37እርሱም እንዲህ አለው፤ "'ጌታ አምላ
ክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣
በፍጹም ሐሳብህ ውደድ፤' 38ይህ የመጀመ
ሪያውና ከሁሉ የሚበልጠው ትእዛዝ ነው፤
39ሁለተኛውም ያንኑ ይመስላል፤ ይህም፣
'ጎረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ' የሚለው
ነው፤ 40ሕግና ነቢያት በሙሉ በእነዚህ ሁለት
ትእዛዛት ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው።"

## ክርስቶስ የማን ልጅ ነው?

22፥41-46 ተጓ ምብ - ማር 12፥35-37፤ ሉቃ 20፥41-44

41ፈሪሳውያን ተሰብስበው ሳሉ ኢየሱስ፣
እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፤ 42"ስለ ክርስቶስ[^]
ምን ይመስላችኋል? የማንስ ልጅ ነው?"
እነርሱም፣ "የዳዊት ልጅ ነው" አሉት።
43እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "ታዲያ፣ ዳዊት
በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ለምን 'ጌታዬ'
ይለዋል? ለምንስ፣ እንዲህ ይለዋል?
44" 'እግዚአብሔር ጌታዬን፤
ጠላቶችህን ከእግርህ በታች
እስካንበረክክልህ ድረስ፣
በቀኜ ተቀመጥ።" '
45ስለዚህ ዳዊት፣ 'ጌታዬ' ብሎ ከጠራው፣
እንዴት ልጁ ሊሆን ይችላል?" 46አንድ
ቃል ሊመልስለት የቻለ ወይም ከዚያን
ቀን ጀምሮ ሊጠይቀው የደፈረ ማንም አል
ነበረም።

## ኢየሱስ ፈሪሳውያንንና የኦሪት ሕግ መምህ ራንን ነቀፈ

23፥1-7 ተጓ ምብ - ማር 12፥38፡39፤ ሉቃ 20፥45-46
23፥37-39 ተጓ ምብ - ሉቃ 13፥34፡35

23 ከዚያም ኢየሱስ ለሕዝቡና ለደቀ
መዛሙርቱ እንዲህ ሲል ተናገረ፤
2"የኦሪት ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን
በሙሴ ወንበር ላይ ተቀምጠዋል። 3ስለዚህ
የሚነግሯችሁን ሁሉ አድርጉ፤ ጠብቁትም፤
ነገር ግን እንደሚናገሩት አያደርጉምና ተግ
ባራቸውን አትከተሉ። 4እንዲሁም ለመሸ
ከም የማይቻል ከባድ ሸክም አስረው በሰ
ዎች ትከሻ ላይ ይጭናሉ፤ ራሳቸው ግን በጣ

^42 ወይም መሲሑ

በያያ የሳንቲም ገንዘብ ነበር (የ20፥2 ማብ ይመ)። በሳንቲሙ አንደኛው ገጽታ የንጉሥ ጢባርዮስ ምስል ሲታይ፣ በግልባጩ ደግሞ በላቲን ቋንቋ "ጢባርዮስ ቄሣር አውግስጦስ፣ የመለኮታዊው የአውግስጦስ ልጅ" የሚል ተጽፎበት ነበር። ሳንቲሙን እያሠራ የሚያወጣው ቄሣር ሲሆን፣ ግብር ለእርሱ የሚከፈለውም በዚሁ ገንዘብ ነበር።

22፥21 *የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር፤* ጌታ ኢየሱስ እንዲህ በማለቱ በቄሣርና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ትልቅ ልዩነት ግልጽ አድርጎአል፤ ከዚህም በላይ በሳንቲሙ ላይ የተጻፈውን (የቍ 19 ማብ ይመ) ሐሰተኛና ባዕድ አምልኮአዊ የይገባኛል ባይነት ስሜት መቃወሙ ይሆናል።

22፥24 *ሙሴ ... ብሎአል፤* ጌታ ኢየሱስ ከሰዱቃውያን ጋር ሲከራከር የጠቀሰው ከአምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ነው፤ ሰዱቃውያን ለእነዚህ መጻሕፍት የተለየ ክብሬታ ይሰጡ ነበርና (የማር 12፥18 ማብ ይመ)። ዘዳ25፥5-6 የተጠቀሰው ባሏ የሞተባት ሴት እንክብካቤ እንዳይጐድልባትና የዘር ሐረጉም እንዲቀጥል የሟቹ ወንድም እንዲያገባት የሚያዘውን ሕግ ነው።

*22፥25-40፤* ማር12፥18-31፤ ሉቃ20፥27-40 እና ማብ ይመ።

22፥37፡39 *ውደድ፤* የግሪኩ ግስ የሚያመለክተው በወዳጆች መካከል የሚኖረውን መፈቃቀር ሳይሆን፣ ለአንድ ሁኔታ ወይም ሰው መሰጠትን፣ አልፎ ተርፎም የውዴታ ግዴታ ውስጥ መግባትን ያመለክታል።

22፥37 *በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህ፤* በሁለመናህ ውደድ ማለት ነው። ዕብራይስጡ በዘዳ6፥5 ላይ "ልብ ... ነፍስ ... ኀይል" ይላል፤ አንዳንድ የሰባ ሊቃናት ትርጕም (ቅጂዎች) "ሐሳብ" የሚለውን ቃል ይጨምራሉ። ጌታ ኢየሱስ አራቱንም ቃላት በማር12፥30 ላይ አቀናጅቶታል።

22፥40 *ሕግና ነቢያት፤* የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት በሙሉ ማለት ነው (የ5፥17 ማብ ይመ)።

22፥41-46፤ የማር 12፥35-40 እና የሉቃ 20፥44-47 ማብ ይመ።

23፥2 *በሙሴ ወንበር ላይ ተቀምጠዋል፤* የሕግ መምህርነት ሥልጣን ተቀብለው፣ በሙሴ እግር የተተኩ ናቸው ማለት ነው።

ታቸው እንኳ አይነኩትም::
5“ለመታየት ሲሉ የሚያደርጉትን ሁሉ
በሰው ፊት ያደርጋሉ፤ አሸንክታባቸውን[ሎ]
ያሰፋሉ፤ የቀሚሳቸውን ዘርፍ ያስረዝማሉ::
6በግብዣ ቦታ የከበሬታ ስፍራ፣ በምኵራ
ብም የመጀመሪያውን መቀመጫ መያዝ
ይወዳሉ:: 7እንዲሁም በገበያ መካከል ሰላ
ምታ መቀበልንና በሰዎች እንደበት ‘መም
ህር’ ተብለው መጠራትን ይሻሉ::
8“እናንተ ግን ‘መምህር’ ተብላችሁ አትጠሩ፤
አስተማሪያችሁ አንድ ብቻ ሲሆን፣ እናንተ
ሁላችሁም ወንድማማቾች ናችሁና:: 9በሰ
ማይ ያለ አንድ አባት ስላላችሁ፣ በምድር
ማንንም ‘አባት’ ብላችሁ አትጥሩ:: 10መም
ህራችሁ አንዱ ክርስቶስ ስለሆነ፣ ‘መምህር’
ተብላችሁ አትጠሩ:: 11ከመካከላችሁ ከሁ
ላችሁ የሚበልጠው አገልጋያችሁ ይሆናል፤
12ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ይዋረዳል፣ ራሱን
የሚያዋርድ ግን ይከበራል::
13“እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህራ
ንና ፈሪሳውያን፤ ሰዎች ወደ መንግሥተ ሰማይ
እንዳይገቡ በሰዎች ላይ በሩን ስለምትዘጉባ
ቸው ወዮላችሁ! እናንተ ራሳችሁ አትገ
ቡም፤ መግባት የሚፈልጉትንም አታስገ
ቡም:: 14እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ መም
ህራንና ፈሪሳውያን፤ ወዮላችሁ! የመበለቶ
ችን ቤት እያራቈታችሁ፣ ለሰው ይምሰል
ረዥም ጸሎት ስለ ምታደርጉ የከፋ ፍርድ
ትቀበላላችሁ::*
15“እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህራ
ንና ፈሪሳውያን፤ አንድን ሰው ወደ አይ
ሁድ ሃይማኖት ለማስገባት በባሕርና በየብስ
ስለምትዞሩ፣ ባመነም ጊዜ ከእናንተ በእ
ጥፍ የባሰ የገሃነም ልጅ ስለምታደርጉት
ወዮላችሁ::
16“እናንተ ዕውር መሪዎች፤ ወዮላችሁ!
‘ማንም በቤተ መቅደስ ቢምል ምንም አይ
ደለም፤ ነገር ግን በቤተ መቅደሱ ውስጥ ባለው
ወርቅ ቢምል መሐላው ይደርስበታል’ ትላ
ላችሁ:: 17እናንተ የታወራችሁ ተላላዎች!
ከወርቁና ወርቁን ከቀደሰው ቤተ መቅደስ
የቱ ይበልጣል? 18እንዲሁም፣ ‘ማንም በመ

23፥5 ዘፀ13፥9፤ዘኍ15፥38፤ዘዳ6፥8፤22፥12፤ማቴ6፥1:2:5:16
23፥6 ሉቃ11፥43፤14፥7፤20፥46
23፥7 ቆ8፤ ማቴ 26፥25:49፤ ማር9፥5፤10፥51፤ዮሐ1፥38:49፤3፥2:26፤20፥16
23፥9 ሚል1፥6፤ ማቴ6፥9፤7፥11
23፥11 ማር9፥35
23፥12 1ሳሙ2፥8፤ መዝ18፥27፤ምሳ3፥34፤ ኢሳ57፥15፤ሕዝ21፥26፤ሉቃ1፥52፤14፥11
23፥13 ቆ15:23:25:27:29፤ሉቃ11፥52
23፥15 ማቴ5፥22፤ ሐሥ2፥11፤6፥5፤13፥43
23፥16 ቆ24፤ ኢሳ 9፥16፤ ማቴ5፥33-35፤15፥14
23፥17 ዘፀ30፥29

[ሎ]5 ከቅዱሳት መጻሕፍት የተወሰዱ ጥቅሶች የተጻፉበት በግንባርና በክንድ ላይ የሚታሰር ትንሽ ጥቅልል ነው

* አንዳንድ ትርጕሞች ይህን ክፍል አይጨምሩም

23፥5 *አሸንክታባቸውን፤* ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ አራት ምንባቦች ያሉት በግንባርና በክንድ ላይ የሚታሰር ክታብ ነበር (ዘፀ13፥1-10፤ 13፥11-16፤ ዘዳ6፥4-9፤ 11፥13-21)::

*23፥8-10፤* ወደ ትዕቢት የሚመራ የክብር ስም ለማግኘት የሚደረገውን ጥረት በመቃወም የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ነው:: እንዲህ ያለውን ትእዛዝ በሕይወታችን ስንፈጽም፣ ትእዛዙን በጥሬ ትርጕም ብቻ እንዳንመለከት መጠንቀቅ ይኖርብናል::

23፥15 *ከእናንተ በዕጥፍ የባሰ የገሃነም ልጅ፤* መዳን ሳያስገኝ እንዲያው መኰራራትንና ባዶ ትምክህትን ለሚያስከትል ውጫዊ የመንጻት ሥርዐት እጥፍ ድርብ የሚጓጓ ማለት ነው::

## (አራቱ) የአይሁድ ወገኖች

### ፈሪሳውያን

ምሥረታቸው ከሁለተኛው ምዕተ ዓመት ዓ.ቅ.ክ ይጀምራል
1.ቶራህን (የሙሴ መጻሕፍት) ጨምሮ ትውፊቶችን ሁሉ እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ይቀበላሉ::
2. ነጻ ፈቃድንና ውሳኔን በተመለከተ መካከለኛ አቋም አላቸው (በእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና በነጻ ፈቃድ መካከል)
3. መላእክትና አጋንንት በተራቀቀ የሥልጣን ተዋረድ እንደ ሚገኙ ይቀበላሉ::
4. ለሙታን የወደፊት ተስፋ እንዳላቸው ያስተምራሉ::
5. የነፍስን አለመጥፋትና ከሞት በኋላ ሽልማት ወይም ቅጣት እንዳለ ያምናሉ::
6. ለሰው እኩልነት የሚቆሙ ነበሩ::
7. የትምህርታቸው ትኵረት ከትምህርተ መለኮት ይልቅ ወደ ሥነ ምግባር ያዘነበለ ነው::

### ሰዱቃውያን

ምሥረታቸው በሀስሞንያን ዘመን እንደ ሆነ ይገመታል (ዓ.ቅ.ክ 166-63). በ70 ዓ.ም. ከኢየሩሳሌም ከተማ መፍረስ ጋር የእነርሱም እንቅስቃሴ አከተመ
1. በትውፊት ውስጥ ያሉ ሕግጋት አይደሉም ባዮች ናቸው::
2. ከፈሪሳውያን ይልቅ የሙሴን ሕግ ቃል በቃል ይተረጕማሉ::
3. በሌዋውያን የመንጻት ሥርዐት ላይ ያተኵራሉ::
4. ሁሉ ነገር በነጻ ፈቃድ እንደሚከናወን ያምናሉ::
5. የሙታን ትንሣኤም ሆነ የዘላለም ሕይወት እንዳለ አያምኑም::
6. መላእክትና አጋንንት እንዳሉ አያምኑም::
7. መንፈሳዊ ዓለም አለ የሚለውን ሐሳብ አይቀበሉም::
8. የሙሴ መጻሕፍትን ብቻ ቅዱሳት መጻሕፍት አድርገው ይቀበላሉ::

### ኤሴናውያን

ምናልባት ከሐሲዲምና ከፈሪሳውያን መካከል የተነሡ ይሆናሉ፤ በኋላም ከእነርሱ ተለዩ (1መቃብያን 2፥42፤ 7፥13) አክራሪና ቀናተኛ የአይሁድ ቡድን ሲሆኑ፣ መቃብያን በአሦራውያን ላይ ባመፁ ጊዜ ተባባሪዎች ነበሩ (ዓ.ቅ.ክ 165-155)
1. የቶራህን የመንጻት ሕግጋት/ሥርዐት በጥብቅ ይፈጽማሉ::
2. የንብረት ይዞታ በኅብረት መሆን አለበት በሚለው አቋማቸው ይታወቃሉ::
3. በጋራ ኀላፊነት ላይ ጠንካራ አቋም ነበራቸው::
4. ከቅዱሳት መጻሕፍታቸው ጥናት ጋር በየዕለቱ የአምልኮ ሥርዐት መፈጸም ዋነኛ ጕዳይ ነበር::
5. የጻድቅ ሕይወት ለመኖርና ታዛዥ ሆኖ ለመገኘት ጥብቅ የሆነ መሐላ ያደርጋሉ::
6. መሥዋዕቶች በተቀደሱ ቀናትና ወቅቶች ይቀርባሉ::
7. ጋብቻ በመመሪያ ደረጃ የተከለከለ ባይሆንም የተተወ ጕዳይ ነው::
8. ሁሉ ነገር በዕድል እንደሚከናወን ያምናሉ::

### ቀናዕያን

በ6 ዓ.ቅ.ክ በታላቁ ሄሮድስ ዘመነ መንግሥት የተጀመረና በ73 ዓ.ም በማሳዳ እንቅስቃሴውን ያቆመ ወገን ነው
1. መገዛት ለእግዚአብሔር ብቻ ነው በማለት ግብርን ለአረማዊ ገዥ አንከፍልም ብለው የተቃወሙ ናቸው::
2. ለአይሁድ ትውፊት መጠበቅ/መከበር በጽኑ የቆሙ ናቸው::
3. በፍልስጥኤም ምድር የግሪክን ቋንቋ ላለመናገር ያመፁ ናቸው::
4. የድነት ቀን እንደሚመጣ ይተነብዩ ነበር::

ሠዊያው ቢምል ምንም አይደለም፤ ነገር
ግን በላዩ ላይ ባለው መባ ቢምል መሐላው
ይደርስበታል’ ትላላችሁ፤ 19እናንተ ዕውሮች፤
ከመባውና መባውን ከቀደሰው መሠዊያ
የቱ ይበልጣል? 20ስለዚህ፣ በመሠዊያው
የማለ፣ በመሠዊያውና በላዩ ላይ ባለው
ሁሉ ይምላል:: 21እንዲሁም በቤተ መቅደሱ
የማለ፣ በቤተ መቅደሱና በውስጡ በሚያድ
ረው ይምላል:: 22በሰማይ የማለም በእግዚአ
ብሔር ዙፋንና በዙፋኑ ላይ በተቀመጠው
ይምላል::

23“እናንት ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህራ
ንና ፈሪሳውያን፤ ወዮላችሁ! ከአዝሙድ፣
ከእንስላልና ከከሙን ዐሥራት እየሰጣችሁ
በሕጉ ውስጥ ዋነኛ የሆኑትን ማለትም
ፍትሕን፣ ምሕረትንና ታማኝነትን ግን ንቃ
ችኋልና፤ እነዚያን ሳትተዉ እነዚህን ማድ
ረግ በተገባችሁ ነበር፤ 24እናንት የታወራ
ችሁ መሪዎች፤ ትንኝን አጥርታችሁ ትጥላ
ላችሁ፤ ግመልን ግን ትውጣላችሁ::

25“እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህራ
ንና ፈሪሳውያን፤ ወዮላችሁ! የጽዋውንና የወ
ጭቱን ውጭ ትወለውላላችሁ፤ በውስጣ
ቸው ግን ቅሚያና ስስት ሞልቶባቸዋል::
26አንተ ዕውር ፈሪሳዊ! አስቀድመህ የጽዋ
ውንና የወጭቱን ውስጥ አጽዳ፤ ከዚያም
ውጩ የጸዳ ይሆናል::

27“እናንት ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህራ
ንና ፈሪሳውያን፤ ውጫቸው በኖራ ተለስ
ነው የሚያምሩ፣ ውስጣቸው ግን በሙታን
ዐፅምና በብዙ ርኵሰት የተሞላ መቃብሮ
ችን ስለምትመስሉ ወዮላችሁ! 28እናንተም
በውጭ ለሰዎች ጻድቃን ትመስላላችሁ፤
ውስጣችሁ ግን በግብዝነትና በክፋት የተ
ሞላ ነው::

29“እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህራንና
ፈሪሳውያን፤ ወዮላችሁ! የነቢያትን መቃ
ብር እየገነባችሁ፣ የጻድቃንንም ሐውልት
እያስጌጣችሁ፣ 30‘በአባቶቻችን ዘመን ብን
ኖር ኖሮ፣ የነቢያትን ደም በማፍሰስ አንተ
ባበራቸውም ነበር’ ትላላችሁና:: 31በዚህም

23፥19 ዘፀ29፥37
23፥21 1ነገ8፥13፤
መዝ26፥8
23፥22 መዝ11፥4፤
ማቴ5፥34
23፥23 ዘሌ27፥30፤
ሚክ6፥8፤ሉቃ11፥42
23፥24 ቊ16
23፥25 ማር7፥4፤
ሉቃ11፥39
23፥27 ሉቃ11፥44፤
ሐሥ23፥3
23፥29
ሉቃ11፥47 :48
23፥31 ማቴ5፥12
23፥32 ሕዝ20፥4፤
1ተሰ2፥16
23፥33 ማቴ3፥7፤
5፥22፤12፥34
23፥34 2ዜና36፥
15:16፤ማቴ10፥17:
23፤ሉቃ11፥49
23፥35 ዘፍ4፥8፤
2ዜና24፥21፤ዘካ1፥1፤
ዕብ11፥4
23፥36
ማቴ10፥23፤
24፥34፤ሉቃ
11፥50:51

23፥37 2ዜና24፥21
፤መዝ57፥1፤61፥4፤
ኢሳ31፥5፤ማቴ5፥12
23፥38 1ነገ9፥7-8፤
ኤር22፥5
23፥39መዝ118፥26
፤ማቴ21፥9
24፥2 ሉቃ19፥44
24፥3 ማቴ13፥39
፤21፥1፤28፥20፤
ሉቃ 17፥30

የነቢያት ገዳዮች ለነበሩት አባቶቻችሁ
ልጆች መሆናችሁን በራሳችሁ ላይ ትመሰ
ክራላችሁ::32እንግዲህ የአባቶቻችሁን ጅምር
ተግባር ከፍጻሜ አድርሱ!

33“እናንተ እባቦች፤ የእፉኝት ልጆች! ከገ
ሃነም ፍርድ እንዴት ልታመልጡ ትችላላ
ችሁ? 34ስለዚህ ነቢያትን፣ ጠቢባንንና መምህ
ራንን እልክላችኋለሁ፤ ከነዚህም አንዳንዶቹን
ትገድላላችሁ፤ አንዳንዶቹን ትሰቅላላችሁ፤
ሌሎቹንም በምኵራቦቻችሁ ትገርፏቸዋላ
ችሁ፤ ከከተማ ወደ ከተማ ታሳድዷቸዋላ
ችሁ:: 35ስለዚህ፣ ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ
በመቅደሱና በመሠዊያው መካከል እስከ
ገደላችሁት እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካ
ርያስ ደም ድረስ በምድር ላይ ለፈሰሰው ንጹሕ
ደም ሁሉ እናንተ ተጠያቂዎች ናችሁ::
36እውነት እላችኋለሁ፤ ላለፈው ነገር ሁሉ
ይህ ትውልድ ይጠየቅበታል::

37“አንቺ ነቢያትን የምትገድዪ፣ ወደ
አንቺ የተላኩትንም በድንጋይ የምትወግሪ
ኢየሩሳሌም ሆይ፤ አንቺ ኢየሩሳሌም! ዶሮ
ጫጩቶቿን በክንፎቿ ሥር እንደምትሰበ
ስብ፣ ልጆችሽን ለመሰብሰብ ስንት ጊዜ
ፈለግሁ! እናንተ ግን ፈቃደኛ አልሆናች
ሁም፤ 38እነሆ፤ ቤታችሁ ወና ሆኖ ይቀርላ
ችኋል! 39እላችኋለሁና፤ ‘በጌታ ስም የሚ
መጣ የተባረከ ነው’ እስክምትሉ ድረስ ዳግ
መኛ አታዩኝም::”

### የዓለም መጨረሻ ምልክቶች

24፥1-51 ተጓ ምብ-ማር13፥1-37፤ ሉቃ21፥5-36

24 ኢየሱስ ከቤተ መቅደስ ወጥቶ ሲሄድ፣
ደቀ መዛሙርቱ የቤተ መቅደሱን
ሕንጻ ሊያሳዩት ወደ እርሱ ቀረቡ:: 2እርሱ
ግን፣ “ይህን ሁሉ ታያላችሁ? እውነት እላ
ችኋለሁ፤ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ተክቦ የም
ታዩት፣ ሳይፈርስ እንዲህ እንዳለ የሚቀር
አንድ ድንጋይ እንኳ አይኖርም” አላቸው::
3በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ተቀምጦ ሳለ፣
ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ
ቀርበው “እስቲ ንገረን፤ የምትለው ሁሉ
መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨ

*23፥23፤* ኢየሱስ እያንዳንዱን ጥቃቅን ሕግ መፈጸምን አልነቀፈም፤ እንዲያውም፣ አንዱንም ሳትተዉ አድርጉ ብሎአል፤ እርሱ የተቃወመው ግን ለታይታ የሆነውን የሕግ አከባበር ነው (የ5፥18-20 ማብ ይመ)::

23፥24 *አጥርታችሁ ትጥላላችሁ፤* አንድ ወግ አጥባቂ ፈሪሳዊ፣ ከነፍሳት አነስተኛና በመንጻቱ ሕግ መሠረት ንጹሕ ያልሆነችውን ትንኝ በሚጠጣው ውሃ ውስጥ እንዳትገኝ ውሃውን በማጥለያ ጨርቅ ያጠላል፤ ነገር ግን በምሳሌው እንደ ተጠቀሰው፣ ይህ ሰው ከትላልቅ እንስሳት መካከል አንዱ የሆነውን ግመል ይውጣል::

23፥27 *በኖራ ተለስነው ... መቃብሮች፤* አንድ ሰው በመቃብር ላይ ተራምዶ ቢያልፍ፣ በመንጻት ሕግ መሠረት ስለሚረክስ (ዘኍ19፥16 ይመ)፣ መቃብሮች በተለይ ሌሊት ጐልተው እንዲታዩ ኖራ ይለሰኑ ነበር::

23፥35 *ከአቤል ... እስከ ዘካርያስ፤* ስለ አቤል ሞት ተጽፎ የሚገኘው በዘፍ4፥8 ላይ ነው፤ ስለ ዮዳሄ ልጅ ስለ ዘካርያስ ሞት ደግሞ በ2ዜና24፥20-22 ተጽፎአል:: በአይሁድ የቅዱሳት መጻሕፍት ቅደም ተከተል፣ መጽሐፈ ዜና መዋዕል የብሉይ ኪዳን የመጨረሻ መጽሐፍ ነው:: “ከአቤል ... እስከ ዘካርያስ” የሚለው አባባል፣ እኛ “ከዘፍጥረት እስከ ራእይ” እንደምንለው ዓይነት ነው::

ጌታ ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተገለጸውን የሰማዕት ታሪክ አጠቃሉ ማቅረቡ ነው::

*24፥1-25፥46፤* ጌታ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ያስተማረው ይህ ትምህርት በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ከሚገኙት ዐበይት ትረካዎች አምስተኛውና የመጨረሻው ነው (የ 5፥1-7፥29፤ የማር 13፥1-37 ማብ ይመ)::

24፥2 *አንድ ድንጋይ እንኳ አይኖርም፤* በ70 ዓ.ም. በቲቶ መሪነት ሮማውያን ኢየሩሳሌምንና የቤተ መቅደሱን ሕንጻ ፈጽመው ባወደሙት ጊዜ ትንቢቱ ቃል በቃል ተፈጽሞአል:: ቤተ መቅደሱን ባቃጠሉት ጊዜ ከጣራው ቀልጦ የሚወርደውን ወርቅ ለማግኘት፣ ድንጋዮቹን እየፈረካከሱ ይፈልጉ ነበር:: *ድንጋይ፤* የማር13፥1 ማብ ይመ:: *ሳይፈርስ፤* እ.ኤ.አ በ1968 በተደረገው ቍፋሮ ወራሪዎች ካፈረሱት ሕንጻ የተቀበሩ ብዙ ድንጋዮች ተገኝተዋል::

*24፥3 በደብረ ዘይት ተራራ፤* የወይራ ዛፍ ያለበት ተራራ ማለት ነው፤ ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ ካለው ከቄድሮን ሸለቆ ራቅ ብሎ የሚገኝ፣ ርዝመቱ ሁለት ኪ.ሜ. ያህል፣ ከፍታውም ከኢየሩሳሌም ከተማ በላይ 62 ሜትር ያህል ከፍ የሚል ጕብታ ነው (የማር11፥1 ማብ ይመ):: *መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክትስ ምንድን ነው?* ኢየሱስ ለእነዚህ ሁለት

ረሻ ምልክትስ ምንድን ነው?" አሉት።
4ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
"ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፤ 5ብዙ
ዎች፣ 'እኔ ክርስቶስ[~] ነኝ' በማለት በስሜ
ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ። 6ስለ
ጦርነትና ጦርነትን የሚያናፍስ ወሬ ትሰ
ማላችሁ፤ እነዚህ ነገሮች የግድ መፈጸም
አለባቸው፤ ሆኖም መጨረሻው ገና ስለ ሆነ
በዚህ እንዳትደናገጡ ተጠንቀቁ። 7ሕዝብ
በሕዝብ ላይ፣ መንግሥትም በመንግሥት
ላይ ይነሣል፤ በተለያየ ስፍራም ራብና የመ
ሬት መንቀጥቀጥ ይሆናል፤ 8ይህ ሁሉ ግን
የምጡ መጀመሪያ ነው።
9"በዚያን ጊዜ ለመከራ አሳልፈው ይሰጧ
ችኋል፣ ይገድሏችኋል፣ በስሜ ምክንያት
በሕዝብ ሁሉ ዘንድ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ።
10በዚያን ጊዜ ብዙዎች ይሰናከላሉ፤ እርስ
በርስ አሳልፈው ይሰጣጣሉ፤ ይጠላላሉም።
11ብዙዎች ሐሰተኛ ነቢያት ይነሣሉ፤ ብዙ
ዎችን ያስታሉ። 12ክፋት ስለሚገን የብዙ
ሰዎች ፍቅር ይቀዘቅዛል፤ 13እስከ መጨረሻ
የሚጸና ግን እርሱ ይድናል። 14ለሕዝብ ሁሉ
ምስክር እንዲሆን፣ ይህ የመንግሥት ወን
ጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፤ ከዚያም
መጨረሻው ይመጣል።
15"እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተነገረው፣
'የጥፋት ርኩሰት' በተቀደሰው ስፍራ ቆሞ
ስታዩ፣ አንባቢው ያስተውል። 16በዚያን ጊዜ
በይሁዳ የሚገኙ ወደ ተራራዎች ይሽሹ፤
17በቤቱ ጣራ ላይ የሚገኝ ማንም ሰው ዕቃ
ውን ከቤቱ ለማውጣት አይውረድ፤ 18በዕ
ርሻ ቦታው የሚገኝ ማንም ሰው ልብሱን
ለመውሰድ አይመለስ። 19'በእነዚያ ቀናት
ለነፍሰ ጡሮችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው!
20እንግዲህ ሽሽታችሁ በክረምት ወይም በሰ
ንበት ቀን እንዳይሆን ጸልዩ፤ 21በዚያን ጊዜ፣
ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ
ሆኖ የማያውቅ፣ ከዚያም በኋላ የሚስተካ
ከለው የሌለ፣ ታላቅ መከራ ይሆናል። 22ቀኖቹ
ባያጥሩ ኖሮ ሥጋ ለባሽ ሁሉ ባልተረፈ
ነበረ፤ ስለ ተመረጡት ሲባል ግን እነዚያ
ቀኖች ያጥራሉ። 23በዚያን ጊዜ ማንም፣
'ይኸውላችሁ ክርስቶስ እዚህ አለ' ወይም
'እዚያ አለ' ቢላችሁ አትመኑ፤ 24ሐሰተኛ
ክርስቶሶችና ሐሰተኛ ነቢያት ይነሣሉና፤ ቢቻል
የተመረጡትን ለማሳት ሲሉ ታላላቅ ምል
ክቶችንና ታምራትን ያደርጋሉ። 25እነሆ፤
አስቀድሜ ነግሬአችኋለሁ።
26"ስለዚህ፣ 'ያውላችሁ እበረሐው ውስጥ
አለላችሁ' ቢሏችሁ ወደዚያ አትውጡ፤ 'ይኸ
ውላችሁ እልፍኝ ውስጥ አለላችሁ' ቢሏችሁ
አትመኑ፤ 27መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ ምዕ
ራብ ድረስ እንደሚያበራ፣ የሰው ልጅ
አመጣጥም እንደዚሁ ይሆናል። 28በድን ባለ
በት ስፍራ ሁሉ አሞሮች ይሰበሰባሉ።
29"ወዲያውኑ ከእነዚያ ከመከራው ቀናት
በኋላ፣ 'ፀሐይ ትጨልማለች፤
ጨረቃ ብርሃኗን ትከለክላለች፤
ከዋክብት ከሰማይ ይረግፋሉ፤
የሰማይ ኃይላትም ይናጋሉ።'
30"በዚህ ጊዜ የሰው ልጅ ምልክት በሰ
ማይ ላይ ይታያል፤ የምድር ወገኖች ሁሉ
ያለቅሳሉ፤ የሰው ልጅም በሰማይ ደመና
ሆኖ በኀይልና በታላቅ ክብር ሲመጣ ያዩ
ታል፤ 31መላእክቱንም ከታላቅ የመለከት
ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፤ እነርሱም ምርጦቹን
ከአራቱም ነፋሳት፣ ከሰማያት ከአንዱ
ዳርቻ ወደ ሌላው ዳርቻ ይሰበስባሉ።
32"ከበለስ ዛፍ ይህን ትምህርት ተማሩ፤
ቅርንጫፏ ሲለመልም፣ ቅጠሏ ሲያቈጠ
ቍጥ፣ ያን ጊዜ በጋ እንደተቃረበ ታውቃላ
ችሁ። 33እንደዚሁም እነዚህን ሁሉ ስታዩ፣
እርሱ በደጅ እንደ ቀረበ ታውቃላችሁ።
34እውነት እላችኋለሁ፤ ይህ ሁሉ እስኪፈጸም

[~]5 ወይም መሲሕ፤ ቍ23 ይመ

24፥4 ማር13፥5
24፥5 ቍ11፡23፡ 24፤1ዮሐ2፥18
24፥7 ኢሳ19፥2፤ ሐሥ11፥28
24፥9 ማቴ10፥17፤ ዮሐ15፥21፤16፥2
24፥11 ማቴ7፥15፤ ማር13፥5
24፥13 ማቴ10፥22
24፥14 ማቴ4፥23፤ ሉቃ2፥1፤4፥5፤ ሐሥ 11፥28፤ 17፥6፤ሮሜ10፥18፤ራ እ3፥10፤ 16፥14
24፥15 ዳን9፥27፤ 11፥31፤12፥11፤ ሐሥ 6፥13
24፥17 1ሳሙ9፥25 ፤ማቴ10፥27፤ሉቃ 12፥3፤ሐሥ10፥9
24፥19 ሉቃ23፥29
24፥21 ሕዝ5፥9፤ ዳን 12፥1፤ኢዩ2፥2
24፥22 ቍ24፥31
24፥23 ሉቃ17፥23፤ 21፥8
24፥24 ዘፀ7፥11፡22 ፤2ተሰ2፥9-11፤ ራእ13፥13፤ 16፥14፤19፥20
24፥27 ሉቃ17፥24፡ 30፤ማቴ8፥20
24፥28 ሉቃ17፥37
24፥29 ኢሳ13፥10፤ 34፥4፤ሕዝ32፥7፤ኢዩ 2፥10፡31፤ሶፎ1፥15፤ ራእ6፥12፡13፤8፥12
24፥30 ራእ1፥7
24፥31 ኢሳ27፥13፤ ዘካ9፥14፤ማቴ13፥41፤ 1ቆሮ15፥52፤1ተሰ4፥ 16፤ራእ8፥2፤10፥7፤ 11፥15
24፥33 ያዕ5፥9
24፥34ማቴ16፥28፤ 23፥36

ጥያቄዎች መልስ ቢሰጥም፣ በተናጠል አያብራራቸውም። ይሁን እንጂ፣ ስለ ዘመኑ ፍጻሜ በቍ4-14፣ ስለ ኢየሩሳሌም መውደም በቍ15-22 (ሉቃ21፥20 ይመ)፣ ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት በቍ23-31 የተገለጸ ይመስላል።

24፥8 *የምጡ፤* የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን፣ መሲሑ ከመምጣቱ በፊት "ምጥ" ይኸውም መከራ ቀድሞ እንደሚከሠት ይናገሩ ነበር።

24፥15 *የጥፋት ርኩሰት፤* የተቀደሰችውን ስፍራ የሚያረክስ አስጸያፊ ነገር ማለት ነው። በመጀመሪያ በዳንኤል ትንቢት የተጠቀሰው ሐሳብ የሚያመለክተው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ168 ዓመት የሆነውን ነው፤ ይህም አንጥያቆስ አጲፋነስ በኢየሩ ሳሌም ቤተ መቅደስ መሠዊያ ላይ "ዜዎስ" ለተባለው ጣዖት መሠዊያ ባቆመ ጊዜ ነበር (ዳን9፥27፤ 11፥31፤ 12፥11፤ ይመ)። አንዳንድ ሊቃውንት በትንቢተ ዳንኤልና በማቴዎስ ወንጌል የተ ነገሩት ትንቢቶች በተከታታይ፣ በሁለት ደረጃ የሚፈጸሙበት ጊዜ እንዳለ ይናገራሉ፤ 1) በ70 ዓ.ም. የቤተ መቅደሱ በሮማውያን እጅ መውደም፤ 2) የክርስቶስ ተቃዋሚ የሆነው የሐሳዊ መሲሑ ምስል በኢየሩሳሌም መቆም (2ተሰ2፥4፤ ራእ13፥14-15 ይመ፤ እንዲሁም የዳን9፥25-27፤ 11፥31 ማብ ይመ)።

24፥16 *ተራራዎች፤* "ፔላ" የተባለ ከተማ በነበረበት አካ ባቢ፣ ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉ ተራራዎች ናቸው። በ70 ዓ.ም. ከነበ ረው የሮማውያን ወረራ ትንሽ ቀደም ብሎ፣ ኢየሩሳሌምን በከ በቡአት ጊዜ በከተማዋ የነበሩት ክርስቲያኖች ወደዚሁ ተራራ ሸሽተው ነበር። አንዳንዶች ወደ ፊት በሚመጣ ሌላ የመከራ ዘመን፣ ተመሳሳይ ሽሽት ይደርሳል ብለው ያምናሉ (ዳን9፥27 ላይ ከተጠቀሰው ከ70ኛው "ሱባዔ" ጋር አንድ ነው ይላሉ)።

24፥20 *በሰንበት፤* ይህን ያከለው ማቴዎስ ብቻ ነው፤ ምክ ንያቱም ማቴዎስ ወንጌሉን የጻፈው፣ በሰንበት ቀን ከ800 ሜትር ያህል በላይ እንዳይጓዙ ለታዘዙት፣ ለአይሁድ ስለ ነበር ነው።

24፥21 *የሚስተካከለው የሌለ፣ ታላቅ መከራ፤* በዚያን ወቅት የነበረው አይሁዳዊ ታሪክ ጸሐፊ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን የኢ የሩሳሌምን ውድመት ከብዙ በጥቂቱ በዚህ መልክ ይገልጻል። አንዳንዶች ደግሞ ይህ የሚያመለክተው ወደ ፊት የሚመጣውንም ታላቅ መከራ ጭምር ነው ይላሉ (ዳን12፥1 ይመ)።

24፥22 *ስለ ተመረጡት፤* የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያመለክ ታል። *ቀኖቹ ባያጥሩ ኖሮ፤* አንዳንዶች መከራው እጅግ የከፋ በመሆኑ፣ ጊዜው ቢራዘም አንድም የሚተርፍ ሰው እንደማይኖር ይናገራሉ፤ ሌሎች ደግሞ አስቀድሞ የተወሰነው የጊዜ ገደብ እንደሚያጥር ኢየሱስ እዚህ ላይ ማመልከቱ ነው ይላሉ (ለምሳሌ በዳን9፥27 ላይ የተገለጸው ሰባኛው "ሱባዔ" ወይም በራእ11፥2፤ 13፥5 ላይ የተጠቀሰው አርባ ሁለቱ ወራት)።

24፥28 *ባለበት ... አሞሮች ይሰበሰባሉ፤* አሞሮች በበድን ዙሪያ ሲሰበሰቡ በግልጽ እንደሚታይ ሁሉ የክርስቶስ ዳግም ምጽአትም በይፋ የሚታይ ይሆናል (ይህ አባባል መለስተኛ በሆነ ልዩነት የተመለከተበትን የሉቃ17፥37 ማብ ይመ)።

24፥29፤ የማር13፥25 ማብ ይመ።

24፥30 *የሰው ልጅ፤* የማር8፥31 ማብ ይመ።

ድረስ ይህ ትውልድ[ሠ] አያልፍም:: [35]ሰማይና
ምድር ያልፋሉ፤ ቃሌ ግን ፈጽሞ አያልፍም::

### የሚመጣበት ቀንና ሰዓት አለመታወቁ

24፥37-39 ተጓ ምብ - ሉቃ 17፥26:27
24፥45-51 ተጓ ምብ - ሉቃ 12፥42-46

[36]ያን ቀንና ሰዓት ግን ከአብ በስተቀር
የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ፣ ወልድም ቢሆን[ሐ]
ማንም አያውቅም:: [37]ልክ በኖኅ ዘመን
እንደ ሆነው የሰው ልጅ መምጣትም እን
ደዚሁ ይሆናል፤ [38]ከጥፋት ውሃ በፊት ኖኅ
ወደ መርከቡ እስከገባበት ቀን ድረስ ሰዎች
ሲበሉና ሲጠጡ፣ ሲያገቡና ሲጋቡ እንደ
ነበሩ፣ [39]እስከዚያ ጊዜ ድረስም ምን እንደ
ሚመጣ ሳያውቁ ድንገት የጥፋት ውሃ እን
ዳጥለቀለቃቸው፣ የሰው ልጅ ሲመጣም
እንደዚሁ ይሆናል:: [40]በዚያን ጊዜ ሁለት
ሰዎች በዕርሻ ላይ ይውላሉ፤ አንዱ ይወሰ
ዳል፤ ሌላው ይቀራል:: [41]ሁለት ሴቶች በወ
ፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዷ ትወሰዳለች፣ ሌላዋ
ትቀራለች::

[42]"እንግዲህ ጌታችሁ የሚመጣበትን ቀን
ስለማታውቁ ነቅታችሁ ጠብቁ:: [43]ይህን
ልብ በሉ፤ ባለቤት ሌሊት ሌባ በየትኛው
ሰዓት እንደሚመጣ ቢያውቅ ኖሮ፣ በንቃም
ቤቱም እንዳይደፈር በተጠባበቀ ነበር::
[44]የሰው ልጅም ባላሰባችሁት ሰዓት ይመጣ
ልና እናንተም እንደዚሁ ዝግጁ ሁኑ::
[45]"በተገቢው ጊዜ ምግባቸውን እንዲሰጣ
ቸው ባለቤቱ በቤተ ሰዎቹ ላይ የሾመው
ታማኝና ብልኅ አገልጋይ እንግዲህ ማነው?
[46]ባለቤቱ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ የተጣ
ለበትን ዐደራ እየፈጸመ የሚያገኘው ያ አገ
ልጋይ የተባረከ ነው፤ [47]እውነት እላችኋ
ለሁ፤ በንብረቱ ሁሉ ላይ ይሾመዋል::
[48]ነገር ግን ያ አገልጋይ ክፉ ቢሆንና ለራሱ፣
'ጌታዬ ይዘገያል' በማለት፣ [49]ተነሥቶ
ሌሎች አገልጋይ ባልንጀሮቹን መምታት
ቢጀምር፣ ከሰካራሞችም ጋር ቢበላና ቢጠጣ፣
[50]እርሱ ባልጠበቀው ቀንና ባላሰበው ሰዓት
ጌታው መጥቶ፣ [51]ይቈራርጠዋል፤ ዕድል ፈን
ታውንም ከግብዞች ጋር ያደርግበታል፤ በዚ
ያም ልቅሶና ጥርስ ማፏጨት ይሆናል::

### የዐሥሩ ልጃገረዶች ምሳሌ

25 "በዚያን ጊዜ መንግሥተ ሰማይ
መብራታቸውን ይዘው ሙሽራውን
ሊቀበሉ የወጡ ዐሥር ልጃገረዶችን ትመ
ስላለች:: [2]ከእነርሱም አምስቱ ልጃገረዶች
ዝንጉዎች፣ አምስቱ ደግሞ አስተዋዮች
ነበሩ፤ [3]ዝንጉዎቹ መብራት ይዘው መጠ
ባበቂያ ዘይት አልያዙም ነበር:: [4]አስተዋ
ዮቹ ግን ከመብራታቸው ጋር መጠባበቂያ
ዘይት በማሰሮ ይዘው ነበር:: [5]ሙሽራው
በዘገየ ጊዜ፣ ሁሉም እንቅልፍ ተጫጫናቸ
ውና ተኙ::

[6]"እኩለ ሌሊት ላይ፣ 'ሙሽራው እየመጣ
ነው፤ ወጥታችሁ ተቀበሉት!' የሚል ጥሪ ተሰማ።
[7]"በዚህ ጊዜ ልጃገረዶቹ ሁሉ ተነሥተው
መብራቶቻቸውን እየተረኰሱ መዘጋጀት
ያዙ:: [8]ዝንጉዎቹ አስተዋዮቹን፣ 'መብራታ
ችን ሊጠፋብን ስለሆነ፣ ከዘይታችሁ ስጡን'
አሏቸው::

[9]"አስተዋዮቹ ልጃገረዶች ግን መልሰው፣
'ያለን ዘይት ለእኛም ለእናንተም ላይበቃ
ስለሚችል፣ ሄዳችሁ ከሻጮች ለራሳችሁ
ግዙ' አሏቸው::

[10]"ዘይት ሊገዙ እንደ ሄዱ፣ ሙሽራው
መጣ፤ ተዘጋጅተው የነበሩት ልጃገረዶችም
ወደ ሰርጉ ግብዣ አብረውት ገቡ፤ በሩም
ተዘጋ::

[11]"ዘግየት ብለው ሌሎቹ ልጃገረዶች
መጥተው፣ 'ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ በሩን
ክፈትልን' አሉ::

[12]"እርሱ ግን መልሶ፣ 'እውነት እላችኋ
ለሁ፣ አላውቃችሁም' አላቸው::

[13]"እንግዲህ ቀኑን ወይም ሰዓቱን ስለማ
ታውቁ ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ::

### የሰነፉ አገልጋይ ምሳሌ

25፥14-30 ማመ - ሉቃ 19፥12-27

[14]"የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋዮቹን
ጠርቶ ያለውን ንብረት በዐደራ በመስጠት
ወደ ሌላ አገር ሊሄድ የተነሣ አንድ ሰውን
ትመስላለች፤ [15]ለእያንዳንዱ እንደ ችሎ
ታው በመደልደል ለአንዱ አምስት ታላ
ንት፣[ሀ] ለሌላው ሁለት፣ ለሌላው ደግሞ
አንድ ታላንት ሰጥቶ ጒዞውን ቀጠለ::
[16]አምስት ታላንት የተቀበለው ሰውዬ ወዲ
ያው በገንዘቡ ንግድ ጀምሮ አምስት ታላ
ንት አተረፈ፤ [17]እንዲሁም ሁለት ታላንት

[ሠ]34 ወይም ዘር
[ሐ]36 አንዳንድ ቅጆች ወልድም ቢሆን የሚለው የላቸውም
[ሀ]15 አንድ ታላንት በሺህ የሚቈጠር ብር የሚያህል ነው

24፥35 ማቴ5፥18
24፥36 ሐሥ1፥7
24፥37 ዘፍ6፥5፤
7፥6-23
24፥38 ማቴ22፥30
24፥39 ሉቃ17፥30
24፥40 ሉቃ17፥34
24፥41 ሉቃ17፥35
24፥42
ማቴ25፥13፤
ሉቃ12፥40
24፥43 ሉቃ12፥39
24፥44 1ተሰ5፥6
24፥45
ማቴ25፥21 :23
24፥46 ራእ16፥15
24፥47
ማቴ25፥21 :23
24፥49 ሉቃ21፥34
24፥51 ማቴ 8፥12
25፥1 ማቴ13፥24፤
ሉቃ12፥35-38፤ሐሥ
20፥8፤ራእ4፥5፤19፥7፤
21፥2
25፥2 ማቴ24፥45
25፥5 1ተሰ5፥6
25፥8 ሉቃ12፥35
25፥10 ራእ19፥9
25፥12 ቍ41፤
ማቴ7፥23
25፥13 ማቴ24፥42
:44፤ማር13፥35፤ሉቃ
12፥40
25፥14 ማቴ21፥33
፤ሉቃ19፥12
25፥15
ማቴ18፥24:25

24፥34 *ይህ ትውልድ፤* የማር13፥30 እና የሉቃ21፥32 ማብ ይመ::

24፥36 *ወልድም ቢሆን፤* የማር13፥32 ማብ ይመ::

25፥1 *ዐሥር ልጃገረዶችን፤* ሙሽራይቱ ሙሽራውን እንድ ትቀበል የሚያዘጋጇት ሴት ሚዜዎች ናቸው:: *መብራታቸው፤* በረጅም እንጨት ጫፍ ላይ በዘይት የተነከረ እራፊ ጨርቅ የተጠመጠመበት ማብሪያ ነበር:: (ከሸክላ የተሠራ አነስተኛ ፋና ከግቢ ውጭ ለሚደረግ ጒዞ አገልግሎቱ እጅግም ነው::)

25፥3 *ዘይት፤* የወይራ ዘይት ነው:: ምሳሌው ላይ የተጠቀ ሰው ዘይት እውነተኛ እምነትን፣ ጽድቅንና በአማኙ ዘንድ የመን ፈስ ቅዱስን መገኘት ያመለክታል::

25፥7 *እየተረኰሱ፤* የተቃጠለውን ክር ወይም ጨርቅ ኵስ ትረው እያስወገዱ ዘይት ጨመሩበት ማለት ነው::

25፥9 *ላይበቃ ስለሚችል፤* ፋናዎች እየበሩ እንዲቆዩ ከተ ፈለገ፣ ብዙ ዘይት ያስፈልጋቸዋል፤ ዘይቱም በተወሰነ ደቂቃ መተካት ነበረበት:: የዐሥሩ ልጃገረዶች ምሳሌ በእምነት መጽናት አስፈላጊ እንደ ሆነና በመንፈሳዊ ረገድም ዝግጁነትን የሚጠይቅ መሆኑን ያመለክታል፤ ዘወትር ተዘጋጅቶ መጠበቅ የሚያስፈል ገው ክርስቶስ ዳግም የሚመጣበት ቀን ስለማይታወቅ ነው::

25፥13 *ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ፤* ጌታ በዚህ ክፍል የሰጠው የዐሥሩ ቈነጃጅት (ልጃገረዶች) ምሳሌ፣ አማኞች ለዳግም ምጽአት ምን ያህል መዘጋጀት እንደ አለባቸው የሚያስረዳ ነው:: ምክን ያቱም ቀኒቱንና ሰዓቲቱን አስቀድሞ የሚያውቅ ስለሌለ ነው::

25፥15 *ታላንት፤* ይህ ቃል አስቀድሞ ለክብደት መለኪያ ያገለግል ነበር (34 ኪ.ግ. ያህል) ነበር፤ ቀጥሎም የሳንቲም ገንዘብ ዋጋ መግለጫ ሆነ::

የተቀበለው ሁለት አተረፈ፤ [18]አንድ ታላ
ንት የተቀበለው ግን መሬት ቈፍሮ የጌታ
ውን ገንዘብ ደበቀ።
[19]"የአገልጋዮቹም ጌታ ከብዙ ጊዜ በኋላ
ከሄደበት ተመልሶ የሰጣቸውን ገንዘብ ተሳ
ሰበ። [20]አምስት ታላንት የተቀበለውም፣
ሌላ አምስት ተጨማሪ ታላንት ይዞ በመ
ቅረብ፣ 'ጌታ ሆይ! አምስት ታላንት ዐደራ
ሰጥተኸኝ ነበር፤ ይኸውልህ አምስት ተጨ
ማሪ ታላንት አትርፌአለሁ' አለው።
[21]"ጌታውም፣ 'ደግ አድርገሃል፤ አንተ
መልካም ታማኝ አገልጋይ፤ በትንሽ ነገር
ላይ ታማኝ ስለሆንህ በብዙ ነገር ላይ እሾ
ምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ' አለው።
[22]"እንዲሁም ሁለት ታላንት የተቀበለው
አገልጋይ ቀርቦ፣ 'ጌታ ሆይ፤ ሁለት ታላ
ንት ሰጥተኸኝ ነበር፤ ይኸው ሁለት ተጨ
ማሪ ታላንት አትርፌአለሁ' አለው።
[23]"ጌታውም፣ 'ደግ አድርገሃል፤ አንተ
መልካም ታማኝ አገልጋይ፤ በትንሽ ነገር
ላይ ታማኝ ስለ ሆንህ በብዙ ነገር ላይ እሾ
ምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ' አለው።
[24]"አንድ ታላንት የተቀበለው አገልጋይ
ቀርቦ፣ 'ጌታ ሆይ፤ አንተ ካልዘራህበት የም
ታጭድ፣ ካልበተንህበትም የምትሰበስብ
ጨካኝ ሰው መሆንህን ዐውቃለሁ፤ [25]ስለዚህ
ፈራሁህ፤ ሄጄም መሬት ቈፍሬ ታላንትህን
ጉድጓድ ውስጥ ደበቅሁት፤ ገንዘብህ ይኸው
ልህ' አለው።
[26]"ጌታውም መልሶ፣ 'አንተ ክፉ፣ ሰነፍ
አገልጋይ፤ ካልዘራሁበት የማጭድ፣ ካልበተ
ንሁበትም የምሰበስብ መሆኔን ታውቅ ኖሮ
አል? [27]ታዲያ፣ በምመለስበት ጊዜ ገንዘ
ቤን ከነወለዱ እንዳገኘው ለለዋጮች መስጠት
ይገባህ ነበር!!
[28]'በሉ እንግዲህ ታላንቱን ወስዳችሁ ዐሥር
ታላንት ላለው ስጡ፤ [29]ላለው ይጨመር
ለታል፤ የተትረፈረፈም ይኖረዋል፤ ከሌለው
ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል። [30]ይህን
የማይረባ አገልጋይ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት
ወዳለበት በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጥ
ታችሁ ጣሉት' አለ።

## የመጨረሻው ፍርድ

[31]"የሰው ልጅ ከመላእክቱ ሁሉ ጋር በክ
ብሩ ሲመጣ፣ በክብሩ ዙፋን ላይ ይቀመ
ጣል፤ [32]ሕዝቦች ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤
እርሱም፣ እረኛ በጎችን ከፍየሎች እንደ
ሚለይ፣ ሕዝቡን አንዱን ከሌላው ይለ
ያል፤ [33]በጎቹን በቀኙ፣ ፍየሎቹን ግን በግራው
ያቆማቸዋል።
[34]"በዚያን ጊዜ ንጉሡ በቀኙ በኩል ያሉ
ትን እንዲህ ይላቸዋል፤ 'እናንት አባቴ የባ
ረካችሁ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተዘ
ጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ፤ [35]ምክንያ
ቱም ተርቤ አብልታችሁኛል፤ ተጠምቼ
አጠጥታችሁኛል፤ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁ
ኛል፤ [36]ታርዤ አልብሳችሁኛል፤ ታምሜ
አስታምማችሁኛል፤ ታስሬ ጠይቃችሁኛል።'
[37]"ጻድቃንም መልሰው እንዲህ ይሉታል፤
'ጌታ ሆይ፤ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህ?
ወይም ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ?
[38]እንግዳ ሆነህ አይተን መቼ ተቀበልንህ?
ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ አለበስንህ?
[39]እንዲሁም ታመህ ወይም ታስረህ አይተን
መቼ ጠየቅንህ?'
[40]"ንጉሡም መልሶ፣ 'እውነት እላችኋ
ለሁ፣ ከእነዚህ አነስተኛ ከሆኑት ወንድ
ሞቼ ለአንዱ ያደረጋችሁት፣ ለእኔ እንዳደ
ረጋችሁት ነው' ይላቸዋል።
[41]"ከዚያም በግራው በኩል ላሉት ደግሞ
እንዲህ ይላቸዋል፤ 'እናንተ የተረገማችሁ፤
ለዲያብሎስና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀው
የዘላለም እሳት ከእኔ ተለይታችሁ ሂዱ፤
[42]ምክንያቱም ተርቤ አላበላችሁኝም፤ ተጠ
ምቼ አላጠጣችሁኝም፤ [43]እንግዳ ሆኜ አልተ
ቀበላችሁኝም፤ ታርዤ አላለበሳችሁኝም፤ ታም
ሜና ታስሬ አልጠየቃችሁኝም።'
[44]"እነርሱም መልሰው፣ 'ጌታ ሆይ፤ ተር
በህ ወይም ተጠምተህ፣ እንግዳ ሆነህ ወይም
ታርዘህ፣ ታመህ ወይም ታስረህ ዐይተን
መቼ አልደረስንልህም' ይሉታል።

25፥19 ማቴ18፥23
25፥21 ቍ23፤ማቴ 24፥45፡47፤ሉቃ 16፥10
25፥23 ቍ21
25፥29 ማቴ13፥12፤ ማር4፥25፤ሉቃ8፥18 ፤19፥26
25፥30 ማቴ8፥12
25፥31 ማቴ19፥28፤ ሉቃ17፥30
25፥32 ሚል3፥18፤ ሕዝ34፥17፡20
25፥34 ማቴ3፥2፤ 5፥3፡10፡9፤19፥14፤ ሐሥ20፥32፤1ቆሮ 15፥50፤ገላ5፥21፤ ዕብ 4፥3፤ 9፥26፤ያዕ2፥5፤ ራእ13፥8፤17፥8
25፥35 ኢዮ31፥32፤ዕብ13፥2
25፥36 ኢሳ58፥7፤ ሕዝ18፥7፤2ጢሞ 1፥16፤ያዕ1፥27፤ 2፥15፡16
25፥40 ማቴ10፥40 ፡42፤ዕብ13፥2
25፥41 ኢሳ66፥24፤ ማቴ3፥12፤5፥22፤ 7፥23፤ማር9፥43፡48፤ ሉቃ3፥17፤ 2ጴጥ2፥4፤ይሁ7

*25፥27 ለለዋጮች፤* የዚህ ቃል የግሪኩ አቻ የመጣው "ጠረ ፔዛ" ከሚለው የግሪክ ቃል ነው፤ በአሁኑ ዘመን ይኸው ቃል በግ ሪክ አገር ባሉ ባንኮች ላይ ተጽፎ ይገኛል። ለዋጮች ከት ንሽ ጠረጴዛ አጠገብ ተቀምጠው ገንዘብ ይመነዝሩ ነበር (ከ21፥12 ጋር ያነጻጽሩ)። *ከነወለዱ፤* በግሪኩም ለዚህ የገባው ቃል "ልጅ ከመውለድ" ጋር የተገናኘ ነው፤ ተቀማጩ ወይም መነሻ ገንዘብ እንደ "ወላጅ"፣ ወለዱ ደግሞ እንደ "ልጅ" ይታ ሰብ ነበር።

*25፥31-46፤* በስፋት ተቀባይነት ያላቸው የዚህ "የመጨረሻ ፍርድ" ትርጓሜዎች፦ (1) ይህ በምድር ላይ እውን በሚሆነው በሺህ ዓመቱ ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ ላይ ነው (ቍ31፡34)፤ ዓላማውም ወደዚህ መንግሥት እንዲገባ የሚፈቀድለት ማን ማን እንደ ሆነ ለመወሰን ነው (ቍ34)። ለፍርድ የሚያበቃው መመ ዘኛም ቀደም ብሎ በሚከሠተው ታላቅ መከራ (ቍ35-40፡ 42-45)፣ "ከእነዚህ አነስተኛ ከሆኑት ወንድሞቼ" (ቍ40) ለተባሉት ለአይሁድ ወገኖች በሚደረገው አቀባበል ላይ የተመሠረተ ይሆ ናል። እንግዲህ አንድ ሰው ድነትን የተቀበለ ወይም ያልተቀበለ መሆኑ የሚታወቀው ለአይሁድ ሕዝብ ባለው አመለካከትና በሚያ ደርገው እንክብካቤ ነው (ቍ41፡46)። (2) በዘመኑ ፍጻሜ በታላቁ ነጭ ዙፋን ፊት የሚሰጠውን ፍርድ ያመለክታል (ራእ 20፥11-15)፤ ዐላማውም የዳኑት በሚወርሱት የዘላለም መንግሥት ማን መግባት እንደሚችልና ማን ደግሞ ለዘላለም ቅጣት ወደ ገሃነም እንደሚወርድ ለመወሰን ነው (ቍ34፡46)፤ ፍርዱም የተመሠ ረተው፣ አንድ ሰው የእግዚአብሔር ለሆኑት በተጨማሪም ስለ ወንድሞች ማቴ18፥15 ማብ ይመ፤ ወገኖች በሚሳየው ፍቅር ላይ ነው (1ዮሐ3፥14-15 ይመ)። (3) ጌታ "ወንድሞቼ" የሚላቸው አጠ ቃላይ የሰውን ልጆች ነው እንጂ በሥጋ ዝምድና ላይ የተመ ሠረተውን አይደለም (ማቴ 12፥46-50 ያዕ 1፥27፤2፥14-17)፤ ስለ ዚህ በምንም ዐይነት ችግርና መሠረታዊ ፍላጎት ላይ የሚገኙን ሰብአዊ ፍጡር ቀርቦ የመርዳት ኀላፊነት ከእውነተኛ አ ማኝ ሁሉ የሚጠበቅ ነው (ሉቃ 10፥29-37፤ ዮሐ 3፥11-18፤ 4፥20-21፤ ገላ 6፥9-10)።

*25፥34-40፤* በመንግሥተ ሰማይ ሽልማት የሚያገኙት ለሽ ልማት ሳይሉ እንዲያው የሚያገለግሉ ናቸው፤ እግዚአብሔር እን ዲሁ በጸጋው ሽልማትን ይሰጣል እንጂ እርሱ የማንም ባለ ዕዳ አይ ደለም።

45“በዚያን ጊዜ እርሱም መልሶ፣ ‘እው
ነት እላችኋለሁ፣ ከእነዚህ አነስተኛ ከሆኑት
ወንድሞቼ ለአንዱ አለማድረጋችሁ፣ ለእኔ
እንዳላደረጋችሁት ነው’ ይላቸዋል።
46“እነዚህም ወደ ዘላለም ፍርድ፣ ጻድቃን
ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።”

## አይሁድ በኢየሱስ ላይ መዶለታቸው

26፥2-5 ተጓ ምብ - ማር 14፥1፡2፤ ሉቃ 22፥1፡2

26 ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች ተናግሮ
ከጨረሰ በኋላ፣ ደቀ መዛሙርቱን፣
2“ከሁለት ቀን በኋላ ፋሲካ እንደሚሆን
ታውቃላችሁ፤ የሰው ልጅም ሊሰቀል አልፎ
ይሰጣል” አላቸው።
3ከዚህ በኋላ የካህናት አለቆችና የሕዝብ
ሽማግሌዎች ቀያፋ በተባለ ሊቀ ካህን ግቢ
ውስጥ ተሰብስበው፤ 4በረቀቀ መንገድ ኢየ
ሱስን ለማስያዝና ለማስገደል ተማከሩ። 5ነገር
ግን፣ “በሕዝቡ መካከል ረብሻ እንዳይነሣ
በበዓል ቀን አይሁን” በማለት ተስማሙ።

## ኢየሱስን ሽቶ የቀባችው ሴት

26፥6-13 ተጓ ምብ - ማር 14፥3-9
26፥6-13 ማመ - ሉቃ 7፥37፡38፤ ዮሐ 12፥1-8

6ኢየሱስ በቢታንያ በለምጻሙ በስምዖን
ቤት ሳለ፣ 7አንዲት ሴት ዋጋው እጅግ
ውድ የሆነ አንድ ብልቃጥ የአልባስጥሮስ
ሽቶ ይዛ ወደ እርሱ ቀረበች፤ በማእድ ላይ
ተቀምጦ ሳለም በራሱ ላይ አፈሰሰችው።
8ደቀ መዛሙርቱ ይህንን በተመለከቱ ጊዜ
ተቈጥተው እንዲህ አሉ፤ “ይህ ሁሉ ብክ
ነት ለምንድነው? 9ሽቶው በብዙ ዋጋ ተሸጦ
ገንዘቡን ለድኾች መስጠት ሲቻል!”
10ኢየሱስ ይህን ዐውቆ እንዲህ አላቸው፤
“ይህችን ሴት ለምን ታስቸግሯታላችሁ?
መልካም ነገር አድርጋልኛለች፤ 11ድኾች
ምንጊዜም ከእናንተ ጋር ናቸው፤ እኔ ግን
ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልሆንም። 12ሽቶ
ውን በሰውነቴ ላይ በማፍሰሷ፣ እኔን ለቀ
ብር ለማዘጋጀት ነው፤ 13እውነት እላችኋ
ለሁ፤ ይህ ወንጌል በሚሰበክበት በዓለም
ዙሪያ ሁሉ፣ በየትኛውም ስፍራ እርሷ ያደ
ረገችው በመታሰቢያነት ይነገርላታል።”

## ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት ተስማማ

26፥14-16 ተጓ ምብ - ማር 14፥10፡11፤ ሉቃ 22፥3-6

14ከዚህ በኋላ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ የነበ
ረውና የአስቆሮቱ ይሁዳ የተባለው ወደ ካህ
ናት አለቆች ሄደ፣ 15“እርሱን አሳልፌ ብሰ
ጣችሁ እናንተስ ምን ትሰጡኛላችሁ?” አላ
ቸው። እነርሱም ሠላሳ ጥሬ ብር ቈጥረው
ሰጡት። 16ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይሁዳ፣ ኢየ
ሱስን አሳልፎ የሚሰጥበትን አመቺ ጊዜ
ይፈልግ ነበር።

## የጌታ ራት

26፥17-19 ተጓ ምብ - ማር 14፥12-16፤ ሉቃ 27፥7-13
26፥20-24 ተጓ ምብ - ማር 14፥17-21
26፥26-29 ተጓ ምብ - ማር 14፥22-25፤ ሉቃ22፥17-20፤
1ቆሮ 11፥23-25

17በቂጣ በዓል የመጀመሪያ ቀን ደቀ
መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ ቀርበው፣ “ፋሲካን
እንድትበላ የት እንድናዘጋጅልህ ትፈልጋ
ለህ?” አሉት።
18እርሱም፣ “ወደ ከተማ ሄዳችሁ እገሌ
የተባለውን ሰው፣ ‘መምህር ጊዜዬ ተቃርቦ
አልና ከደቀ መዛሙርቴ ጋር ፋሲካን በቤ
ትህ አከብራለሁ ብሏል’ በሉት” አላቸው።
19ደቀ መዛሙርቱም ኢየሱስ ባዘዛቸው መሠ
ረት የፋሲካን ራት አዘጋጁ።
20በመሸም ጊዜ ኢየሱስ ከዐሥራ ሁለቱ
ጋር በማእድ ተቀመጠ፤ 21በመብላት ላይ
ሳሉም፣ “እውነት እላችኋለሁ፣ ከእናንተ
አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል” አላቸው።
22እነርሱም እጅግ አዝነው፣ ተራ በተራ፣
“ጌታ ሆይ፤ እኔ እሆን ይሆን?” አሉት።
23እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ “አሳ
ልፎ የሚሰጠኝ ከወጭቱ ውስጥ አብሮኝ ያጠ

25፥45 ምሳ14፥31፤ 17፥5
25፥46 ዳን12፥2፤ ማቴ19፥29፤ዮሐ3፥15 ፡16፡36፤5፥29፤17፥2፡ 3፤ሐሥ24፥15፤ሮሜ 2፥7፤ገላ6፥8፤1ዮሐ 1፥2፤5፥11፡13፡20
26፥1 ማቴ7፥28
26፥2 ዮሐ11፥55
26፥3 ቍ57፤መዝ 2፥2፤ሉቃ3፥2፤ዮሐ 11፥47-53፤18፥13፡ 14፡24፡28፤ሐሥ4፥6
26፥4 ማቴ12፥14
26፥5 ማቴ27፥24
26፥6 ማቴ21፥17
26፥11 ዘዳ15፥11
26፥12 ዮሐ19፥40
26፥14 ቍ25፡47፤ ማቴ10፥4
26፥15 ዘፀ21፥32፤ ዘካ11፥12
26፥17 ዘፀ12፥18-20፤ ዘዳ16፥5-8
26፥18 ማር14፥35፡ 41፤ዮሐ7፥6፡8፡30፤ ዮሐ8፥20፤12፥23፤ 13፥1፤17፥1
26፥21 ሉቃ22፥21- 23፤ዮሐ13፥21
26፥23 መዝ41፥9፤ ዮሐ13፥18

26፥2 *ፋሲካ፤* የማር14፥1 ማብ ይመ። *የሰው ልጅ፤* የማር 8፥31 ማብ ይመ።

26፥3 *ቀያፋ፤* ከ18-36 ዓ.ም. ሊቀ ካህናት ሆኖ ያገለገለ ሲሆን፣ እርሱም ቀደም ሲል ከ6-15 ዓ.ም. ሊቀ ካህናት የነበረው የሐና (ዮሐ18፥13) አማች ነበረ።

26፥5 *ረብሻ እንዳይነሣ፤* በመቶ ሺህ የሚቈጠሩ የአይሁድ አማኞች ለፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ይመጡ ነበር፤ በዚህም ወቅት ረብሻ መፈጠሩ የተለመደ ነበር። የሃይማኖት መሪዎችም (ቍ3) አብዛኛው ሕዝብ ኢየሱስን እንደሚያደንቅ የተገነዘቡት ነገር ነበር።

26፥6 *በለምጻሙ በስምዖን፤* በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት “ስምዖን” የሚለው ስም በአይሁድ ዘንድ የተለመደ ቢሆንም፣ የተጠቀሰው በዚህ ቦታና በማር14፥3 ላይ ብቻ ነው። ይህ ሰው ኢየሱስ ያዳነው ዕውቅ ለምጻም ሳይሆን አይቀርም።

26፥7 *የአልባስጥሮስ ሽቶ፤* አብዛኛው የጥንት ዘመን “አል ባስጥሮስ” እብነ በረድ ነበር (የማር14፥3 ማብ ይመ)።

26፥10 *መልካም፤* ለዚህ የገባው የግሪኩ አቻ ቃል የሥነ ውበትንና የሥነ ምግባርን ትርጒም የያዘ ነው።

26፥14 *የአስቆሮቱ፤* ያማር 3፥19 ማብ ይመ።

26፥15 *ሠላሳ ጥሬ ብር፤* 120 ዲናር ያህል ነው፤ የቀን ሠራተኞች ብዙውን ጊዜ በቀን አንድ ዲናር ይከፈላቸው ነበር (20፥1-16 ይመ)።

26፥17 *በቂጣ በዓል መጀመሪያ ቀን፤* ‘ኒሳን’ የተባለው ወር (መጋቢት - ሚያዝያ) የዐሥራ አራተኛው ቀን ሲሆን፣ ከዚ ህም ሌላ የፋሲካ በዓል መዘጋጃ ቀን ይባል ነበር። የፋሲካ እራት የሚ በላው በዐሥራ አራተኛው ቀን፣ ፀሓይ ስትጠልቅ በመሆኑ፣ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ በዐሥራ አምስተኛው ቀን እንደ ተበላ ይቈጠራል፤ ምክንያቱም በአይሁድ ልማዳዊ አቈጣጠር አንድ ቀን ፀሓይ ስትጠልቅ ያከትማል። የቂጣ በዓል በኒሳን ወር ከ15 ኛው-21ኛው ቀን፣ ሰባት ቀን ይቈይ ነበር (ዘሌ23፥5-6 ይመ)፤ ነገር ግን ክርስቶስ በአካለ ሥጋ በምድር ላይ በነበረበት ዘመን አጠቃላይ ሰሞኑ (ኒሳን 14-21)፣ የመጀመሪያውን ቀን ጨምሮ፣ በዚሁ ስም ይጠራ ነበር (የማር14፥12 ማብ ይመ)።

*26፥18-30፤* ኢየሱስ ከስቅለቱ በፊት በዋዜማው ሌሊት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፋሲካን እራት መብላቱን እነዚህ ጥቅ ሶች በግልጽ ያመለክታሉ። ስለ ጌታ እራት በይበልጥ ለመረዳት የማር14፥22፡24 ማብ ይመ።

26፥20 *በማእድ ተቀመጠ፤* የማር14፥18 ማብ ይመ።

26፥23 *ከወጭቱ ውስጥ አብሮኝ ያጠቀሰው፤* ዛሬም ቢሆን በአንዳንድ የመካከለኛው ምሥራቅ ክፍሎች ከተቀቀለ ፍሬ ተሠ ርቶ ገበታ ላይ ከቀረበው ወጥ ውስጥ እንጀራ አጥቅሶ መብላት የተለመደ ነው። *አሳልፎ የሚሰጠኝ፤* በአሁኑ ዘመን በዓረቦች ዘንድ እንደሚደረገው፣ በዚያ ዘመን በነበረው ባህል መሠረት ከአንድ ሰው ጋር አብሮ መብላት፣ “እኔ ወዳጅህ ነኝ፤ ጕዳት

| | |
|---|---|
| **የክርስቶስ ምድራዊ ሕይወት** | |
| ማስታወሻ:- በአጠቃላይ ቀናቱና ዓመታቱ በትክክል አይታወቁም:: | |
| **የልጅነት ዘመን** | |
| | የኢየሱስ መወለድ (ቤተልሔም) ማቴ1፥18-25፤ ሉቃ2፥1-7 |
| ዓ.ቅ.ክ 6/5 | በእረኞች መጐብኘት (ቤተልሔም) ሉቃ2፥8-20 |
| | የመቅደስ ሥርዐት (ኢየሩሳሌም) ሉቃ2፥21-40 |
| | በምሥራቅ ጠቢባን መጐብኘት (ቤተልሔም) ማቴ2፥1-12 |
| | ወደ ግብፅ መሰደድ (ግብፅ) ማቴ2፥13-18 |
| | ወደ ናዝሬት መመለስ (ገሊላ) ማቴ2፥19-23 |
| 7/8 ዓ.ም | |
| | በልጅነቱ ወደ ቤተ መቅደስ መሄዱ (ኢየሩሳሌም) ሉቃ2፥41-52 |
| **አገልግሎት የጀመረበት ዓመት** | |
| በጋ | |
| 26 ዓ.ም | ኢየሱስ ተጠመቀ (ዮርዳኖስ ወንዝ) ማቴ3፥13-17፤ማር1፥9-11 3፥21-23፤ ዮሐ1፥29-39 |
| | ኢየሱስ በሰይጣን ተፈተነ (ምድረ በዳ) ማቴ4፥1-11፤ማር1፥12-13፤4፥1-13 |
| መፀው | |
| | የኢየሱስ የመጀመሪያ ታምር (ቃና) ዮሐ2፥1-11 |
| ክረምት | |
| 27 ዓ.ም | ኢየሱስ ቤተ መቅደሱን አጠራ ዮሐ2፥14-22 |
| 27 ዓ.ም | ኢየሱስና ኒቆዲሞስ (ኢየሩሳሌም) ዮሐ3፥1-21 |
| | ኢየሱስ ከሰማርያዋ ሴት ጋር ተነጋገረ (ሰማርያ) ዮሐ4፥5-42 |
| | ኢየሱስ የሹሙን ልጅ ፈወሰ (ቃና) |
| ፀደይ | |
| | ኢየሱስ የገዛ አገሩ ሰዎች ሊገድሉት ሞከሩ (ናዝሬት) ሉቃ4፥16-31 |
| **በሕዝብ የታወቀበት ዓመት** | |
| በጋ | |
| 27 ዓ.ም | አራት ዓሣ አጥማጆች የኢየሱስ ተከታዮች ሆኑ (በገሊላ ባሕር በቅፍርናሆም) ማቴ4፥18-22፤ ማር1፥16-20፤ ሉቃ5፥1-11 |
| | ኢየሱስ የጴጥሮስን ዐማት ፈወሰ (ቅፍርናሆም) |
| መፀው | |
| | ኢየሱስ የመጀመሪያ የስብከት ጉዞውን በገሊላ በኩል አደረገ ማቴ4፥23-25፤ ማር1፥35-39፤ ሉቃ4፥42-44 |
| | ማቴዎስ ኢየሱስን ለመከተል ወሰነ (ቅፍርናሆም) ማቴ9፥9-13፤ ማር2፥13-17፤ሉቃ5፥27-32 |
| ክረምት | |
| 28 ዓ.ም | ኢየሱስ ዐስራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት መረጠ (ማር3፥13-19፤ ሉቃ6፥12-15) |
| ፀደይ | |

| | |
|---|---|
| | ኢየሱስ የተራራውን ስብከት ሰበከ (ማቴ5፥1-7:29፤ሉቃ6፥20-49) |
| | ኃጢአተኛ ሴት የኢየሱስን እግር ቀባች (ሉቃ7፥36-50) |
| በጋ | |
| | ኢየሱስ እንደ ገና በገሊላ በኩል አለፈ (ሉቃ8፥1-3) |
| | ኢየሱስ ስለ መንግሥቱ ምሳሌ ተናገረ (ማቴ13፥1-52፤ ማር4፥1-34፤ ሉቃ8፥4-18) |
| መፀው | |
| | ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ አደረገ (የገሊላ ባሕር) ማቴ8፥23-27፤ ማር4፥35-41፤ ሉቃ8፥22-25 |
| | ኢየሱስ የኢያኢሮስን ልጅ ከሞት አስነሣ (ቅፍርናሆም) ማቴ9፥18-26፤ ማር5፥21-43፤ ሉቃ8፥40-56 |
| | ኢየሱስ 12ቱን ደቀ መዛሙርት እንዲሰብኩና እንዲፈውሱ ላከ (ማቴ9፥35-11፥1፤ማር6፥6-13፤ ሉቃ9፥1-6) |
| **ተቃውሞ የተነሣበት ዓመት** | |
| ክረምት | |
| 28 ዓ.ም | መጥምቁ ዮሐንስ በሄሮድስ ተገደለ (መቃሪየስ) ማቴ14፥1-12፤ ማር6፥14-29፤ ሉቃ9፥7-9 |
| ፀደይ | |
| 29 ዓ.ም | ኢየሱስ 5,000 ሰዎችን መገበ (ቤተ ሳይዳ አጠገብ) ማቴ14፥13-21፤ማር6፥30-44፤ ሉቃ9፥10-17፤ ዮሐ6፥1-14 |
| | ኢየሱስ በባሕር ላይ ተራመደ (ማቴ14፥22-23፤ማር6፥45-52፤ዮሐ6፥16-21) |
| | ኢየሱስ ወደ ጢሮስና ሲዶና ሄደ (ማቴ15፥21-28፤ ማር7፥24-30) |
| | ኢየሱስ 4,000 ሰዎችን መገበ (ማቴ15፥32-39፤ማር8፥1-9) |
| | ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ጴጥሮስ ተናገረ (ማቴ16፥13-20፤ ማር8፥27-30፤ሉቃ9፥18-21) |
| በጋ | |
| | ኢየሱስ በቅርብ ጊዜ እንደሚሞት ለደቀ መዛሙርቱ ተናገረ (ቂሣርያ ፊልጶስ) ማቴ16፥21-26፤ ማር8፥31-37፤ ሉቃ9፥22-25 |
| | የኢየሱስ መልክ ተለወጠ (ማቴ17፥1-13፤ማር9፥2-13፤ ሉቃ9፥28-36) |
| መፀው | |
| | ኢየሱስ የቤተ መቅደስ ግብር ከፈለ (ማቴ17፥24-27) |
| 29 ዓ.ም | ኢየሱስ የዳስ በዓልን አከበረ (ኢየሩሳሌም) |
| | ኢየሱስ ከተወለደ ጀምሮ ዐይነ ሥውር የተበረውን ሰው ፈወሰ (ኢየሩሳሌም) ዮሐ9፥1-41 |
| | ኢየሱስ ማርያምንና ማርታን ጉበኘ (ቢታንያ) ሉቃ10፥38-42 |
| ክረምት | |
| 29 ዓ.ም | ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት አስነሣ (ቢታንያ) ዮሐ11፥1-44 |
| | ኢየሱስ የመጨረሻ ጉዞውን ወደ ኢየሩሳሌም አደረገ፤ 30 ዓ.ም ሉቃ17፥11 |
| | ኢየሱስ ሕፃናትን ባረከ (ዮርዳኖስ ማዶ) ማቴ19፥13-15፤ ማር10፥13-16፤ ሉቃ18፥15-17 |
| | ኢየሱስ ከወጣቱ ሀብታም ጋር ተነጋገረ (ማቴ19፥16-30፤ ማር10፥17-31፤ሉቃ18፥18-30) |
| | ኢየሱስ ስለ ሞቱና ትንሣኤው እንደ ገና ተናገረ (ዮርዳኖስ አጠገብ) ማቴ20፥17-19፤ ማር10፥32-34፤ ሉቃ18፥31-34 |
| | ኢየሱስ ዐይነ ሥውሩን በርጠሜዎስን ፈወሰ (ኢያሪኮ) ማቴ20፥29-34፤ማር10፥46-52፤ሉቃ18፥35-43 |
| | ኢየሱስ ከዘኬዎስ ጋር ተነጋገረ (ሉቃ19፥1-10) |

| | |
|---|---|
| | ኢየሱስ ማርያምንና ማርታን ለመጐብኘት ወደ ቢታንያ ዮሐ11፥55-12፥1 |
| **የመጨረሻው ሳምንት** | |
| **ፀደይ** | |
| 30 ዓ.ም | ወደ ኢየሩሳሌም በክብር መግባት -እሁድ ማቴ21፥1-11፤ማር11፥1-10፤ ሉቃ19፥29-44፤ የሐ12፥12-19 |
| | ኢየሱስ የበለሲቱን ዛፍ ረገመ -ሰኞ ማቴ21፥18-19፤ ማር11፥12-14 |
| | ኢየሱስ ቤተ መቅደሱን አጠራ -ሰኞ ማቴ21፥12-13፤ ማር11፥15-18 |
| | የኢየሱስ ባለ ሥልጣንነት ተጠየቀ -ማክሰኞ ማቴ21፥23-27፤ ማር11፥27-33፤ ሉቃ10፥1-8 |
| | ኢየሱስ በቤተ መቅደስ አስተማረ -ማክሰኞ ማቴ21፥28-23፥39፤ ማር12፥1-44፤ ሉቃ20፥9-21፥4 |
| | ኢየሱስ ሽቱ ተቀባ (ቢታንያ) -ማክሰኞ ማቴ26፥6-13፤ማር14፥3-9፤ዮሐ12፥2-11 |
| | በኢየሱስ ላይ የተደረገ ሤራ -ረቡዕ ማቴ26፥14-16፤ ማር14፥10-11፤ሉቃ22፥3-6 |
| | የመጨረሻው እራት -ሐሙስ ማቴ26፥17-29፤ማር14፥12-25፤ ሉቃ22፥7-20፤ዮሐ13፥1-38 |
| | ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን አጽናና -ሐሙስ ዮሐ14፥1-16፥33 |
| | ኢየሱስ በጌቴሴማኒ -ሐሙስ ማቴ26፥36-46፤ ማር14፥32-42፤ ሉቃ22፥40-46 |
| | የኢየሱስ መታሰርና በፍርድ ፊት መቅረብ -ሐሙስ ማቴ26፥47-27፥26፤ ማር14፥43-15፥15፤ ሉቃ22፥47-23፥25፤ ዮሐ18፥2-19፥16 |
| | የኢየሱስ መሰቀልና መሞት (ጎልጎታ) -ዐርብ ማቴ27፥27-56፤ ማር15፥16-41፤ሉቃ23፥26-49፤ዮሐ19፥17-30 |
| | የኢየሱስ መቀበር (የዮሴፍ መቃብር) -ዐርብ ማቴ27፥57-66፤ማር15፥42-47፤ሉቃ23፥50-56፤ዮሐ19፥31-42 |
| **ከትንሣኤ በኋላ** | |
| 30 ዓ.ም | ባዶው መቃብር (ኢየሩሳሌም) -እሁድ ማቴ28፥1-10፤ ማር16፥1-8፤ ሉቃ24፥1-12፤ ዮሐ20፥1-10 |
| | መግደላዊት ማርያም ኢየሱስን በአትክልት ስፍራ አየች (ኢየሩሳሌም) -እሁድ ማር16፥9-11፤ ዮሐ20፥11-18 |
| | ኢየሱስ ወደ ኤማሁስ ይሄዱ ለነበሩት ለሁለቱ ታየ -እሁድ ማር16፥12-13፤ ሉቃ24፥13-35 |
| | ኢየሱስ ለዐሥሩ ደቀ መዛሙርት ታየ (ኢየሩሳሌም) -እሁድ ማር16፥14፤ ሉቃ24፥36-43፤ ዮሐ20፥19-25 |
| | ኢየሱስ ለዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ታየ (ኢየሩሳሌም) -ከአንድ ሳምንት በኋላ ዮሐ20፥26-31 |
| | ኢየሱስ ከአንዳንድ ደቀ መዛሙርቱ ጋር ተነጋገረ (ገሊላ ባሕር) ከአንድ ሳምንት በኋላ ዮሐ21፥1-25 |
| | ኢየሱስ ወደ አባቱ ዐረገ (ደብረ ዘይት) -ከ40 ቀናት በኋላ ማቴ28፥16-20፤ማር16፥19-20፤ ሉቃ24፥44-53 |

ቀሰው ነው፤ 24የሰው ልጅ ስለ እርሱ እንደ
ተጻፈው ይሄዳል፤ ነገር ግን የሰውን ልጅ
አሳልፎ ለሚሰጠው ሰው ወዮለት፤ ለዚያ
ሰው ሳይወለድ ቢቀር ይሻለው ነበር::"
25አሳልፎ የሚሰጠው ይሁዳም፣ "መምህር
ሆይ፣ እኔ እሆንን?" አለው::
እርሱም፣ "አንተ አልህ"[ሀ] አለው::
26እየበሉ ሳሉ፣ ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ
ባረከ፤ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ በመስጠት፣
"እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ሥጋዬ ነው" አላቸው::
27ከዚያም ጽዋውን አንሥቶ አመስገነ፤
ለደቀ መዛሙርቱም በመስጠት እንዲህ አላ
ቸው፤ "ሁላችሁም ከዚህ ጠጡ፤ 28ስለ ብዙ
ዎች የኀጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ
ኪዳን ደሜ ይህ ነው:: 29እላችኋለሁ፤ በአ
ባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር በአዲስ መልክ
እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ፣ ከእ
ንግዲህ ከዚህ የወይን ፍሬ አልጠጣም::"
30መዝሙር ከዘመሩ በኋላ ወደ ደብረ ዘይት
ተራራ ወጡ::

### የጴጥሮስ ክህደት አስቀድሞ መነገሩ

26፥31-35 ተጓ ምብ - ማር 14፥27-31፤ ሉቃ 23፥31-34

31ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤ "ሁላ
ችሁም በዚህች ሌሊት በእኔ ተሰናከላችሁ
ትሄዳላችሁ፤ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤

" 'እረኛውን እመታለሁ፤
የመንጋውም በጎች ይበተናሉ::'

32ነገር ግን ከተነሣሁ በኋላ ቀድሜአችሁ
ወደ ገሊላ እሄዳለሁ::"
33ጴጥሮስም መልሶ፣ "ሌሎች በሙሉ ባንተ
ምክንያት ቢሰናከሉ እንኳ እኔ በፍጹም
አልሰናከልም!" አለው::
34ኢየሱስም፣ "እውነት እልሃለሁ፤ በዛሬዋ
ሌሊት ዶሮ ከመጮኹ በፊት ሦስት ጊዜ
ትክደኛለህ" አለው::
35ጴጥሮስ ግን "ከአንተ ጋር መሞት ቢያ
ስፈልግ እንኳ ከቶ አልክድህም!" አለው::
ሌሎቹም ደቀ መዛሙርት በሙሉ እንደዚሁ
አሉ::

### የኢየሱስ ጸሎት በጌቴሴማኒ

26፥36-46 ተጓ ምብ - ማር 14፥32-42፤ ሉቃ 22፥40-46

36ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር ጌቴሴማኒ ወደሚባል ስፍራ ሄደ፤ እነ
ርሱንም፣ "ወደዚያ ሄጄ በምጸልይበት ጊዜ
እናንተ እዚህ ተቀመጡ" አላቸው:: 37ከእር
ሱም ጋር ጴጥሮስንና ሁለቱን የዘብዴዎስ
ልጆች ይዞ በመሄድ ይተክዝና ይጨነቅ
ጀመር፤ 38ከዚያም፣ "ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ
እጅግ አዝናለች፤ ከእኔ ጋር በመትጋት
እዚሁ ቈዩ" አላቸው::
39ጥቂት ዕልፍ ብሎ በግንባሩ በመደ
ፋት፣ "አባቴ ሆይ፤ ቢቻል ይህ ጽዋ ከእኔ
ይለፍ፤ ነገር ግን እኔ እንደምፈልገው ሳይ
ሆን አንተ እንደምትፈልገው ይሁን" ብሎ
ጸለየ::
40ከዚያም ተመልሶ ወደ ደቀ መዛሙርቱ
ሲመጣ፣ ተኝተው አገኛቸው፤ ጴጥሮስንም
እንዲህ አለው፤ "እናንተ ሰዎች፤ ከእኔ ጋር
ለአንድ ሰዓት እንኳ መትጋት አቃታች
ሁን? 41ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ፤
መንፈስ ዝግጁ ነው፤ ሥጋ ግን ደካማ ነው::"
42እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ ሄዶ፣ "አባት
ሆይ፤ ይህ ሳልጠጣው የማያልፍ ጽዋ ከሆነ፣
ፈቃድህ ይፈጸም" ብሎ ጸለየ::
43እንደገናም በመጣ ጊዜ ዐይኖቻቸው
በእንቅልፍ ከብደው ስለ ነበር ተኝተው አገ
ኛቸው::
44ትቶአቸውም እንደገና በመሄድ ለሦስተኛ
ጊዜ ቀደም ብሎ የጸለየውን ጸሎት ደገመ::
45ከዚያም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ተመልሶ
እንዲህ አላቸው፤ "አሁንም ዐርፋችሁ ተኝ
ታችኋል? እነሆ፣ ሰዓቱ ቀርቦአል፤ የሰው
ልጅ በኀጢአተኞች እጅ ዐልፎ ይሰጣል፤ 46
ተነሡ! እንሂድ፤ አሳልፎ የሚሰጠኝም እየ
መጣ ነው::"

### የኢየሱስ መያዝ

26፥47-56 ተጓ ምብ - ማር 14፥43-50፤ ሉቃ 27፥47-53

47በመናገር ላይ እያለ፣ ከዐሥራ ሁለቱ
አንዱ ይሁዳ መጣ፤ ከካህናት አለቆችና
ከሕዝቡ ሽማግሌዎች ዘንድ የተላኩ ሰይፍና
ዱላ የያዙ ብዙ ሰዎችም አብረውት ነበሩ::
48ይሁዳም፣ "እኔ የምስመው እርሱ ነው፤
ያዙት" ብሎ ምልክት ሰጥቶአቸው ስለነ
በር፣ 49በቀጥታ ወደ ኢየሱስ ሄዶ፣ "መምህር
ሆይ፤ ሰላም ለአንተ ይሁን" በማለት ሳመው::
50ኢየሱስም፣ "ወዳጄ ሆይ፤ የመጣህበትን

26፥24 ቍ31:54: 56፤ኢሳ53፤ዳን9፥26፤ ማር9፥12፤ ሉቃ24፥25-27:46፤ ሐሥ17፥2:3፤ 26፥22:23፤ 1ጴጥ1፥ 10:11
26፥25 ማቴ10፥4፤ 23፥7
26፥26 ማቴ14፥19
26፥27 1ቆሮ10፥16
26፥28 ዘፀ24፥6-8፤ ዘካ9፥11፤ሚል2፥5፤ ማቴ20፥28፤ማር1፥4፤ ዕብ9፥20፤10፥29፤ 13፥20
26፥29 ሐሥ10፥41
26፥30 ማቴ21፥1
26፥31 ዘካ13፥7፤ ማቴ11፥6፤ዮሐ16፥32
26፥32 ማቴ28፥7: 10:16
26፥34 ቍ75፤ ዮሐ 13፥38
26፥35 ዮሐ13፥37
26፥37 ማቴ4፥21
26፥38 ቍ40:41፤ ዮሐ12፥27
26፥39 ቍ42፤ መዝ 40፥6-8፤ ኢሳ50፥5፤ ማቴ6፥10፤20፥22፤ ዮሐ4፥34፤5፥30፤ 6፥38
26፥40 ቍ38
26፥41 ማቴ6፥13
26፥42 ቍ39
26፥45 ቍ18
26፥47 ማቴ10፥4
26፥49 ቍ25፤ ማቴ23፥7
26፥50 ማቴ20፥13፤22፥12

ሀ25 *"ወይም አንተ ራስህ ተናገርህ"*

አላደርስብህም" ማለት ነበር:: ይህ ሁኔታ የይሁዳን አድራጎት የባ
ሰውን ነውረኛ ያደርገዋል (ከመዝ41፥9 ጋር ያነጻጽሩ)::
26፥24 *ስለ እርሱ እንደ ተጻፈው፤* የማር14፥21 ማብ ይመ::
26፥26-28፤ የማር14፥22 ማብ ይመ::
26፥30 *መዝሙር፤* በፋሲካ በዓል ምክንያት የሚኖረው
የምእመኑ የኅብረት ጊዜ፣ የዳዊት የምስጋና (የሃሌ ሉያ) መዝሙር
ሁለተኛው አጋማሽ ክፍል በመዘመር ያከትም ነበር (መዝ115-118)::
26፥31 *ተሰናክላችሁ ትሄዳላችሁ፤* ጴጥሮስ ብቻ ሳይሆን፣
ዐሥራ አንዱም ትተውት ይሄዳሉ (ይሁዳ አስቀድሞ ትቶት ሄዶ
አል፤ ዮሐ13፥30):: ኢየሱስ "ተሰናክላችሁ ትሄዳላችሁ" ያለው
በጴጥሮስ ክህደትና (ቍ69-75) በሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ተደና
ግጦ መሸሽ ታይቶአል (ቍ56):: *እረኛውን እመታለሁ፤* የዘካ
13፥7 ማብ ይመ::
26፥32 *ወደ ገሊላ፤* ከ 28፥10:16-20፤ ከማር16፥7፤ ከዮሐ
21፥1-23 ጋር ያነጻጽሩ::
26፥34 *ዶሮ ከመጮኹ በፊት፤* በሮማውያን የጊዜ አቈጣጠር
የሌሊቱን ሦስተኛውን ክፍል የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም
(የ14፥25 ማብ ይመ፤ በተጨማሪ ማር 13፥35 ይመ)፤ ወይም
ሊነጋጋ ሲል ዶሮ የሚጮኽበትን ጊዜ ሊያመለክት ይችላል::
26፥36 *ጌቴሴማኒ፤* የስሙ ትርጕም ዘይት ከወይራ ፍሬ
ተጨምቆ የሚወጣበት "የዘይት መጭመቂያ ቦታ" ማለት ነው::
26፥39 *ጽዋ፤* የጥልቅ ኀዘንና መከራ ምልክት ነው፤ እዚህ
ቦታ ላይ፣ ኀጢአት የሌለበት እርሱ ስለ እኛ ኀጢአት በሆነ ጊዜ
(የኀጢአት መሥዋዕት በሆነ ጊዜ)፣ አባቱ ፊቱን ከእርሱ በማዞሩ
የተሰማውን የሐዘን ስሜት ያመለክታል (27፥46፤ 2ቆሮ5፥21 ይመ)::
26፥41፤ የማር14፥38 ማብ ይመ::
26፥48 *እኔ የምስመው፤* የሉቃ22፥47 ማብ ይመ::

ፈጽም"* አለው::
በዚህ ጊዜ ሰዎቹ ቀርበው ኢየሱስን
ያዙት፤ አሰሩትም:: 51ከኢየሱስ ጋር ከነበሩት
አንዱ፣ ሰይፉን መዝዞ በመሰንዘር የሊቀ
ካህናቱን አገልጋይ ጆሮውን ቈረጠው::
52ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "በል ሰይፍ
ህን ወደ ሰገባው መልስ፤ ሰይፍን የሚመ
ዝዙ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉ:: 53ከፈለገ አባ
ቴን ብጠይቀው ከዐሥራ ሁለት ክፍለ ሰራ
ዊት የሚበልጡ መላእክት የማይሰድልኝ
ይመስልሃል? 54ይህ ቢሆን ደግሞ ቅዱሳት
መጻሕፍት ይሆናል ያሉት ነገር እንዴት
ይፈጸማል?"
55በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ሕዝቡን እንዲህ
አላቸው፤ "ወንበዴ እንደሚይዝ ሰው ሰይ
ፍና ዱላ ይዛችሁ ልትይዙኝ መጣችሁ? በየ
ዕለቱ በቤተ መቅደስ ተቀምጬ ሳስተምር
አልያዛችሁኝም ነበር፤ 56ነገር ግን ይህ ሁሉ
የሆነው ነቢያት በቅዱሳት መጻሕፍት የተ
ናገሩት ይፈጸም ዘንድ ነው::" በዚያን ጊዜ
ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ጥለውት ሸሹ::

## ኢየሱስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት

26፥57-68 ተጓ ምብ - ማር 14፥53-65፤ ዮሐ 18፥12፡13፡19-24

57በዚህ ጊዜ ኢየሱስን የያዙት ሰዎች፣
የኦሪት የሕግ መምህራንና የሕዝብ ሽማግሌ
ዎች ተሰብስበው ወደ ነበሩበት፣ ወደ ሊቀ
ካህናቱ ወደ ቀያፋ ወሰዱት:: 58ነገር ግን
ጴጥሮስ ከርቀት ሆኖ እስከ ሊቀ ካህናቱ
ቅጥር ግቢ ይከተለው ነበር፤ ወደ ውስጥ
ገብቶም የሁኔታውን መጨረሻ ለማየት
ከጠባቂዎች ጋር ተቀመጠ::
59በዚህ ጊዜ የካህናት አለቆችና የአይሁድ
ሸንጎ በሙሉ ኢየሱስን ለማስገደል የሐሰት
ማስረጃ ይፈልጉ ነበር፤ 60ብዙ የሐሰት ምስ
ክሮች ቢቀርቡም በቂ ማስረጃ አላገኙም፤
በኋላ ግን ሁለት ሰዎች ቀርበው፣ 61"ይህ
ሰው፣ 'የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ አፍርሼ፣
በሦስት ቀን ውስጥ መልሼ ልሠራው እችላ
ለሁ' ብሎአል" በማለት ተናገሩ::
62በዚህ ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ተነሥቶ በመ
ቆም፣ "እነዚህ ሰዎች ለሚመሰክሩብህ ሁሉ
ምንም መልስ አትሰጥምን?" አለው:: 63ኢየ
ሱስ ግን ዝም አለ::
ሊቀ ካህናቱም፣ "በሕያው እግዚአብሔር
ስም አምልሃለሁ፤ አንተ ክርስቶስ[a] የእግዚአ
ብሔር ልጅ እንደ ሆንህ ንገረን" አለው::
64ኢየሱስም፣ "አንተው ራስህ ብለኸዋል፤
ነገር ግን ለሁላችሁም ልንገራችሁ፤ ወደ
ፊት የሰው ልጅ በኃያሉ ቀኝ ተቀምጦ በሰ
ማይ ደመና ሲመጣ ታዩታላችሁ" አለው::
65በዚህ ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ልብሱን ቀዶ፣
"በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል ተናግሮ
አል፤ ከዚህ ሌላ ምን ምስክርነት ያስፈልገ
ናል? በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል መና
ገሩን እናንተው ራሳችሁ ሰምታችኋል፤
66ምን ይመስላችኋል?" አላቸው::
እነርሱም፣ "ሞት ይገባዋል!" ብለው መለሱ::
67በዚህ ጊዜ ፊቱ ላይ እየተፉ በጡጫ
መቱት፤ ሌሎቹም በጥፊ እየመቱት፣ 68"ክር
ስቶስ ሆይ፤ ማነው የመታህ? እስቲ ትንቢት
ንገረን!" አሉት::

## ጴጥሮስ ኢየሱስን ካደ

26፥69-75 ተጓ ምብ - ማር 14፥66-72፤
ሉቃ 22፥55-62፤ ዮሐ 18፥16-18፡25-27

69ከዚህ በኋላ ጴጥሮስ በሊቀ ካህናቱ ግቢ
ውስጥ ተቀምጦ ሳለ አንዲት የቤት ሠራ
ተኛ ወደ እርሱ ቀርባ፣ "አንተም ከገሊላው
ኢየሱስ ጋር ነበርህ" አለችው::
70እርሱ ግን፣ "ምን እንደምትናገሪ አላው
ቅም" በማለት በሁላቸውም ፊት ካደ::
71ከግቢው መውጫ ወደ ሆነው በር ሲያ
መራ ሌላዋ ሠራተኛ ተመልክታው፣ በዚያ
ለነበሩት ሰዎች፣ "ይህ ሰው ከናዝሬቱ ኢየ
ሱስ ጋር ነበር" አለች::
72እርሱም በመሐላ ቃል፣ "ሰውየውን አላ
ውቀውም!" ሲል ዳግመኛ ካደ::
73ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ በዚያ ቆመው የነ
በሩት ሰዎች ቀርበው ጴጥሮስን፣ "አነጋገ
ርህ ስለሚያጋልጥህ፣ በእርግጥ አንተም ከእ
ነርሱ አንዱ ነህ!" አሉት::
74እርሱም እየማለና እየተገዘተ፣ "እኔ ሰው
የውን አላውቀውም!" አላቸው::
ወዲያውም ዶሮ ጮኸ:: 75በዚህ ጊዜ
ጴጥሮስ፣ "ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደ
ኛለህ" ብሎ ኢየሱስ የተናገረው ቃል ትዝ
አለው፤ ጴጥሮስም ወደ ውጭ ወጥቶ መራራ
ልቅሶ አለቀሰ::

*50 ወይም "ወዳጄ ሆይ፤ ለምን መጣህ?"
[a]63 ወይም "መሲሑ"፤ ቍ 68 ይመ

26፥51 ሉቃ22፥36፤ ዮሐ18፥10
26፥52 ዘፍ9፥6፤ዘፀ 21፥12፤ራእ13፥10
26፥53 2ነገ6፥17፤ ዳን7፥10፤ማቴ4፥11
26፥54 ቍ24፤ ማቴ1፥22
26፥55 ማር12፥35፤ ሉቃ21፥37፤ ዮሐ7፥14፡28፥18፥20
26፥56 ቍ24፤ ማቴ1፥22
26፥57 ቍ3
26፥58 ቍ69፤ ማር14፥66፤15፥16፤ ሉቃ11፥21፤22፥55፤ ዮሐ7፥32፡45፡46፤ 18፥15
26፥59 ማቴ5፥22
26፥60 ዘዳ19፥15፤ መዝ27፥12፤35፥11፤ ሐሥ6፥13
26፥61 ዮሐ2፥19
26፥63 ዘሌ5፥1፤ ማቴ4፥3፤16፥16፤ ማር14፥61፤ ሉቃ22፥67
26፥64 ማቴ27፥11፤ ማር16፥19፤ሉቃ 22፥70፤ራእ1፥7
26፥65 ማር14፥63
26፥66 ዘሌ24፥16፤ ዮሐ 19፥7
26፥67 ማቴ16፥21
26፥68 ሉቃ22፥63-65
26፥75 ቍ34፤ ዮሐ 13፥38

26፥53 *ክፍለ ሠራዊት፤* አንድ የሮማውያን ክፍለ ጦር በውስጡ 6000 ወታደሮች ነበሩ::

26፥54 *ቅዱሳት መጻሕፍት ... ይፈጸማል፤* ከቍ56 አንጻር ሲታይ ዘካ13፥7 ላይ ያለውን ሳያመለክት አይቀርም::

*26፥57-27፥26፤* ኢየሱስ ተከሶ ለምርመራ የቀረበባቸውን ሁለት ደረጃዎች፣ ማለትም የካህናቱን ሸንጎና የመንግሥቱን ችሎት አካቶ የያዘ ክፍል ነው፤ ይህን ክስ በተመለከተ የማር 14፥53-15፥15 ማብ ይመ::

26፥59 *የአይሁድ ሸንጎ፤* የማር14፥55 ማብ ይመ::

26፥61 *የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ አፍርሼ፤* የኢየሱስን ቃል (ዮሐ2፥19) ሆን ብለው አጣመው እንዳቀረቡት ያሳያል::

26፥63 *በሕያው እግዚአብሔር ስም አምልሃለሁ፤* ጌታ ኢየሱስ ቍ62 ላይ የቀረበለትን ጥያቄ ለመመለስ ፈቃደኛ አልሆነም ነበር (ቍ63 ይመ)፤ ነገር ግን ሊቀ ካህናቱ በዚህ መልክ ጥያቄውን በማቅረቡ፣ ከሕጋዊ ግዴታ የተነሣ መልስ መስጠት ነበረበት::

26፥65 *ልብሱን ቀዶ፤* በመሠረቱ ሊቀ ካህናት ልብሱን እንዳይቀድ ሕጉ ይከለክለዋል (ዘሌ10፥6፤ 21፥10)፤ ይህ ሁኔታ ግን እጅግ የተለየ አጋጣሚ ተደርጎ ታይቶአል:: ሊቀ ካህናቱ በቍ64 ላይ የተመለከተውን የኢየሱስን መልስ በእግዚአብሔር ላይ እንደ ተሰነዘረ ስድብ ቈጥሮታል (የማር14፥64 ማብ ይመ)::

*26፥67-68፤* ሰዎቹ የኢየሱስን ዐይን ሸፍነው እንደ ነበር ማርቆስ ይገልጻል (ማር14፥65)፤ ይህም "ማን ነው የመታህ? ... ትንቢት ተናገር" የሚለውን የፌዝ ጥያቄ መልክ ይገልጻል::

26፥73 *አነጋገርህ ስለሚያጋልጥህ፤* የጴጥሮስ አነጋገር እንደ ገሊላ ሰዎች ስለ ነበር፣ በኢየሩሳሌም ካሉት ተለይቶ የሚታወቅ ነበር::

## ይሁዳ ራሱን ሰቀለ

27 ጠዋት በማለዳ ላይ፣ የካህናት አለ
ቆችና የሕዝብ ሽማግሌዎች ሁሉ
ኢየሱስ ስለሚገደልበት ሁኔታ ተመካከሩ፤
2ካሰሩትም በኋላ ወስደው ለገዥው ለጲላ
ጦስ አሳልፈው ሰጡት።
3አሳልፎ የሰጠው ይሁዳም ኢየሱስ እንደ
ተፈረደበት ባየ ጊዜ ተጸጸተ፤ የወሰደውን
ሠላሳ ጥሬ ብር ለካህናት አለቆችና ለሕዝቡ
ሽማግሌዎች መልሶ በመስጠት፣ 4"ንጹሕ
ሰው አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ" አለ።
እነርሱም፣ "ታዲያ እኛ ምን አገባን፤ የራ
ስህ ጉዳይ ነው!" አሉት።
5ስለዚህ ይሁዳ ብሩን በቤተ መቅደስ ውስጥ
ወርውሮ ወጣ፤ ሄዶም ራሱን ሰቅሎ ሞተ።
6የካህናት አለቆች ብሩን አንሥተው፣
"የደም ዋጋ ስለሆነ ወደ መባ ልንጨምረው
አይፈቀድም" አሉ፤ 7ተመካክረውም ለእንግ
ዶች የመቃብር ስፍራ እንዲሆን በገንዘቡ
የሸክላ ሠሪውን ቦታ ገዙበት። 8ስለዚህም ያ
ቦታ እስከ ዛሬ ድረስ "የደም መሬት" ተብሎ
ይጠራል። 9በዚህም በነቢዩ ኤርምያስ እንዲህ
ተብሎ የተነገረው ተፈጸመ፤ "ለእርሱ ዋጋ
ይሆን ዘንድ የእስራኤል ልጆች የገመቱትን
ሠላሳ ጥሬ ብር ተቀበሉ፤ 10እግዚአብሔርም
ባዘዘኝ መሠረት ለሸክላ ሠሪው ቦታ ከፈሉ።"

## ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት

27፥11-26 ተጓ ምብ - ማር 15፥2-15፤
ሉቃ 23፥2:3:18-25፤ ዮሐ 18፥29-19፥16

11በዚህ ጊዜ ኢየሱስ አገረ ገዥው ፊት
ቀረበ፤ አገረ ገዥውም፣ "አንተ የአይሁድ
ንጉሥ ነህን?" በማለት ጠየቀው።
ኢየሱስም፣ "አንተው እንዳልኸው ነው"
ሲል መለሰለት።
12የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች ሲከሱት
ግን ምንም መልስ አልሰጠም። 13በዚህ ጊዜ
ጲላጦስ፣ "ስንት ነገር አቅርበው እንደሚከ
ሱህ አትሰማምን?" አለው። 14እርሱ ግን አገረ
ገዥው እስኪገረም ድረስ ለቀረበበት ክስ
አንዲት ቃል እንኳ አልመለሰም።
15አገረ ገዥው ሕዝቡ በበዓሉ እንዲፈታላ
ቸው የሚጠይቁትን አንድ እስረኛ የመፍ
ታት ልማድ ነበረው። 16በዚያን ጊዜ በፀ
መፅ የታወቀ በርባን የሚባል እስረኛ ነበር።
17ሕዝቡ እንደተሰበሰቡ ጲላጦስ፣ "ከበርባንና
ክርስቶስ ከሚባለው ከኢየሱስ፣ ማንን እንድ
ፈታላችሁ ትፈልጋላችሁ?" አላቸው፤ 18ጲላ
ጦስም በቅናት አሳልፈው እንደ ሰጡት
ያውቅ ነበርና።
19በፍርድ ወንበር ላይ ተቀምጦ ሳለ ሚስቱ፣
"በእርሱ ምክንያት ዛሬ በሕልም ብዙ ስለተ
ሠቃየሁ፣ በዚያ ንጹሕ ሰው ላይ ምንም ነገር
እንዳታደርግ" የሚል መልእክት ላከችበት።
20ነገር ግን የካህናት አለቆችና ሽማግሌ
ዎች በርባን እንዲፈታላቸው ኢየሱስ ግን
እንዲገደል ይለምኑ ዘንድ ሕዝቡን ያግባቡ
ነበር።
21አገረ ገዥውም፣ "ከሁለቱ ማንን እንድ
ፈታላችሁ ትፈልጋላችሁ?" በማለት ጠየቀ።
እነርሱም፤ "በርባንን!" በማለት መለሱ።
22ጲላጦስም፣ "ታዲያ ክርስቶስ የተባለውን
ኢየሱስንስ ምን ላድርገው?" አላቸው።
ሁሉም፣ "ይሰቀል!" አሉ።
23ጲላጦስም፣ "ለምን? ምን ክፉ ነገር አድ
ርጎአል?" በማለት ጠየቃቸው።
እነርሱ ግን አብዝተው እየጮኹ፣ "ይሰ
ቀል!" አሉ።
24ጲላጦስ ሁኔታው ሽብር ከማስነሣት በስ
ተቀር ምንም ፋይዳ የሌለው መሆኑን ተመ
ልክቶ፣ "እኔ ከዚህ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ፤
ከእንግዲህ ኀላፊነቱ የራሳችሁ ነው" በማለት
ውሃ አስመጥቶ በሕዝቡ ፊት እጆቹን ታጠበ።
25ሕዝቡም በሙሉ፣ "ደሙ በእኛና በልጆ
ቻችን ላይ ይሁን!" ብለው መለሱ።
26በዚህ ጊዜ በርባንን ፈታላቸው፤ ኢየሱ
ስን ግን ካስገረፈው በኋላ እንዲሰቀል አሳ
ልፎ ሰጠው።

## ኢየሱስ በሮማውያን ወታደሮች እጅ

27፥27-31 ተጓ ምብ - ማር 15፥16-20

27ከዚያም የአገረ ገዥው ወታደሮች ኢየ
ሱስን ወደ ገዥው ግቢ ወሰዱት፤ ሰራዊቱ
ንም ሁሉ በዙሪያው አሰባሰቡ። 28ልብሱን
ገፈው ቀይ ልብስ አጠለቁለት፤ 29እሾኽ ጉን
ጉነው አክሊል በመሥራት ራሱ ላይ ደፉበት፤

27፥1 ማቴ12፥14፤ ማር15፥1፤ ሉቃ22፥66
27፥2 ማቴ20፥19፤ ማር15፥1፤ሉቃ13፥1፤ ሐሥ3፥13፤1ጢሞ 6፥13
27፥3 ማቴ10፥4፤ 26፥14:15
27፥4 ቍ24
27፥5 ሉቃ1፥9:21፤ ሐሥ1፥18
27፥8 ሐሥ1፥19
27፥9 ማቴ1፥22
27፥10 ኤር32፥6-9፤ ዘካ11፥12:13
27፥11 ማቴ2፥2
27፥12 ማር14፥61
27፥13 ማቴ26፥62
27፥14 ማር14፥61
27፥15 ዮሐ18፥39
27፥17 ቍ22፤ ማቴ1፥16
27፥19 ቍ24፤ዘፍ 20፥6፤ዘኍ12፥6፤1ነገ 3፥5፤ኢዮ33፥14-16፤ ማቴ1፥20፤2፥12:13: 19:22፤ዮሐ19፥13
27፥20 ሐሥ3፥14
27፥22 ማቴ1፥16
27፥24 ቍ4፤ዘዳ 21፥6-8፤መዝ26፥6፤ ማቴ26፥5
27፥25 ኢሱ2፥19፤ ሐሥ5፥28
27፥26 ኢሳ53፥5፤ ዮሐ19፥1
27፥27 ዮሐ18፥28: 33፤19፥9
27፥28 ዮሐ19፥2
27፥29 ኢሳ53፥3፤ ዮሐ19፥2:3

27፥1 *ጠዋት በማለዳ ላይ፤* የአይሁድ የፍርድ ሸንጎ የተለመደ ሕጋዊ ጉባኤውን በሌሊት ሊያካሂድ ስለማይችል፣ የሞት ውሳኔውን (26፥66) ሕጋዊ ለማድረግ ሲነጋ ልዩ ስብሰባ ጠራ።

27፥2 *ለ ... ጲላጦስ አሳልፈው ሰጡት፤* የቤተ መቅደሱን አጥር ጥሶ በገባ ባዕድ ላይ ካልሆነ በቀር የአይሁድ ሸንጎ በማንም ሰው ላይ የሞት ፍርድ እንዳይፈርድ በሮማውያን መንግሥት ተገድቦ ነበር። ስለዚህ ኢየሱስ የሞት ፍርድ ይፈረድበት ዘንድ ለጲላጦስ አልፎ መስጠት ነበረበት። ስለ ጲላጦስ የበለጠ ለመረዳት የማር15፥1 ማብ ይመ።

27፥3-10፤ ሐሥ1፥16-19 ይመ።

27፥5 *ራሱን ሰቅሎ፤* የሐሥ1፥18 ማብ ይመ።

27፥8 *"የደም መሬት" ተብሎ ይጠራል፤* በኤር19፥6 ላይ "የእርድ ሸለቆ" ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ።

27፥9 *ኤርምያስ፤* እዚህ ላይ የተጠቀሰው ጥቅስ የዘካ 11፥12-13 እና የኤር19፥1-13 ጥምር ይመስላል (ምናልባትም ኤር 18፥2-12 ወይም ኤር32፥6-9 ሊሆን ይችላል)። ማቴዎስ ግን ከዐበይት ነቢያት አንዱ የሆነው ኤርምያስ ነው ብሏል፤ ማርቆስም (1፥2-3) ከሚል3፥1 እና ከኢሳ40፥3 አቀናጅቶ ከጠቀሰ በኋላ፣ ሁለቱንም ጥቅሶች ዐቢይ ነቢይ በሆነው በኢሳይያስ ስም ጽፎታል።

27፥15 *አገረ ገዥው ... ልማድ፤* ስለዚህ ልማድ በወንጌሎች ከተገለጸው ውጭ የሚታወቅ ነገር የለም።

27፥19፤ በዚህ ጥቅስ ላይ የተጠቀሰው ታሪክ የሚገኘው በማቴዎስ ወንጌል ብቻ ነው።

27፥26 *ካስገረፈው በኋላ፤* የሮማውያን አገራረፍ ከፍተኛ ጭካኔ የተሞላበት ስለ ነበር፣ አንዳንድ ጊዜ የሚገረፈው ሰው ገና ሳይሰቀል በመገረፍ ላይ እያለ ሕይወቱ ያልፍ ነበር (የማር 15፥15 ማብ ይመ)።

27፥27 *ገዥው ግቢ፤* አገረ ገዢው በኢየሩሳሌም ገዢ እስከ ሆነበት ጊዜ ድረስ የሚሰጠው መደበኛ መኖሪያ ነበረው (የማር 15፥16 ማብ ይመ)።

27፥28 *ቀይ ልብስ፤* የሮማውያን ወታደሮች ከላይ የሚደርቡት አጠር ያለ ካባ ነው።

የሸምበቆ በትር በቀኝ እጁ በማስያዝ በፊቱ
ተንበርክከው፣ “የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፤
ሰላም ለአንተ ይሁን” በማለት አሾፉበት፤
30ተፉበትም፤ የሸምበቆ በትሩን ከእጁ
ወስደው ራሱ ላይ በሸምበቆው ደግመው
ደጋግመው መቱት፤ 31ካሾፉበት በኋላም
ቀዩን ልብስ ገፈው የራሱን መጐናጸፊያ
አለበሱት፤ ሊሰቅሉትም ይዘውት ሄዱ።

## የኢየሱስ መስቀል

27፥33-44 ተጓ ምብ - ማር 15፥22-32፤ ሉቃ 23፥33-43፤ ዮሐ 19፥17-24

32ይዘውትም ሲሄዱ ስምዖን ተብሎ
የሚጠራ የቀሬና ሰው አገኙ፤ መስቀሉንም
እንዲሸከም አስገደዱት።
33ትርጕሙ፣ “የራስ ቅል” ከሆነው ጎልጎታ
ከተባለው ቦታ ሲደርሱ፣ 34ከሐሞት ጋር
የተቀላቀለ የወይን ጠጅ እንዲጠጣ ሰጡት፤
እርሱ ግን ቀምሶ ሊጠጣው አልፈቀደም።
35ከሰቀሉትም በኋላ ዕጣ ጥለው ልብሱን
ተካፈሉ፤† 36በዚያም ተቀምጠው ይጠብቁት
ነበር። ከራስጌውም፣ 37“ይህ የአይሁድ ንጉሥ
ኢየሱስ ነው” የሚል የክስ ጽሑፍ አኖሩ።
38ሁለት ወንበዴዎች አንዱ በቀኙ፣ አንዱ
በግራው አብረውት ተሰቅለው ነበር።
39መንገድ ዐላፊዎችም በኀይል እየተሳደ
ቡና ራሳቸውን እየነቀነቁ፣ 40“ቤተ መቅደ
ስን አፍርሰህ በሦስት ቀን ውስጥ የምትሠ
ራው፤ እስቲ ራስህን አድን! የእግዚአብሔር
ልጅ ከሆንህ በል ከመስቀል ውረድ!” ይሉት
ነበር።
41የካህናት አለቆችም ከኦሪት ሕግ መምህ
ራንና ከሽማግሌዎች ጋር ሆነው እያሾፉበት
እንዲህ ይሉ ነበር፤ 42“ሌሎችን አዳነ፤ ራሱን
ግን ማዳን አይችልም! የእስራኤል ንጉሥ
ከሆነ አሁን ከመስቀል ይውረድ፤ እኛም
እናምንበታለን። 43በእግዚአብሔር ታምኖ
አል፤ ‘የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ’ ይል ስለ
ነበር እስቲ ከወደደው አሁን ያድነው!” 44ከእ
ርሱ ጋር የተሰቀሉት ወንበዴዎችም እንደ
ዚሁ የስድብ ቃል ያወርዱበት ነበር።

27፥30 ማቴ16፥21
27፥31 ኢሳ53፥7
27፥32 ማር15፥21፤ ሉቃ23፥26፤ሐሥ2፥10፤6፥9፤11፥20፤13፥1፤ዕብ13፥12
27፥33 ዮሐ19፥17
27፥34 ቊ48፤ መዝ 69፥21
27፥35 መዝ22፥18
27፥36 ቊ54
27፥38 ኢሳ53፥12
27፥39 መዝ22፥7፤ 109፥25፤ ሰቆ2፥15
27፥40 ቊ42፤ ማቴ4፥3፡6፤ዮሐ2፥19
27፥42 ዮሐ1፥49፤ 3፥15፤12፥13
27፥43 መዝ22፥8
27፥45 አሞ8፥9
27፥46 መዝ22፥1
27፥48 ቊ34፤ መዝ 69፥21
27፥50 ዮሐ19፥30
27፥51 ቊ54፤ ዘፀ26፥31-33፤ ዕብ9፥3፡8፤10፥19፡20
27፥53 ማቴ4፥5
27፥54 ቊ36፥ማቴ 4፥3፤17፥5
27፥55 ሉቃ8፥2፡3
27፥56 ማር15፥47፤ ሉቃ24፥10፤ ዮሐ 19፥25
27፥60 ማቴ27፥66

## የኢየሱስ መሞት

27፥45-56 ተጓ ምብ - ማር 15፥33-41፤ ሉቃ 23፥44-49

45ከቀኑ ስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ
ሰዓት ድረስ በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ
ሆነ። 46በዘጠኝ ሰዓት ገደማ፣ ኢየሱስ
ድምፁን ከፍ አድርጎ፣ “ኤሎሄ! ኤሎሄ! ላማ
ሰበቅታኒ?” እያለ ጮኸ፤ ትርጕሙም “አም
ላኬ፤ አምላኬ፤ ለምን ተውኸኝ?” ማለት
ነው። 47በዚያ ቆመው ከነበሩት አንዳን
ዶቹ ጩኸቱን ሲሰሙ፣ “ኤልያስን እየ
ተጣራ ነው!” አሉ።
48ወዲያውም ከእነርሱ አንዱ ሮጦ ሰፍነግ
በመውሰድ የኮመጠጠ ወይን ጠጅ ውስጥ
ነከረው፤ ሰፍነጉንም በሸምበቆ ዘንግ ጫፍ
ላይ በማድረግ እንዲጠጣው ለኢየሱስ አቀ
ረበለት። 49የቀሩት ግን፣ “ተዉት፤ እስቲ
ኤልያስ መጥቶ ሲያድነው እናያለን!” አሉ።
50ኢየሱስ እንደ ገና ከፍ ባለ ድምፅ ጮኸ፤
መንፈሱንም አሳልፎ ሰጠ።
51በዚያን ጊዜ የቤተ መቅደስ መጋረጃ
ከላይ እስከ ታች ለሁለት ተቀደደ፤ ምድር
ተናወጠች፤ ዐለቶችም ተሰነጣጠቁ፤ 52መቃ
ብሮች ተከፈቱ፤ አንቀላፍተው የነበሩትም
ብዙዎች ቅዱሳን ተነሡ፤ 53ከመቃብርም
በመውጣት ከኢየሱስ ትንሣኤ በኋላ ወደ
ቅድስት ከተማ ገብተው ለብዙዎች ታዩ።
54የመቶ አለቃውና አብረውት ኢየሱስን
ይጠብቁት የነበሩት የመሬት መናወጡንና
የሆነውን ነገር ሁሉ ባዩ ጊዜ እጅግ ፈሩ፤
ከዚያም፣ “በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ
ነበር!” አሉ። 55ከገሊላ የመጡና ኢየሱስን
በሚያስፈልገው ነገር ለማገልገል የተከተ
ሉት ብዙ ሴቶች ሁኔታውን ከርቀት እየተ
መለከቱ በአካባቢው ነበሩ። 56ከእነርሱም
መካከል ማርያም መግደላዊት፣ ማርያም
የያዕቆብና የዮሴፍ እናት እንዲሁም የዘብ
ዴዎስ ልጆች እናት ነበሩ።

†35 ጥቂት የጥንት ቅጆች “በነቢዩ *ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፤ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ* የተባለው ይፈጸም ዘንድ” የሚል አላቸው

27፥29 *በትር፤* ሊያሾፉበት ያዘጋጁት የውሸት በትረ መንግሥት ነበር።

27፥32 *የቀሬና ሰው፤* ቀሬና በሰሜን አፍሪካ የምትገኝ ከተማ ነበረች። *ስምዖን … መስቀሉንም እንዲሸከም፤* የማር 15፥21 ማብ ይመ።

27፥33 *ጎልጎታ፤* የማር15፥22 ማብ ይመ።

27፥34 *ከሐሞት ጋር የተቀላቀለ፤* የኢየሩሳሌም ሴቶች ይህን መሰል የሥቃይ ማስታገሻ አዘጋጅተው ለሚሰቀል እስረኛ ያቀርቡ እንደ ነበር በዘልማድ ይነገራል። ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት፣ ገና ነፍሱን እያወቀ ሥቃዩን ለመቀበል ስለ ፈለገ፣ የሥቃይ ማስታገሻውን አልጠጣም አለ (ቊ50)።

27፥35 *ከሰቀሉትም፤* የማር15፥24 ማብ ይመ። *ዕጣ ጥለው፤* በዮሐ19፥23-24 ላይ በይበልጥ ተብራርቷል።

27፥37፤ የማር 15፥26 ማብ ይመ።

27፥46 *ኤሎሄ! ኤሎሄ! ላማ ሰበቅታኒ?* የአራማይክና የዕብራይስጥ ቋንቋ ቅይጥ ሲሆን፣ ማቴዎስ ለአንባቢዎቹ ሲል ተርጕሞታል (የማር15፥34 ማብ ይመ)።

27፥49፤ የማር15፥35 ማብ ይመ።

27፥51 *መጋረጃ፤* በቤተ መቅደስ ውስጥ ቅድስተ ቅዱሳኑን ከቅድስት ስፍራ የሚለየው ውስጠኛ መጋረጃ ነው። የመጋረጃው መቀደድ፣ ምእመናን ወደ ህልዎተ እግዚአብሔር እንዲደርሱ ክርስቶስ ማስቻሉን ያሳያል (ዕብ9፥1-14፤ 10፥14-22 ይመ)።

*27፥52-53፤* ይህ ታሪክ የሚገኘው በማቴዎስ ወንጌል ብቻ ነው፤ ምናልባት ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሠራው የማዳን ሥራ፣ ሞትን ማሸነፉን የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም።

27፥54 *የመቶ አለቃውና፤* የ8፥5 ማብ ይመ። *የእግዚአብሔር ልጅ፤* ይህ ሐረግ በዚህ ላይ በሁለት መልክ ሊታይ ይችላል፤ በአንድ በኩል እንደ አንድ ክርስቲያን ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አምኖ መመስከሩ ሊሆን ይችላል፤ በሌላ በኩል ደግሞ መቶ አለቃው በቀድሞው አመለካከቱ ኢየሱስ ከበደል ነጻ መሆኑን አማልክት መመስከራቸውንና በእነርሱም መወ ደዱን ማመልከቱ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን አይሁድ ቀደም ሲል ካላ ገጡበት አኳያ ሲታይ (ቊ40)፣ የማቴዎስ ሐሳብ የመጀመሪያው ሳይሆን አይቀርም።

*27፥56፤* የማር15፥40 ማብ ይመ።

## የኢየሱስ መቀበር

27፥57-61 ተጓ ምብ - ማር15፥42-47፤
ሉቃ23፥50-56፤ ዮሐ19፥38-42

57ምሽት ላይ ዮሴፍ የሚባል ሀብታም
ሰው ከአርማትያስ መጣ፤ እርሱ ራሱም
የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ነበረ። 58ጲላጦስ
ፊት ቀርቦ የኢየሱስን በድን ለመነው፤ ጲላ
ጦስም እንዲሰጠው አዘዘ። 59ዮሴፍም በድ
ኑን ወስዶ በንጹሕ የበፍታ ጨርቅ ከፈነው፤
60ለራሱ ከዐለት አስፈልፍሎ ባዘጋጀው
መቃብር ውስጥ አኖረው፤ ከዚያም ትልቅ
ድንጋይ አንከባሎ የመቃብሩን በር ዘግቶ
ሄደ። 61በዚህ ጊዜ ማርያም መግደላዊትና
ሌላዋ ማርያም ከመቃብሩ ትይዩ ተቀምጠው
ነበር።

## የመቃብሩ ጥበቃ

62በማግስቱ፣ ከሰንበት ዝግጅት በኋላ
ባለው ቀን፣ የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን
ጲላጦስ ፊት ቀርበው እንዲህ አሉት፤ 63"ክ
ቡር ሆይ፤ ያ አታላይ በሕይወት ሳለ፣
'ከሦስት ቀን በኋላ እነሣለሁ' ያለው ትዝ
ብሎናል፤ 64ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ አስከ
ሬኑን ሰርቀው ለሕዝቡ፣ 'ከሙታን ተነሥ
ቶአል' ብለው እንዳያስወሩ መቃብሩ እስከ
ሦስተኛው ቀን ድረስ እንዲጠበቅ ትእዛዝ
ስጥልን፤ አለዚያ የኋለኛው ስሕተት ከፊተ
ኛው የባሰ ይሆናል!"
65ጲላጦስም፣ "ጠባቂዎች አሏችሁ፤ ሂዱ
ችሁ በምታውቁት መንገድ አስጠብቁ" አላ
ቸው። 66እነርሱም ሄደው መቃብሩን በማኅ
ተም አሽገው ጠባቂ አቆሙበት።

## የኢየሱስ ከሙታን መነሣት

28፥1-8 ተጓ ምብ - ማር 16፥1-8፤ ሉቃ 24፥1-10

28 ሰንበት ካለፈ በኋላ፣ በሳምንቱ መጀ
መሪያ ቀን ጎህ ሲቀድ፣ ማርያም
መግደላዊትና ሌላዋ ማርያም መቃብሩን
ሊያዩ ሄዱ።
2በድንገት ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤
የጌታም መልአክ ከሰማይ ወርዶ ወደ መቃ
ብሩ በመሄድ ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ላይ
ተቀመጠበት፤ 3መልኩ እንደ መብረቅ ብሩህ
ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበር። 4ጠባ
ቂዎቹ መልአኩን ከመፍራት የተነሣ ተን
ቀጠቀጡ፤ እንደ በድንም ሆኑ።
5መልአኩም ሴቶቹን እንዲህ አላቸው፤
"አትፍሩ፤ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንደም
ትፈልጉ አውቃለሁና፤ 6እርሱ በዚህ የለም፤
እንደ ተናገረው ተነሥቶአል፤ ኑና ተኝቶ
በት የነበረውን ቦታ እዩ። 7አሁንም ፈጥና
ችሁ ሂዱና ለደቀ መዛሙርቱ፣ 'ከሙታን
ነሥቶአል፤ ቀድሞአችሁ ወደ ገሊላ ይሄዳል፤
በዚያ ታዩታላችሁ' ብላችሁ ንገሯቸው።
እንግዲህ ነግሬአችኋለሁ!"
8ሴቶቹም በፍርሀትና በደስታ ተሞልተው
ለደቀ መዛሙርቱ ለመንገር በፍጥነት እየ
ሮጡ የመቃብሩን ስፍራ ትተው ሄዱ።
9ወዲያው ኢየሱስ አገኛቸውና፣ "ሰላም ለእ
ናንተ ይሁን!" አላቸው። እነርሱም ወደ ኢየ
ሱስ ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት።
10ኢየሱስም፣ "አትፍሩ፤ ሂዱና ወደ ገሊላ
እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ንገሯቸው፤ በዚያ
ያዩኛል" አላቸው።

## የጠባቂዎች ምስክርነት

11ሴቶቹ በመንገድ ላይ ሳሉ፣ ከጠባቂዎቹ
ጥቂቶቹ ወደ ከተማ በመሄድ የሆነውን
ሁሉ ለካህናት አለቆች አወሩላቸው። 12የካ
ህናት አለቆችም ከሽማግሌዎች ጋር ተሰብ
ስበው ተማከሩ፤ ለወታደሮቹ በቂ ገንዘብ
በመስጠት 13እንዲህ አሏቸው፤ " 'ተኝተን
ሳለን ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት መጥተው
ሰረቁት' በሉ፤ 14ይህ ወሬ በገዥው ዘንድ
ቢሰማ እንኳ፣ እኛ እናስረዳዋለን፤ ምንም
ክፉ ነገር እንዳይደርስባችሁ እናደርጋለን።"
15ወታደሮቹም ገንዘቡን ተቀብለው እንደ
ታዘዙት አደረጉ። ይህም ታሪክ እስከ ዛሬ
ድረስ በአይሁዶች ዘንድ በሰፊው እንደተሰ
ራጨ ነው።

## ታላቁ ተልእኮ

16ከዚያም ዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት
በገሊላ ወዳለው ኢየሱስ ወዳመለከታቸው
ተራራ ሄዱ። 17ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት፤
ጥቂቶች ግን ተጠራጠሩ። 18ኢየሱስም ደቀ
መዛሙርቱ ወዳሉበት ቀርቦ እንዲህ አላ
ቸው፤ "ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር

፤28፥2፤ማር16፥4፤
ሐሥ13፥29
27፥63 ማቴ16፥21
27፥64 ማቴ28፥13
27፥65 ቊ66፤
ማቴ28፥11
27፥66 ቊ60፤
ዳን 6፥17፤
ማቴ28፥2፡11
28፥1 ማቴ27፥56፤
ሉቃ8፥2
28፥2 ማቴ27፥51፡
60፤ዮሐ20፥12፤
ሐሥ 5፥19
28፥3 ዳን7፥9፤
10፥6፤
ማር9፥3፤ዮሐ20፥12
28፥5 ቊ10፤
ማቴ14፥27
28፥6 ማቴ16፥21
28፥7 ቊ10፡16፤
ማቴ26፥32
28፥9 ዮሐ20፥14-18
28፥10
ማቴ12፥50 ፤25፥40፤
ማር3፥34፤
ዮሐ20፥17፤ሮሜ
8፥29፤ዕብ2፥11-13፡ 17
28፥11
ማቴ27፥65 ፡66
28፥13 ማቴ27፥64
28፥14 ማቴ27፥2
28፥16 ቊ7፡10፤
ማቴ26፥32
28፥18 ዳን7፥13፡14
፤ሉቃ10፥22፤ዮሐ3፥3
5፤13፥13፤17፥2፤1ቆሮ
15፥27፤ኤፌ1፥20-22
፤ፊል2፥9፡10

27፥57 *ከአርማትያስ፤* ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን ምዕራብ 32 ኪ.ሜ. ያህል ርቃ፣ በኤፍሬታ ኩረብታማ ምድር የነበረች መንደር ናት።

27፥58 *የኢየሱስን በድን ለመነው፤* የሉቃ23፥52 ማብ ይመ።

*27፥59-60፤* የማር 15፥46 ማብ ይመ።

27፥62 *በማግስቱ፣ ከሰንበት ዝግጅት በኋላ ባለው ቀን፤* በሰንበት ቀን፣ ቅዳሜ ዕለት ማለት ነው፤ የሰንበት መዘጋጃ ቀን ዓርብ ዕለት ነበር (ከዓርብ ጀንበር መጥለቂያ እስከ ቅዳሜ ጀንበር መጥለቂያ ያለው ጊዜ ሰንበት ይባላል)።

27፥64 *የኋለኛው ስሕተት ከፊተኛው የባሰ ይሆናል!* የመጀመሪያው ስሕተት ኢየሱስ መሲሑ ነው የሚለው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኑ ከሙታን ተነሥቶአል የሚለው ነው።

27፥65 *ጠባቂዎች አሏችሁ፤* ጲላጦስ ሮማውያን ጠባቂ ወታደሮችን ሰጣቸው (28፥4፡11-12)።

28፥1 *በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን፤* የሉቃ24፥1 ማብ ይመ።

*ሌላዋ ማርያም፤* የቀለዮጳ ሚስት ስትሆን ስሟ በሌሎች ወንጌሎችም ተጠቅሶአል (27፥56፡61፤ ማር16፥1፤ ዮሐ19፥25 ይመ)።

28፥2 *ሆነ፤* የቃሉ አገባብ "እንዲህ ሆኖ ነበር" የሚል ግንዛቤን ይሰጣል። አቻ ከሆኑት ትረካዎች (ማር16፥2-6፤ ሉቃ24፥1-7፤ ዮሐ20፥1) አንጻር ሲታይ፣ በቊ2-4 የተገለጸው ሁኔታ በመሠረቱ የተከሠተው ሴቶቹ ከመቃብሩ ስፍራ ከመድረሳቸው በፊት ነበር። *ታላቅ የምድር መናወጥ፤* ስለዚህና ልክ ኢየሱስ ሲሞት ስለ ተከሠተው የምድር መናወጥ (27፥51፡54) የጻፈው ማቴዎስ ብቻ ነው።

*28፥11-15፤* ጠባቂዎች ስለ መቆማቸው የሚተርከው ማቴዎስ ብቻ ነው (27፥62-66)፤ እነዚህ ጠባቂዎች ለበላዮቻቸው ስለ ሁኔታው የሚናገሩትንም በመመርኰዝ ትረካውን ይቀጥላል።

28፥16 *ዐሥራ አንዱ፤* ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ የነበረው ይሁዳ ራሱን ስለ ገደለ (27፥5)፣ ዐሥራ አንድ ብቻ ናቸው። *ወዳመለከታቸው፤* ቊ10 ይመ።

ተሰጥቶኛል፤ 19ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ
በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም
እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርቴ አድር
ጓቸው፤ 20ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ
አስተምሯቸው፤ እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ
ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።”

28፥19 ኢሳ49፥6፤ ማር16፥15፡16፤ሉቃ 24፥47፤ሐሥ1፥8፤ 2፥38፤8፥16፤14፥21፤ ሮሜ6፥3፡4፤ገላ3፥27፤ ቈላ2፥12

28፥20 ዘዳ31፥6፤ 1ነገ8፥57፤ሐጌ1፥13፤ ማቴ13፥39፤18፥20፤24፥3፤ዮሐ14፥26፤ ሐሥ2፥42፤18፥10

28፥19 *ሕዝቦችን ሁሉ፤* በ10፥5-6 ላይ ካለው ጋር ያነጻጽሩ። የእነዚሁኑ ቍጥሮች ማብ ይመ (በተጨማሪም ሐሥ10፥34፤ ሮሜ 1፥16 ይመ)። *እያጠመቃችኋቸው፤* ከክርስቶስ ጋር ለመተባበራቸውን ሕይወታቸውንና ለእርሱ ለማስረከባቸው ምልክት እንዲሆን ማለት ነው (የሐሥ2፥38፤ የሮሜ6፥3-4 ማብ ይመ)።

28፥20 *ከእናንተ ጋር፤* ማቴዎስ ወንጌሉን የሚደመድመው፣ “እግዚአብሔር ከእኛ ጋር” ወይም “አማኑኤል” (1፥23) ሊሆን ወደ ምድር በመጣው፣ በጌታ ኢየሱስ ዋስትና ሰጪና አበረታታች ቃል ነው።